ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር፣

# ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ማስተማር፣አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣ ፣የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና መፈተሽ፤ (በፓዊ ወረዳ በቀጠና ሁለት መንደር ሁለት 2ኛደረጃ ትምህርት-ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

መንግስት ቁምላቸው

በአማርኛ ቋንቋና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ

የቀረበ ጥናተዊ ጽሑፍ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ነሐሴ 2008ዓ.ም

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ(አማርኛ)ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር**

**ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ማስተማር፣አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና መፈተሽ፤ (በፓዊ ወረዳ በቀጠና ሁለት መንደር ሁለት 2ኛደረጃ ትምህርት-ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)**

**በ**

**መንግስት ቁምላቸው**

**አማካሪ**

**ማንያለዉ አባተ (ዶር.)**

**አቶ መሐመድ አደም**

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**ነሐሴ 2008ዓ.ም**

## ምስጋና

በቀዳሚነት፣ ከመጀመሪያ ጀምሮ ጥናቱ ለፍጻሜ እስኪደርስ ድረስ ረቂቁን በማረም፣በፈተናዎች ላይና በማስተማሪያ ቴክስቶች ላይ ጠቃሚ ማስተካከያዎችን በመስጠትና ጥናቱ የተነሳበትን ዓላማ ስቶ ፈር እንዳይለቅ፣አቅጣጫ በማስያዝና ገንቢ የሆኑ አስተያየቶችን በመስጠት፣ትዕግስትና ቅንነት የተሞላበት ሙያዊና ሞራላዊ ድጋፋቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ለዶር. ማንያለው አባተ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ እንዲሁም የጥናቱን ረቂቅ በማረምና ስህተቶችን በማስተካከል፣ጥናቱ የተቃና እንዲሆን ብርቱ ጥረት ላደረጉልኝ ረዳት አማካሪዬ አቶ መሐመድ አደም ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ የተለያዩ መረጃዎችን እንዳገኝ አቅጣጫ በመጠቆም፣ ከትልመ-ጥናት እስከ ፍጻሜ ድረስ በፈታኝነት ተግባር ጥልቅ አስተያየትና ማስተካከያዎች በመስጠት ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝና በሞራል ላበረታቱኝ ለዶር.አብይ አሰፋ፤እንዲሁም ጥናቱን በማንበብ አስተያየቶች በመስጠት ክፍተቶችን እንዳስተካክል ለረዱኝና በሞራል ላበረታቱኝ አቶ መሐመድ ጀማል ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

በመቀጠልም በመረጃ ስብሰባው ወቅት የማቴሪያልና የሞራል ድጋፍ ላደረጉልኝ የቀጠና ሁለት መንደር ሁለት ርዕሰ መምህር፣እንዲሁም ጠቃሚ አስተያየት በመስጠት፣ ፈተና በመፈተን፣በኮምፒዩተር ጽሑፎችን በመጻፍ ድጋፋቸው ላልተለየኝ የትምህርት ቤቱ መምህራንና ሰራተኞች፣የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ በተጨማሪም የማስተማሪያ ቴክስቱንና የፈተና ጥያቄዎችን በመገምገምና በማስተካከል ሙያዊ እገዛ ላደረጉልኝ ለግልገል በለስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ዲፓርትመንት መምህራን፣በተለይም ሙያዊና ሞራላዊ ድጋፋቸውን በመስጠት ላበረታቱኝ አቶ ክፍሌ ስበረው ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

በመጨረሻም ሁልጊዜ በስራዬ እንድበረታና በጽናት የየእለት ተግባሬን እንዳከናውን በቅን አስተሳሰቡዋና በሞራል ድጋፏ ያልተለየችኝን ባለቤቴ አስረስ ካሳውን፣ ልጆቻችንን ሜሮንና ሄኖክን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር፣ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና መፈተሽ ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በፓዊ ወረዳ በቀጠና ሁለት መንደር ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት-ቤት በ2008 ዓ.ም 9ኛ ክፍል በመማር ላይ ያሉ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ክፍሉ የተመረጠው በዓላማ ተኮር ዘዴ ነው፡፡ ካሉት የ9ኛ፣ 4ክፍሎች መካከል አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ከሆኑ 141 ተማሪዎች 60 ተጠኝዎች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ ከእያንዳንዱ የጥናት አካላይ ተመጣጣኝ ናሙና ለመውሰድ ሲባል ስብጥራዊና ተራየዕጣ ንሞናን በማቀናጀት ናሙና ተመርጧል (ተወስዷዋል)፡፡

ጥናቱ በዋናነት መጠናዊ የአጠናን ስልትን የተከተለ ሲሆን በዓይነታዊ መንገድ የተሰበሰቡ መረጃዎች ከመጠናዊ መረጃዎች ጋር ተቀናጅተው ተተንትነዋል። ከተጠኝ ተማሪዎች በፈተና፣ በጽሑፍ መጠይቅና በምልከታ መረጃ ተሰብስቧል። ፈተናው በቅድመ-ልምምድና በድህረ-ልምምድ ፈተና የተከፈለ ነው። ቅድመ-ልምምድ ፈተናው እንዲሁ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ክፍል አንድ 25ጥያቄዎችን፣ክፍል ሁለት ደግሞ 20ጥያቄዎችን፣በድምሩ 45ጥያቄዎችን የያዘ ነው። ቅድመ-ልምምድ ፈተናው በመጀመሪያ ደረጃ ተጠኝ ተማሪዎችን በቡድን ደረጃ ተመጣጣኝ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድን ብሎ ለመክፈል አስችሉዋል። ከዚህም በተጨማሪ ከድህረ-ልምምድ ፈተናው ጋር በማነጻጸር ለስታቲስቲካዊ ትንተናው አገልግሉዋል። የድህረ-ልምምድ ፈተናውም ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ክፍል አንድ 20 ጥያቄዎችን፣ክፍል ሁለት 25 ጥያቄዎችን ፣በድምሩ 45 ጥያቄዎችን የያዘ ነው። በፈተናና በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በስታቲስቲካዊ ስልት በኣማካይ ውጤት፣በመደበኛ ልይይት፣በጉልህነት ደረጃና በቲ-ቴስት ተተንትነዋል። በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ ጥያቄዎችን እንደ ጽንሰሃሳባዊ ቅርርባቸው በአራት የተዛምዶ ምድቦች በማስቀመጥ በዓይነታዊ ስልት በቋንቋ ገለጻ ተተንትነዋል። በምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎችም ከመጠናዊዎቹ ጋር ተቀናጅተው ተብራርተዋል። በዚህም መሰረት የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት 21.23 ሲሆን፣የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ፈተና

*አማካይ ውጤት ደግሞ 21.28 ሆኑዋል፡፡ የጉልህነት ደረጃም (P>0.05) ነው፡፡ ስለሆነም በቅድመ-ልምምድ ጊዜ በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራ ቡድኑ መካከል በአንብቦ መረዳት ችሎታ የጎላ ልዩነት የለም፡፡ የቁጥጥር ቡድኑ የድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት 21.60 ሲሆን፣ የሙከራ ቡድኑ የድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት 26.68 ሁኑዋል፡፡ ስለሆነም በድህረ-ልምምድ ጊዜ የሙከራ ቡድኑ ከፍተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንዳለው ያሳያል፡፡ በቁጥጥር ቡድኑ እና በሙከራ ቡድኑ የድህረ-ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት (P<0.05) ታይቷል፡፡ ይህም ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ማስተማር አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንደሚያሻሽል አመላክቷል፡፡*

*የጽሑፍ መጠይቁ፣በዓይነታዊ እና በመጠናዊ መንገድ የተተነተነ ሲሆን በተገኘው ምላሽ መሰረትም በአጭር ልቦለድ ቋንቋን የተማሩ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና ስለ አንብቦ መረዳት ያላቸው ግንዛቤ ተሻሽሏል፡፡ የምልከታው ውጤት እንደሚያሳየውም፣በነበረው የልምምድ ሂደት ተጠኝ ተማሪዎች በአጭር ልቦለድ ቋንቋን መማራቸው የእርስ በእርስ ተራክቦዋቸው ጨምሩዋል፡፡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን የመስራት ችሎታቸው ተሻሽሏል፡፡*

ማውጫ

ገጽ

ምስጋና-----------------------------------------------------------------------------------------I
አጠቃሎ ---------------------------------------------------------------------------..II
የሠንጠረዥማውጫ-----------------------------------------------------------------------------VI
የአባሪ መውጫ------------------------------------------------------------------------------VIII

**ምዕራፍ አንድ**---------------------------------------------------------1
1.መግቢያ----------------------------------------------------------------------------------1
1.1 የጥናቱ ዳራ------------------------------------------------------------------------1
1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር------------------------------------------------------------------5
1.3 የጥናቱ ዓላማ----------------------------------------------------------------------9
1.3.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ-------------------------------------------------------------9
1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች----------------------------------------------------9
1.4 የጥናቱ ጥያቄዎች------------------------------------------------------------ 10
1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት----------------------------------------------------------------10
1.6 የጥናቱ ወሰን------------------------------------------------------------------------10
**ምዕራፍ ሁለት፤**-------------------------------------------------------12
2 ተዛማጅ ጽሁፎች -----------------------------------------------------------------------12
2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት-----------------------------------------------------------------12
2.1.1 በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን የማስተማር አጀማመር--------------------------------------12
2.1.2 ስነ-ጽሁፍ ለቋንቋ ትምህርት ያለዉ ሚና (አስፈላጊነት)-----------------------------14
2.1.2.1 ስነ-ጽሁፍ በእውነተኛ ቋንቋ የሚቀርብና ዋጋ ያለዉ መሆኑ--------------------14
2.1.2.2 ስነ-ጽሁፍ በባህልና በቋንቋ አጠጠቃቀም የበለጸገ መሆኑ--------------------------17
2.1.2.3 ስነ-ጽሁፍ መነሳሳትንና ተሳትፎን የሚያሳድግ መሆኑ----------------------------19
2.1.3 የአጫጭር ልቦለድ ምንነትና ባህሪያት----------------------------------------------21
2.1.4 አጭር ልቦለድ አንብቦ መረዳትን ለማሻሻል ያላቸዉ ሚና----------------------------22
2.1.5 የአንብቦ መረዳት ምንነትና ስልቶች--------------------------------------------------26
2.2 ተዛማጅ ጥናቶች----------------------------------------------------------- -----------28
**ምዕራፍ ሦስት**---------------------------------------------------------------------34
3 የአጠናን ዘዴ------------------------------------------------------------------------------34
3.1 የተጠኝዎች አመራረጥ--------------------------------------------------------------------34
3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች-------------------------------------------------------------37
3.2.1 ቅድመ-ልምምድና ድህረ-ልምምድ ፈተናዎች-------------------------------------------37
3.2.1.1 ቅድመ-ልምምድ ፈተና-----------------------------------------------------------------38
3.2.1.2 ድህረ-ልምምድ ፈተና-------------------------------------------------------------39

3.2.2 የጽሁፍ መጠይቅ ------------------------------------------------------------------41
3.2፤3 ምልከታ---------------------------------------------------------------------------- 42
3.3 የማስተማሪያ ጽሑፎች(ቴክስት) አዘገጃጀትና አቀራረብ-------------------------------------43

3.3.1 የምንባቦች አመራረጥ-------------------------------------------------------------------45
3.3.2 የመልመጃዎች አዘገጃጀት------------------------------------------------------- ----------46
3.3.2.1 ቅድመ-ንባብ ተግባራት------------------------------------------------------------------46
3.3.2.2 የንባብ ጊዜ ተግባራት-------------------------------------------------------------------47
3.3.2.3 ድህረ-ንባብ ተግባራት-------------------------------------------------------------------47
3.4 መረጃ አተናተን----------------------------------------------------------------------------------
47
3.4.1 ከፈተናዎች የተገኘ መረጃ አተናተን------------------------------------------------------48
3.4.2 ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ አተናተን---------------------------------------------48
3.4.3 ከምልከታ የተገኘ መረጃ አተናተን------------------------------------------------------ 49
**ምዕራፍ አራት**----------------------------------------------------------------50
4 የውጤት ትንተናና ማብራሪያ-----------------------------------------------------------------50
4.1 የጥናት ውጤት ትንተና--------------------------------------------------------------------50
4.1.1 ከፈተናዎች የተገኘ የጥናት ውጤት ትንተና-------------------------------------------50
4.1.2 ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ የጥናት ውጤት ትንተና------------------------------------54
4.1.2.1 ከጽሑፍ መጠይቅ በዓይነታዊ የተገኘ የጥናት ውጤት ትንተና-------------------54
4.1.2.2 ከጽሑፍ መጠይቅ በመጠናዊ የተገኘ የጥናት ውጤት ትንተና--------------------75
4.1.3 ከምልከታ የተገኘ የጥናት ውጤት ትንተና-------------------------------------------78
4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ--------------------------------------------------------------------88
**ምዕራፍ አምስት ----------------------------------------------------------------90**
5. ማጠቃለያ መደምደሚያ አስተያየት----------------------------------------------------------
90
5.1 ማመቃለያ---------------------------------------------------------------------------------
90
5.2 መደምደሚያ-----------------------------------------------------------------------------
97
5.3 የመፍትሔ ሃሳቦች---------------------------------------------------------------------
98
ዋቢ ጽሁፎች-----------------------------------------------------------------------------------
99

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ1. የቅድመ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ የውጤት ንጽጽር በ ቲ-ቴስት ----- 50
ሰንጠረዥ2 የድህረ ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ንጽጽር በቲ-ቴስት፣ -------------------51
ሰንጠረዥ3 የቡድቦች የቅድመና የድህረ ልምምድ የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት
ተናጠላዊ ንጽጽር በ‹‹t-ቴስት››፣ ------------------------------------------------------------53
ሰንጠረዥ4 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ ማጠይቅ ምላሽ
(ለዓይነ ታዊ ትንተና)----------------------------------------------------------------------55
ሰንጠረዥ5 የሙከራ ቡድን ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ ማጠይቅ ምላሽ
(ለዓይነ ታዊ ትንተና)---------------------------------------------------------------------55
ሰንጠረዥ6 የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ -ልምምድ የጽሑፍ ማጠይቅ ምላሽ
(ለዓይነ ታዊ ትንተና)----------------------------------------------------------------- 57
ሰንጠረዥ7 የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ ማጠይቅ ምላሽ
(ለዓይነ ታዊ ትንተና)---------------------------------------------------------------------57
ሰንጠረዥ8 የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ ማጠይቅ ምላሽ
(ለዓይነ ታዊ ትንተና)---------------------------------------------------------------------59
ሰንጠረዥ9 የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ ማጠይቅ ምላሽ
(ለዓይነ ታዊ ትንተና) -------------------------------------------------------------------59
ሰንጠረዥ10 የቁጥጥር ቡድኑ ዲህረ-ልምምድ የጽሑፍ ማጠይቅ ምላሽ
(ለዓይነ ታዊ ትንተና)-------------------------------------------------------------------61
ሰንጠረዥ11 የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ ማጠይቅ ምላሽ
(ለዓይነ ታዊ ትንተና)-------------------------------------------------------------------61
ሰንጠረዥ12 የቅጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ ማጠይቅ ምላሽ
(ለዓይነ ታዊ ትንተና) -----------------------------------------------------------------64
ሰንጠረዥ13 የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ ማጠይቅ ምላሽ
(ለዓይነ ታዊ ትና ታዊ)------------------------------------------------------------------65
ሰንጠረዥ14 የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ ማጠይቅ ምላሽ
(ለዓይነ ታዊ ትንተና)-------------------------------------------------------------------67
ሰንጠረዥ15 የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ ማጠይቅ ምላሽ-------------------------69
ሰንጠረዥ16 የሙከራ ቡድኑ ቅድመል ምምድ የፅሁፍ ማጠይቅ ምላሽ-----------------------71
ሰንጠረዥ17 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ ማጠይቅ ምላሽ---------------------71
ሰንጠረዥ18 የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ ማጠይቅ ምላሽ-----------------------73
ሰንጠረዥ19 የሙከራቡድኑ ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ ማጠይቅ ምላሽ--------------------------74
**ሰንጠረዥ 20 የጽሑፍ መጠይቅ ታይለት ቴስት የተደረገበት መላሽ---------------------------76**
**ሰንጠረዥ 21 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ-------------------76**
**ሰንጠረዥ 22 የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ--------------------76**
**ሰንጠረዥ 23 የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ……………..---77**
**ሰንጠረዥ 24 የሙከራ ቡድን ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ…………----------77**

## የአባሪዎች ማውጫ

አባሪ ‹‹ሀ›› የቁጥጥር ቡድን ‹‹ሀ›› ቅድመልምምድ የፈተና ውጤት፣-----------------------104
አባሪ ‹‹ለ›› የሙከራ ቡድን ‹‹ለ›› ቅድመልምምድ የፈተና ውጤት፣-------------------------105
ርአባሪ ‹‹ሐ›› የቁጥጥር ቡድን ‹‹ሀ›› ድህረልምምድ የፈተና ውጤት፣-----------------------106
አባሪ ‹‹መ›› የሙከራ ቡድን ‹‹ለ›› ድህረልምምድ የፈተና ውጤት፣--------------------------107
አባሪ ‹‹ሠ›› የፅሁፍ መጠይቁ የአስተማማኝነት ስሌት፣----------------------------------------108
አባሪ ‹‹ረ›› የቅድመ-ልምምድ ፈተና የታይለት ውጤት 25 ጥያቄዎች-----------------------109
አባሪ ‹‹ሰ›› የቅድመ-ልምምድ ፈተና የታይለት ውጤት 20 ጥያቄዎች-----------------------110
አባሪ ‹‹ሸ›› የድህረ-ልምምድ ፈተና የታይለት ውጤት 20 ጥያቄዎች-----------------------111
አባሪ ‹‹ቀ›› የድህረ-ልምምድ ፈተና የታይለት ውጤት 25 ጥያቄዎች-----------------------112
አበሪ ‹‹በ››የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የቅድመና የድህረ ልምምድ አማካይና መደበኛ ልይይት ውጤት የተሰላበት፣-------------------------------------------113
አባሪ ‹‹ተ›› የጽሑፍ መጠይቅ ፓይለት ቴስት የተደረገበት ምላሽ፣--------------------------114
አባሪ ‹‹ቸ›› የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ፣ ------------------115
አባሪ ‹‹ኀ›› የሙከራ ቡድኑ ቅድመልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ፣--------------------116
አባሪ ‹‹ነ›› የቁጥጥር ቡድኑ ድህረልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ፣-------------------117
አባሪ ‹‹ኘ›› የሙከራ ቡድኑ ድህረልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ፣-------------------118
አባሪ ‹‹አ›› ለቁጥጥርና ሙከራ ቡድኑ የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ፣-----------------------119
አባሪ ‹‹ከ›› ቅድመልምምድ ፈተና ክፍል አንድ፣--------------------------------------------121
አባሪ ‹‹ኸ›› ቅድመልምምድ ፈተና ክፍል ሁለት፣--------------------------------------------125
አባሪ ‹‹ወ›› ድህረልምምድ ፈተና ክፍል አንድ፣---------------------------------------------130
አባሪ ‹‹ዐ›› ድህረልምምድ ፈተና ክፍል ሁለት፣--------------------------------------------134
አባሪ ‹‹ዘ›› የማስተማሪያ ጽሑፎች (ቴክስት))፣----------------------------------------------140

## ምዕራፍ አንድ

# 1.መግቢያ

በዚህ ክፍል የጥናቱ ዳራ፣የጥናቱን ለማጥናት መነሳሻ የሆነው ምክንያት፣የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ የመጠናት አስፈላጊነትና የጥናቱ ውስንነት በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን የማስተማር ፍላጎት እያደገ የመጣው፣የውጭ ወይም የሁለተኛ ቋንቋ የትምህርት አሰጣጥ ለንግግር ቋንቋ ማለትም ለተግባቦታዊ የቋንቋ አጠቃቀም ትኩረት እየሰጠ በመምጣቱ እንደሆነ (Khatib and Rahimi (2012;32-38) ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ፣ስነጽሑፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም የሚለው ጽንሰ ሀሳብ እየታወቀ የመጣው በ19ኛው ክፍለ ዘመን ነው፡፡ ከዚያ በፊት የነበረው የቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ ስዋሰዋዊ የአቀራረብ ዘዴ የተከተለ ነበር፡፡ በዚህም ተማሪዎች የቀረበላቸውን ጽሁፍ ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋኣቸው በመተርጎም፣ቃላትና ስዋሰውን እንዲማሩ ይደረግ እንደነበር (Khatib and Rahimi :2012) በግልጽ ያስረዳሉ፡፡ በኋላ ግን፣ Khatib and Rahimi (2012) እንደገለጹት፣ የቋንቋ ትምህርት ወደ ተግባቦታዊ አቀራረብ በማዘንበሉ የተነሳ፣መዋቅራዊ አቀራረብና ቀጥተኛ እዝን አፋዊ /audio lingual method/ ዘዴዎች እየታወቁ መጡ ፡፡ ለዚህም ትኩረት ማጣት ምክንያት በወቅቱ ስነጽሑፍ በቋንቋ ማስተማሪያ መሣሪያነት መጠቀም ያለውን ሚና በተመለከተ ጥናቶች አጉልተው አለማሳየታቸው እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

ነገር ግን ከ1980ዎቹ ጀምሮ በስነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር የሚለው ፍላጎትና ተነሳሽነት እንደገና ተሻሽሎ እንደቀጠለ በማስረዳት፣ ይህ የሆነበትን ምክንያትም ስነጽሑፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለውን ሚና የሚያሳዩ በርካታ መጽሐፍት መታተማቸውን ተከትሎ እንደሆነ (Duff maley, 1991, Gower & pearson, 1986, Hill,1986, lazar, 1993 maley , Duff, Mcrae 1991)ን ዋቢ በማድረግ (Khatib and Rahimi, 2012) ያስረዳሉ፡፡

ከላይ የቀረቡትን አስረጅዎች ስንመለከት፣ ስነጽሑፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም የሚለው ጽንስ ሀሳብ መነሻው የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ ለንግግር ቋንቋ ማለትም፣ ተግባቦታዊ የቋንቋ አጠቃቀም ከፍተኛ ትኩረት እያገኘ በመምጣቱ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን በሌላ በኩል ደግሞ ቋንቋን ለማስተማር ስነጽሑፍን መጠቀም አለመጠቀም የሚለው ሀሳብ በወቅቱ አወዛጋቢ እንደነበረም (Khatib and Rahimi 2012) ገልጸዋል፡፡ ብዙዎቹ ቋንቋን እንደ ውጭ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን እንደሚሉት ስነጽሑፍ ራሱ ጥበብ እንደሆነና ይኸንን ጥበብ ለመረዳት ደግሞ ተማሪዎች በጥበቡ ላይ ያላቸውን ብቃት የሚጠይቅ ጉዳይ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

ይሁን እንጂ መምህራን ስነጽሑፍን በቋንቋ መማር ማስተማሩ ሂደት እንደ ክፍተት መሙያ አድርገው ይጠቀሙበት እንደነበር አመልክተዋል፡፡ ከዚህ በማያያዝ ስነጽሑፍ የተማሪዎችን የቋንቋ እውቀት እንደሚገነባ፣እንደሚያሰፋ፣ በትርጉም ወይም በፍቺ የበለጸገ መሆኑን (Povey, 1967, Pugh, 1989) ዋቢ በማድረግ (Khatib and Rahimi፣ 2012) አብራርተዋል፡፡

አስቀድሞ ከቀረቡት አስረጅዎች በመነሳት ስነጽሑፍን በቋንቋ ማስተማር ሂደት ውስጥ እንደማስተማሪያ መሣሪያ አድርጎ መጠቀም፣ከማስተማሪያ ዘዴዎች አቀራርብ መለወጥ ጋር ተያይዞ መምጣቱን እንገነዘባለን፡፡ ሂደቱም እንደየዘመኑ የጥናት አተያይ /አመለካከት/ ስነጽሑፍ በቋንቋ ትመህርት ውስጥ መጠቀም፣ አለመጠቀም የሚለው ጉዳይ በርካታ ክርክሮችን እያስከተለ ዛሬ የደረሰበት ደረጃ መድረሱን መረዳት ይቻላል፡፡

ስነጽሑፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም፣አለመጠቀም የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ ከመነሻው ያወዛገበ ቢሆንም፣ያለውን ጠቀሜታ ከተለያዩ ሁኔታዎች አንጻር በሰፊው የሚያብራሩም አሉ፡፡ በዚህም መሰረት የስነጽሑፍን ጠቀሜታ አጉልተው የሚያሳዩ ገለጻዎችን ስንመለከት፣ ስነጽሑፍ የሰው ልጅ ወግና ልማድ፣ባህል፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች የሚገለጹበት መሆኑ፣ የእውነተኛ ቋንቋ መገለጫና ሳቢ የንግግር ቋንቋ የሚቀርብበት፣ ሳቢነት ያለውና በባህል የበለጸገ መሆኑ፣ተማሪዎች ቋንቋን እንደ ውጪ ቋንቋ ወይም እንደሁለተኛ ቋንቋ ሲማሩ ከቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ጋር የበለጠ የሚያቀራርብና የሚያስተዋውቅ በመሆኑ የቋንቋ ትምህርት እንዲፋጠን የላቀ ድርሻ አለው በማለት (Hernandez :Noviembre: 2010) ያስረዳሉ፡፡

ስነጽሑፍ ተግባቦታዊ የቋንቋ አጠቃቀምን ያጎለብታል፣ይህም የሚሆነው ተማሪዎች በስነጽሑፍ ሥራ የቀረበላቸውን ጽንሰ ሀሳብ ወይም መልዕክት መሠረት በማድረግ እንዲከራከሩ፣የተለያዩ ቃለምልልሶችን እያደረጉ እንዲማሩ፣ ሲያስችላቸው ነው፡፡ ይህን በተመለከተ (Yeasmin, Azad, Ferdoush :December 2011)፣ (kramasch, 1993)ን ዋቢ በማድረግ ያስቀመጡትን ስንመለከት፣ ለተግባቦታዊ የቋንቋ አጠቃቀም ሲባል በስነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር፣ ተማሪዎች በቀረበው ጽሑፍ ዙሪያ ክርክሮች እንዲያደርጉ፣ እንዲጽፉና እንዲነጋገሩ፣ የተለያዩ ፍቺዎች እንዲያመነጩ በማስቻል፣የእርስ በእርስ መስተጋብራቸው የበለጠ ጎልቶ እንዲታይ ያደርጋል፣ በማለት ያብራራሉ፡፡

ከዚህ በተመሳሳይ ሁኔታ (Yeasmin, Azad, Ferdoush :December 2011) ፡ ( Alam 2007:381)ን ዋቢ በድረግ ያስፈሩትን ስናጤን ፣የስነጽሑፍ ይዘቶች የተማሪዎችን ምናባዊነት ያነሳሳሉ፣እውነተኛውን ቋንቋ እንዲጠቀሙ፣የቡድን ውይይቶች ላይ እንዲሳተፉ፣ ቃለ-ምልልሶችን እንዲያደርጉ እና የግል ስሜታቸውን እንዲገልጹ ያስችሉዋቸዋል በማለት አብራርተዋል፡፡ ከገለፃዎቹ የምንረዳው በስነጽሑፍ ይዘቶች ቋንቋን ስናስተምር የተማሪዎች ተሳትፎ የላቀ ይሆናል፤የሀሳብ መግለጽ ነፃነት ይኖራቸዋል፡፡ ማለትም የቋንቋ ትምህርቱ ላይ የተማሪዎች የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያስችላል፣ሀሳባቸውን እንዲገልጹም ሰፊ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ ይህም ተነሳሽነታቸውን የበለጠ ያሳድገዋል፡፡

የስነጽሑፍ ይዘቶች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች ማነቃቃትና ፣ማነሳሳት በተመለከተ፣ስነጽሑፍ በየሀገሮች ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው ጥበብ ነው፤ በመሆኑም ተማሪዎች በራሳቸው ቋንቋ ሰነጽሑፎችን የሚያነቡ ከሆነ ፣ወይም የማንበብ ልምድ ካላቸው እንደሁለተኛ ቋንቋ የቀረበን ስነጹሑፍ በማወዳደርና በማመሳሰል ሁኔታ በተነሳሽነት ያነቡታል፡፡ የትምህርቱ አቀራረብም ተማሪዎች አስቀድሞ በራሳቸው ቋንቋ የተለያዩ ቃላዊ ትረካዎችን እንዲናገሩ በማድረግ በሁለተኛ ቋንቋ የቀረቡላቸውን ትረካዎች እንዲያነቡ ሲደረግ የበለጠ እንደሚነሳሱ (Lazar,1993: 15) ይገልፃሉ ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ስነጽሑፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሚያሰርጻቸውን ስሜቶች በተመለከተ፣በድሉ (1996፣6-9) እንደገለጹት፣ ስነጽሑፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ክሂሎችን ለማጎልበት ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ተማሪዎች የስነጽሑፍ ሥራዎችን በተነሳሽነት ያነባሉ፣ሲነበብላቸውም በተመስጦ ያዳምጣሉ፣በአነበቡትና ባዳመጡት ነገር ላይ ተመስርተው ሀሳባቸውን ያንፀባርቃሉ፡፡ በንባባቸው ስለሕይወት የተለያዩ ገጽታዎች ግንዛቤ ያገኛሉ፡፡ በዚህም አዕምሮአቸው ጥልቅ አሳቢ ይሆናል፡፡ በዚህ ሂደት ተማሪዎች የባህሪ ለውጥን እንዲያመጡ ስነጹሑፍ የላቀ ሚና እንዳለው ያስረዳሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ቋንቋን በስነጽሑፍ ይዘቶች ማስተማር የተማሪዎችን የመገመትና ትርጓሜ የመስጠት ችሎታን እንዲዳብሩ ያስችላቸዋል፡፡ ምክንያቱም ስነ-ጽሁፋዊ ይዘቶች የተለያዩ ደረጃዎች ባላቸው ትርጉሞች የበለፀጉ በመሆናቸው አንባቢ ወይም ተማሪው በንቃት በመሳተፍ ፊት ለፊት ያልተገለጹ ነገሮችንም አውጥተው ማየት እንዲችሉ ያስችላቸዋል በማለት (Lazar, 1993 :19) ያብራራሉ፡፡

ከገለጻዎቹ የምንረዳው የስነ-ጽሁፍ ይዘቶችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም፣ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ለተማሪዎቹ

የመመራመርና አእምሮን የማስላት ሁኔታን ስለሚፈጥርላቸው በቋንቋ ትምህርት የበለጠ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንዲያገኙ የሚያስችል አቀራረብ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

የስነ-ጽሁፍ ይዘቶች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ስላላቸው ሚና ከተለያዩ አስረጅዎች አንፃር ባጭሩ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በማስከተል ደግሞ ይህ ጥናት ትኩረት ወደአደረገበት ከስነጽሁፍ ዘሮች ውስጥ አንዱ በሆነው በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር ከተማሪዎች አንብቦ መረዳት ጋር ያለውን ትስስር፣የተለያዩ ምሁራን ወይም አጥኝዎች የተመለከቱበትን ሁኔታ እንቃኛለን፡፡

እንደሚታወቀው አንብቦ መረዳት/ Reading Comprehension) ዋና የቋንቋ ክሂል ነው፡፡ አንብቦ መረዳት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰፊ ድርሻ አለው፡፡ አንብቦ መረዳት ሲባል፣ቋንቋን በአእምሮ መገንዘብ ብቻ ሳይሆን ቴክስቱ የሚያስተላልፈውን መልዕክት መረዳት፣መገንዘብ ነው በማለት (Ghasemi and Hajizadeh :2011) ያስረዳሉ ፡፡

ተማሪዎች ቋንቋን እንደ ውጪ ቁንቋ እና እንደሁለተኛ ቋንቋ ሲማሩ የአንብቦ መረዳት ብቃት ለማሳደግ የተለያዩ ምንባቦች ሊቀርቡላቸው ይችላሉ፡፡ ይህንን የአንብቦ መረዳት ብቃት ለማምጣት ደግሞ አጫጭር ልቦለዶች ቀዳሚውን ቦታ እንደሚይዙ እና ለዚህም ዋናው ተጠቃሽ ምክንያት የሚሆነው አጫጭር ልቦልዶችን ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ በሳቢነታቸው ስለሚማረኩ ነው፡፡ በቴክስቱ ውስጥ ባለው ሀሳብ የመስማማት፣ የመከራከር፣ የመረዳዳት፣የመነሳሳት ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፤ ተማሪዎች በላዕላይ ከተላለፈው መልዕክት ባሻገር በሚስጢር ያሉ ሀሳቦችንም ለመረዳት ትልቅ ጉጉት ያድርባቸዋል፡ በዚህም እርካታን ያገኛሉ፡፡ ሌሎች ስነ-ጽሁፍ ያልሆኑ ጽሁፎችን ሲያነቡ ግን የሚረዱት ቀጥታ ጽሁፉ ላይ ያለውን ሀሳብ ብቻ እንደሆነ (Ghasemi and Hajizadeh :2011) ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ በማያያዝ አጫጭር ልቦለዶች፣በባህሪያቸው ተዋቂነትና ዘመናዊነት ያላቸው መሆኑ፣ እንዲሁም በዓይነት የተለያዩ መሆናቸው፡፡ ለቋንቋ ተማሪዎች ሳቢ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፡፡ ለዚህም ዳረጃቸውን የጠበቁ ሥራዎች፣ ለክፍል ደረጃው በሚመጥን ሁኔታ መመረጥ እንዳለባቸው (Ghasemi and Hajizadeh:2011:69) ያስገነዝባሉ፡፡

ከዚህ ጋር በተመሳሳይ መልኩ ተማሪዎች አጫጭር ልቦልዶችን በሚያነቡበት ጊዜ ያልደረሱበትን ታሪክ ለማወቅ ሲሉ በከፍተኛ ተነሳሽነት ያነባሉ፡፡ ይህም ተማሪዎች ትረካውን በተመስጦ እንዲያነቡ ያስችላቸዋል፤ባነበቡት ነገር ላይም ምላሽ ይስጣሉ፡፡ እነዚህ መሰል

ተግባራት ስንመለከት ስነ-ጽሁፍ ክፍል ውስጥ ያለውን የመማር ማስተማር ሁኔታ ከተማሪዎች ህይወት ጋር ስለሚያስተሳስር ፣ተማሪዎች በንቁ መንፈስ እንዲከታተሉት ያደርጋል በማለት (lazar,1993:15) አስረዳሉ፡፡ ተማሪዎች የስነ-ጹሁፍ ምንባቦች ሲያነቡ፣ራሳቸውን በታሪኩ ውስጥ እንዳሉ በመቁጠር፣ እንዲተነብዩ ፣ ራሳቸውን ከታሪኩ ጋር እንዲያዋህዱና ስለአካባቢያቸው ያላቸውን አስተውሎት ከታሪኩ አንፃር እንዲያዩ በማድረግ፣ግላዊ ተሳትፎአቸው እንዲጉለበት ያስችላቸዋል፤በማለት (collie and Slater 1987፣ 6)ን ዋቢ በማድረግ (lazar, 1993 : 15) ያብራራሉ፡፡

Lazar (1993) በተከታታይ ከሰጡት ማብራሪያ መገንዘብ እንደሚቻለው አጫጭር ልቦለዶች የአንባቢን ስሜት የሚገዙ መሆናቸው፣ተማሪዎች ቀጣዩ ምን ይሆን በማለት በጉጉት ያነቡዋቸዋል፡፡ ሌላው በህሪያቸው ተዋቂነት፣ዘመናዊነትና የተለያዩ ዓይነት መሆናቸው ሳቢነታቸውን ያጎለዋል፡፡ ተማሪዎች አስደናቂና ዘመናዊ ትረካዎችን ማንበብ እንዲችሉ ሰፊ አማራጮችን ይፈጥርላቸዋል፡፡ በአነበቡት ነገር ላይ ተመስርተውም ከነባራዊው ዓለም ጋር በማስተሳሰር ጥያቂዎችን እንዲጠይቁ፣ እንዲወያዩ፣ እንዲከራከሩና ሰሜታቸውን እንዲገልጹ ያስችላችዋል፡፡ ስለሆነም እነዚህ የስነጽሁፍ አሃዶች ለክፍል ደረጃው በሚመጥን መልኩ እየተመረጡ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ቢካተቱ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የማመዛዘን ችሎታ እንደሚያሻሽሉ መረዳት ይቻላል፡፡

### 1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር

የዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ማስተማር፣አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣ ፣የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና መፈተሽ፤የሚል ነው፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢ ከመነሻዉ በተጠቀሰው ርዕሰ ጉዳይ ለማጥናት ያነሳሳው ምክንያት፣ በተከታታይ ለአስር አመታት በሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ትምህርት-ቤት እያስተማረ ባለበት ያስተዋለው የአንብቦ መረዳት ችግር መኖሩ ነው፡፡ ይህም ችግር፣አጥኚው በመማር ማስተማር ሂደት እንዳስተዋለው፣ የሁለተኛ ደረጃ (ከ9ኛ-10ኛ) ያሉት ተማሪዎች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የአማርኛ ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ ቃላትን በተቆራረጠ ድምጽ ፣አዝጋሚ በሆነ ፍጥነት በመታገል የሚያነቡ መሆናቸው ፣አንዳንዴም ድምጽ በማሰማት እንዲያነቡ ሲጠየቁ ፍቃደኛ አለመሆናቸውን ተገንዝቧል፡፡ በዚያው ልክ የአንብቦ መረዳት ጥያቂዎችን የመመለስ አቅማቸው ያነሰ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በመጸሐፉ ለቀረቡ የቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች የመተንበይና አጠቃላይ ሀሳብ የመስጠት አቅማቸው ዝቅተኛ መሆኑ፣ከምንባብ የወጡ የ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› ጥያቄዎችን እንዲሁ ‹‹እውነት›› ወይም‹‹ሐሰት›› በማለት ከመመለስ ባሻገር በምክንያት አስደግፈው እንዲመልሱ

ሲታዘዙ የተብራራ መልስ ለመስጠት ሲቸገሩ አስተውሏል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ጥልቅ ግንዛቤ የሚጠይቁ በአመስጥሮ ሊገኙ የሚችሉ ሃሳቦችን የመገንዘብ አቅማቸው ያነሰ መሆኑን አጥኝው አስተውሏል። ይህ ችግር ደግሞ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በሆኑ ተማሪዎች ላይ በተደጋጋሚ እንደሚታይ አጥኝው ተገንዝቧል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በተጠቀሰው ክፍል ውስጥ የተካተቱት ምንባቦች አብዛኛዎቹ በተለያዩ እውነታዎች ላይ ያተኮሩ እና ተማሪዎችን ለንባብ የማያነሳሱ መሆናቸውን አስተውሎዋል፡፡ አንብቦ የመረዳት ችግር በዘጠነኛ ክፍል በተለይም አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ጎልቶ እንደሚታይ አጥኝው አስተውሏል፡፡ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች አማርኛ ለማንበብ ተነሳሽነት ማነስና የአንብቦ መረዳት ችግር እንዴት ሊቃለል ወይም ሊፈታ ይችላል? የሚለው አጥኝውን ሲያሳስበው የነበረ ጥያቄ መሆኑ፣ለጥናቱ መነሻ ምክንያት ሆኑዋል ማለት ይቻላል፡፡ ከችግሩ አሳሳቢነት በመነሳትም አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችግር ለማቃለል የቋንቋ ትምህርቱ በአጭር ልቦለድ መሳሪያነት ቢሰጥ ችግሩ ሊቃለል ይችላል የሚል መላምት አጥኝው ነድፏል፡፡ በማስከተልም አጥኝው ይዞት ከተነሳው የጥናት መላምት ጋር የሚቀራረቡ ጥናቶችን ለመነሻነት ተመልክቱዋል፡፡

በመሆኑም በስነ-ጽሁፍ ቋንቋ ማስተማር በተመለከ በሪሃና (2007) "የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በስነ-ጹሁፍ ቋንቋን ሲያስተምሩ የሚጠቀሙባቸው አሃደች መምረጫ መስፈርት ፍተሻ በድሪዳዋ መሰተዳደር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት-ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዋቢነት" በሚል ርዕስ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናት እናገኛለን፣ የጥናቱ  ዋና ትኩረቱ መምህራን ወደ ክፍል የሚወስዱዋቸውን ተጨማሪ የስነ-ጹሁፍ አህዶች ምን ዓይነቶች እንደሆኑና አህዶችን የሚመርጡባቸው መስፈርቶችን መፈተሽ ነው፡፡ አጥኚዋ በዋናነት የተጠቀሙት የመረጃ መሰብሰቢያ መንገድ ምልከታና የጽሑፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተውም መምህራን በብዛት ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመርጡዋቸዉ የልቦልድ ድርስቶችን ሲሆን፣ መምህራን የስነ-ጽሁፍ አህዶችን ሲመርጡ ከተማሪዎች ሁኔታና ከመምረጫ መስፈረቶች አንፃር ሳይሆን ብዙውን ጊዜ በራሳቸው ልምድ በመመራት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር  መምህራን የስነ-ጹሁፍ አሃዶችን የማግኘት ችግር እንደሚያጋጥማቸውና በስነ-ጹሁፍ ቋንቋ ማስተማር በሚለው ጽንስ ሀሳብ ዙሪያም የግንዛቤ ችግር እንዳለባቸዉ አጥኛዋ አመላክተዋል፡፡

ከበሪሃና (2007) ጥናት መገንዘብ እንደሚቻለው መምህራን አብዛኛውን ጊዜ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ወደ ክፍል ውስጥ የሚወስዱት ልቦለዶችን እንደሆነ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት አቅራቢ ከስነ-ጽሑፍ አህዶች አጭር ልቦለድ ከአንብቦ መረዳት ጋር ያለውን ሚናና ተያያዥነት ለማጥናት መነሳሳትን ፈጥሮበታል፡፡

በተጨማሪም አማረ (2001) "ተራክቦአዊ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለዉ ተጽኖኦ ፍትነታዊ ጥናት" በሚል ርዕስ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናት መመልከት ይቻላል፡፡ የጥናቱ ትኩረት ተራክቦአዊ የማስተማሪያ ሞዴልን መጠቀም በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ሊያመጣ የሚችለውን ተጽዕኖ መመርመር ሲሆን፣ ተጠኝዎቹ በባህርዳር ከተማ መሰናዶ ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በተራ የዕጣ ንሞና መሰረት 40ተማሪዎች የቁጥጥር፣40ተማሪዎች ደግሞ የሙከራ ቡድን ሆነው የተመደቡ ሲሆን፣የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው መንገድ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ፣የሙከራ ቡድኑ ደግሞ የተራክቦአዊ ሞዴል ስልቶችን ለማስተማር በተዘጋጀው ሞዴል እንዲማሩ ተደርጉዋል፡፡ ጥናቱ የተከተለው መጠናዊ የአጠናን ሥልት ነው፡፡ በዚህም ፈተና፣ ምልከታ፣የጽሁፍና የቃል መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት አገልግለዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችም መጠናዊዎቹ፣በአማካይና በመደበኛ ልይይትና በቲ-ቴስት የተተነተኑ ሲሆን ዓይነተዊዎችም ጣልቃ እየገቡ በገለጻ ተተንትነዋል፡፡በጥናቱ ውጤት ላይ እንደተገለጸውም በተለመደው ዘዴ ከተማሩት ይልቅ በተራክቦአዊ መንገድ የተማሩት የላቀ የአንብቦ የመረዳት ውጤት እንዳመጡ ተገልጿል፡፡

ከአማረ (2007) ጥናት መገንዘብ እንደሚቻለው ተራክቦአዊ ሞዴል የተጠኝዎችን የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ሊያመጣ የሚችለውን ተጽዕኖ የሚመረምር ነው፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢ ከዚህ አስተውሎት በመነሳት በራሱ አካባቢ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች ቋንቋ በአጭር ልቦለድ አማካይነት ሲማሩ በአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ላይ ያለውን ሚና ለመመርመር ወስኗል፡፡

አጥኚው ይዞት ከተነሳዉ ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚዛመዱ የውጭ ጥናቶችንም ቃኝቷል፡፡ ይኸውም Mohamed Khatib and Atefeh Nasrollahi (2012) "በአጭር ልቦለድ ተጠቅሞ እንግሊዝኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን በማስተማር፣የአንብቦ መረዳት ችሎታን ማሻሻል" በሚል ርዕስ በኢራን የተጠና ጥናት እናገኛለን፡፡ ጥናቱ፣ ስነ-ጽሁፍ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ያለውን ጠቀሜታ በመግለጽ፣ በአጫጭር ልቦለዶች ቋንቋን ማስተማር ከአንብቦ መረዳት መሻሻል ጋር ያለው ዝምድና በሚለዉ ጽንሰ-ሀሳብ ላይ

በማተኮር ሙከራዊ ጥናት ያደረገ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴም ቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት ፈተና ነው፡፡ ፈተናውም እንግሊዝኛን እነደ ሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር ከተዘጋጁ የተለያዩ መጽሐፍት የተውጣጡ ምንባቦች የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ድምዳሜ መሰረትም በስነ-ጽሁፍ ይዘቶች በተማሩት ተማሪዎችና በተለመደው መንገድ በተማሩ ተማሬዎች መካከል የጎላ የአንብቦ መረዳት ልዩነት እንዳልታየ ተገልጿል፡፡ ጥናቱ በርግጥ የዚህ ጥናት አቅራቢ ይዞት የተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም በውጭ አገር የተጠና መሆኑ፣ የቦታና የጊዜ ርቀት ክፍተት እንዳለ ማስተዋል ይቻላል፡፡ ከዚህም ባሻገር በጥናቱ የተደረሰበት ውጤት እንደሚያመለክተው በሙከራ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል እምብዛም የአንብቦ መረዳት ብቃት ልዩነት እንደሌለ ነው፡፡ ነገር ግን የዚህ ጥናት አቀራቢ ርዕሰ ጉዳዩን በራሱ አካባቢ በማጥናት ያለውን ብዥታ አጥረቶ ማሳየት ተገቢ እንደሆነ በማመን ሙከራዊ ጥናት ለማድረግ መወሰን ችሉዋል፡፡

እላይ ካየነው በተጨማሪ ሌላም በውጭ የተጠና ጥናት እናገኛለን፣ይኸውም በ (Yeasmin, Kalam, Azad, Ferdoush; December 2011)"በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር ሂደት ተገቢ የክፍል ውስጥ ተግባቦትን ማደራጀት"በሚል ርዕስ የተጠና ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ በመጀመሪያ ደረጃ ስነ-ጽሁፈዊ ይዘቶች በቋንቋ ማስተማሪያነት ሲያገለግሉ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉዋቸዉ ያስረዳሉ፡፡ ዘርዘር አድርገው ለማሳየት እንደሞከሩት፣ አጫጭር ትረካዎች እና አጫጭር ልቦለዶች የእውነተኛ ቋንቋ አጠቃቀም ገጽታ ያላቸው፣ሳቢና የዘመኑን ሁኔታ የሚገልጹ፣ስሜት የሚገዙና ፈጠራን የሚያበረታቱ፣መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች ስሜታቸውን በመግለጽ በቡድን ውይይት ይሳተፋሉ፤ ተነሳሽነታቸውና የትምህርት ፍላጎታቸው ያድጋል፤ ከነበረባቸዉ ፍርሃትና ጭንቀት ይላቀቃሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡ ጥናቱም በመደምደሚያዉ እንዳመለከተው ስነ-ጽሁፋዊ ይዘቶች ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሲመረጡ የተማሪዎችን ፍላጎትና ደረጃ ባገናዘበ ሁኔታ መሆን እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

ጥናቱ ያተኮረው የስነ-ጽሁፍ ይዘቶች በተለይም አጫጭር ልቦለዶች ለቋንቋ ማስተማሪያነት እንዴት ይመረጣሉ? የክፍል ውስጥ አደረጃጀትና አተገባበር ምን ይመስላል? በሚለው ላይ ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው የስነ-ጽሑፍ ዘሮች በተለይም አጫጭር ልቦለዶች ለቋንቋ ማአስተማሪያነት መጠቀም የተማሪዎችን ስሜት በማነሳሳት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፤ በስሜት ተማርከው የተለያዩ ተግባራትን ስለሚፈጽሙ ከነበረባቸው ጭንቀትም እንደሚላቀቁ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን ጥናቱ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ

ብቻ በማተኮር አጫጭር ልቦለዶችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት በመጠቀም አንብቦ መረዳት ምን ያህል ማሻሻል እንደሚቻል የሚፈትሽ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ፣በመጀመሪያ ደረጃ የዚህ ጥናት አቅራቢ በተጨባጭ ከመነሸው ለመጠቆም እንደሞከው በመማር ማስተማር ሂደት ያስተዋለው የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችግር መኖር፣ ጥናት ለማካሄድ ዋነኛ አነሳሽ ምክንያት ሆኑዋል ማለት ይቻላል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የዚህ ጥናት አቅራቢ ባደረገው ፍተሻ መሰረት፣ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችግር ለማቃለል የተደረጉ ጥናቶች ቢኖሩም፣ማስተማሪያ ሞጁልን መሰረት ያደረጉ፣የስነ-ጽሑፍ ዘሮች ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡበንት መንገድ የተመለከቱ ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር የአንብቦ መረዳትን ችግር ለማቃለል ሌላም መንገድ ሊኖር ይችላል በሚል አነሳሽ ምክንያት፣ አጫጭር ልቦለዶችን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችግር ሊያቃልል ይችላል የሚል መለምት መንደፍ ተችሏል፡፡ ይህን መነሻ ሀሳብ መሰረት በማድረግ ይህ ጥናት የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት አድርጓል፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

### 1.3.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር፣ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና መፈተሽ ነው፡፡

### 1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

1. አማርኛ ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ማስተማር እና አማርኛ ቋንቋን በተለመደው መንገድ ማስተማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ተጽዕኖ መመርመር፣
2. አማርኛ ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ማስተማር አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣ በአንባቦ መረዳት ሂደት ሃሳብን ጠልቆ የመረዳትና የማመዛዘን ችሎታ ላይ ሊኖረው የሚችለውን ሚና መፈተሽ፣

## 1.4 የጥናቱ ጥያቄዎች

1. በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር፣ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣ የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ያለው ሚና ምን ያህል ነው?
2. ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ማስተማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ፍላጎት ላይ ያለው ተጽዕኖ ምንድን ነው?

3. አማርኛ ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ማስተማር ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ሂደት፣ ጥልቅ አስተሳሰብን ፣ማመዛዘንና የነገሮችን ምክንያታዊ ትስስር መረዳትን እንዲያዳብሩ ያለው ሚና ምን ያህል ነው?
4. በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር፣በአንብቦ መረዳት ሂደት፣ የተማሪዎችን ተራክቦና ክንዋኔ ለማበረታታት ያለው ሚና ምን ይመስላል?

### 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ለማስገኘት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡

1. አማርኛ ቋንቋን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ የሚሻሻልበትን ሁኔታ ምላሽ ለማስገኘት ያስችላል፡፡
2. ቋንቋን በአጭር ልቦልድ መሳሪያነት ማስተማር አማርኛ ቋንቋን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና በመረዳት መምህራንም ሆኑ ሥርዓተ-ትምህርት አዘጋጆች አቀራረባቸውን እንዲቀይሱ ያስቾላቸዋል፡፡
3. በሰነ-ጹሁፍ ይዘቶች ቋንቋን ማስተማር በተመለከተ ለሚነሱ ጥናቶች እንደመነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡

### 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር፣ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና መፈተሽ፣ በሚል ርዕስ የተጠና ነው፡፡ ጥናቱ በፓዊ ወረዳ በቀጠና ሁለት መንደር ሁለት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2008 ዓ.ም ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎችን ያካተተ ሲሆን፣ አማርኛ አፈ-ፈት የሆኑትን አልጨመረም፡፡ አጥኝው የቁጥጥር ቡድኑን በተለመደው መንገድ ያስተማረ ሲሆን፣ የሙከራ ቡድኑን ደግሞ ቋንቋን ለማስተማር  የተጠቀመው፣አጭር ልቦለድን እንጅ ሌሎች የስነ-ጽሑፍ ዘሮችን አይደለም፡፡ በዚህም አጭር ልቦለድ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አንብቦ መረዳት  ላይ ያለውን ሚና መርምሯል፡፡ በሌሎች ክሂሎች ማለትም በንግግር፣በማዳመጥና በመጻፍ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ተጽዕኖ  ትኩረት አላደረገም፡፡ ስለሆነም የጥናቱ ዋና ትኩረት በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር  አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ሚና፣ መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም  በተጠቀሱት ነጥቦች ምክንያት ጥናቱ ውስን ነው ማለት ይቻላል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት፤

### 2. ተዛማጅ ጽሑፎች

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር፤ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና መፈተሽ ነው። ይህን መሠረታዊ ጽንስ ሀሳብ ለማብራራት በትኩረት ነጥቡ ዙሪያ ያሉ ተዛማጅ ጽሑፎችን ለመዳሰስና ትንታኔ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል።

### 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

#### 2.1.1 በስነ- ጽሁፍ ቋንቋን የማስተማር አጀማመር፣

ስነ-ጽሁፍ ከመነሻው በቋንቋ ስርዓተ-ትምህርት ውስጥ ሊካተት የቻለባቸውን ክስተቶች እንደሚከተለው እንቃኛለን፡፡ የስነ-ጽሁፍ ትምህርት ይሰጥ የነበረው በኮሌጅ ደረጃ ሲሆን፣ ደራሲያን ራሳቸውን ለማዝናናትና ለማስደሰት ሲሉ ሰፊ ንባብ ያደርጉ እንደነበር (Hall, 2005) ያስገነዝባሉ፡፡ ከጊዜ በኃላ ግን ስነ-ጽሁፍ በኮሌጅ ደረጃ ብቻ ተወስኖ መቅረት የለበትም የሚል አመለካከት በመምጣቱ፣ ክላሲካል ስነ-ጽሁፍ በግሪክና በላቲን፤ በአብዛኛው ማዕከላዊ አውሮፓ የትምህርቱ አካል ሆኖ መስፋፋት ጀመረ፡፡ ይህ የስነ-ጽሁፍ መስፋፋት ዓላማው ቋንቋውን ዓለማቀፋዊ ባህሪ እንዲኖረው ለማድረግ ነበር፡፡ ይህ አመለካከት ወደ እንግልዝኛ ቋንቋም ተሸጋገረ፡፡ ይህ በመሆኑም በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት በነበረችው ሕንድ ወንድና ሴት ሰራተኞች እንግሊዝኛ ማንበብ እንዲችሉ ትምህርቱ በስነ-ጽሁፍ መሳሪያነት ይቀርብላቸው ነበር በማለት (Hall,2005) በዝርዝር አብራርተዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ (Hall, 2005) እንደገለጹት ፣በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በእንግሊዝ ዩኒቨርስቲዎች ስነ-ጽሁፍ ይሰጥ ነበር፡፡ ሂደቱ ቀጥሎ በ1980ዎቹ የእንግሊዝ የስነ-ጽሁፍ ትምህርት እስከ ታችኛው የህብረተሰብ እርከን ደረስ መሰጠት መቻሉን ያስረዳሉ፡፡ እንዲሁም ከቾምስኪ (1960) ዎች በኃላ የመጡ ምሁራን እንደሚያስረዱት፣ ደረቅ ሳይንስን ይከተል ለነበረው ስነ-ልሳናዊ ትምህርት ሰነ-ጽሁፍ እንደ እንግዳ ደራሽ ሆኖለታል በማለት (Hall, 2005) ያስረዳሉ፡፡ በሂደትም የእንግሊዝ ስነ-ጽሁፍ ስነ-ምግባርን የመቅረጽ፣ ፍላጎትን የማነሳሳት፣ እውቀትንና ሞራል የመገንባት፣ አመለካካትን የማስረዳት አገልግሎት ላይ በመዋሉ የበለጠ ሊስፋፋ ችሉዋል፡፡ በመሆኑም ስነ-ጽሁፍ የስዎችን ስሜት መያዝ መቻሉ፣ የንባብ ፍላጎትን ማሳደግ እንደሚያስችል (Hall, 2005) ፤ (palmer , 1965 ;65 )ን መሠረት በማድረግ አብራርተዋል፡፡

በተከታታይ ከቀረቡት ከHall (2005) ገለጽዎች እንደምንረዳው ፣ የስነ-ጽሁፍ ትምህርት በመጀመሪያ ተወስኖ የነበረው በኮለጅና በዩኒቨርስቲ ደረጃ ነው ፡፡ በዚህ ደረጃም በዘርፉ የተሰማሩ ደራሲያን ስፊ ንባብ በማድረግ የሚዝናኑበት ፣ የሚደሰቱበት ነበር እንጂ ወደ ብዙሃኑ ትምህርቱ አልተሰፋፋም ነበር፡፡ በኃላ ግን በተለይም ቀኝ ገዥ ሀገራት ቋንቋን ለማስፋፋትና ወደ ብሔራዊ ደረጃ የማሳደግ ፍላጎት መከሰት እና ቋንቋ ተናጋሪዎችም እንዲግባቡና ቋንቋን የበለጠ ማንበብ እንዲችሉ ሲባል በስነ-ጽሁፍ መሳሪያነት ትምህርቱ መጀመሩን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ TURKER (1991)‹‹ስነ-ጽሁፍ በቋንቋ ማስተማር ውስጥ›› በሚለው የጥናታቸው መግቢያ ላይ እንደገለጹት፣ በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር የሚለው ጽንሰ-ሀሳብ መነሻው መምህራን የውጭ ቋንቋን ለማስተማር አሰለቺና አድካሚ ከነበረው እዝነ አፋዊ ዘዴ ( Audio lingual method ) ተላቀው የተለየ ዘዴና ቴክኒክ ከመፈለጋቸው የተነሳ እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡ የስነ-ጽሁፍ ይዘቶችን መጠቀም እንደ

አዲስና ቀልጣፋ ዜዴ ተደርጎ መቆጠሩ 1950 ጀምሮ መምህራን ዘዴውን ሊጠቀሙበት ችለዋል፡፡ በዚህ ሂደትም ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ መሆን እንደጀመረ ያስረዳሉ፡፡ ተግባቦታዊ ዘዴም ለእውነተኛ ቋንቋ አጠቃቀም ከፍተኛ ትኩረት የሚስጥ፣ በተደራጀ ድግግሞሽ የታገዘ አቀራረብን የተከተለ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡

በአንጻሩ ደግሞ TURKER (1991 ) ፤ (Wddouson,1982 Topping, 1968 )ን መሠረት በማድረግ እንደአብራሩት፣ ስነ-ጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መካተት የለበትም የሚሉ እንዳሉ ያሳያሉ፡፡ ምክንያታቸውም፣ ስነ-ጽሁፍ ወጥነት ያለው ስዋሰው የለውም፣ የውጭ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ተግባራዊ ስዕብና የቋንቋ ብቃት ማምጣት አይችልም የሚሉ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ TURKER (1991)፤(Oster, 1985፡75) ን በመጥቀስ ስነ-ጽሁፍ የተማሪዎችን ስሜትና እስተሳሰብ መያዝ ስለሚችል በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለው አገልግሎት በአግባቡ መጠናት እንዳለበት ያብራራሉ፡፡ ነገር ግን ቀጥለው TURKER (1991 )፤ (povey,1967) ን ዋቢ በማድረግ ቋንቋን በስነ-ጽሁፍ ማስተማር የንባብ ልምድን እንደሚያዳብር ሰፊ ቃላትንና ውስብስብ መዋቀርን ማስገኘት እንደሚያስችል አክለው ገልጸዋል፡፡

ከላይ የ TURKER (1991)ን ማብራሪያዎች ስንመለከት መምህራን የውጭ ቋንቋን ያስተምሩበት ከነበረው አስለቺ ዘዴ ተላቀው ስነ-ጽሁፍን እንደቋንቋ ማስተማሪያ በመጠቀም በማነሳሳት ማስተማር መምረጣቸውን እናጤናለን፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በስነ-ጽሁፍ የማስተማር ሂደቱን የሚቃወሙ እንደነበሩ ተጠቁሙዋል፡፡ የመቃወማቸው ምክንያትም ስነ-ጽሁፍ ወጥነት ያለው ስዋሰው የለውም፣ ማለታቸው ከነበረው ዘዴ መላቀቅ አለመድፈራቸውን ማጤን ይቻላል፡፡ መጠነኛ ተቃውሞ ቢኖርም በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር ያለውን ፋይዳ በምክንያት የሚያስረዱም እንዳሉ ማየት ተችሉዋል፡፡ ስነ-ጽሁፍ የተማሪዎችን ስሜት ይቀሰቅሳል፤ በትምህርቱም ንቁ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ ስነ-ፁሁፍ የእውነተኛ ቋንቋ መገለጫ መሆኑ፣ ተማሪዎች በሕይወት ውስጥ የሚያስተውሉትን ነገር በክፍል ውስጥ በተመሳሳይ መልኩ ሲንፀባረቅ የተግባቦታዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ይመራቸዋል፡፡ ስነ-ጽሁፍ የንባብ ልምዳቸውን ከማሻሻሉ ባሻገር በውስጡ ሰፊ መድበለ ቃላትንና መዋቀርን ማስገኘቱ የስነ-ጽሁፍን ተፈላጊነት አጉልቶ እንደሚያሳይ መገንዘብ ይቻላል፡፡

Hill (1986) እንዳስቀመጡት ደግሞ ስነ-ጽሁፍን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መጠቀም አለመጠቀም የሚለው ጉዳይ ለበርካታ ጊዜ የትምህርት ተመራማሪዎችን ያከራከረ ጉዳይ እንደነበረ ያስረዳሉ፡፡ በማስከተልም በርካታ የተደረጉ ጥናታዊ ግምገማዎች፣ ስነ-ጽሁፍ

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ዋጋ ያለው ስራ መሆኑን ለማሳየት ሞክርዋል፡፡ ለዚህ ተቀባይነት የሚያበቁትን በሃሪያት አያይዘው እንደገለጹት፣ ስነ-ጽሁፍ ለተማሪዎች አጠቃላይ እውቀትን፣ የማሰብ ችሎታንና የማህበረሰቡን ሞራላዊ እድገት የሚያበለጽግ፣ ስሜትን መግለፅ የሚያስችል እና ዓለማቀፋዊነት ገፅታ ያለው መሆኑ፣ በቋንቋ ትምህርት የመካተቱን ጠቀሜታ አመልካች መግለጫዎች እንደሆኑ በመዘርዘር ያስረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር አጀማመር የሚለው መሰረታዊ ሀሳብ ጠቅለል ባለ ሁኔታ ሲታይ ፣ ከቅኝ ግዛት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ቋንቋን ለማስፋፋትና ተግባቦታዊ ተግባርን ለማስገኘት ሲባል የተከሰተ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በሂደቱ በርካታ የቋንቋ ተመራማሪዎች በቋንቋ ስርዓተ-ትምህርት ውስጥ መካተት አለበትና የለበትም በሚሉ መሠረታዊ ልዩነቶች ላይ የየራሳቸውን አሳማኝ ነጥቦች ዋቢ በማድረግ ተከራክረዋል፡፡ ይህም በስነ-ጽሁፍ ላይ የሚደረጉ ምርምሮች እንዲበራከቱና በስተኃላም ስነ-ጽሁፍ በቋንቋ ማስተማሪያነት የመዋሉ ጉዳይ የበለጠ ተቀባይነትን እያገኘ መምጣቱን ከላይ በተከታታይ ከቀረቡት አስረጂዎች መረዳት ተችሎዋል፡፡ ይህን በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር አነሳስ መቃኘቱ ዛሬ የስነ-ጽሁፍ ዘሮችን በዓይነታቸው በመለየት ለየትኛው የቋንቋ ክሂል መዳበር የበለጠ አስተዋፅኦ አላቸው ? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት መሠረት ሊሆን ይችላል፡፡

### 2.1.2 **ስነ-ጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ያለው ሚና (አስፈላጊነቱ)፣**

ስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ለማስተማር በስርዓተ-ትምህርት ውስጥ ሊካተት የቻለበትን ሁኔታ አጀማመሩን ለመቃኘት ተሞክራዋል፡፡ ቀጥሎም ደግሞ ስነ-ጽሁፍ ለቋንቋ ትምህርት ያለውን ሚና በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

#### 2.1.2.1 **ስነ-ጽሁፍ በእውነተኛ ቋንቋ የሚቀርብና ዋጋ ያለው መሆኑ፣**

ስነ-ጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለውን ሚና በተመለከተ Hall (1986 :1-2) እንደገለጹት ስነ-ጽሁፍ ቋንቋን የበለጠ ለመረዳት የሚረዳ፣ ስነ-ልሳናዊ ትምህርት ግባትን በመፍጠር ሰፊ ንባብ ለማድረግ ያስችላል፡፡ እውነተኛ የቋንቋ አውድን በመፍጠር ተማሪዎች በራሳቸዉ ጥረት በቋንቋው የመግባባት አቅማቸው እንዲያሳድጉ ያደርጋል፡፡ በቋንቋው ውስጥ የተለያዩ ቅርጾች በማስገኘት ተማሪዎች ለትምህርቱ እንዲነሳሱ እድል ይፈጥራልቸዋል በማለት ያስረዳሉ፡፡

ከገለጻው መረዳት እንደሚቻለው የስነ-ጽሁፍ ስራ በእውነተኛው አውድ መቅረብ ስለሚችል የተለያዩ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮችና የቋንቋ ቅርጾችን የማሳየት አቅም አለው ተማሪዎችም

በቀረበው አውድ መሠረት የተለያዩ ተግባራትን መስራት መቻላቸው በቋንቋው የመግባባት እድላቸውን ያሰፋዋል፡፡

ስነ-ጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ እውነተኛ አውድን መፍጠር መቻሉ በተለይም ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በቋንቋ ለመግባባት እንዲችሉ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ይህን አስመልክቶ Hall (1986 ፡1-3) ፤ Fowler (1971) ን በመጥቀስ ሲያስረዱ ' አፈ-ፌት ተናጋሪዎች ዘጠና በመቶ የሚሆኑ ቃላትን ከዕለት ከዕለት ማህበራዊ ግንኙነት ትርጉማቸውን ይረዳሉ፡፡ እንግዳ የሆኑ ቃላት በሚገጥማቸው ጊዜ ከቋንቋ ስነ-ልሳናዊ አገባብ ዙሪያ ትርጉሙን ለመረዳት ይጥራሉ እንጂ መዝገበ ቃላት ፍለጋ ላይሄዱ ይችላሉ በማለት ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን የውጭ ቋንቋ ተማሪዎች የተጠቀሰውን አይነት መስተጋብር ላያጋጥማቸው ይችላል፡፡ በመሆኑም ከሚቀርብላቸው አውድ የስዋሰውን እና የቃላት ትርጉምን ለመረዳት ይሞክራሉ፡፡ ስለዚህ ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች በቂና ሰፊ ለደረጃው የሚመጥን እውነተኛ አውድ ሊፈጥርላቸው ይገባል በማለት ያስረዳሉ፡፡ እውነተኛና ተማሪዎች ሊገነዘቡት የሚችሉት የትምህርት መሳሪያ፣ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እንዲሰሩ ያበረታታቸዋል፡፡ ተማሪዎች ከሚቀርቡላቸው የተለያዩ አውዶች የቋንቋ መዋቅርን፣ የቃላት አውዳዊ ፍቺን፣ በተለያዩ ሀረጋትና ዓርፍተ ነገሮች ያሉ ገለጻዎችንና ጽንስ ሀሳቦችን በነቃ መንፈስ ይከታተላሉ፡፡ ሰፊ የንባብ አጋጣሚም ይፈጥረላቸዋል በማለት (Hall, 1986 ፡7-8)፤ (Krashen, 1985)ን ዋቢ በማድረግ ያስረዳሉ፡፡

ከገለፃዎች ልንገነዘብ የምንችለው ነገር፣ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች አፈ-ፌት በመሆን ሊያገኙት ይችሉት የነበረውን ማህበራዊ አውድ በስነ-ጽሁፋዊ አውድ በመተካት የቋንቋ ትምህርቱን ለመረዳት እንደሚቻል ነው፡፡ የቋንቋ መዋቅርን የቃላት ፍቺን ሀረጋዊና ዓርፍተ ነገራዊ ገለጻዎችንና መልዕክትን ተጨባጭ ከማድረግ አንጻር ስነ-ጽሁፍዊ አውድን እንደግባት መጠቀም መሠረታዊ ጠቀሜታ እንዳለው ማጤን ይቻላል፡፡ ከዚህም ባሻገር ሰፊ የንባብ ልምድን ስለሚያስገኝ ተማሪዎች ከክፍል ውስጥ ተግባራት በተጨማሪ በራሳቸው ተነሳሽነት ከቋንቋው ጋር እንዲዋሀዱ ያስችላቸዋል፡፡

አስቀድመን ያነሳነውን ሀሳብ ለማጠናከር ስለ አውዳዊ አቀራረብ Lazar (1993) የሰጡትን ማብራሪያ ስንመለከት በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን መማር የቋንቋ ለመዳን ያፋጥናል፡፡ ተማሪዎች ልቦለዶችን በሚያነቡበት ጊዜ በትልሙ አወቃቀር ፣በገፀባህሪያቱ ሁኔታ በመሳብ ሰፊ ንባብ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ በሰፊ ንባባቸው ደግሞ የተለያዩ አዳዲስ ቃላትን የቋንቋ አጠቃቀሞችን እንደግብዓት ያገኛሉ፡፡ ይህን ተከትሎም ተማሪዎች ስሜታቸውን በመግለጽ ማለትም

በመናገር፣ በክርክር፣ ለቃላት ትርጓሜ በመስጠት ሲሳተፉ ቋንቋውን የመዋሃድ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥርላቸው ያስረዳሉ፡፡

ከ Lazar (1993) ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አውዳዊ አቀራረብ መኖር ቋንቋ ለመዳን ማፋጠን እንደሚችል ነው፡፡ ምክንያቱም ስነ-ጽሁፍ እውነተኛ ቋንቋ አጠቃቀም የሚንጸባረቅበት በመሆኑ ተማሪዎች በስነ-ጽሁፍ ይዘቶች ቋንቋን ሲማሩ የቋንቋው ተናጋሪዎች የሚጠቀሙባቸውን የአርፍተ ነገር አወቃቀር፣ የቃላት አጠቃቀምን ያገኛሉ፡፡ ይህን መሰል አውዳዊ ገጽታ፣ ተማሪዎች ከቋንቋው ተናጋሪዎች ጋር የበለጠ ማቀራረብ እንደሚችል መረዳት ይቻላል፡፡

በድሉ (1996) ስለ እውነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለውን ዋጋ አስመለክቶ የሰጠው ማብራሪያ ከላይ ያነሳነውን ሀሳብ ያጠናከራዋል፡፡ ይህም የስነ-ጽሁፍ ስራ ያለው ዋጋ የሚመዘነው ስለ ሰዎች መሰረታዊ ጉዳዮች የሚሰጠው መረጃ (ግንዛቤ) አንጻር የሚመዘን ነው፡

> በአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን የተፃፋት የሼክሲፒር ተውኔቶች ዛሬም ስለሰው ልጅ መሰረታዊ ባህሪያት የሚሰጡት መረጃ ከፍተኛ ነው፡፡ ዘመንና ባህል አያግዳቸውም ከተፃፋበት ባህልና ዘመን አድማስ ባሻገር ቅናትን፣ፍቅርን፣ጀግንነትን፣ስስትን ወዘተ. የመሳሰሉ የሠዎችን መሰረታዊ ባህሪያት በሕይወት ውስጥ የሚያስከትሉትን በጎና ክይሲ ለውጦች ያሳያሉ (በድሉ 1996፣12)፡፡

በአንጻሩ ሆን ተብሎ ለማስተማሪያ የሚዘጋጁ ምንባቦች ትኩረት የሚያደርጉት ለቃላት መረጣና ለዓረፍተ ነገር ግንባታ ስለሆነ ምንባቦቹ ትክክለኛ የቋንቋ ተናጋሪውን ለዛና እውነተኛ አገላለፅ አያሳዩም ፡፡ የስነ-ጽሁፍ ስራዎች ግን የሚያንጸባርቁት ሕይወትን በቋንቋ በመግለጥ መሆኑ ሆን ተብሎና ለማስተማሪያነት ከተዘጋጁ ምንባቦች ይለያሉ በማለት (በድሉ 1996፣11-13) በውል ያስረዳሉ፡፡ ከተሰጠው ማብራሪያ መረዳት እንደሚቻለው ስነ-ጽሁፍ የሚያነሳው የሰውን ጉዳይ ነው፡፡ ሰዋዊ በመሆኑም በየትም ዘመንና ቦታ የተገለጸና የተወሳ ጉዳይ ከዛሪው ዘመን ጋር የሚያስተሳስረው ባህሪ ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህ ባህሪም ስነ-ጽሁፍ እውነተኛ አውድን መሠረት ያደረገ የቋንቋ አጠቃቀም መገለጫነቱን ያስገነዝበናል፡፡ ከዚህ በመነሳት ስነ-ጽሁፍ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሲውል ከቦታና ከዘመን አንጻር የቃላትና የቋንቋ አጠቃቀምን ከተጨባጩ አውድ ጋር በማዛመድ ማቅረብ እንደሚያስችል እንረዳለን፡፡

በአጠቃላይ ስነ-ጽሁፍ የእውነተኛ ቋንቋ አጠቃቀምና ዋጋ ያለው ስራ ስለመሆኑና ይህም ሁኔታ ለቋንቋ ትምህርት በተለይም ቋንቋን እንደሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ

ተማሪዎች ዘንድ ያለውን ጠቀሜታ፣ የተለያዩ ድርሳናት የሰጡትን ማብራሪያ ለማቅረብ ተሞክሩዋል ። በቀጣይ ስነ-ጽሁፍ ከባህል ጋር ያለውን ተዛምዶ፤ እንዲሁም ቋንቋን ከማስተማር አንጻር ያለውን ሚና እንቃኛለን።

#### 2.1.2.2 **ስነ-ጽሁፍ በባህልና በቋንቋ አጠቃቀም የበለፀገ መሆኑ፣**

ቋንቋ የተለያዩ ነገሮችን ጠቋሚና አስተላላፊ መሳሪያ ነው። ይህውም የሰዎችን ልማድ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ይተላለፋበታል። እነዚህ ደግሞ የባህል መገለጫዎች ናቸው። ባህል በቋንቋ ይገለጣል ፤ የሰው ልጅ በልቦለድ፤ በግጥም ፤ በድራማ አማካኝነት በእውነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም ባህሉን ይገልጻል። ስለሆነም ባህል በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መካተቱ ፤ ቋንቋን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው አፋቸውን ከፈቱት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል በማለት (Hernandez, 2010) ያስረዳል። በእርግጥ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ባህል ይካተት አይካተት የሚለው ሀሳብ ለዘመናት ያከራከረ ጉዳይ ነበር፤ አሁን ግን መታሰብ ያለበት የመቅረቡ ጉዳይ ሳይሆን የሚቀርብበት መንገድ ነው። ይህ ሲባል ባህል እንደ አምስተኛ ክሂል ሆኖ ይሰጥ ሳይሆን ባህል ከመጻፍ፤ ከማንበብ፤ ከማዳመጥና ከመናገር ክሂሎች ጋር አውዳዊ ሚና እንዲኖረው አድርጎ ማቅረብ የሚቻልበት መንገድ መታሰብ አለበት የሚል ነው።

ከቀረበው ገለጻ መረዳት የሚቻለው የሕዝቦች ባህል በቋንቋ ይገለጣል፣ የተለያዬ ባህልን ለመግለጥ ሰዎች አጫጭር ታሪኮችን፤ ልቦለድን ግጥሞችና ድራማን ሊጠቀሙ ይችላሉ። የህዝቦች ባህል የተንጸባረቀባቸው የስነ-ጽሁፍ ስራዎች ለቋንቋ ማስተማሪያነት በሚቀርቡበት ጊዜ ለተማሪዎች የባህል እውቂያን ያስገኛሉ፤ ግንዛቢያቸው ይሰፋል። በዚህ ሂደት የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችና የሀሳብ አገላለጾችን፣ ትርጓሜ አሰጣጥን እንዲረዱ ሰፊ ግባትንና አውድን እንደሚፈጥርላቸው መገንዘብ ይቻላል።

ይህን ሀሳብ የሚያጠናክርልንን ገለጻ ቀጥለን እንመልከት፣ ባህል በሕዝቦች መካካል እውቂያን ማሳደጊያና የሰውን ስሜት የሚገዛና አነሳሽ ነው። ባህል ለቋንቋ ትምህርት ሲቀርብ ተማሪዎች የሚያዳብሩት ክሂል ፣ በሁለቱ ባህሎች መካከል ያለ ባህልን መተርጎም ተዛምዶዋቸውንና ግንኙነታቸውን በመመርመር ለመገንዘብ ያስችላቸዋል፤ አንዱ ከሌላው ጋር መስተጋብር እንዲፈጠርም ያደርጋል በማለት (Hernandez, 2010):(Tucker and Lamberu Samouar, Perter and Join)ን በመጥቀስ ያስረዳሉ። በማያያዝም የባህል እውቂያ ካለ ከሚነገረው ቃል በኃላ ያለውን መልዕክት መገንዘብ

ይቻላል፡፡ ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማር ዘዴ እንዲተገበር ባህል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል በማለት አስረድተዋል፡፡

ከማብራሪያው መረዳት የሚቻለው ባህላዊ ገጽታን የሚያንጸባርቁ የስነ-ጽሁፍ ስራዎች በሚቀርቡበት ጊዜ ተማሪዎች የራሳቸውን ባህል ከሚማሩበት የሁለተኛ ወይም የውጭ ቋንቋ ባህል ጋር እያገናዘቡ ተዛምዶኣቸውን የመመርመር የሚተላለፈውን መልዕክትም የመረዳት አቅማቸውም እየበረታ ይሄዳል፡፡ አንዱ የሌላውን ባህል ከራሱ ጋር እያመዛዘነ የተለያዩ የባህል መገለጫዎችን መረዳት ሲችል አንዱ ስለሌላው የሚገልጽውና ይህም በተራው የቋንቋ ትምህርቱ ተግባቦታዊ እንዲሆን ያግዛል፡፡ ሌላው ስነ-ጽሁፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት የመጠቀማችን ምክንያት ስነ-ጽሁፍ የባህል መገለጫ መሆኑ ነው፡፡ ስነ-ጽሁፍ የአንድ ማህበረሰብ ማህበራዊ፤ ፖለቲካዊ እና ታሪካዊ ሁነቶች ከተለያዩ አቅጣጫዎች ይንጸባረቁበታል፡፡ ልቦለዶች፣ አጫጭር ታሪኮች፣ ድራማዎችና ግጥሞች የህብረተሰብን ባህል በተለያዩ መንገዶች ይገልጻሉ፡፡ በተለይ ደግሞ ግጥም በተዘዋዋሪ መንገድ ከእውነታው ዓለም ጋር የተያያዘ ትርጉም እንዳለው (Lazar, 1993) : (Weiddowson,1984 ፣149) ን በመጥቀስ ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የስነ-ጽሁፍ ሥራዎችን በሚያነቡበት ጊዜ አውዳዊ እውቂያን ይፈጥርላቸዋል፤ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችንም ያስታውሳሉ በማለት (Lazar, 1993 ፣ 14-21) ማብራሪያ ሰጠዋል፡፡

ከ Lazar (1993 : 14-21) ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው፣ የአንድ ማህበረሰብ ባህል በተለያዩ የስነ-ጽሁፍ ዘሮች አማካይነት ይገለጣል ወይም ይተላለፋል፡፡ አንባቢ ባህልን በተለያየ መንገድ የሚያንጸባርቁ ልቦለዶችን፣ ታሪኮችን ፣ ግጥሞችና ድራማዎችን በሚያነብበት ጊዜ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችን ይገነዘባል፡፡ የባህል እውቂያን ይፈጥርለታል፡፡ የባህል እውቂያው በተራው የሚተላለፈውን መልዕክት አንባቢ በቀላሉ እንዲረዳው ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ስለ ባህል የሚያውሱ የስነ- ጽሁፍ ዘሮች ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሲውሉ ጠቀሜታቸው ዘርፈ ብዙ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በተመሳሳይ መልክ በድሉ (1996 ፤ 13-14 ) ስነ -ጽሁፍ ህብረተሰቡ ባህል ጋር ያለውን ትስስር ሲገልጽ፤ ስነ-ጽሁፍ የህብረተሰብ ባህላዊ እሴት ምንነቱ ይገለጽበታል ፡፡ የተናጋሪው አስተሳሰብ አለባበስና አመጋገብ፤ ጀግንነትና ድፍረት፤ ደስታና ሀዘን ምኞት ፍላጎቱን ያሳያል በማለት ያስረዳናል ፡፡ በተጨማሪም ስነ-ጽሁፍ በአንድ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሰዎች እንዴት ይኖሩ እንደነበረ፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች

በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስል እንደነበር ያሳያል በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከ በድሉ (1996 ፣ 13-14) ገለጻ መገንዘብ እንደሚቻለዉ፣ ባህል በቋንቋ ሲገለጥ አንባቢ ከዘመኑ እና ከእሱ አድማስ ውጪ የነበሩና ሊኖሩ የሚችሉ ሁነቶችን በቋንቋ አማካኝነት ይረዳል ፡፡ ባህልን ለማወቅና ለመረዳት በሚያደርገው ንባብ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችን፣ ገለጻዎችን፣ ይገነዘባል፡፡ የንባብ ክሂልንም ያዳብራል፡፡

በዚህ ንዑስ-ርዕስ ስነ-ጽሁፍ በባህልና በቋንቋ አጠቃቀም የበለፀገ ስለመሆኑ፣ ከዚህ ገጽታው በመነሳት ለቋንቋ ማስተማሪያነት ያለውን ፋይዳ በተመለከተ የተሰጡ ማብራሪያዎችን በአጭ ተመልክተናል፡፡ በመቀጠል ስነ- ጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሊከሰት የሚችለውን፣ የተነሳሽነትና የአሳታፊነት ሚና ለማብራራት ጥረት ተደርጓል፡፡

### 2.1.2.3 ስነ-ጽሁፍ መነሳሳትንና ተሳትፎን የሚያሳድግ መሆኑ፣

በቋንቋ ትምህርት ክፍል ጊዜ ውስጥ ስነ-ጽሁፍን ከምንጠቀምባቸው ምክንያቶች አንዱ ተነሻሽነትን ማስገኘት መቻል ነው፡፡ ተማሪዎች አፍ በፈቱበት ቋንቋ ለስነ-ጽሁፍ እውቀት ቅርብ ከሆኑ፣ ቋንቋን እንደውጭ ወይም እንደሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩበት ጊዜ ትምህርቱን ከራሳቸው ቋንቋ ጋር ለማዛመድ ይቀላቸዋል፡፡ ምክንያቱም ስነ-ጽሁፍ የእውነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም መገለጫ በመሆኑ ትምህርቱ በስነ-ጽሁፍ ይዘቶች አመካይነት ሲቀርብ ከራሳቸው ሕይወትና ልምድ ጋር በማመዛዘን የበለጠ ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ተማሪዎች ልቦለድን ሲያነቡ ከአዳዲስ ጭብጦችና አገላለጾች ጋር ተጋልጠ ይኖራቸዋል፡፡ በታሪኩም በመመስጥ በተነሳሽነት ስሜት እንዲያነቡ ያስችላቸዋል በማለት (Lazar, 1993 ፡ 14-21) ያስረዳሉ፡፡

እዚህ ላይ ለመግለጽ የተፈለገው መሠረታዊ ጉዳይ በቋንቋ ክፍል ጊዜ ውስጥ ስነ- ጽሁፍን መጠቀም መነሳሳትን እንዴት ሊከሰት ይችላል የሚለው ነው፡፡ የስነ-ጽሁፍ ስራዎች እውነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም ስለሚንፀባረቅባቸው ተማሪዎች አፍ ከፈቱበት ቋንቋ ጋር ለማመዛዘን ጥረት ያደርጋሉ፡ ከሕይወት ገጠመኞቻቸው ጋር በማስተሳሰር ማብራሪያ ይሰጣሉ፣ ማለትም ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች አጫጭር ትረካዎችን ፣ ልቦለዶችን ሲያነቡ ከአዳዲስ ጭብጦችና አገላለጾችን ሊያገኙ ስለሚችሉ፣ በተነሳሽነት በንባባቸው ይገፋሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

ስነ-ጽሁፍ ቋንቋን፣ እንደሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት ሲያገለግል ያለውን የቀስቃሽነት ዋጋ አስመልክቶ Hall (2005 : 47-48) ያስቀመጣቸውን ነጥቦች ስንመለከት፤ ስነ-ጽሁፍ የሰውን ጉዳይ የያዘ ፤ አነሳሽና አስደሳች መሆኑ፣ባህላዊ እውቀትን እና ልምዶችን የሚያስገኝ መሆኑ፣ስነ-ባህሪያዊ ስነ-ልሳን አኳያ ደግሞ የቋንቋ ቅርፅ ፣ንግግርና ትንታኔዎች መልዕክትን በአመስጥሮ የማግኘት ልምድን፣ በአወዛጋቢ ሁኔታዎች ላይ የሚተገብሩ መቻቻሎች፣ የመሳሰሉ ጥቅሞችን የያዘ መሆኑ ተመራጭ ያደርገዋል በማለት አስረድተዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ዝርዝር አድርጎ ያሳፈረውን ስንቃኝ ስነ-ጽሁፍ የቃላት ዕውቀትን ያሰፋል፤ ቋንቋ ለመዳን ያፋጥናል፤ አንደበተ ርዕቱ አንባቢ መሆንን ያጎለብታል ፤ የመተርጎም አመሳጥሮ መረዳትን ያዳብራል፤የባህል ለባህል መተዋወቅን ያስገኛል፤ ከስነ-ልሳን መዋቅር አንጻር ሊረሱ የማይችሉ አገላለጾችን ያስገኛል፡፡ በንባብ ሂደቱም ያዝናናል፤ ደስታን ይፈጥራል፤ በማለት ያብራራሉ፡፡

ከ Hall (2005:47-48) ገለጻዎች የምንረዳው ስነ- ጽሁፍ በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋዊ ጉዳይን በመያዙ ተማሪሪዎች ከራሳቸውን ሁኔታ አንጻር እያመዛዘኑ በተነሳሽነት እንዲያነቡ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ያስችላል፡፡ በተለይም በሁለትኛ ቋንቋ ትምህርት፣ የቋንቋውን ተናጋሪ በህል ወግና ልማድ እንድሁም የአገላለጽ ሁኔታዎች መረዳት ያስችላል፡፡ ስነ-ጽሁፍ እያስደሰተ፣ እያዝናና የቃላት እውቀት ማካበት ያስችላል፡፡ በጥቅሉ የቋንቋው ተነጋሪ ማህበረሰቦች ስሜት ለመረዳት ያስችላል፡፡የቋንቋው ተማሪዎችም የራሳቸውን ስሜት ለማንጸባረቅ ምቹ አውድን ይፈጥርላቸዋል፡፡ስለሆነም የክፍል ውስጥ ተግባራት በስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች ግባትነት መቅረባቸው የመማርማስተማሩን ሂደት ተጨባጭ፣ሳቢና አሳታፊ ሊያደርገው ይችላል፡፡

ስነ-ጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት የመካተቱን እስፈላጊነት ከብዙ ዓመታት በፊት Hill (1986 3-4); (Willbelm ran Humbold) የተናገረውን መሠረት አድርገው የሰጡትን ማብራሪያ ስንመለከት ደግሞ፣ ቋንቋን በአንዱ ወይም በአጭር ጊዜ ውስጥ ማውቅ አደጋች ነው፡፡ መሆን ያለበት ለቋንቋው ትምህርት ተሰማሚ አውድ እና ተግባቦታዊ ተግባራት ለማቅረብ የሚያስችል በተለይም ዳግሞ የሚያስደስት፣ የሚያዝናና የተማሪዎችን ስሜት መቆጣጠር መቻል እንዳለበት አብራርተዋል፡፡ አንባቢ፣ ምንም እንኳን የጽሁፉ ስነ-ልሳናዊ ሁኔታ ቢያስቸግረውም በቀጣይ ምን ይከሰት ይሆን በማለትና ሰዋዊ ጉዳዩችን ከራስ ጋር ለማመሳሰል በመሞከር በከፍተኛ ተነሳሽነት እንደሚያነብ (Hill, 1986: 5); (Reeves, 1986)ን በማስታወስ ይገልጻሉ፡፡ በማያያዝም (Hill, 1986; 5) አንዳንዴ ተማሪዎችን የሚቀሰቅሱ እና አስደናቂ የሆኑ አጫጭር ልቦለዶችን ሲያነቡ

ተነሳሽነታቸው የበለጠ እንደሚያደግ ያብራራሉ። ለምሳሌ፣ በታሪኩ ውስጥ ያሉት ገፀባህሪያት ጀግኖች ከሆኑ አንባቢዎች ባለታሪኩን በመከተል ምን ይከሰት ይሆን በማለት በጉጉት እንደሚያነቡት ያብራራሉ።

ከ Hill (1986) ገለጻዎች መገንዘብ እንደሚቻለው፣አንብቦ መረዳትን ለማዳበር የተማሪዎችን ተነሳሽነት የሚያሳድግ፣ ስሜታቸውን ተቆጣጥሮ የሚይዝ አውድ ማቅረብ ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ ነው። በተለይም ተማሪዎች አስገራሚና ቀስቃሽ የሆኑ ትረካዎች በሚያነቡበት ጊዜ በታሪኩ ውስጥ ያሉ ገጸባህሪያት ምንነትና የሚያጋጥማቸውን ነገር ለማወቅ በንባባቸው ወደፊት እንደሚገሰግሱ መገንዘብ ይቻላል። ይህ ዓይነት አቀራረብ ቋንቋን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማሳደግ፣ ተነሳሽነትን ለማዳበር የሚያስችል በመሆኑ ተመራጭነት ይኖረዋል ማለት ይቻላል።

ስነ-ጽሁፍ የተማሪዎችን ተሳትፎ በመጨመር ተነሳሽነታቸውን ከፍ እንዲል ያደርጋል። የተማሪዎች ተሳትፎ የሚጨምርበትን ሁኔታ (Lazar, 1993 ፡ 14-21) ሲያስረዱ፣ ስነ-ጽሁፍ ሰዋዊ ጉዳይ ስለሚንፀባረቅበት ሁሉንም ሰው ለማስተማር ያገለግላል። ሰዎች በአነበቡት ሀሳብ ላይ ተመርኩዘው የራሳቸውን ሀሳብ ሲገልጹ፣ በአነበቡት ላይ አስተያየት ሲሰጡ፣ የማመዛዘን፣ የመተርጎም ፣ መላምንቶችን የመንደፍ፣ መልዕክትን በአመስጥሮ የመረዳት ችሎታቸው ይዳብራል። የአስተሳሰብ አድማሳቸው ይሰፋል በማለት፣ ስነ-ጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለውን ሚና አብራርተዋል።

### 2.1.3 የአጭር ልቦለድ ምንነትና ባህርያት

አጭር ልቦለድ ፈጣን አተራረክ እና ድርጊት የሚታይበት፣ገጠመኞችን የያዘ አጓጊና ወደ አንድ አርኪ መቋጫ የሚደርስ እንደሆነ ዘሪሁን (2007) ቼኾቭንን በመጥቀስ ያብራራሉ። ከዚህ በማያያዝም ዘሪሁን (2007) አጭር ልቦለድ ከሌሎች የስነ-ጽሑፍ ዘሮች ተለይተው የሚታወቁበትን ባሕሪያት ሲገልጹ አጭር ልቦለድ ሰብሰብ ያለ ጥብቅ ጥስስር ያለው፣ እንዲሁም ብቸኛ የትኩረት ነጥብ ያለው መሆኑን አብራርተዋል። ከዚህ በማከልም አጭር ልቦለድ አካባቢንና ማህበረሰብን ለመረዳት ያስችላል በማለት ገልጸዋል። ትረካዎች ማለት ከመጠን አንጻር እስከ አምስት መቶ ቃላት የያዙ ትረካዎች ናቸው። አጫጭር ትረካዎች እስከ አስራ አምስት ሺህ ቃላት የሚደርስ የሚይዙ ከሆነ አጭር ልቦለድ ይባላሉ። አጫጭር ትረካዎች እንደ ቀልድ ቀላል የሆኑ ወይም ውስብስብነት ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። በእየለት ውሎዎቻችን የምናደርጋቸው ቃለ ምልልሶች፣ ውይይቶች በአጫጭር ትረካዎች የተሞሉ ናቸው ማለት ይቻላል። አጫጭር ትረካዎች

የተለያዩ ልምዶችን፣ ጽንስ ሀሳቦችን ለመናገር ያስችላሉ። ምናልባትም አጫጭር ትረካዎች ስንሰማቸው፣ ስናነባቸው ሊያስደንቁን ይችላሉ፤ በተለያየ ቦታና ጊዜ ስላሉ ሰዎች እንድናውቅ ያደርጋሉ። እንዲሁም የራሳችንን ሕይውት ከሌላው ጋር በማወዳደር ስለሕይወት የተለያዩ ፈርጆች ግንዛቤ ማስገኘት የሚያስችሉ ናቸው በማለት BACHMAN (1999) ስለ አጫጭር ትረካዎች ምንነት አብራርተዋል።

## 2.1.4 አጭር ልቦለድ አንብቦ መረዳትን ለማሻሻል ያለው ሚና፣

አጭር ልቦለድ እንደሌሎች የስነ-ጽሁፍ አህዶች ባህላዊ እውቂያን ፣ተነሳሽነትንና የቋንቋ እውቀት በማስገኘት የቋንቋ ትምህርቱን የበለጠ ያሳድጋል በማለት (Khatib and Nasrollahi, 2012፣241);Murdoch(2000)ን መሠረት በማድረግ ያስረዳሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ Krashen ( 2000 ) በሆንግ ኮንድ ባደረጉት የዳሰሳ ጥናት መሠረት የስነ-ጽሁፍ አሃዶቹን ያነበቡ ተማሪዎች ቃላትን የማንበብ ችሎታቸው እንደሚዳብር ይገልጻሉ። እንዲሁም Erkaya (2005 ); Young (1996) ን ዋቢ በማድረግ ተማሪዎች የስነ-ጽሁፍ ቴክስቶችን (ጽሁፎችን) ሲያነቡ የሚያገኙትን ጠቀሜታ ሲያብራሩ፣ ተማሪዎች የስነ-ጽሁፍ ቴክስቶችን ሲያነቡ ጥልቅ አሳቢ ፣ ተንታኝ ፣ ተመራማሪ፣ ፈጠሪና አመዛዛኝ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል።ማለትም አጫጭር ልቦለዶች ለአንባቢዎች ጥልቅ አሳቢነትን፣ተመራማሪነትን ያሰርጻሉ፤ይህሁኔታምለአእምሮአቸው ደስታን ስለሚፈጥርላቸው፣በንባባቸው እንዲቀጥሉበት መንገድ ይከፍትላቸዋል።

ከ Krashen ( 2000 ) ዳሰሳ ጥናት የምንረዳዉ ነገር፣ አጫጭር ልቦለዶች በቋንቋ ትምህርት፣ ከአንብቦ መረዳት ጋር የጠበቀ ትስስር እንዳላቸዉ ማጤን ይቻላል። ተማሪዎች ባነበቡት ነገር ላይ ተንተርሰው ከቃላት ዕውቀትና ባህላዊ ተረካው በመነሳት፤ መልዕክትን አንጥሮ ለመለየት የመጠየቅና የመመርመር ተግባርን ሲሰሩ፣ነገሮችን ከቀድሞ እውቀታቸው ጋር ሲያመዛዝኑ ፣ በታሪኩ በመሳብ ቀጣዩን ለማወቅ ወደፊት በመጓዝ ሲያነቡ፣ የአንብቦ መረዳት አቅማቸው በዚያው ልክ እንደሚያደግ መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ ላይ አንብቦ መረዳት ከለዕላይ መዕልክት እስከ ውስጣዊ ጥልቅ ምርምር ድረስ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ከችግሩ መነሻ ላይ እንደተጠቆመው የዚህ ጥናት አቅራቢ በሚሰራበት ትምህርት-ቤት አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ዋነኛ ችግራቸው አንብቦ መረዳት ነው ። የአንብቦ መረዳት ችግር ካለ ደግሞ ሌሎች ክሂሎችን ለመገንዘብ ወይም ለማዳበር የበለጠ ጫናን ይፈጥራል።

በዚህ ስራ ላይ Khatib and Nasrollahi (2012 ፤ 241 -242 ) ; Arigol (2001) የጠቀሰውን Hismanoglu,(2005) መሠረት በማድረግ አጭር ልቦለድ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚሰጠውን ጠቀሜታ ጠቅልል አድርገው አስቀምጠዋል፡፡ እነዚህም አጫጭር ልቦለዶች የተማሪዎችን የንባብ ተግባር ቀናና ቀልጣፋ እንደሚያደርጉ፣ ምክንያቱም ቀላልና አጫጭር በመሆናቸው፣ለሌሎች በህል የተሻለ እውቂያ መፍጠር መቻላቸው፣ በተጨማሪም አጫጭር ልቦለዶችና ታሪኮች ዓለም አቀፋዊ ባህርይ ስላላቸው ባህለ ብዙነት አስተሳሰብን እንዲያዳብሩ የሚያደርጉ መሆናቸውን ያስገነዝባሉ፡፡ በዋናነት ደግሞ አጫጭር ልቦለዶች ሳቢና ምናባዊ ዓለምን መፍጠር የሚያስችሉ መሆናቸው ተማሪዎች ትኩረት እንዲሰጡ፣ በጥልቅ እንዲያስቡ፣ ፈጣሪና ተንታኝ እንዲሆኑ ያደርጋሉ ፡፡ በዚህም ረገድ ተማሪዎች ፍረሃትና ጭንቀትን በማስወገድ የበለጠ ዘና ብለው እንዲማሩ እንደሚያስችሉ፣አጫጭር ልቦለዶች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ያለቸውን ድርሻ አጉልተው ለማሳየት ጥረት አደርገዋል፡፡

አጫጭር ልቦለዶች የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የአነባቦ መረዳት ችሎታ ከማጎልበት አንፃር የተዘረዘሩትን ጠቀሜታዎች ስናጤን፣ አጭርነታቸውንና ሳቢነታቸውን በመጠቀም የክፍል ውስጥ የንባብ ተግባራትን በተለያዩ አማራጮች አቀናጅቶ ለማቅረብ የሚያመቹ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ሳቢነታቸውና ለመተንተን የሚችሉ መሆናቸው፣ የተማሪዎችን ስሜት ገዝቶ የመያዝና በንባብ ላይ ሳይሰለቹ እንዲቆዩ ማድረግ ያስችላሉ፡፡ ተማሪዎች ተስበው በተነሳሽነት ወደንባቡ ከገቡ በኋላ ጽፍሁን በመተንተን፣በማመዛዘን፣ጥያቄ በመጠየቅ የተላለፈውን መልዕክት ለመረዳት ይጥራሉ፡፡

ከዚህ በመነሳት በጥልቀት የመረዳትና የመገነዘብ አቅማቸዉን ማሳደግ እንደሚያስችሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አንብቦ በመረዳት ሂደት ተማሪዎች ላይ ያለን አልችልም ከሚል ፍራሃት እንዲላቀቁ ማስቻላቸው አጫጭር ልቦለዶች በአንባቦ መረዳት ሂደት የላቀ ድርሻ እንዳላቸው ከቀረበው ገለጻ መረዳት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ስነ-ፅሁፍ ባህልን የሚያንፀባርቅ መሆኑና የሰውን ጉዳይ የሚዳስስ መሆኑ፣አንባቢው በጽሁፉ፣ ከቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያለውንም ሆነ፣በውጭው ዓለም መካከል የጠበቀ ትስስር እንዲኖር ያስችላል፡፡ ከዚህ አንፃር የአጫጭር ልቦለዶች ሚና ሲታይ ከአጠቃላይ ስነ-ጽሁፍ ባህሪ ጋር የሚመሳሰል ሆኖ የሚለዩበት ባህሪም አላቸው፡፡ እነዚህም ተደናቂነት፤ ዘመናዊነት፤ የተለያዩ አይነት መሆንናቸው በቋንቋ ትምህርት፤ተፈላጊ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል በማለት Ghasemi(2011) ያብራራሉ፡፡ በመሆኑም አጫጭር ልቦለዶች

ተማሪዎች፣ በጣም ጥሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣እንዲወያዩ ያደርጋሉ፡፡ ውይይት ሲያደርጉም በጽሁፍ ያገኙትን መልዕክት ከራሳቸው ዳራ ጋር በማገናዘብ ለመረዳት ይጥራሉ፤ በማስከተልም ሀሳቡን ከውጭው ዓለም ወይም ሁኔታ ጋር በማስተሳሰር ግንዛቢያቸውን እንዲያሰፋ መሰረት ይሆናሉ በማለት ያስገነዝባሉ፡፡

ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለው አጫጭር ልቦለዶች ከሌሎች የስነ-ጽሁፍ ዘሮች የሚለዩባቸው ባህሪያት ተደናቂነት፤ የዘመኑ ሁኔታ መግለጽ መቻልና የተለያዩ አይነት አማራጮች ያላቸው መሆኑ፣ ተገልጿል፡፡ ተማሪዎች በንቁ መንፈስ ኢንዲያነቡ ያስችላል፡፡ እንዲሁም ከራሳቸው የሕይወት ዳራና አጠቃላይ ስለ ህይወት የሚሰጡትን መልዕክት በማስተሳሰር ትርጉም ለመስጠት ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በማስከተልም ሰፊ ውይይት ለማድረግ እንደሚያስችሉ እንገነዘባለን፡፡

ለተሳካ አንብቦ መረዳት ችሎታ ዳራዊ እውቀት መኖር ማለትም የይዘት እውቀት ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው (Ghasemi, 2011፣266) ያስረዳል፡፡ ስለሆነም በንባብ ጊዜ ተማሪዎች ዳራዊ እውቀታቸውን መሰረት አድርገው ለአነበቡት ነገር ትርጓሜ በመስጠት መረዳት ያስችላቸዋል፡፡ አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት አጫጭር ልቦለዶች የተለያየ ሚና እንዳላቸው አስቀድሞ ለመጠቀም ተሞክሩዋል፡፡ በአሁኑም በተጨማሪ ማውሳት የሚቻለው፤ አጫጭር ልቦለዶች በአንብቦ መረዳት ተጽኖ ፈጣሪ አህዶች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ተማሪዎች አጫጭር ልቦለዶችን እያነበቡ በቀጥታ ባላዕላይ ፍቺ የተላለፈውን መልዕክት ይገነዘባሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የመረዳት አቅማቸው እየጠለቀ ሲሄድ ፊት ለፊት ያልተገለጡ ነገሮችን፤ መልዕክትን መረዳት የሚችሉበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህም ሁኔታ ተማሪዎች ከጽሁፍ የተለያዩ መልዕክተቶችን ለማግኘት ሲሉ ጽሑፎችን በከፍተኛ ተነሳሽነት እንዲያነቡ ያስችላቸዋል፡፡

አንብቦ የመረዳት ችሎታና የመጻፍ ችሎታ ስነ-ልሳናዊ ግዛቤ ብቻ አይደሉም፡፡ የጽሁፉን መልዕክት መረዳትን ይጠይቃሉ፡፡ ስለዚህ የይዘት ዕውቀት የቀረበውን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት አስፈላጊ ጉዳይ እንደሆነ (Ghasemi, 2011፣266) ፣ Hammadou ን በመጥቀስ ይገልጻሉ፡፡ በገለጻውም ለማስረዳት እንደሞከረው ዳራዊ እውቀት አንብቦ ለመረዳት ወሳኝ ነገር ነው፡፡ አንብቦ ለመረዳት ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር ቢኖር የይዘት እውቀት ነው፡፡ አንብቦ መረዳትን ለማሻሻል የሚያስችሉና የሚመቹ ደግሞ የስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች ናቸው፡፡ በተለይም ደግሞ ልቦለዶችን መጠቀም የተማሪዎችን የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ለማሻሻል ያስችላሉ በማለት ያስገነዝባሉ፡፡

አጫጭር ልቦለዶች(ትረካዎች) እምቅ የሆኑ የስነ-ጽሁፍ አሃዶች ናቸው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በግልጽ ያለንና ድብቅ ሆኖ የመጣን መልዕክት ለመረዳት በተነሳሽነት ያነባሉ፡፡ የሚነበበው ነገር የስነ- ጽሁፍ አሀድ ካልሆነ ግን ተማሪዎች የሚገነዘቡት ላዕለይ መልዕክትን ነው፡፡ የሥነ-ጽሁፍ አሀድ ያልሆኑ ጽሁፎች መልዕክትን በእምቅነት የማስተላለፍ አቅማቸው አነስተኛ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ አጫጭር ልቦለዶች ተነባቢ እንዲሆኑ ያስቻላቸው የሚለዩበት ባህሪያት ስላላቸው ነው፡፡ እነዚህም አጫጭር ልቦለዶች(ትረካዎች) ዓለማቀፋዊ ባህሪ አላቸው፤ የሚያስተላልፉት መልዕክት የተስፋፋና ከተጠቀሱበት ቦታ፤ጊዜና ሁኔታ አልፎ በሌላው ዘንድም ትርጓሜ መስጠት የሚቻልበት ደረጃ እንዳለ መረዳት ይቻላል፡፡ አጫጭር ልቦለዶች(ትረካዎች) የተለያዩ እና ሳቢ ናቸው፤ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችን የያዙና ለማንበብ ሳቢነት ያላቸዉ መሆኑን (Ghasemi, 2011) ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም የእውነተኛ የሀሳብ ልውውጥን መፍጠር የሚያስችሉ፤ አንባቢ እራሱን ከጽሁፉ ታሪክ ጋር በማስተሳሰርና ከራሱ ዳራ በማገናኘት መልዕክትን ለመረዳት የሚጥርበት እንጅ ፍዝ አንባቢ አያደርገውም በማለት (Ghasemi, 2011) ያስረዳሉ፡፡

ከላይ ያነሳነው ሀሳብ የሚያጠናክርልን፣ ብቁ የሆኑ አንባቢዎች የጽሁፉን መልዕክት ለመገንዘብ ሁለት ሂደቶችን መከተል እንደሚችሉ Ghasemi(2011) ፣ Knutson (19993)ን በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡ አንደኛው መንገድ ታች ላይ ሂደት bottom up process) ነው፡፡ ታች ላይ አንብቦ የመረዳት ሂደት አንባቢ እያንዳንዱ የጽፍን አካል በማገናኘት አጠቃላይ ትርጉምን ለመረዳት የሚቻልበት ስልት ነው፡፡ ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ላይ ታች (up bottom process) አንብቦ የመረዳት ሂደት ነው፡፡ በላይ ታች አንብቦ የመረዳት ሂደት አንባቢ ስለሚያነበው ጽሁፍ መላምት በመምታትና አስቀድሞ በመተንበይ ከዚያም ወደ ንባብ በመግባት ትርጉምን ለመረዳት ጥረት የሚያደርግበት ሂደት ነው፡፡ እነዚህን ሁለት ስልቶች በተመሳሳይ ጊዜ በመጠቀም የተሳካ ንባብ ማካሄድ ይቻላል፡፡ በእነዚህ ስልቶች አንብቦ መረዳትን ለማሻሻል አጫጭር ልቦለዶች(ትረካዎች) ስነ-ጽሁፍ ካልሆኑ ጽሁፎች የበለጠ ተስማሚ ናቸው፡፡ ቅድመ-ንባብ ተግባራትን በአጫጭር ልቦለዶች(ትረካዎች) ላይ መተግባር ይቻላል፡፡ እንዲሁም አጫጭር ልቦለዶች(ትረካዎች) ከርዕሳቸዉ ተነስቶ ለመተንበይ ፤ለመተንተን ተራኪ መዋቅር መኖሩ የላይ -ታች አንባቦ የመረዳት ሂደትን ያፋጥናል በማለት ያስረዳሉ፡፡

በተከታታይ ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለው፣በመጀመሪያ ደረጃ አጫጭር ልቦለዶች(ትረካዎች) ተራና ዋጋ የሌላቸው አይደሉም፡፡ ይልቁንስ የተለያዩ ሰዋዊ ጉዳዮችን

የያዙና ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸዉን ግንዛቢዎች የሚያስገኙ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህም ባሻገር ሳቢና ባጭር ጊዜ ውስጥ ሊነበቡ መቻላቸው፣እውነተኛ የሃሳብ ልውውጥ ስለሚከስቱ አንባቢ በንቃት እንዲወያይ፣ ሃሳብ እዲሰነዝር፣ እንዲከራከር ያስችላሉ፡፡ አጫጭር ልቦለዶች(ትረካዎች)በቂ ስነ-ልሳናዊ ቅርጽና የተለያዩ አገላለጾች ያካተቱ መሆናቸው፣አስደናቂ እና ከዘመኑ ጋር የሚሄዱ የተለያዩ ዓይነቶች መሆናቸው ሰዎችን ሙሉ ተሳተፊ ያደርጋቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት አንባቢ ፊትለፊት ከተገለጸው መልዕክት ጥላ ስር ነጥረው ሊወጡ የሚችሉ ትርጉሞችንም መገንዘብ ያስችላሉ፡፡ አንባቢ ከራሱ ዳራዊ እውቀትና ከዘመኑ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማስተሳሰር የራሱን ትርጓሜ ለመስጠት እንደሚያስችሉት መረዳት እንችላለን፡፡

አጫጭር ልቦለዶች(ትረካዎች) በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የመማሪያ ምንባብ ለማዘጋጀት ተመራጭ የሚያደርጋቸው ባህሪያትን Ghasemi(2011) ፣ (John povey)ን በመጥቀስ እንደገለጹት፣ በቀላሉ የሚዘጋጁና በተወሰነ የትምህርት ክፍለ ጊዜያት ሊቀርቡ መቻላቸው፣ በቅርብ የሚገኙ መሆናቸው፣ሳቢነታቸው፣ዘመናዊና የባህል ነጸብራቅ መሆናቸው እንደሆነ አስገንዝበዋል፡፡ እነዚህ የአጫጭር ልቦለዶች ገጽታዎችን በማጤን፣ በቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም አማርኛን እነደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችግር ሊያቃልሉ ይችላሉ ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

### 2.1.5 የአንብቦ መረዳት ምንነትና ስልቶች

እለት በዕለት ከምናደርገው የመማር ማስተማር ተግባር እንደምንገነዘበው ማንበብ መሰረታዊ ተግባር ነው፡፡ የተለያዩ ተግባራት ከንባብ እና አንብቦ መረዳት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ አንብቦ መረዳትን አስመልክቶ Texas education Agency (2002) እንደሚከተለው አብራርቷል፡፡ ማንበብ ለማንኛውም ትምህርታዊ ተግባር መሰረት ነው፤ የትምህርት ማዕከላዊ አካል ነው ማለት ይችላል፡፡ በትምህርት-ቤት በስራ ቦታ  በአጠቃላይ በህይወት ውስጥ ለዛሬም ሆነ ለወደፊት ህይወት ማንበብ ወሳኝ ነገር እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ በቴክሳስ ከ1996 ተጀምሮ የነበረውን የማንበብ ንቅናቄ መነሻ ሲጠቁም፣ በወቅቱ በአሜሪካ ፕሬዝዳነት የነበሩት ጆርጅ ደብሌው ቡሽ ‹‹ ማንኛውም ህፃን ማንበብን መማር አለበት›› የሚል አላማ አስቀምጠው እንደነበር ይገልፃል፡፡ ከዚህም በወቅቱ ለአንብቦ መረዳት ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱን መረዳት ይቻላል፡፡ አንብቦ መረዳት በማንኛውም የትምህርት ዘርፍ ውጤታማ ሆኖ ለመቀጠል መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን፣ በህይወት ውስጥ የተለያዩ መረጃዎችን በስፋትና በጥልቀት ለመገንዘብ፣ የተለያዩ ምርምሮችን ለማካሄድና የኑሮን አቅጣጫ ለመትለም አንብቦ መረዳት አብይ ትምህርታዊ ተግባር መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

ከቴክሳሱ ትምህርታዊ ኤጀንሲ ዓላማ መገንዘብ የሚቻለው አንብቦ መረዳት ከትምህርት አጀማመር ጀምሮ ተማሪዎች እያደጉ በሚሄዱባቸው የትምህርት እርከኖች ሁሉ ወሳኝ ትምህርታዊ ተግባር ነው ማለት ይቻላል፡፡ ስለሆነም አንብቦ መረዳት ችግር በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ጎልቶ ስለሚስተዋል አንብቦ፤ መረዳትን ለማሻሻል በመጀመሪያ አንብቦ መረዳትን ምንነትና ስልቶችን ማወቅና መተግበር መቻልን ይጠይቃል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ አንብቦ መረዳትን ሊያሻሽሉ የሚችሉ የማስተማሪያ ይዘቶችም እንድንመርጥም መንገዱን ሊያመቻች ይችላል፡፡

የቴክሳሱ ትምህርታዊ ኤጀንሲ (2002) በ1970ዎቹ የተጠና ጥናት ዋቢ በማድረግ እንደገለጸው፣ አንብቦ መረዳት ማለት አንድን የተሰጠ መመሪያ ወይም ቅደም ተከተል ጠብቆ የተሰጠ ተግባርን ሞልቶ መጨረስ ማለት እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የስነ-ልቦና የጥናት ቡድን፣ ስነ-ልሳን፣ የኮምፒዩተር ሳይንስ ተመራማሪዎች ትኩረት ያደረጉት አእምሮ እንዴት እንደሚሰራ፣ ሰዎች እንዴት እንደሚያስቡና እንደሚማሩ ይገልፃል፡፡ የስነ-አእምሮ ሳይንስ ትኩረት የሚያደርገው፣ አንባቢ ከሚያነበው ነገር ተነስቶ እንዴት ትርጉም መገንባት እንደሚቻል፣ የጥሩ አንባቢ አእምሮአዊ ተግባር ምንምን እንደሆነ ገልጿል፡፡ እንደ አንብቦ መረዳት አዲስ ጽንስ ሀሳብ አንብቦ መረዳት ውስብስብና የሚከተሉትን ትርጉም የመገንባት ተግባራት እንደሚያካትት አክሎ ገልጿል፡፡

- አንባቢው ከጽሁፉና አውዱ ጋር የመሄድና የመመርመር ተግባር መፈጸም፣
- አንባቢ ለሚያነበው ነገር ዓላማ ሊኖረው ይገባል፤ ከሚያነበው ነገር ላይ ትርጉም ለማደራጀት የተለያዩ የታቀዱ ስልቶችን ሊጠቀም ይችላል፣
- አንባቢ በአንድ ተግባር ላይ የተጠቀመበትን አንብቦ የመረዳት ስልት በሌላ በተለየ ምንባብ ላይ ሊተገብረው ይችላል፣

የቴክሳሱ ትምህርታዊ ኤጀንሲ (2002) ስለ ጥሩ አንባቢነት እንደገለፀው ጥሩ አንባቢዎች ቃላትን በትክክልና በፍጥነት ያነባሉ፤ የቃላትንና የሀረጋትን ትርጉም ይረዳሉ፡፡ የአንዱን ዓረፍተ-ነገር ትርጉም ከሌሎች ዓረፍተ-ነገሮች መልዕክት ጋር በማስተሳሰር መልዕክት ይገነዘባሉ፤ ዳራዊ እውቀታቸውን ተጠቅመው የጽሁፍን መልዕክት ያብራራሉ፡፡ እራሳቸውን ከጽሁፉ ጋር በማዋሃድ፤ ጥያቄ በመጠየቅ፣የወደፊቱን በመተንበይ፣ ስለ ጽሁፉ ሀሳብ በመሰንዘር መስተጋብር በመፍጠር ያለማቋረጥ ጽሁፉን ይመረምራሉ፡፡ ጥሩ አንባቢች ከራሳቸዉ ዓላማ ጋር የተሳሰረውን መርጠው ያነባሉ፡፡ ብዙ ጊዜ በምንባቡ ላይ ተጨማሪ ትርጉም ይሰጣሉ፤ምዕናባዊ ምስል ይፈጥራሉ፤የማንብ ስልቶችን ይጠቀማሉ በማለት

ያስረዳል። በአንጻሩ ጥሩ ያልሆኑ አንባቢዎች ለንባባቸው ስልት የላቸውም፤የአእምርአዊ ተግባር እውቂያና ስለሚያነቡት ነገር የተደራጀ ግብ የላቸውም። ባልቀለጠፈ ፍጥነት ያነባሉ በዚህ የተነሳ ሀሳብን የመያዝና የመገንዘብ ችግር ይፈጠርባቸዋል በማለት ያስረዳል።

ባጠቃላይ በተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ስር በመጀመሪያ ደረጃ ስነጽሑፍ ለቋነቋ ትምህርት ለመጠቀም የተቻለባቸውን ክሰተቶች ሂደትና በሌላ በኩል ደግሞ ስነጽሑፍን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ አለመጠቀም የሚሉና የነበሩ ወዝግቦችን ለማሳየት ጥረት ተደርጓል። በማስከተልም ስነጽሑፍን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የመጠቀም አስፈላጊነትን አጉልተው ያሳዩ ስራዎችን በመጥቀስ ለማብራራት ተሞክሩዋል። ከዚህም ባሻገር ከስነጽሁፍ ይዘቶች ውስጥ አጭር ልቦለድን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መጠቀም ያለውን ጠቀሜታና የተማሪዎችን አንብቦ የመረት ችሎታ ጋር ያለውን ተያያዥነት ያነሱ ጥናቶችን ለመቃኘት ጥረት ተደርጓል። ከዚህ በማስከተል ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር በተቀራረበ ሁኔታ የተሰሩ ጥናቶች ተቃኝታዋል፤ተዳሰዋል።

## 2.2. ተዛማጅ ጥናቶች

በዚህ ክፍል የዚህ ጥናት አቅራቢ ይዞት ከተነሣው የጥናት ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተለያዩ ሁኔታዎች ሊዛመዱ የሚችሉ ስራዎች ተቃኝተዋል። ቅኝቱ መሰረት ያደረገባቸው ነጥቦችም ከጥናት ርዕስ ፣ የጥናት አካላዮች፣የጥናት ዘዴ፣ ከመረጃ መሰብሰቢያዎችና ከጥናት ውጤቶች አንጻር አንድነትና ልዩነትታቸውን በመዳሰስ ያለውን ክፍተት መሙላት ላይ ነው።

በኢትዮጵያ የተጠኑ ጥናቶችን ስንፈትሽ፣አንብቦ መረዳትን በተመለከተ የተሰራ ጥናት እንድሪስ(2000)ን እናገኛለን። የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ “የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን መማር በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ዉስጥ አንብቦ መረዳት ትምህርት ዉጤት ጋር ያለውን ዝምድና መፈተሽ ” የሚል ነዉ። ጥናቱ የተጠናው በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በፓዊ ወረዳ በቀጠና ሁለት መንደር ሁለት ከፍተኛ ሀለተኛ ደረጃ ትምርህርት-ቤት አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው። ጥናቱ የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድን በማለት በሁለት የተከፈለ ሲሆን የተጠቀመባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችም ቅድመና ድህረ-ልምምድ ፈተና፣ መጠይቆች፣ጽብረቃና የዕለት ማስታወሻዎች ናቸው። አንብቦ የመረዳት ስልቶችን ለማስተማር ስነ-ጽሁፋዊ የሆኑና ያለሆኑ ምንባቦችንና የተለያዩ ቅንጫቢዎችን ተጠቅሟል።

የእንድሪስ(2000) ጥናት ዋና ትኩረት የእንብቦ መረዳት ስልቶችን ማስተማር የአንብቦ መረዳት ችሎታን ሊጨምር ይችላል የሚል መላምት ይዞ የተነሳ ሲሆን የዘህ ጥናት አቅራቢ ደግሞ በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ሚና የሚል ነው፡፡ ስለሆነም የሁለቱ ጥናቶች አቀራረብ ላይ ልዩነት እንዳለ ማስተዋል ይቻላል፡፡ ማለትም እንድሪስ (2000) የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማሳደግ ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን መማር አለባቸው የሚል መላምት መሰረት አድርጎ ያጠና ሲሆን፣ የዚህ ጥናት አቅራቢ ደግሞ በአጭር ልቦለድ ቋንቋ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችግር ሊያቃለል ይችላል የሚል መላምት በማያዝ አጥንቷል፡፡ በዚህም ረገድ ሁለቱም ይለያያሉ፡፡ የአጠናን ዘዴያቸዉ በዋናነት መጠናዊ የአጠናን ስልትን የተከተለ መሆኑ፣በሙከራ ላይ የተመሰረተ ፈተናን ወሳኝ የመረጃ መሰብሰቢያ አድርገው የሚጠቀሙ መሆናቸው ያመሳስላቸዋል፡፡ የእንድሪስ (2000) የጥናት ውጤትም የአንብቦ መረዳት ስልቶችን የተማሩ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ስልቶችን ካልተማሩት ተማሪዎች የተሸለ ውጤት እንዳመጡ አሳይቷል፡፡

በቀጣይነት በመሰረት (2007)‹‹በአንከሻ ወረዳ በሚገኙ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ክሂል የትምህርት አቀራረብ ቅኝት››በሚል ርዕስ ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናት እናገኛለን፡፡ በመሰረታዊነት መምህራን ለማንበብ ክሂል የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል ነው? አቀራረባቸውስ ምንይመስላል? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የተሰራ ነው፡፡ በዋናነት ጥቅም ላይ የዋሉት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ለመምህራን የቀረቡ የጽሁፍ መጠይቆችና ምልከታ ሲሆኑ የጥናቱ ውጤትም መምህራን ለማንበብ ክሂል ዝቅተኛ ትኩረት መስጠትና ለዚህም ሌሎች ተጽዕኖ አድራሽ ጉዳዮች እንዳሉ ተገልጿል፡፡

ከተሰጠው ማብራሪያ እንደምንመለከተው፣የመሰረት (2007) ጥናት ገላጭ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን፣ የዚህ ጥናት አቅራቢ ደግሞ መጠናዊ የአጠናን ዘዴን የተከተለ በመሆኑ ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የዚህ ጥናት አቅራቢ አጭር ልቦለድን እንደ ቋንቋ ማስተማሪያ በመጠቀም በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ላይ ሊያመጣ የሚችለውን ተጽዕኖ የሚፈትሽ ነው፡፡ የመሰረት (2007) ጥናት ደግሞ የንባብ ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበርን የሚመለከትና የሚገልጽ መሆኑ የአካሄድና የዓላማ ልዩነት አላቸው፡፡

በወይንሸት(2007) የተሰራ ጥናት ስንቃኝ ደግሞ “መህበረ-ስሜታዊ ብልሃት የአማርኛን ቋንቋ እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ላይ የአንብቦ መረዳት ችሎታን እና የማንበብ

ፍላጎትን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና" በሚል ርዕስ  በጫንጮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት-ቤት በዘጠነኛ ክፍል ላይ የተሰራ ጥናት እናገኛለን፡፡ መረጃዎች በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ ተሰብስበዋል፡፡ የጥናቱ ውጤትም መህበረስሜታዊ ብልሃት የተማሪዎችን የንባብ ፍላጎት በመጨመር የአንብቦ መረዳት ችሎታን በማሻሻል ረገድ አዎንታዊ ሚና እንዳለው ተገልጿል፡፡ እዚሁላይ ወይንሸት(2007) ፣ አድማስ(2006) የሰጡትን ትንታኔ መሰረት በማድረግ ያቀረቡትን ገለጻ ስንመለከት፣ ማህበረስሜታዊ ብልሃት፣ የሰው ልጅ በቋንቋ አማካንነት መስተጋብር ሲፋጠን ሀሳብን ያለ ፍርሃት  የመግለጽ ሁኔታ ይዳብራል፤የቋንቋ ችሎታም ይሸሻላል በማለት ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም ማህበረስሜታዊ ብልሃት የተማሪዎችን ፍርሃት በማስወገድ በመማር ማስተማሩ ሂደት ኃላፊነት እንዲወስዱ እንደሚያስችላቸው አብራርተዋል፡፡

የዚህ ጥናት አቅራቢ እንዳስተዋለው የመሰረት(2007) የጥናት ትኩረት የንባብ ክሂል አተገባበር ላይ ሲሆን ለኪህሉ ማስተግበሪያ ሊቀርቡ ስለሚችሉ ግባቶች አልጠቀሰም፡፡ እንዲሁም የወይንሸት(2007) ጥናት ስንመለከት ማህበረ-ስሜታዊ የአቀራረብ ስልት  አንብቦ መረዳትን እንደሚያሻሽል ተገልጿል፡፡ እዚህ ላይ ማህበረ-ስሜታዊ መስተጋብር ለመፍጠር የሚያስችሉት የተማሪዎችን ስሜት የሚስቡና ተነሳሽነትን ሊፈጥሩ የሚችሉ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት አቅራቢ አጭር ልቦለድን ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሊያሻሽል ይችላል የሚለውን መላምት ለመፈተሸ መነሻ ምክንያት ሆኑዋል ማለት ይቻላል፡፡

በሪሃና(2007)"የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በስነ-ጹሁፍ ቋንቋን ሲያስተምሩ የሚጠቀሙባቸው አሃዶች መምረጫ መስፈርት ፍተሻ በድሪዳዋ መስተዳደር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዋቢነት" በሚል ርዕስ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናት እናገኛለን፣ የጥናቱ  ዋና ትኩረት መምህራን ወደ ክፍል የሚወስዱዋቸውን ተጨማሪ የስነ-ጹሁፍ አህዶች ምን ዓይነቶች እንደሆኑና አህዶችን የሚመርጡባቸው መስፈርቶችን መፈተሽ ነው፡፡ አጥኚዋ በዋናነት የተጠቀሙት የመረጃ መሰብሰቢያ መንገድ ምልከታና የጽሑፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተውም መምህራን በብዛት ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመርጡዋቸው  የልቦልድ ድርስቶችን ሲሆን፣ መምህራን የስነ-ጽሁፍ አህዶችን ሲመርጡ ከተማሪዎች ሁኔታና ከመምረጫ መስፈረቶች አንፃር ሳይሆን ብዙውን ጊዜ በራሳቸው  ልምድ በመመራት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም አማረ (2001) "ተራክቦአዊ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተጽዕኖ ፍትነታዊ ጥናት" በሚል ርዕስ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናት መመልከት ይቻላል። የጥናቱ ትኩረት ተራክቦአዊ የማስተማሪያ ሞዴልን መጠቀም በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ሊያመጣ የሚችለውን ተጽዕኖ መመርመር፣ በተራ የዕጣ ንሞና መሰረት 40ተማሪዎች የቁጥጥር፣40ተማሪዎች ደግሞ የሙከራ ቡድን ሆነው የተመደቡ ሲሆን፣የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው መንገድ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ፣የሙከራ ቡድኑ ደግሞ የተራክቦአዊ ሞዴል ስልቶችን ለማስተማር በተዘጋጀው ሞዴል እንዲማሩ ተደርጉዋል። ጥናቱ የተከተለው መጠናዊ የአጠናን ሥልት ነው። በዚህም ፈተና፣ ምልከታ፣የጽሁፍና የቃል መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት አገልግለዋል። የተሰበሰቡት መረጃዎችም መጠናዊዎቹ፣በአማካኝና በመደበኛ ልይይትና በቲ-ቴስት የተተነተኑ ሲሆን ዓይነተዊዎችም ጣልቃ እየገቡ በገለጻ ተተንትነዋል። በጥናቱ ውጤት ላይ እንደተገለጸውም በተለመደው ዘዴ ከተማሩት ይልቅ በተራክቦአዊ መንገድ የተማሩት የላቀ የአንብቦ የመረዳት ውጤት እንዳመጡ ተገልጿል።

ወርቁ(2000) " የሥነጽሑፍ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት አተገባበር በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች " በሚል ርዕስ በባህርዳር ዩኒቨርስቲ ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናት እናገኛለን:: ተጠኝዎቹም በባህርዳር ከተማ በጣና ሀይቅና በፋሲሎ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣በ1999ዓ.ም አማርኛ ቋንቋን ከዘጠነኛ እስከ አስረኛ የሚያስተምሩ መምህራን ናቸው። እንዲሁም የሁለቱ ክፍሎች መማሪያ መጽሐፎች፣ መርሃ-ትምህርቶችና በ1999ዓ.ም የሁለተኛ መንፈቀ ዓመት የማጠቃለያ የክፍል ፈተናዎች ሌሎቹ ተጠኞዎቹ ናቸው። ወርቁ(2000) የተጠቀመባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችም ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ፣ሰነድ ምርመራና ፈተናዎች ሲሆኑ የተከተለው የመረጃ መተንተኛ ዘዴም ገላጭ፣ ቅኝታዊና ገምገሚ ስልትን ነው። በመጨረሻም በጥናቱ ውጤት እንዳስቀመጠው፣ ስነጽሑፍን ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት በመጠቀም ረገድ በመርሀ-ትምህርቶችና በመማሪያ መጽሐፎች መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት እንደሌለ፣ በመጽሐፎች ውስጥ የተካተቱት የስነጽሑፍ ዘሮች ስነጽሑፍን ከማስተማር ያለፈ ዓላማ እንደሌላቸው፣ስነጽሑፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት በመጠቀም ረገድ በመምህራን ላይ የእውቀት ክፍተት መኖሩን ገልጿል። ከቀረበው ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው ወርቁ(2000) የስነ-ጽሁፍ ዘሮች ያላቸውን አተገባብርና ለምን ዓላማ እንዳገለገሉ መገመገም ሲሆን፣ የዚህ ጥናት አቅራቢ ደግሞ ከስነ-ጽሁፍ ዘሮች ውስጥ በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር፣አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በሆኑ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ሊያመጣ የሚችለውን ተጽዕኖ መፈተሽ ነው።

በአጠቃላይ በእነዚ ዳሰሳዎች መሰረት የስነ-ጽሁፋዊ ይዘቶች አቀራረብና አተገባበር ትኩረት እንደተሰጠው ማየት ተችሏል፡፡ ሌላው ደግሞ የንባብ ክሂልና አንብቦ መረዳት ላይ ሰፊ ዳሰሳ መደረጉን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው በተማሪዎች ላይ አንብቦ የመረዳት ችግር አሁንም በተለያዩ አካባቢዎችና የክፍል ደረጃዎች ላይ ያለ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት የዚህ ጥናት አቅራቢ በተማሪዎች ዘንድ የሚታየውን አንብቦ የመረዳት ችግር ለማቃለል፣ቋንቋን አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ማስተማር በአንብቦ መረዳት ላይ ያለውን ተጽዕኖአ ፈትሿል፡፡

ከአጥኚው ርዕሰ ጋር በተዛመደ መልኩ በውጭ ሀገር የተጠኑ ሰራዎችን ስንቃኝ የ (Yeasmin, Kalam, Azad, Ferdoush 2011)ን እናገኛለን የጥናቱ ዓላማ ስነ-ጽሁፍ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ያለውን ውጤታማነት ማሳየት ነው፡፡ጥናቱ መሰረት ያደረገው በብሪታኒያ መማክርት "የአንባቢዎች እድገት ፕሮግራም" የሚለውን አቅጣጫ የተከተለ ነው፡፡ ጥናቱ የተሰራው በባንግላዲሽ ነው፡፡ ጥናቱ በዓላማው መሰረት በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር መካከል ያለውን የክርክርና ስምምነት ሁኔታ መርምሯል፡፡ በስነ-ጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ አጫጭር ልቦለዶች የዘመኑን ሁኔታ የሚገልጹ ተማሪዎች የተለያዩ ውይይቶች፣ ክርክሮች፣ግለገለጻዎች እንዲያደርጉ የሚያነሳሱ መሆናቸው፣ በክፍል ወስጥ የተለያዩ ተግብራትን ለማዘጋጀት እንደሚያስችል አብራርቷል፡፡ ስለሆነም ለከፍል ደረጃው የሚመጥኑ የስነ-ጽሁፍ ይዘቶች ተመርጠው መዘጋጀት እዳለባቸው አሳስቡዋል፡፡

ከተሰጠው ማብራሪያ መረዳት እንደሚቻለው፣ ስነ-ጽሁፍ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ የዘላቂ አንባቢነት ተግባርን ለማሳደግ እንደሚያስችል፣እንዲሁም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የውይይት፣የክርክር፣ሀሳብን የመግለጽ ተግብራትን እዲያከናውኑ ያስችላቸዋል፡፡ ይህ ጥናት፣ የዚህ ትናት አቅራቢ ይዞት ከተነሳው ዓላማ ጋር ተመሳሳይንት አለው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በሁለቱም ጥናት ተተኳሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ናቸው፡፡ እንዲሁም መሰረታዊ ዓላማቸው ከተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ነገር ግን የዚህ ጥናት አቅራቢ ከራሱ አካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ በተጨማሪም ከስነ-ጽሁፍ ዘሮች፣ አጭር ልቦለድ ላይ በማተኮር በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ሊመጣ የሚችለውን ለውጥ የሚፈትሽ በመሆኑ የተለየ ያደርገዋል ማለት ይቻላል፡፡

የ Souhila (2013/2014) ጥናት ስንመለከት አንብቦ መረዳት በሁለተኛ ቋንቋ ውስጥ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያሉ፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ስልትን ቢያውቁ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ሊሻሻል ይችላል የሚለውን ማረጋገጥ ነው፡፡ በጥናቱ

ለመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ የዋለው የጽሁፍ መጠይቅና ተከታታይ ተግባራዊ ልምምዶች ናቸው፡፡ በመረጃ ትንተናው ውጤት መሰረት ተማሪዎች ከበፊቱ የተሻለ የአንብቦ መረደት ችሎታቸው መሻሻሉን ገልጸዋል፡፡

ከተሰጠው ማብራሪያ መገንዘብ እንደሚቻለው የ Souhila (2013/2014) ጥናት ዋና ዓላማ አንብቦ የመረዳት ስልቶችን ለተማሪዎች ማሳወቅ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ሊያሻሽል ይችላል የሚል በመሆኑ፣ የዚህ ጥናት አቅራቢ ይዞት ከተነሳው ዓላማ ማለትም በአጫጭር ልቦለዶች ቋንቋ ማስተማር ከሚለው ጋር ልዩነት አለው፡፡

Ahmed Sallal, I.(2014) ያጠኑት ደግሞ አጫጭር ትረካዎች በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ያላቸዉን ሚና መለየት በሚል ዓላማ ነው፡፡ እንዲሁም አጫጭር ትረካዎች የንባብ ስሜትን የመቀስቀስ ሚና ምንያህል እንደሆነ ለመለየት ጥረት ተደርጓል፡፡ ጥናቱ በቁጥጥርና በሙከራ ቡድኖች የተከፈለ ሲሆን ለሙከራ ቡድኑ በአጫጭር ትረካዎች የታገዘ ትምህርት ሲሰጥ፣ ለቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ በተለመደው መንገድ እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም የአንብቦ መረዳት ችሎታን እና የማንበብ ተነሳሽነትን የሚመዝኑ ጥያቂዎች ተፈትነዋል፡፡ በዚህም መሰረት በአጫጭር ትረካዎች የተማሩ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸው ተሸሽሏል፤ተነሳሽነታቸውም ጨምሩአል፡፡ የሚሉ ማጠቃለያዎች ላይ መደረሱን ያስገነዝባሉ፡፡

የዚህ ጥናት አቅራቢ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተጠቀመው አጫጭር ልቦለዶችን ሲሆን፣ Ahmed Sallal, I.(2014) ደግሞ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተጠቀሙት አጫጭር ትረካውችን ነው፡፡ በዚህም መጠነኛ ልዩነት እንዳለ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በእርግጥ አጫጭር ትረካዎች እውናዊ እንዲሁም ፈጠራዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት አቅራቢ አጭር ልቦለድን ለቋንቋ ማስተማሪያነት በመጠቀም በራሱ አካባቢ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችግር ላይ የታየውን ክፍተት ለመሙላት ጥረት አድርጓል ፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

### 3. የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት በዋናነት የተከተለው መጠናዊ የምርምር (experimental research) ስልትን ነው፡፡ ጥናቱ ሙከራዊ ሆኖ፣የተሰበሰቡት መረጃዎችም በስታቱስቲካዊ መንገድ ንጽጽራቸው ተተንትኖ ተገልጿል (ተብራርቷል)፡፡ አይነታዊ የአጠናን ስልትም በአጋዥነት አገልግሏል፡፡

### 3.1. የተጠኚዎች አመራረጥ

የጥናቱ አካላይ፣በፓዊ ወረዳ ውስጥ ካሉ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት-ቤቶች ውስጥ አንዱ የሆነው የቀጠና 2 መንደር 2 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ የትምህርት ቤቱ አመራረጥ ዓላማ ተኮር ናሙና አመራረጥ (purposive sampling) ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ ምክንያቱም ትምህርት-ቤቱ፣ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች በብዛት የሚገኙበት፣ አጥኝው በዚያው ትምህርት-ቤት እያስተማረ መሆኑና ሙከራዊ ጥናቱን በቅርበት በእየለቱ የመከታተልና የማስተማር፣ የመፈተን ተግባር ለማከናወን ስለሚያመች ነው፡፡ አጥኝው ለጥናቱ አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትን ናሙና በዓላማ ተኮር ይመርጣል፤በማለት Gray(2004፣87) ያስረዳሉ፡፡ ትምህርት-ቤቱ ዘጠነኛ እና አስረኛን አካቶ የያዘ ነው፡፡ ነገር ግን የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ብሔራዊ ፈተና የሚወስዱ በመሆናቸው ሙከራዊ ጥናት ለማካሄድ ከጊዜና ከዝግጅት አንፃር አስቸጋሪ ሊሆን ስለሚችል በጥናቱ አልተካተቱም፡፡ ስለዚህ በጥናቱ የተካተቱት በዓላማ ተኮር የናሙና አመራራጥ ዘዴ በ2008 ዓ.ም ዘጠነኛ ክፍል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ናቸው፡፡

አጥኝው ሰነዶችን በመመርመር፣ በአካል በትምህርት ቤቱ በመገኘትና ፣ተማሪዎችን በመጠየቅ ባረጋገጠው መሰረት፣በዘመኑ ማለትም በ2008 ዓ.ም አራት የዘጠነኛ ክፍል ሴክሽኖች ያሉ ሲሆን በየክፍሉ ያሉ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ብዛት ደግሞ፣

9ኛ "A" ወ 24 ሴ 11 ድ 35

9ኛ "B" ወ 21 ሴ 15 ድ 36

9ኛ "C" ወ 17 ሴ 23 ድ 40

9ኛ "D" ወ 18 ሴ 12 ድ 30

ጠቅላላ ድምር ወ 80 ሴ 61 ድ 141 ናቸው:::

ከላይ በተጠቀሰው መሰረት በየክፍሉ ካሉ አማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ከሚማሩ ተማሪዎች መካከል ከየክፍሉ 15 ተጠኝዎች ለመምረጥ ታቅዶ፣ነገር ግን በየክፍሉ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች እኩል ስርጭት ስሌለላቸው ስብጥራዊ ናሙና አመራረጥ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በስብጥራዊ ቀመር መሰረት፣የቀመሩን የጋራ አብዥ

ለማግኘት አጠቃላዩን የናሙና ብዛት፣ለጥናት አካላይ ብዛት ማካፈል ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሰረት በተገኘው የጋራ አብዢ የእያንዳንዱን ቡድን ናሙና በማባዛትና የተገኘውን ውጤት በማጠጋጋት ተመጣጣኝ ናሙና መውሰድ ተችሉዋል፡፡ በመሆኑም በስብጥራዊ ናሙና አመራረጥ ቀመር መሰረት፣ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ከሆኑ ተማሪዎች መካከል ከ9ኛ "A" 35 ተማሪዎች ውስጥ 14.7 ሲጠጋጋ 15፤ ከ9ኛ "B" 36 ተማሪዎች ውስጥ15.3 ስለማይጠጋጋ 15፤ ከ9ኛ "C" 40 ተማሪዎች ውስጥ 17.02 ስለማይጠጋጋ 17፤ከ9ኛ "D" 30 ተማሪዎች ውስጥ 13 በጠቅላላ 60 ተጠኝዎች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ከሆኑት 141 ተማሪዎች ውስጥ 60 ተማሪዎች በናሙናነት መመረጣቸው ከጥናቱ አካላዮች አንጻር በፐርሰንት ሲሰላ 42.5% ናቸው፡፡ ስለዚህ በልምምድ ጊዜ አጥኝው ተጠኝ ተማሪዎችን ለመቆጣጠር እንዲችልና ተገቢውን ትምህርት ማስተላለፍ እንዲችል በናሙናነት 60 ተማሪዎች መመረጣቸው ተገቢ ነው ማለት ይቻላል፡፡

እነዚህን 60 ተጠኝዎች የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን ብሎ ለመለየት ጥቅም ላይ የዋለው ቅድመ-ልምምድ ፈተና ነው፡፡ አጥኝው የተለያዩ  አጫጭር ልቦለዶችን እና ትረካዎችን መሰረት በማድረግ፣ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎችን ለደረጃው በሚመጥን ሁኔታ ያሉበትን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ሊለኩ የሚችሉ፣ ሁለት ተከታታይ ፈተናዎች አዘጋጅቷል፡፡ ፈተናዎቹ ለተጠኝዎች ከመቅረባቸው በፊት በአማካሪው እና በሁለት አማርኛን በኮሌጅ ደረጃ በሚያስተምሩ መምህራን ተገምግመገው ማስተካከያዎች ተሰጠባቸዋል ፡፡

የመጀመሪያው የቅድመ-ልምምድ ፈተና ክፍል ‹‹ሀ›› ‹‹ትንሽ ቢገርማችሁ›› እና ክፍል ‹‹ለ›› ‹‹ደብደቤው›› በሚሉ ርእሶች የቀረቡ ሲሆን፣ ‹‹ትንሽ ቢገርማችሁ›› በሚል ርዕስ  ስር 5ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት መልስ የሰጡበት፣መልሳቸውንም በምክንያት አስደግፈው ያብራሩበት፣10 ጥቄዎች ደግሞ በምንባቡ መሰረት በምርጫ መልስ የሰጡበት ነው፡፡ ‹‹ደብዳቤው›› በሚለው ስር ደግሞ 4 ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት ለሰጡት መልስ በምክንያት የተደገፈ ማብራሪያ ያቀርቡበት ሲሆን በቀጣይ የቀረቡት 6 ጥያቄዎች ደግሞ በምንባቡ መሰረት በምርጫ መልስ የሰጡባቸው ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የመጀመሪያው የቅድመ-ልምምድ ፈተና በድምር 25 ጥያቄዎችን የያዘ ነው፤በአባሪ‹‹ከ››ተመልክቱዋል፡፡

የመጀመሪያው ቅድመ-ልምምድ ፈተና ለተጠኝ ተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት፣ ተጠኝ ሆነው ካልተካተቱ ነገር ግን አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ 10 ተማሪዎች በተራ ዕጣ ንሞና

ተመርጠው እንዲፈተኑት ተደርጓል፡፡ የፈተናው አስተማማኝነትም በክሮባኽ አልፋ ቀመር መሰረት ሲለካ /0.580/ ሆኑዋል፡፡ ይህም የአስተማማኝነት ልኬታው ከግማሽ በላይ በመሆኑ ተገቢነው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ፈተናው ተጠኝ ተማሪዎች እንዲፈተኑት ተደርጓል፡፡ በአባሪ ‹‹ረ›› ይመልከቱ፡፡ የመጀመሪያው ቅድመ-ለምምድ ፈተና ሚያዚያ 3/8/2008 ለስድሳዎቹ (60) ተጠኝዎች በሁለት የመፈተኛ ክፍሎች ከ8፡30 እስከ 10፡00 ባለው ጊዜ ውስጥ ተሰጥቷል፡፡

ሁለተኛው የቅድመ-ልምምድ ፈተና (ቅድመ-ልምምድ ፈተና ክፍል ሁለት) ‹‹የልደት በዓል ጥሪ›› በሚል አጭር ልቦለድ ምንባብ መሰረት የቀረበ ሲሆን፣ በምንባቡ መሰረት የሚሰሩ 11 የምርጫ ፣5 የማዛመድ፣ 4 ክፍት ማብራሪያ የሚሰጥባቸው ጥያቂዎችን በድምሩ 20 ጥቄዎችን የያዘ ነው፡፡ በአባሪ ‹‹ኸ›› ተመልክቷል፡፡ ሁለተኛው የቅድመ-ልምምድ ፈተናም ለፓይለት ሙከራ የተመረጡ 10 ተማሪዎች እንዲፈተኑት ተደርጓል፡፡ የሁለተኛው የቅድመ-ልምምድ ፈተና፣ በክሮንባኽ አልፋ መለኪያ መሰርት አስተማማኝነቱ /0.631/ ሆኑዋል፡፡ ስለሆነም የተገኘው የአስተማማንነት ደረጃ ከግማሽ በላይ ከፍ ያለ በመሆኑ ተጠኝ ተማሪዎች እንዲፈተኑት ተደርጓል፡፡ በአባሪ ‹‹ሰ›› ይመልከቱ፡፡ ሁለተኛው የቅድመ-ልምምድ ፈተና ሚያዚያ 7/8/2008 ለስድሳዎቹ (60) ተጠኝዎች በሁለት የመፈተኛ ክፍሎች ከ8፡30 እስከ 10፡00 ባለው ጊዜ ውስጥ ተሰጥቱዋል፡፡

ቅድመ-ልምምድ ፈተናው ተከፋፍሎ በተከታታይነት እንዲሰጥ የተደረገው ፈተናው ባንድ ጊዜ ቢሰጥ በፈተናው ውስጥ የተካተቱት ምንባቦች በመካከለኛ ደረጃም ቢሆን ረዥም በመሆናቸው እንዲሁም በአንዴ ብዙ ጥያቄዎችን ተማሪዎች እንዲሰሩ ማድረግ መሰላቸትንና መጨናነቅን ሊፈጥር ይችላል ከሚልና ተማሪዎቹም በአንድ ቀን ውስጥ የሚኖራቸው ስሜት ከሌላው ቀን ሊለይ ስለሚችል በአራት ቀን ልዩነት ተከታትሎ ተሰጥቱዋል፡፡ የመጀመሪያው የቅድመ-ልምምድ ፈተና 25 ጥያቂዎች፣የሁለተኛው ቅድመ-ልምምድ ፈተና 20 ጥያቄዎች በድምር 45 ጥያቄዎች ተጠኝዎች የነበሩበትን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመመዘን ቀርቧዋል፡፡ በማስከተልም የእያንዳንዱ ተማሪ ድምር ውጤት ከ45 ስንት እንደሆነ ተመዝግቧል፡፡ ይህም ውጤት የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኖችን በተመጣጣኝ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዋቀር አስችሉዋል፡፡

የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኑን ለማዋቀር ተማሪዎች በቅድመ-ልምምድ ከ45 ባመጡት ውጤት መሰረት ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ በቅድም ተከተል ተደርድረዋል፤በማስከተልም ከከፍተኛው ውጤት አንድ፣ከመጨረሻው ዝቅተኛ ውጤት አንድ በማጣመድ ሁሉም

ተጠኝዎች በውጤታቸው መሰረት ከተጣመዱ በኋላ፣ አንድ አንድ ጥንዶች በሁለት ረድፍ ቁልቁል በተራና በቅደም ተከተል እንዲደረደሩ ተደርጉዋል። በዚህም መሰረት በመጀመሪያው ረድፍ 15ጥንዶች ማለትም 30 ተማሪዎች፣በሁለተኛው እረድፍ15 ጥንዶች ማለትም 30 ተማሪዎች በቡድን ደረጃ በውጤት አቻ ሆነው ተመድበዋል። መጀመሪያው ረድፍ ‹‹ሀ›› ሁለተኛው ረደፍ ደግሞ ‹‹ለ›› የሚል ስያሜ የተሰጣቸው ሲሆን፣ በድጋሜ ተራ የእጣ ንሞና በመጠቀም በረድፍ ‹‹ሀ›› ስር የተቀመጡት የቁጥጥር ቡድን፣ በረድፍ ‹‹ለ›› ስር የተቀመጡት የሙከራ ተብለው ተለይተዋል፤ይህም የቁጥጥር ቡድን ቅድመ-ልምምድ የፈተና ውጤት በአባሪ ‹‹ሀ›› ተመልክቱዋል፤እንዲሁም የሙከራ ቡድን ቅድመ-ልምምድ የፈተና ውጤት በአባሪ ‹‹ለ›› ተመልክቱዋል።

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መስሪያዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ  አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር፣ አማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ሚና መፈተሸ ነው። ስለሆነም የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ ቅድመ-ልምምድና ድህረ-ልምምድ አንብቦ መረዳት ችሎታን ያካተቱ ፈተናዎች፣ አንብቦ መረዳትን መሰረት ያደረጉ ለተማሪዎች የቀረቡ የፅሑፍ መጠይቆች እና በልምምድ ጊዜ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተከትሎ ሊተገበር የሚችል የክፍል ውስጥ ተራክቦ  መሰረት ያደረገ ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ጥቅም ላይ ውለዋል።

### 3.2.1. ቅድመ- ልምምድናድህረ-ልምምድ ፈተናዎች

የቅድመ-ልምምድም ሆነ የድህረ-ልምምድ ፈተናዎች ዋና ትኩረት የተጠኝ ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመመዘን ነው። በዚህም መሰረት አጥኝው የአንብቦ መረዳት ፈተናዎችን ሲያወጣ፣ እነ Pettit and Cockriiel (1974); Robinson (1966) ን በመጥቀስ የአንብቦ መረዳት ሞዴሎች የሚያካትቱትን ማለትም የጸሐፊውን መልዕክት መረዳትን፤ ጸሐፊው ትኩረት ያደረገበትን ትርጉም መረዳትን፣ የጽሑፉን ዓላማ መገንዘብን መሰረት አድርጎ ነው። Pettit (1970) እንደገለጹት፣አንብቦ መረዳትን ጠቅለል ባለ ሁኔታ በሁለት ክፍሎች ለማስቀመጥ ሞክረዋል። እነዚህም የምንባቡን ገጻዊ ወይም ቀጥተኛ መልዕክት መረዳትን እና በምንባቡ የተገለጸውን በመመርኮዝ በመተንበይ፣በመገመት ጥልቅ ግንዛቤ ማግኘት የሚሉ ናቸው። ስለሆነም Pettit (1970) እንደሚያስረዱት፣ለአንብቦ መረዳት ፈተና የሚመረጡ ምንባቦች ለተማሪዎች ሳቢ፣ግልጽና ቅርብ መሆን አለባቸው። የሚቀርቡ ጥያቄዎች በምርጫ እንዲሁም በመግለጽ የሚሰሩ ሆነው፣ ጥያቄዎቹ ጥልቅ ግንዛቤን፤ ዋና ሃሳብን፤የድርጊት ቅደም ተከተልን፤ ማወዳደርን፣ምክንያትና ውጤት ትስስርን፣የገጸባህርያት

ገለጻን ያካተቱ ናቸው፡፡ ስለዚህ የዚህ ጥናት አቅራቢም እነዚህን ባህርያት መሰረት በማድረግ የቅድመ-ልምምድና ድህረ-ልምምድ ፈተናዎችን ለማዘጋጀት ችሏል፡፡

### 3.2.1.1. ቅድመ-ልምምድ ፈተና

በመጀመሪያ ደረጃ ለተጠኝ ተማሪዎች የቀረበላቸው የቅድመ-ልምምድ ፈተና ነው፡፡ ይህ ፈተና ተጠኝ ተማሪዎች አስቀድሞ ያላቸውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በመመዘን፣ በአንብቦ መረዳት ችሎታቸው መሰረት በችሎታ አቻ ወይም ተመጣጣኝ የሆኑ የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ብሎ ለመመደብ ያስቻለ ፈተና ነው፡

ቅድመ-ልምምድ ፈተናው ሁለት ክፍሎችን የያዘ ሲሆን፣የመጀመሪያው ቅደመ- ልምምድ ፈተና በራሱ ሁለት ምንባቦችን አጣምሮ የያዘ ነው፡፡ በዚሁ ስር አንደኛው ‹‹ትንሽ ቢገርማችሁ›› የሚለው ካጭር ትረካ ላይ የተወሰደ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ‹‹ደብዳቤው›› በሚል ርዕስ የቀረበ አጭር ልቦለድ ነው፡፡ ምንባቦቹ ለደረጃው በሚመጥንና ለፈተና በሚያመች መልኩ መጠነኛ ማስተካከያዎች ተደርጎባቸዋል፡፡ የጥያቄዎችን አደረጃጀት ስንመለከት ደግሞ ‹‹ትንሽ ቢገርማችሁ›› ከሚለው ምንባብ 5ቱ ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት በምክንያት ተደግፈው መልስ የሚሰጥባቸው ጥያቄዎች ሲሆኑ፣ከ6 እስከ 15 ያሉት 10 ጥያቄዎች በአማራጭ መልስ የቀረቡ ናቸው፡፡ በዚሁ ስር በሁለተኛው ማለትም ‹‹ደብዳቤው›› በሚል ርእስ የቀረበው 4 ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት በምክንያት ተደግፈው መልስ የሚሰጥባቸው ጥያቄዎች ሲሆኑ፣ከ5 እስከ 10 ያሉት 6 ጥያቄዎች በአማራጭ መልስ የቀረቡ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት የመጀመሪያው ቅድመ-ልምምድ ፈተና በድምር 25 ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ይህ ፈተና በአማካሪ እና በኮሌጅ ደረጃ አማርኛ ቋንቋን በሚያስተምሩ መምህራን ከተገመገመ በኋላ ማስተካከያዎች ተደርጎበታል፡፡ በዚህም መሰረት ችግር ያለባቸው ጥያቄዎች እንዲስተካክሉ ተደርጓል፡፡

በዚህም መሰረት የተዘጋጁ ጥያቄዎች (የቅድመ-ልምምድ ፈተናው) የሙከራ ጥናቱ በቀጥታ ልምምዱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ለተጠኚ ተማሪዎች ተሰጥቱዋል፡፡ ፈተናው ከልምምድ በፊት የተሰጠበት ምክንያትም ተጠኝዎቹ ያላቸውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመመዘን ሲባል ነው፡፡ አስቀድሞ በተገለጸው መሰረት የተዘጋጀው የመጀመሪያው የቅድመ-ለምምድ ፈተና ልምምዱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ሚያዚያ 3/8/2008 ለስድሳዎቹ (60) ተጠኝዎች በሁለት የመፈተኛ ክፍሎች ከ8፡30 እስከ 10፡00 ባለው ጊዜ ውስጥ ተሰጥቱዋል፡፡በአባሪ ‹‹ከ››ይመልከቱ፡፡ ፈተናው በአጥኝው እና በሁለተኛ ደረጃ በዚያው ትምህርት-ቤት

በተመመሳሳይ ደረጃ አማርኛ ቋንቋ በምታስተምር መምህርት ታርሙዋል፡፡ ሁለቱ የፈተና አራሚዎች የተስማሙበት ውጤት ለእያንዳዱ ተማሪ ተመዝግቧል፡፡

የሁለተኛው የቅደመ-ልምምድ ፈተና ‹‹የልደት በዓል ጥሪ›› በሚል የአጭር ልቦለድ ምንባብ ስር የቀረበ ሲሆን፣ምንባቡ ለደረጃው በሚመጥንና ለፈተና በሚስማማ መልኩ ማሻሻያዎች ተደርጎበታል፡፡ የጥያቄዎች አደረጃጀት ስንመለከት ከ1 እስከ 11 ያሉት ጥያቄዎች በምርጫ የቀረቡ ሲሆኑ፣ከ12 እስከ16 ያሉት 5ቱ ጥያቄዎች፣ በምንባቡ መሰረት የተለዩ አገላለጾችንና ጽንሰ ሃሳቦችን በማዛመድ የሰሩበት ናቸው፡፡ በማስከተልም ከ17 እስከ 20 የተቀመጡት 4ቱ ክፍት ጥያቄዎች፣ አጭር የጽሁፍ ማብራሪያ እንዲሰጡ የተደረጉበት ናቸው፡፡ ይህ ፈተና በኮሌጅ ደረጃ አማርኛ ቋንቋ በሚያስተምሩ መምህራን ከተገመገመ በኋላ ማስተካከያዎች ተደርገውበታል፡፡ በዚህ መሰረት የተደራጀው ሁለተኛው የቅድመ-ልምምድ ፈተና ሚያዚያ 7/8/2008 ከሰዕት በኃላ በሁለት የመፈተኛ ክፍሎች ከ8፡30 እስከ 10፡00 ባለው ጊዜ ውስጥ ለስድሳዎቹ (60) ተጠኚዎች ተሰጥቷቸዋል፡፡በአባሪ ‹‹ኸ›› ይመልከቱ፡፡ ሁለተኛው ቅድመ-ልምምድ ፈተና በአጥኚው እና በዚያው ትምህርት-ቤት በተመመሳሳይ ደረጃ አማርኛ ቋንቋ በምታስተምር መምህርት ታርሙዋል፡፡ ሁለቱ የፈተና አራሚዎች የተስማሙበት ውጤት ለእያንዳዱ ተማሪ ተመዝግቧል፡፡

አስቀድሞ እንደተገለጸው የመጀመሪያው የቅድመ-ልምምድ ፈተና 25 ጥያቄዎችን፣ሁለተኛው የቅድመ-ልምምድ ፈተና ደግሞ 20 ጥያቄዎችን፣በድምሩ 45 ጥያቄዎች የተጠኚ ተማሪዎችን የቅድመ-ልምምድ የእንብቦ መረዳት ችሎታ ለመመዘን አስችሉዋል፡፡ አስቀድሞ እንደተገለጸው የቅድመ-ልምምዱ የፈተና ውጤት ተጠኚ ተማሪዎችን በተመጣጣኝ ችሎታ፣የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን ብሎ ለመክፈል አገልግሉዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተጠኚዎቹ የቅድመ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መመዘኛ ፈተና ውጤት ከድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መመዘኛ ፈተና ውጤትጋር በማነጻጸር ስታቴስቲካዊ ትንታኔ ለመስጠት አስችሉዋል፡፡

### 3.2.1.2. ድህረ-ልምምድ ፈተና

ድህረ-ልምምድ ፈተናው መሰረት አድርጎ የተዘጋጀው የተሰጠውን ትምህርት (ልምምድ) ነው፡፡ አጥኚው ልምምዱ ከሚጠናቀቅበት ቀን አስቀድሞ በሰጠው የልምምድ አቀራረብና አተገባበር መሰረት የድህረ-ልምምድ የፈተና ጥያቄዎችን አዘጋጅቱዋል፡፡ ድህረ-ልምምድ ጥያቄዎች የተዘጋጁት በሁለት የተለዩ ክፍሎች ነው፡፡ ክፍል አንድ ‹‹ክፍተት›› በሚል ርዕስ የተጻፈ አጭር ልቦለድ ምንባብ መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡ ልቦለድ ምንባቡ ለደረጃው

በሚመጥን መልኩና ለፈተና ተስማሚ እንዲሆን ሲባል መጠነኛ ማስተካከያዎች ተደርገውበታል፡፡ በዚህ ፈተና ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት በምክንያት ተደግፈው የሚመለሱ ናቸው፡፡ ከተራ ቁጥር 5 እስከ 12 የተዘጋጁት ጥያቄዎች ደግሞ በአማራጭ መልስ የቀረቡ ሲሆኑ፣በማስከተለም ከ13 እስከ 17 የቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ገለጻዎችንና ጽንሰ ሀሳቦችን በማዛመድ የሚመለሱ ናቸው፡፡ ከተራ ቁጥር18 እስከ 20 የቀረቡት ጥያቂዎች ደግሞ ክፍት ጥቄዎች ሲሆኑ፣ተማሪዎች ከምንባቡ የተረዱትን ሀሳብ መነሻ በማድረግ በጽሑፍ ማብራሪያ የሚሰጡባቸው ናቸው፡፡ በዚህ በክፍል አንድ ስር በእጥኝው የተዘጋጀው ፈተና፣ በአማካሪው እና አማርኛን በኮሌጅ ደረጃ በሚያስተምሩ መምህራን ከተገመገመ በኋላ በሰጡዋቸው አስተያየቶች መሰረት ማስተካከያዎች ተደርገው የተዘጋጀ ነው፡፡

ድህረ-ልምምድ ፈተናው ለተጠኝ ተማሪዎች ከመሰጠቱ በፊት፣ አስቀድሞ በተገለጸው መሰረት ለ10 ተማሪዎች በፓይለት ፈተና ተፈትሿል፡፡ በዚህ መሰረት ክፍል አንድ ድህረ-ልምምድ ፈተና የአስተማማኝነት ደረጃ /0.726/ ነው፡፡ በመሆኑም አስተማማኝነቱ ከፍ ያለ በመሆኑ ለተጠኝ ተማሪዎች ቀርቧል፡፡ በአባሪ ‹‹ሸ›› ይመልከቱ፡፡ ይህ ፈተና ሰኔ 1/10/2008 ከሰዓት በኋላ ከ8፡30 እስከ 10፡00 ሰዓት፣ በሁለት የመፈተኛ ክፍሎች በኣጥኝውና በሌሎች ሁለት መምህራን አማካይነት ተሰጡዋል፡፡ ይህ ድህረ-ልምምድ ፈተና ክፍል አንድ በአባሪ ‹‹ወ›› ተመልክቱዋል፡፡

ክፍል ሁለት የድህረ-ልምምድ ፈተና የተዘጋጀው ‹‹ጆርዳን›› በሚል ርዕስ ከተጻፈ አጭር ልቦለድ ምንባብ ነው፡፡ ምንባቡ ለደረጃው በሚመጥንና ለፈተና በሚያመች መልኩ መጠነኛ ማስተካከያዎች ተደርጎበታል፡፡ በዚህ ፈተና ተማሪዎች ስለምንባቡ አጠቃላይ ግንዛቤ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ፣ ከተራቁጥር1 እስከ 6 ያሉ ጥያቄዎች ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት የሚመልሱዋቸው እና ለመልሳቸውም ምክንያት የሚሰጡባቸው፣ ከተራቁጥር 7 እስከ 18 የምርጫ ጥያቄዎች፣ከተራቁጥር 19 እስከ 23 የማዛመድ ጥያቄዎች፣ከተራቁጥር24 እስከ 25 ክፍት የሆኑ አጭር ማብራሪያ የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡ ይህ ፈተና በአጥኝው ከተዘጋጀ በኋላ በአጥኝው አማካሪ፤ አማርኛን በኮሌጅ ደረጃ በሚያስተምሩ ሁለት መምህራን ተገምግሞ መስተካከያዎች ተሰጦበታል፡፡ ክፍል ሁለት ድህረ-ልምምድ ፈተና እንዲሁ ለፓይለት ጥናት ማለትም፣ ከጥናቱ አካባይ ለተመረጡ 10 ተማሪዎች እንዲፈተኑት ተደርጓል፡፡ በክሮንባኽ አልፋ ቀመር መሰርት አስተማማኝነቱም /0.609/ ነው፡፡ የአሰተማማኝነት ደረጃ ከግማሽ በላይ ሆኖ በመገኘቱ ተጠኝ ተማሪዎች እንዲፈተኑት ተደርጓል፡፡ አባሪ ‹‹ቀ›› ይመልከቱ፡፡ ይህ ፈተና ሰኔ 5/10/2009 ከሰዓት በኋላ

ከ8፡30 እስከ 10፡00 ሰዓት በሁለት የመፈተኛ ክፍሎች ለተጠኝ ተማሪዎች በኣጥኝውና በሌሎች ሁለት መምህራን አማካይነት ተሰጡዋል፡፡ ይህም የድህረ-ልምምድ ፈተና ክፍል ሁለት በአባሪ ‹‹ዐ›› ተመልክቱዋል፡፡

ድህረ-ልምምድ ፈተናው ‹‹ክፍተት›› በሚል ምንባብ ስር የተዘጋጁ 20 ጥያቄዎችን እንዲሁም ‹‹ጆርዳን›› በሚል ምንባብ ስር የተዘጋጁ 25 ጥያቄዎችን በድምሩ 45 ጥያቄዎችን ያካተተ ነው፡፡ ይህም ድምር ውጤት ከ45 ተጠቃሎ ለውጤት ትንተና ተገባር ላይ ውሏል፡፡

### 3.2.2 የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ ለዚህ ጥናት አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ አገልግሏል፡፡ መጠይቁ በሚዘጋጅበት ጊዜ መላሾች ወደ ተዛባ አቅጣጫ እንዳያመሩ ጥንቃቄ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ ጥያቄዎች ደረጃቸውን የጠበቁና ምክንያታዊ ምላሽ ማስገኘት እዲችሉ ሆነው እንዲቀርቡ ጥረት ተደርጓል፡፡ መጠይቆቹ ግልጽ፣የማያሻሙ እያንዳንዱም ጥያቄ ራሱን ችሎ የሚቆም መሆን እንዳለበት፣ Gray(2004፣189) እነ Arksey and knight (1999)ን በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡ ስኬል ያላቸው ጥያቄዎች ተለዋዋጮችን ለመለካት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ የተለመደው የስኬል አቀራረብ ጥያቄ ደግሞ Likert scale የተባለው ነው፡፡ ይህ እስኬል ባለአራት ወይም ባለአምስት ስኬል ሊሆን ይችላል Gray(2004፣197) በማለት ግሬይ ያስረዳሉ፡፡

የጽሁፍ መጠይቁ መሰረት አድርጎ የተዘጋጀው ‹‹እንግሊዝኛን እንደ ውጭ ወይም እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር፣አጭር ልቦለድን በክፍል ውስጥ መጠቀም›› በሚል ርዕስ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ መሰረት አድርጎ ነው፡፡ ማለትም በዚህ ጥናት ላይ የቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ አጥኝው በመተርጎምና መጠነኛ ማሻሻያ በማድረግ አዘጋጅቷል ( Dr. Nimer A, Abu Zahara, Dr. Mohammd A, Farrah (2016)) :: በዚህ መሰረት በአጥኝው ተተርጉሞ የተዘጋጀው የጽሁፍ መጠይቅ በኮሌጅ ደረጃ አማርኛ ቋንቋ በማስተማር ላይ ባሉ ሁለት መምህራን ከተገመገመ በኋላ፣ማስተካከያ ተደረጎበት 20 ነጥቦችን ያካተተ መጠይቅ ለመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሉዋል፡፡ የጽሁፍ መጠይቁን በአባሪ ‹‹ለ›› ይመልከቱ፡፡

በጽሁፍ መጠይቁ ውስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች እያንዳንዳቸው የአራት አማራጮች ነጥብ፣መልስ መስጫ መለኪያዎችን /Likert scales/ መሰረት በማድረግ ተዘጋጅተዋል፡፡ በእያንዳንዱ ጥያቄ ፊትለፊት በሰንጠረዥ ውስጥ ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ፣በጣም እስማማለሁ (4) እስማማለሁ (3) አልስማማም (2) እና በጭራሽ አልስማማም (1) የሚሉ አማራጮችን

እንዲይዙ ተደርጓል። የእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ መወሰኛ ነጥብ አራት ብቻ እንዲሆኑ የተደረገበት ምክንያት ያለው(2004) እንደገለጹት፣ ተጠኚዎቹ፣“እርግጠኛ አይደለሁም” የሚለዉን ጨምሮ አምስት አማራጮች ቢቀርቡላቸዉ ኃላፊነትና ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ መሀለኛውን (3ኛውን) የመምረጥ አዝማሚያ እንደሚያሳዩ ይገመታል። ስለዚህ ይህ አማራጭ እንዲወገድ ተደርጓል።

በዚህ ሂደትም 20 ነጥቦችን የያዘ የጽሁፍ መጠይቅ ተዘጋጅተዋል። የጽሁፍ መጠይቁ በፓይለት ጥናት ተፈትሾ በክሮንባኽ አልፋ ቀመር መሰርት አስተማማኝነቱ /0.748/ እንደሆነ ተረጋግጧል። ከላይ የተጠቀሱትን ሂደቶች አሟልቶ የተዘጋጀው የጽሁፍ መጠይቅ ለቁጥጥር ቡድኑም ሆነ ለሙከራ ቡድኑ ከልምምድ በፊት በ5/8/2008ዓ.ም ከልምምድ በኋላ ደግሞ በ3/10/2008ዓ.ም ተሰጥቶ መረጃዎችን እንዲሞሉ ተደርጓል። ማለትም ምላሽ እንዲሰጥባቸዉ ተደርጎ የተገኘው ምላሽም ለትንታኔ ቀርቦዋል።

### 3.2.3 ምልከታ

በዚህ ጥናት የተጠኝ ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ መሰረት አድርጎ ሊታይ የሚችለውን የክፍል ውስጥ ተራክቦ ምን እንደሚመስል ለመቃኝትና አጋዥ መረጃ ለማግኘት ሲባል ምልከታ ተግባር ላይ ውሏል። በምልከታ ጊዜ የተመልካቹን ግለሰባዊነት ተጽዕኖ ለመቀነስ ሲባል፣ጉዳዩ በቀጥታ የማይመለከተው ሰው መረጃውን ቢሰበስብ ጥሩ እንደሆነ ያለው (2004) ያስረዳል። በዚህም መሰረት አጥኝው በሚሰራበት ትምህርት-ቤት በተመሳሳይ ደረጃ አማርኛ ቋንቋን በምታስተምር መምህርት ምልከተው ተከናውኗል። አጥኝው አስቀድሞ መረጃውን ለሞላችለት መምህርት ስለምልከታው የትኩረት ነጥብ እና ምልከታው ስለሚካሄድበት ፕሮግራም ማብራሪያ ሰጥቷል።

የምልከታው የትኩረት ነጥብ የሙከራ ቡድኑ ተጠኝዎች አማርኛ ቋንቋን በአጭር ልቦለድ አማካይነት እየተማሩ ባሉበት ጊዜ ያላቸውን ተሳትፎና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን የመስራት ችሎታ ላይ የተመሰረተ ነው። በዚህም መሰረት ስድስት ምልከታዎች ተደርገዋል። ምልከታ1 በቀን 12/8/2008 ፣የትምህርት ርዕስ ‹‹ክንፋም ሕልሞች ክፍል አንድ››ትምህርት አንድ፣ በክፍለ ጊዜ አንድ። ምልከታ2 በቀን 19/8/2008፣፣የትምህርት ርዕስ ‹‹ክንፋም ሕልሞች ክፍል አንድ››ትምህርት አንድ፣ ክፍለ ጊዜ ሁለት። ምልከታ3 በቀን 20/8/2008 ፣የትምህርት ርዕስ ‹‹ክንፋም ሕልሞች ክፍል ሁለት›› ትምህርት ሦስት፣ክፍለ ጊዜ ሁለት። ምልከታ4 በቀን 3/9/2008፣የትምህርት ርዕስ ‹‹ክንፋም ሕልሞች ክፍል ሦስት›› ትምህርት ሦስት፣ክፍለ ጊዜ ሁለት።ምልከታ5 በቀን 10/9/2008፣፣የትምህርት ርዕስ

‹‹ክንፋም ሕልሞች ክፍል አራት››ትምህርት ሦስት። ምልከታ6 በቀን 11/9/2008፤፤የትምህርት ርዕስ ‹‹በወርቅ የተሞላ ገደል›› ትምህርት አምስት፣ ክፍለ ጊዜ አንድ ላይ ተካሂደዋል።

### 3.3 የማስተማሪያ ጽሑፍ አዘገጃጀትና አቀራረብ

በዚህ ጥናት የሙከራ ቡድኑን በአጭር ልቦለድ ቋንቋን በማስተማር በተጠኚዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ተጽዕኖ ለመመርመር ይረዳ ዘንድ በአጥኚው የማስተማሪያ ጽሑፍ(ቴክስት) ተዘጋጅቷል። ቴክስቱ አማርኛን በኮሌጅ ደረጃ በሚያስተምሩ ሁለት መምህራን ተገምግሞ፣በአማካሪው አስተያየት ተጠሰጥቶበት፣ ማስተካከያዎች ተደርገውበት የተዘጋጀ ነው። የማስተማሪያ ቴክስቱን በአባሪ ‹‹ዘ›› ይመልከቱ። የማስተማሪያ ጽሑፉ(ቴክስቱ) ሲዘጋጅ፣ ሙከራ ቡድኑን ለማስተማር የተመረጡና የተዘጋጁ ምንባቦች በዋናነት ትኩረት የተደረገባቸው አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎችን አንብቦ መረዳትን ለማስተማር በሚያስችሉ መልኩ ነው።

በመሆኑም ጽሑፉ(ቴክስቱ) አምስት ምንባቦችን የያዘ ነው። ክንፋም ሕልሞች ከሚለው አጭር ልቦለድ ውስጥ በራሳቸው ሙሉ ሊሆኑ በሚችሉ በአራት ክፍሎች የተደራጁ ምንባቦች ቀርበዋል። እነዚህም ‹‹ክንፋም ሕልሞች ክፍል አንድ››፣ ‹‹ክንፋም ሕልሞች ክፍል ሁለት››፣‹‹ክንፋም ሕልሞች ክፍል ሦስት››እና‹‹ክንፋም ሕልሞች ክፍል አራት››ናቸው።አምስተኛው ምንባብ ደግሞ ‹‹በወርቅ የተሞላ ገደል››የሚል አጭር ልቦለድ ነው። አጭር ልቦለዶች በምንባብነት ሲመረጡ ከርዕሳቸው ጀምሮ ተማሪዎችን የሚያጓጉ፣ለንባብ የሚያነሳሱ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል።

የማስተማሪያ ጽሑፉ(ቴክስቱ) አደረጃጀት ከእያንዳንዱ ምንባብ በፊት ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች ቀርበዋል።የቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች ተግባርም ስለምንባቡ አጠቃላይ ግንዛቤ የሚሰጡ፣ተማሪዎቹ ወደ ንባብ ከመግባታቸው በፊት ዳራዊ እውቀታቸውን እንዲያስሱ የሚያስችሉ እና ስለምንባቡ ፍንጭ የሚሰጡ ሆነው ተዘጋጅተዋል። በመቀጠል የተቀመጡት የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ናቸው። የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ተማሪዎች ንባባቸውን ገታ አድርገው ስላነበቡት ሃሳብ ማጠቀለያ መስጠት የሚያስችላቸው ተግባር ነው። በመቀጠልም ቀጣዩ ምን መሆን እንደሚችል የሚተነብዩበት ክፍል ነው።

ምንባቦችን ተከትሎ በቀዳሚነት የተደራጁት ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት በምክንያት ተደግፈው መልስ የሚሰጥባቸው ጥያቄዎች ናቸው። እነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች

ተማሪዎች በምንባቡ የተላለፉትን መልዕክቶች በውል በማጤን በቂ ማብራሪያ መስጠት የሚያስችሉ ሲሆን፣ተማሪዎች ምንባቡን ደጋግመው እነዲያነቡ የሚያስችሉ ናቸው። በቀጣይነት የተደራጁት ደግሞ በምንባቡ መሰረት የሚሰሩ የምርጫና የማዛመድ መልመጃዎች ናቸው። በየምንባቦቹ የቀረቡት እነዚህ መልመጃዎች ተማሪዎች የነገሮችን ወይም የጽንሰ-ሃሳቦችን አንድነትና ልዩነት፣የሚያስተላልፉትን መልዕክት በጥልቀት መመርመር የሚያስችሏቸው ናቸው። እነዚህ ዓይነት መልመጃዎች በሚስጢር ያለውን የሚፈቱበት፣ ጽንሰ-ሃሳቦችንና ባህሪያትን የሚያዋግኑብት ክፍል ነው።

በመጨረሻ የተደራጁት ክፍት ጥያቄዎች ሲሆኑ፣አጠቃላይ የምንባቡን መልዕክት ከአካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ትርጉም ለመስጠጥ ጥረት የሚደርጉበት ነው። በዚህ ክፍል ተማሪዎች ስለገጸባህሪያት ምንነት የሚገልጹበት፣በምንባቡ የተላለፈውን መልዕክት መሰረት በማድረግ የራሳቸውን አስተያየትና ድምዳሜ የሚሰጡበት ነው። ክፍት ጥያቄዎች  የተለያዩ ውይይቶችንና ክርክሮችን ለማድረግ የሚያስችሉና  የላቀ ግንዛቤ የሚያስገኙ ሆነው ተዘጋጅተዋል። ምንባቦችን ተከትሎ ለቀረቡት ዝርዝር የመልመጃዎች ዓላማ፣መመሪያ፣ የክፍለ ጊዜ ድልድል እና አተገባበር በአባሪው ስር ተካቶ ቀርቧል።

በአጠቃላይ አጥኝው የማስተማሪያ ጽሑፉን ሲያዘጋጅና ሲያደራጅ የሚከተሉት ምሁራን የተጠቀሙበትን ስልትና ንድፈ-ሃሳብ ለመከተል ሞክሩዋል። የማስተማሪያ ጽሑፎች ወይም ቴክስቱሲዘጋጅ እነ Ghasemi (2011) እና Pourkalhor, Koham (2013) የተጠቀሙባቸውን፣አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የሚያስችሉ አደረጃጀቶችን መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል። እንዲሁም Freeman (2000) የገለጻቸው ተግባቦታዊ ስልቶችን መለትም ትምህርቱን ከይዘትና ተግባር ተኮር ተሳትፎ ጋር በማስተሳሰር ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል። ተግባቦታዊ አቀራረብ የተማሪዎችን ማህበራዊ፣ታሪካዊ፣ማህበራዊ ጉዳዮችን በሚነሳሳ መልኩ እንደሚካሄድም ተገልጹዋል። ስለሆነም አጥኝው ሙከራዊ ቡድኑን በተጠቀሱት አቀራረቦች ለማስተማር ጥረት አድርጓል።

ከዚህ በተጨማሪ፣ በስነ-ጽሑፍ ይዘቶች ቋንቋን ስናስተምር፣ በክፍል ውስጥ መማር ማስተማር ሂደት የሚመረጡና የሚደራጁ ጽሑፎች የሚከተሉት ባህሪያትንና አደረጃጀቶችን ማሟላት እንዳለባቸው (collie and slater, 1987) ያስረዳሉ። ስነ-ጽሑፉ ወይም የሚመረጠው ምንባብ ሳቢና ለተማሪዎች ፍላጎት ቅርብ የሆነ፣ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ተግባራትን ማሰራት የሚያስችል መሆን እንዳለበት ገልጸዋል። ከዚህም በተጨማሪ ምንባቦች በማስተማሪያ ጽሑፎች ውስጥ ሲካተቱ ከተለያዩ ስነ-ጽሑፋዊ ስራዎች መሆን እደለባቸውና

ይህም ለተማሪዎች ፍላጎት የተሸለ የአንብቦ መረዳት ፍላጎትን ማምጣት እንደሚችል አስገዝበዋል፡፡

ከ collie and slater (1987) ገለጻ መረዳት የሚቻለው አፊ-ፊት ላልሆኑ ወይም ሁለተኛ ቋንቋ ለሆኑ ተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት የሚደራጁ ስነ-ጽሑፋዊ ቴክስቶች፣ ሳቢና ተማሪዎችን በቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ውስጥ የተለያዩ ተግባራት ማሰራት የሚያስችሉ፣የተማሪዎችን ፍላጎት በመቀስቀስ የዘላቂ ሕይወት አንባቢነት የሚያሻግሩ መሆን እንዳለባቸው ነው፡፡

### 3.3.1 የምንባቦች አመራረጥ

አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የተመረጡ ምንባቦች ከተማሪዎቹ ፍላጎት፣ ለደረጃው ከተመረጠው የትምህርት ዓላማ አንጻር እንዲሁም የክፍል ደረጃ ጋር የተገናዘቡ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል፡፡ ምንባቦቹ ወይም አጫጭር ልቦለዶች ከተለያዩ የአጭር ልቦለድ መድብሎች ከርዕሳቸውና ከይዘታቸው ቅርበት አንጻር ተመርጠዋል፡፡ አጭር ልቦለዶቹ ላይ ያለው አቀነጃጀት፣ የቃላትና የተለያዩ ማብራሪያዎች ለማስተማርና ለተማሪዎች ተስማሚ ከማድረግ አንጻር ማሻሻያዎች ተደርገውባቸዋል፡፡ በተቻለ መጠን እንዲያጥሩም ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት በአንድና በሁለት ክፍልጊዜ የሚለማመዱዋቸው ሆነው ተዘጋጅተዋል Ghasemi (2011) ማለት ይቻላል፡፡ ምንባቦቹ ሲመረጡም፣ Hill (1986)፣ Nuttall (1982)፣ lazar (1993) አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የሚያስችሉ ብለው ያስቀመጡዋቸውን የመምረጫ መስፈርቶች በማገናዘብ ነው፡፡ የምንባብ መምረጫ መስፈርቶችም፡-

- ከተማሪዎቹ ማህበረ በህላዊ ልምድ ጋር የሚጣጣም ይዘት ያለው፤
- ለተማሪዎች አዲስ ይዘትን የሚያስተዋውቅ ርዕስ ጉዳይ የያዘ፤
- ተማሪዎች የራሳቸውን አመለካከት ከሌሎች ጋር እንዲያነጻጽሩ እድል የሚፈጥር፤
- ከተማሪዎች የእውቀት አድማስ ጋር የሚጣጣም ይዘት ያለው፤
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ለማዘጋጀት የሚያስችል፤ የሚሉት ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አጫጭር ልቦለዶች ሲመረጡ፣ ሰቢ፣ አንድን ነገር በተለዬ መልኩ የሚገልጹ ከዘመኑ ሁኔታ ጋር የተዛመዱና የዘመኑን አካባቢያዊ ባህል የሚገልጹ ለተማሪዎች ቅርብ መሆናቸው ሊተኮርበት ይገባል፡፡ የልቦለዶች የቋንቋ ብቃት ለተማሪዎች የሚስማሙ፣ ተማሪዎች ለስነጽሁፍ በቀረቡና በተጋለጡ ቁጥር በስነ-ጽሁፍ ተወዳዳሪና ብቁ ሊያደርጓቸው የሚችሉ መሆናቸው ሊጤን ይገባል፡፡ አጫጭር ልቦለዶቹ ከስነ-ልቦና አንጻር ተማሪዎችን የሚያረኩና የበለጠ ለማንበብ እንዲተጉ የሚያስችሉ መሆን እንዳለባቸው Ghasemi (2011) ያስረዳሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ስነ-ጽሑፋዊ ምንባቦች ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሲመረጡ ትኩረት የሚደረግባቸውን ነጥቦች Brumfit (1985) በዝርዝር አስቀምጠዋል፡፡ እነዚህም የምንባቡ የቋንቋ መዋቅር ለተማሪዎች ተስማሚነት ያለው፤ ቋንቋው የዕለት ከዕለት የቋንቋ አጠቃቀም መገለጫ የሆነ፤አሉታዊ ያልሆነና አዎንታዊ ባህሪን የሚያስተምር፤በቂ የሆነ ባሕላዊ ዳራዊ ዕውቀትን የሚያስገኝ፤ተማሪዎችን የሚያነሳሳ ሳቢነት ያለው፤ ለተማሪዎች ሰፊ እይታን መፍጠር የሚችል መሆን እንዳለበት አስገንዝበዋል፡፡ ስለሆነም ምንባቦቹ በቋንቋ ትምህርት ሂደት አንብቦ መረዳትን ለማጎልበት ሲባል ከተለያዩ መድብሎችና መጽሐፎች ለምንባብ በሚያመች መንገድ የቀረቡትን ንድፈ ሃሳቦች ላይ በመመስረት ማስተካከያዎች በማድረግ ተወስደዋል፡፡

### 3.3.2. የመልመጃዎች አዘገጃጀት

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በአጭር ልቦለድ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የተለያዩ መልመጃዎች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ልምምዶችን ለመስራት የቡድን ተግባር በሚያከናውኑበት ጊዜ አንዱ ቡድን፡ስድስት አባላትን የያዙ አምስት ቡድኖች ተዋቅረዋል፡፡ ልምምዶች ሲጀምሩ የልቦለዶች ቅጅዎች ለተማሪዎች እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ በጥቅሉ የመልመጃዎች አደረጃጀትና ልምምዶች በሶስት እርከኖች ተከፋፍለዋል፡፡ እነዚህም ቅድመ ንባብ፣የንባብ ጊዜ እና ድህረ ንባብ ተግባራት ተብለው ተከፋፍለዋል፡፡ በዚህም Ghasemi (2011) የተጠቀሙባቸውን የአዘገጃጀትና የአተገባበር ስልቶች ተግባረዊ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ በየሂደቱ ተግባራዊ የሆኑ ድርጊቶች በቅድመ ተከተል ተገልጽዋል፡፡

#### 3.3.2.1 ቅድመ-ንባብ ተግባራት

ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የቀደመ-እውቀታቸውን መሠረት በማድረግ ስለምንባቡ ርዕሰ ጉዳይ ግንዛቤ የሚያገኙበት የቅድመ-ንባብ ተግባር ነው፡፡ በዚህ ሂደት ተማሪዎች ስለ ታሪኩ ቅድመ ትንቢያ እንዲሰጡ ተደርጓል፣ ስለታሪኩ ዳራ በቅድ-ምንባብ ጥያቄዎች መነሻነት በቡድን በመወያየት ሀሳብ ይሰነዝራሉ፡፡ በቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች አማካኝነት ከምንባቡ ርዕስ በመነሳት ቀጣዩ ምን ሊሆን እንደሚችል ፍንጭ እንዲያገኙ፣ ስለጭብጡ ግንዛቤ እንዲይዙ ያስችላሉ፡፡ ከቀረበው ምንባብ ተመርጠው ለወጡ ቃላት የነበራቸው እውቀት መነሻ በማድረግ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡ እንዲሁም የቃላትን ፍቺ ከምንባቡ አገባብ ባላቸው ፍች ተመስርተው ያዛምዳሉ፡፡

#### 3.3.2.2 የንባብ ጊዜ ተግባራት

ተማሪዎች ወደ ንባብ ሲገቡ፣በቃል ድምጽእያሰሙ እንዲያነቡ ተደርጓል፤ይህም የተማሪዎችን መናገርና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ሊያዳብር ይችላል። እንዲሁም ምንባቦችን በጽሞና(ድምጽአልባ) ንባብ እንዲያነቡም ተደርጓል፤በዚህን ጊዜ ተማሪዎች የምንባቡን መልዕክት የበለጠ እዲረዱ ሊያደርጋቸው ይችላል። ተማሪዎች በንባብ ሂደት ላይ እያሉ ንባባቸውን ገታ አድርገው ሁለት ወይም ሶስት ጥያቄዎች በማቅረብ እስከ አነበቡት ድረስ ባለው ማጠቃለያ እንዲሰጡ ተደርጓል። በዚህ ሂደት ጅምር ዓረፍተነገሮችን በመስጠት እንዲቋጩ ማድረግ፣ እንዲሁም ቀጣዩ የታሪኩ ክፍል ምን ሊሆን እንደሚችል እንዲተነብዩ ተደርጓል። የተወሰኑ ቃላትና ሐረጋትን በመግለጽ ተማሪዎች ገፀ-ባህሪያትን እንዲገልጹ፣በአነበቡት ተግባር ጥልቅ ውይይት እንዲያደርጉ ጥረት ተደርጓል።

#### 3.3.2.3 የድህረ-ንባብ ተግባራት

በዚህ ሂደት ተማሪዎች (ተጠኝዎች) ከምንባቡ ለወጡ ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት ከመለሱ በኋላ የተብራራ ምክንያት የሚሰጡባቸው፣ የቃላትናሐረጎች ምንነትና በተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦች ተደግፈው የቀረቡ የምርጫና የማዛመድ ጥያቄዎችን ትክክለኛ መልስ የሚመርጡበት፣በታሪኩ ላይ ጥልቅ እሳቤና ትንታኔ ለመስጠት የሚያስችሉ ክፍት ጠያቄዎች የተዋቀሩበት፣አጠቃላይ የሆኑ ጥያቄዎች በመስጠት፣ውይይትና ክርክር እንዲያደርጉ የሚያስችሉ፣የትረካውን የትኩረት ነጥብ ለመገንዘብ በሚያስችሉ ጥያቄዎች ተደራጅቶ የቀረበ ነው። እንዲሁም በትረካው መሰረት በተለያዩ እሳቢዎች ላይና የገጸባህሪያት አመለካከት ላይ በጽሑፍና በቃል ማብራሪያ መስጠት የሚያስችሉ ሆነው ተዘጋጅተዋል። በአጠቃላይ የመልመጃዎች አደረጃጀትና አቀራረብ (Lazar, 1993፣83-86) መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው ማለት ይቻላል።

### 3.4 የመረጃ አተናተን

በዚህ ጥናት ውስጥ፣የተነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስና የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከተጠኝ አካላት የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደባሕሪያቸው በአግባቡ ከተደራጁ በኋላ በአማካይ ውጤት፣በመደበኛ ልይይት፣በባዕድ ወይም ነጻ ናሙና ቲ-ቴስት መሰረት በማድረግ ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ሁኔታ ተተንትነዋል። ይህን አስመልክቶ Dornyei (2007፣179)፣Brown (2001)ን ዋቢ በማድረግ ሲገልጽ፣መረጃ መሰብሰብ የአንድ የጥናት ስራ ግማሽ አካል እንደሆነ ብንወስድ ቀሪው ግማሽ ስራ መረጃውን መተንተን ነው በማለት ያስረዳል። ከዚህም፣መረጃ መተንተን የጥናቱ መሰረተዊ አካልና ወደ ውጤት የሚያመራን እንደሆነ እንረዳለን። እንደ መረጃዎቹ ምንጭ ዝርዝር አተናተናቸው የሚከተለውን ይመስላል።

### 3.4.1 ከፈተናዎች የተገኘ መረጃ አተናተን

ተጠኝዎችን በቁጥጥር ቡድንና በሙከራ ቡድን መካከል ባላቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተመጣጣኝነት ለማደራጀት የቀረቡት ሁለት ተከታታይ የቅድመ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናዎች በድምር ውጤታቸው ማለትም ከ45 ውጤት ቡድኖችን ለማደራጀት ተግባር ከዋለ በኋላ የየቡድኖቹ አማካይ ወጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልቷል፡፡ በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራ በቡድኖች መካከል የጎላ ልዩነት መኖር አለመኖሩንም በቲ-ቴስት ስሌት ተፈትሾአል በሰንጠረዥ 1 ተመልክቱዋል፡፡ የቁጥጥር ቡድኑ በመደበኛው መንገድ፣ የሙከራ ቡድኑ ደግሞ ባጭር ልቦለድ ምንባቦች አማካኝነት በተደራጁ መልመጃዎች ተምረው ልምምዱ ከተጠናቀቀ በኋላ ሁለቱም ቡድኖች ሁለት ተከታታይ በሆኑ የድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናዎች በድምር ከ45 ውጤታቸው፣ ከተለየ በኋላ ለየቡድኖቹ አማካኝ ውጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልተዋል፡፡ ይህንንም መሰረት በማድረግ የሁለቱ ቡድኖች ከልምምድ በኋላ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤታቸው አንጻር ልዩነት እንዳላቸውና እንደሌላቸው በቲ-ቴስት / t-test/ ተሰልቶ ተተንትኑዋል፡፡ እያንዳንዱ ቡድን በቅድመ-ልምምድና በድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ውጤታቸው መካከል ልዩነት እንዳለውና እንደሌለው በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት /repeated measures sample t-test /አማካኝነት ተሰልቶ /በሰንጠረዥ 2 እና 3 ተመልክቱዋል/ ትንታኔም ተሰጦበታል፡፡

### 3.4.2 ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ አተናተን

በዚህ ጥናት የሙከራ ቡድን ተጠኝዎች በቅድመ-ልምምድ ደረጃ እና ከልምምድ በኋላ ከስነ-ጽሑፍ ዘሮች ውስጥ በአጭር ልቦለድ ቋንቋን መማር አንብቦ መረዳት ችሎታን ከማሻሻል አንጻር ያለውን ሚና በተመለከተ ያላቸውን ግንዛቤ ለመመርመር ከልምምድ በፊትና ከልምምድ በኋላ በጽሑፍ መጠይቅ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ተጠኝ ተማሪዎች በቅድመ-ልምምድ የግንዛቤ መለኪያ መጠይቁ እና በድህረ-ልምምዱ የግንዛቤ መለኪያ መጠይቁ የሰጡት ምላሽ በመጀመሪ የመጠይቁ አረፍተ ነገሮችን እንደ ጽንሰ-ሃሳባዊ ተዛምዶአቸው በአራት በመክፈል በፐርሰነት በማስደገፍ በገለጻ መልክ ለማብራራት ተሞክሯል፡፡ በማስከተል ደግሞ በአማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልቷዋል፡፡ እንዲሁም በቅድመና በድህረ-ልምምድ የፍተሻ መጠይቆች ለውጥ አሳይተው ወይም አላሳዩ እንደሆነ ቲ-ቴስት ቀመር ተሰልቷል፡፡ ይህም ሰንጠረዥ7 እና 8 ተመልክቷል፡፡

### 3.4.3 ከምልከታ የተገኘ መረጃ አተናተን

በዚህ ጥናት ውስጥ ምልከታ እንደ ደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ አገልግሏል፡፡ በምልከታ ሂደት መረጃ ሰብሳቢው ከተጠኝዎች ጋር አብሮ በመሆን ወይም በመገኘት ተጠኝዎቹ የሚያደርጉትን እያየና እየሰማ የተከታታለውን እየመዘገበ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ እንደሆነ ያለው (2004) ያስረዳል፡፡ ምልከታ በሚደረግበት ወቅት መረጃ ሰብሳቢው ተጠኝዎቹ በሚያውቁበት ወይም ባላወቁበት ሁኔታ ተጠኝዎች በሚገኙበት ቦታ በመሆን እርስ በእርሳቸው ያላቸውን መስተጋብር፣ምን እንደሚናገሩ፣ምን እንደሚሰሩ በሚመቸው መንገድ መረጃ የሚሰበሰብበት መንገድ ነው፤ያለው (2004)፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ በምልከታ መረጃ ሲሰበሰብ ትኩረት የተደረገው ተጠኝ የሙከራ ቡድኑ አጥኝው ባዘጋጀው ቴክስት መሰረት አማርኛ ቋንቋ እየተማሩ ባለበት ወቅት፣የተማሪዎች ተሳትፎና የቀረቡላቸውን መልመጃዎች እንዴት እንደሚሰሩ መከታተልና መመዝገብ ነው፡፡ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ትክክለኛና ስህተት መልሶች እየተደመሩ በፐርሰንት ገለጻ ተሰጠባቸዋል፡፡ የ‹‹እውነት›› ወይም‹‹ሐሰት›› የምርጫ፣የማዛመድ፣የክፍት ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ በተደራጁ ቡድኖች እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡ትክክለኛና ስህተት መልሶች ተደምረው ወደ ፐርሰንት በመለወጥ በገለጻ ተተንትነዋል፡፡

## ምዕራፍ አራት

### 4. የውጤት ትንተናና መብራሪያ

### 4.1 የጥናት ውጤት ትንተና

ይህ ጥናት አላማ አድርጎ የተነሳው በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና መፈተሽ የሚል ነው፡፡ ለዚህም በቅድመ-ልምምድና በድህረ-ልምምድ ፈተናዎች፣ በጽሑፍ መጠይቅና በምልከታ አማካይነት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ስለሆነም በዚህ ክፍል የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### 4.1.1 ከፈተናዎች የተገኘ የጥናቱ ውጤት ትንተና

በፈተናዎች፣የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደየ ባህሪያቸው ተደራጅተው በቅደም ተከተላቸው መሰረት እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡ የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑን ተጠኝዎች ከልምምዱ በፊት ያላቸውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ መረጃ መለየት አስፈላጊ በመሆኑ፣ በተሰጣቸው የቅድመ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና የቁጥጥር ቡድኑ ከ45 ያስመዘገበው ውጤት በአባሪ‹‹ሀ›› ተመልክቷል፡፡ የሙከራ ቡድኑ የቅድ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ውጤት በአባሪ ‹‹ለ›› ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሰረት የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ በቅድመ-ልምምድ ያስመዘገቡት ውጤት ንጽጽር እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 1 ተሰልቶ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ1. የቅድመ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ የውጤት ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት

| የቁጥጥር ቡድን | | | የሙከራ ቡድን | | | የነጻነት ደረጃ (df) | የ"P" ዋጋ (tab) | የተሰላ የ"t" ዋጋ (test) | ጉልህነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የተጠኝ ቁ. | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የተጠኝ ቁ. | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | | | | |
| 30 | 21.23 | 8.95 | 30 | 21.28 | 9.14 | 58 | 0.98 | -0.021 | የለም |

$p>0.05$

ከሰንጠረዥ1. መረዳት እንደሚቻለው የቁጥጥር ቡድኑ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ወጤት 21.23 ሲሆን፣ የሙከራ ቡድኑ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ወጤት ደግሞ 21.28 ነው፡፡ የሁለቱም ቡድኖች የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ወጤት ተመሳሳይነት ያላቸው ይመስላሉ፡፡ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ የመደበኛ ልይይት 8.95 ሲሆን፣የሙከራ ቡድኑ የመደበኛ ልይይት ደግሞ 9.14 ነው፡፡ ይህም የሁለቱም ቡድኖች የመደበኛ ልይይት ውጤት ተቀራራቢነት እንዳለው ያሳያል፡፡ ከዚህም በሁለቱ ቡድኖች የተመዘገቡት የፈተና ውጤቶች ካማካያቸው የተመሳሳይ ርቀት ስርጭት እንዳላቸው ያሳያል፡፡ ነገር ግን የአማካኝ

ውጤትን ብቻ በማየት በመካከላቸው ያለው ልዩነት አስተማማኝ መሆኑን ማረጋገጥ አይቻልም(ያዳግታል)፤ ይሁን እንጅ በስታቲስቲክ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ይህም በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተፈትሾ የ " t " ስሌት ዋጋ /tab/ 0.98 ሲገኝ በ0.05 የጉልህንት ደረጃ /significance level/፣በ58 የነጻነት ደረጃ /Degree of freedom/ ባለሁለት ጫፍ ፍተሻ የ " t " ሰንጠረዥ ዋጋ ወይም / test / 0.021 ሆኑዋል፡፡ በዚህም መሰረት የ " t " ዋጋ /0.021/ ነው፡፡ከዚህም የመንረዳው ተጠኝ ተማሪዎች ከልምምድ በፊት በቡድን ደረጃ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ተመጣጣኝ እንደነበር ነው፡፡

ሌላው በፈተና አማካይነት የተሰበሰበው መረጃ የድህረ-ልምምድ የፈተና ውጤት ነው፡፡ የቁጥጥር ቡድኑ በመደበኛው መንገድ፣ የሙከራ ቡድኑ ደግሞ አጥኝው ባዘጋጀው፣ በአጭር ልቦለድ አማካኝነት አማርኛ ቋንቋ ከተማሩ በኋላ ሁለቱም ቡድኖች አንድ ዓይነት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ተፈትነው ያስመዘገቡት ውጤት፣ የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የፈተና ውጤት በአባሪ ‹‹ሐ›› ይመልከቱ፡፡ የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የፈተና ውጤት በአባሪ ‹‹መ›› ይመልከቱ፡፡ በዚህ መሰረት የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የድህረ-ልምምድ የፈተና ውጤት በሰንጠረዥ2 ተነጻጽሮ ቀርቡዋል፡፡

ሰንጠረዥ 2 የድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት

| የቁጥጥር ቡድን | | | የሙከራ ቡድን | | | የነጻነት ደረጃ (df) | የተሰላ የ " p" ዋጋ (tab) | የተሰላ የ"t" ዋጋ (test) | ጉልህ ነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የተጠኝ ቁ | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የተጠኝ ቁ | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | | | | |
| 30 | 21.60 | 7.26 | 30 | 26.68 | 7.36 | 58 | 0.009 | 2.69 | አለ |

$p<0.05$

ከሰንጠረዥ2 መረዳት እንደሚቻለው፣ የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት /21.63/ ሲሆን፣የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት ደግሞ /26.68/፣ ነው፡፡ የሙከራ ቡድኑ አማካኝ ውጤት፣ከቁጥጥር ቡድኑ አማካኝ ውጤት በ5.05 ብልጫ አሳይቷል፡፡ ይህም ሁለቱ ቡድኖች ከልምምድ በኋላ ከአንብቦ መረዳት ችሎታቸው አንጻር መበላለጥ እንደታየባቸው የሚያመለክት ይመስላል፡፡ ልዩነቱም ምንያህል ጉልህ እንደሆነ በባአድ ናሙና በ"t " ቴስት ስሌት ተፈትሿል፡፡ በዚህም የ"p" ስሌት ዋጋ /tab/ 0.009 ሲሆን በ0.05 የጉልህነት ደረጃ፣በ54 ነጻነት ደረጃ በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ የ "t" ሰንጠረዥ ዋጋ /tort/ 2.69 ሆኑዋል፡፡ የተሰላው የ" p " ዋጋ /0.009/ ከሰንጠረዥ የ"t " ዋጋ /2.62/ ያነሰ በመሆኑም በድህረ ልምምድ የአንብቦ መረዳት ፈተናው ከፍተኛ አንብቦ የመረዳት አማካኝ ውጤት

26.68 ያለው የሙከራ ቡድኑ ዝቅተኛ አማካኝ ውጤት 21.60 ካለው የቁጥጥር ቡድን የበለጠ የአንብቦ መረዳት ውጤት ማስመዝገቡን ያመለክታል፡፡

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው፣በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር፣ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣ አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ እንዳለው ነው፡፡ ምክንያቱም በተለመደው መንገድ ከተማሩት ይልቅ በአጭር ልቦለድ ምንባቦች በተዘጋጀው ጽሑፍ(ቴክስት) የተማሩት ተማሪዎች የተሸለ ውጤት ማስመዝገብ ችላዋል፡፡እንዲሁም ልቦለድ ምንባቦችን ተከትሎ የሙከራ ቡድኑ የተለማመደባቸው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ምክንያት የመስጠት፣ጽንሰ-ሃሳቦችን የመመርመርና የማዛመድ፣ጥልቅ ግንዛቤን የሚፈጥሩ መሆናቸው፤ አማርኛ ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ማስተማር ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ሂደት፣ጥልቅ አስተሳሰብን፣ ማመዛዘንንና የነገሮችን ምክንያታዊ ትስስር መረዳትን እንዲያዳብሩ ያለው ሚና ከፍ ያለ እንደሆነ የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ያሳየው ብልጫ አመላክተዋል፡፡

የቁጥጥር ቡድኑን እና የሙከራ ቡድኑን የድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ውጤት መደበኛ ልይይቶች አንጻር በተደረገው ንጽጽር የሙከራ ቡድኑ /7.36/ ሲሆን የቁጥጥር ቡደኑ መደበኛ ልይይት ደግሞ /7.26/ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህም በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው የውጤት ልዩነት ተቀራራቢ እንደሆነ ቢያሳይም በሙከራ ቡድኑ መካከል በአንጻራዊነት መጠነኛ የውጤት መራራቅ በተጠኝዎች መኖሩን የሚጠቁም ይመስላል፡፡ ከትምህርት በኋላም ደግሞ ሁለቱ ቡድኖች በተናጠል በአንብቦ መረዳት ችሎታቸው መሻሻል እዳላቸውና እንደሌላቸው ንጽጽር ተደርጉዋል፡፡ ይህንንም በሰንጠረዥ3 ለማሳየት ተሞክሩዋል፡፡

ሰንጠረዥ3 የቡድኖቹ የቅድመና የድህረ-ልምምድ የእንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ተናጠላዊ ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት

| ተጠኝ ቡድን | የፈተና አይነት | የአንብቦ መረዳት ውጤት | | | ተቀንሶ የተገኘ የልዩነት አማካይ ነጥብ $\overline{D}$ | ተቀንሶ የተገኘ የልዩነት መደበኛ ልዩነት | የነጻነት ደረጃ (df) | የተሰላ የ "p" ዋጋ (p-value) | የተሰላ የ "t" (t-test) | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | | | | | | |
| ቁጥጥር | ቅድመ ልምምድ | 30 | 21.28 | 9.14 | 0.32 | 3.2 | 29 | 0.592 | 0.542 | የለም |
| | ድህረ ልምምድ | 30 | 21.6 | 7.26 | | | | | | |
| ሙከራ | ቅድመ ልምምድ | 30 | 21.23 | 8.95 | 5.45 | 4.06 | 29 | 0.000 | 7.347 | አለ |
| | ድህረ ልምምድ | 30 | 26.68 | 7.36 | | | | | | |

ሰንጠረዥ 3 እንደሚያሳየው የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት /21.6 / ከቅድመ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት 21.28 ጋር ሲነጻጸር በልጦ የታየው በ0.32 ብቻ ነው፡፡ ይህም ልዩነት ጉልህነት እንዳለውና እንደሌለው በዳግም ልኬታ ናሙና "t -ቴስት" repeated measure sample t-test ተፈትሿል፡፡ በፍተሻውም የ " t " ስሌት ዋጋ /tab/ 0.592 ሲሆን በ0.05 የጉልህነት ደረጃ ፣ በ29 የነፃነት ደረጃ ባለሁለት ፍተሻ " t " ሠንጠረዥ ዋጋ /tort/ 0.542 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት የ " t " ስሌት ዋጋ /0.592/ ከሰንጠረዥ የ " t " ዋጋ /0.542/ ሲነፃፀር የጎላ ልዩነት አይታም፡፡ ይህም ቡድኑ በድህረ-ልምምድና በቅድመ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት ጉልህ ልዩነት አለማሳየቱን ሊያመለክት ችሉዋል፡፡ በመሆኑም የቁጥጥር ቡድኑ ተጠኝዎች በተለመደው የማስተማሪያ መጽሐፍ መማራቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን በማሻሻል ረገድ የጎላ አስተዋጽኦ እንደሌለው የሚያሳይ ይመስላል፡፡ ማለትም የቁጥጥር ቡድኑ፣ከልምምድ በፊትም ሆነ ከልምምድ በኋላ አጭር ልቦለድ ምንባብን መሰረት አድርገው በተዘጋጁ መልመጃዎች ስላልተለማመዱ ምክነያታዊ፣ጥልቅና ማመዛዘንን የሚጠይቁ ጥያቄዎችን የመስራት አቅማቸው እንዳልጎለበተ ማየት ተችሉዋል፡፡

በሌላ መልኩ ሲታይ ግን የሙከራ ቡድኑ የድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት /26.68/፣ከቅድመ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት /21.23/ ጋር ሲነፃፀር በ5.45 ልቆ ታይቷል፡፡ ልዩነቱ የጎላ መሆኑን ብሎም ብልጫ እንዳለው የሚያሳይ ይመስላል፡፡ ስለዚህም ሙከራ ቡድኑ ከልምምድ በፊትና ከልምምድ በኋላ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ሙከራ ቡድኑ በአጭር ልቦለድ አማካይነት የአንብቦ መረዳት ትምህርት በመማሩ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ቀድሞ ከነበረው የተሻለ

ግንዛቤን አግኝቷል ማለት ይቻላል፡፡ ከዘህም በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር፣ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣ አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ እንዳለው ያመለከተ ሲሆን፣ የማንበብ ፍላጎት ሲጨምር የአንብቦ መረዳት ችሎታም በዚያው መጠን እደሚሻሻል የተገኘው ውጤት አመላክቷል፡፡

### 4.1.2. ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ የጥናት ውጤት ትንተና

#### 4.1.2.1 ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ የጥናት ውጤት ትንተና (በዓይነታዊ መንገድ)

የጽሑፍ መጠይቁ ውስጥ የተካተቱ ጥያቄዎች ወይም አረፍተ ነገሮች እንደያዙት ጽንሰ-ሃሳብ ተዛምዶ በአራት ክፍሎች ለመዛመድ(ለመቦደን) ጥረት ተደርጓል፡፡ አጥኝው ይህን ተዛምዶ ለማደራጀት የሞከረው ጥያቄዎቹ የያዙትን ጽንሰ-ሃሳብ ከጥናቱ ርዕስና ጥናቱ ከሚያነሳቸው ጥያቄዎች መሰረታዊ ሃሳብ ጋር በማገናዘብ ነው፡፡ በአራት ክፍሎች የተዛመዱትን የመጠይቁ ጥያቄዎች(አረፍተ ነገሮች) የተጠኝዎች ምላሽ በየተዛምዶአቸው በገለጻ ለማብራራት ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህም በእያንዳንዱ ጥያቄ የተሰጠን ምላሽ በተናጠል በመተንተን የሚወስደውን ቦታና ጊዜ ለመቆጠብና የተሰጠውን ምላሽ ጠቅለል አድርጎ ለመግለጽና ለመተርጎም ስለሚያስችል ነው፡፡ ስለሆነም ከምድብ አንድ እስከ አራት ያሉትን የተዛምዶ ምላሾች እንደሚከተለው በገለጻ ተተንትነዋል፡፡

በምድብ አንድ ውስጥ የተዛመዱት የመጠይቁ ጥያቄዎች (አረፍተ ነገሮች)

ተራ ቁጥር 1. አጭር ልቦለድ ማንበብ ማህበራዊ ተግባቦትን ያጎለብታል፡፡

ተራ ቁጥር 12. አጭር ልቦለድ ማንበብ የሌሎችን ስሜት መረዳትን ያጎለብታል፡፡

ተራ ቁጥር 15. አጭር ልቦለድ ተማሪዎች ስለሌሎች ባህል እንዲያውቁ ፍንጭ ይሰጣል፡፡

የሰንጠረዥ4፣ የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምልሽ (ለዓይነታዊ ትንተና)

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | የተማሪዎች ምላሽ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ | አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም |
| 1 | በቁጥር | 8 | 15 | 6 | 1 | 23 | 7 |
| | በፐርሰንት | 26.6% | 50% | 20% | 3.3% | 76.6% | 23.3% |
| 12 | በቁጥር | 4 | 18 | 7 | 1 | 22 | 8 |
| | በፐርሰንት | 13.3% | 60% | 23.3% | 3.3% | 73.3% | 26.6% |
| 15 | በቁጥር | 2 | 16 | 11 | 1 | 18 | 12 |
| | በፐርሰንት | 6.6% | 53.3% | 36.6% | 3.3% | 60% | 40% |
| | አማካይ | 15.5% | 54.4% | 26.6% | 3.3% | 69.9% | 29.9% |

ሰንጠርዥ5፣ የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምልሽ (ለዓይነታዊ ትንተና)

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | የተማሪዎች ምላሽ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ | አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም |
| 1 | በቁጥር | 3 | 16 | 10 | 1 | 19 | 11 |
| | በፐርሰንት | 10% | 53.3% | 33.3% | 3.3% | 63.3% | 36.6% |
| 12 | በቁጥር | 7 | 17 | 5 | 1 | 24 | 6 |
| | በፐርሰንት | 23.3% | 56.6% | 16.6% | 3.3% | 80% | 20% |
| 15 | በቁጥር | 2 | 19 | 7 | 2 | 21 | 9 |
| | በፐርሰንት | 6.6% | 63.3% | 23.3% | 6.6% | 70% | 30% |
| | አማካይ | 13.3% | 57.7% | 24.4% | 4.4% | 71% | 28.8% |

ከሰንጠረዥ4፣እና ከሰንጠረዥ5፣ እንደሚታየው ለጥያቄ1 ‹‹አጭር ልቦለድ ማህበራዊ ተግባቦትን ያጎለብታል›› ለሚለው የተሰጡ ምላሾችን ብዛት ስናወዳድር፣ የቁጥጥር ቡድኑ

በቅድመ-ልምምድ ጊዜ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ ለሚሉ አዎንታዊ መልስ የሰጡት 76.6% (ፐርሰንት) ሲሆኑ፣ አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም በማለት አሉታዊ መልስ የሰጡት ብዛት 23.3% ናቸው፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ በማለት የመለሱት 63.3% ሲሆኑ፣ አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም በመለት የመለሱት 36.6% (ፐርሰንት) እንደሆነ ያሳያል፡፡ ከዚህ አንጻር የቅድመ-ልምምድ ምላሽ እና የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ምላሽ ተቀራራቢ እነደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች አጭር ልቦለድ ማንበብ ማህራዊ ተግባቦታቸውን እንደሚያዳብርላቸው ግንዛቤው አላቸው ማለት ይቻላል፡፡

ከሰንጠረዥ4 እና 5፣እንደተመለከተው ለጥያቄ12 አጭር ልቦለድ ማንበብ የሌሎችን ችግርና ስሜት መረዳትን ያጎለብታል፣ለሚለው በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ላይ ‹‹በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ›› ብለው መልስ የሰጡት 72.3% ሲሆኑ፣አልስማማምና ጭራሽ አልስማማም በማለት አሉታዊ መልስ የሰጡት ደግሞ 26.6% (ፐርሰንቱ) ናቸው፡፡ በዚሁ በጥያቄ12 ላይ የሙከራ ቡድኑ የቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ፣ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ ብለው የመለሱ ተማሪዎች ብዛት 80% (ፐርሰንቱ) ሲሆኑ፣አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም ብለው የመለሱት 20% (ፐርሰንቱ) ናቸው፡፡

ለጥያቄ15፣ማለትም አጭር ልቦለድ ማንበብ ተማሪዎች ስለሌሎች ባህል እንዲያዉቁ ፍንጭ ይሰጣል ለሚለው መጠይቅ የተሰጡ ምላሽችን ስንቃኝ ደግሞ፣ በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ምላሽ መሰረት በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ ብለው የመለሱ 60% (ፐርሰንቱ) ሲሆኑ፣ አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም ብለው የመለሱ 40% (ፐርሰንቱ) ናቸው፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድኑን በቅድመ-ልምምድ ጊዜ ለጥያቄ15፣የሰጡትን ምላሽ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት መልስ የሰጡ 70% ሲሆኑ፣አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም ብለው የመለሱ ተማሪዎች 30% (ፐርሰንቱ) ናቸው፡፡

ከዚህ አንጻር አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በቅድመ-ልምምድ ወቅት አጭር ልቦለድ ማንበብ ስለሌሎች ባህል ለማወቅ ፍንጭ እንደሚሰጥ ግንዛቤ እንዳላቸው ያሳያል፡፡ በአንጻራዊነት ደግሞ በተጠቀሰው መጠን መሰረት ጥቂት የማይባሉ ተማሪዎች አጭር ልቦለድ ማንበብ ስለሌሎች ባህል እውቂያ ወይም ፍንጭ እንደሚሰጥ ግነዛቤው የላቸውም ማለት ይቻላል፡፡

የሰንጠረዥ6፣ የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምልሽ

(በዓይነታዊ ትንተና)

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | የተማሪዎች ምላሽ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ | አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም |
| 1 | በቁጥር | 3 | 16 | 9 | 2 | 19 | 11 |
| | በፐርሰንት | 10% | 53.3% | 30% | 6.6% | 63.3% | 36.6% |
| 12 | በቁጥር | 10 | 14 | 6 | — | 24 | 6 |
| | በፐርሰንት | 33.3% | 46.6% | 20% | — | 80% | 20% |
| 15 | በቁጥር | 6 | 16 | 7 | 1 | 22 | 8 |
| | በፐርሰንት | 20% | 53.3% | 23.3% | 3.3% | 73.3% | 26.6% |
| | አማካይ | 21.1% | 51% | 24.3% | 3.3% | 72.2% | 27.7% |

የሰንጠረዥ7፣ የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምልሽ (በዓይነታዊ ትንተና)

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | የተማሪዎች ምላሽ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ | አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም |
| 1 | በቁጥር | 8 | 10 | 8 | 4 | 18 | 12 |
| | በፐርሰንት | 26.6% | 33.3% | 26.6% | 13.3% | 60% | 40% |
| 12 | በቁጥር | 11 | 15 | 4 | — | 26 | 4 |
| | በፐርሰንት | 36.6% | 50% | 13.3% | — | 86.6% | 13.3% |
| 15 | በቁጥር | 8 | 17 | 4 | 1 | 25 | 5 |
| | በፐርሰንት | 26.6% | 56.6% | 13.3% | 3.3% | 83.3% | 16.6% |
| | አማካይ | 29.9% | 46.6% | 17.7% | 5.5% | 76.6% | 23.3% |

በሰንጠረዥ6፣እና7 የቀረበውን ውጤት ስንመለከት ደግሞ ከጥያቄ1 አንጻር በቅድመ-ልምምድ ወቅት በቁጥጥር ቡድኑም ሆነ በሙከራ ቡድኑ የተመዘገበው ውጤት ከሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ ውጤት ጋር ሲነጻጸር ልዩነት አልታየበትም። ነገር ግን በጥያቄ12፣በቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ-ልምምድ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ የሚለው ምላሽ 72% (ፐርሰንት) ሲሆን፣የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ ውጤት ደግሞ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ የሚለው ምላሽ ድምር 86.6% (ፐርሰንት) ነው። ይህም የ14.6% (ፐርሰንት) ልዩነት መሻሻል እንዳለ ያመላክታል። በጥያቄ15፣ በሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የተሰጡ ምላሾች ድምር 70% ሲሆን፣በአንጻሩ በሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የተሰጡ መላሾች ድምር 83.3% (ፐርሰንት)ነው። ይህም የ13.3% (ፐርሰንት) ልዩነት፣መሻሻል እንዳለ ያመላክታል።

ከተጠቀሱት መረጃዎች በመነሳት መረዳት የሚቻለው የሙከራ ቡድኑ በነበረው በአጭር ልቦለድ ቋንቋን የመማር ሂደት አጭር ልቦለድ ማንበብ ስለተለያዩ ባሕሎች ለማወቅ መንገድ ከፋች መሆኑን ከነበሩበት ሁኔታ የበለጠ ግንዛቢያቸውን ማስፋት መቻላቸውን ነው። ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በነበረው በአጭር ልቦለድ መማር ማስተማር ሂደትከባህል እውቂያ አንጻር የተሻለ ግንዘቤ አግኝተዋል ማለት ይቻላል። ከዚህ በተያያዘ መንገድ ስነ-ጽሑፍ የተለያዩ ባህሎችን የሚገልጽና በባህል የበለጸገ መሆኑ፣በቋንቋ አጠቃቀም የዳበረና የበለጸገ መሆኑ፣በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሊያመጣ የሚችለውን በጎተጽንኦ አመላካች ነው በድሉ ዋቅጅራ (1996)። ይህም አጭር ልቦለድ አንዱ የስነ-ጽሑፍ ዘር በመሆኑ በጥያቄ1፣12 እና 15 የቀረቡት የአንብቦ መረዳት ችሎታ የግንዛቤ መፈተሻ ጥያቄዎች ተዛማጅነት ያላቸው መሆኑን ያሳያል ማለት ይቻላል። በዚህም መሰረት ጥያቄ1፣አጭር ልቦለድ ከማህበራዊ ተግባቦትን ከማጎልበት፣ ጥያቄ12፣ አጭር ልቦለድ የሌሎችን ስሜት ከመረዳት እንዲሁም ጥያቄ15፣ አጭር ልቦለድ ከራስ በሃል ውጭ ያሉ ስለሌሎች ባህል ለማወቅ ፍንጭ ከመስጠት አንጻር የቀረቡ በመሆናቸው ተመሳሳይስሎአቸው የጠበቀ በመሆኑ ተጣምረው ሊተነተኑ ችለዋል።

በምድብ ሁለት ውስጥ የተዛመዱት የመጠይቁ ጥያቄዎች (አረፍተ ነገሮች)

ተራ ቁጥር 3. አጭር ልቦለድ ማንበብ የንባብ ክሂልን ያዳብራል።

ተራ ቁጥር 8. አጭር ልቦለድ የቋንቋ መማር ሂደትን ሳቢና ማራኪ ያደርገዋል።

ተራ ቁጥር 9. አጭር ልቦለድ ለቋንቋ መማር ሂደት እውነተኛ አውድን ይፈጥራል።

የሰንጠረዥ8፣ የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምልሽ

(ለዓይነታዊ ትንተና)

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | የተማሪዎች ምላሽ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ | አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም |
| 3 | በቁጥር | 12 | 16 | 2 | — | 28 | 2 |
| | በፐርሰንት | 40% | 53.3% | 6.6% | — | 93.3% | 6.6% |
| 8 | በቁጥር | 6 | 18 | 3 | 3 | 24 | 6 |
| | በፐርሰንት | 20% | 60% | 10% | 10% | 80% | 20% |
| 9 | በቁጥር | 2 | 11 | 11 | 6 | 13 | 17 |
| | በፐርሰንት | 6.6% | 36.6% | 36.6% | 20% | 43.3% | 56.6% |
| | አማካይ | 22.2% | 49.9% | 17.7% | 15% | 72.1% | 27.7% |

የሰንጠረዥ9፣ የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምልሽ
(ለዓይነታዊ ትንተና)

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | የተማሪዎች ምላሽ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ | አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም |
| 3 | በቁጥር | 7 | 17 | 6 | — | 24 | 6 |
| | በፐርሰንት | 23.3% | 56.6% | 20% | — | 80% | 20% |
| 8 | በቁጥር | 7 | 15 | 6 | 2 | 22 | 8 |
| | በፐርሰንት | 23.3% | 50% | 20% | 6.6% | 73.3% | 26.6% |
| 9 | በቁጥር | 3 | 14 | 11 | 2 | 17 | 13 |
| | በፐርሰንት | 10% | 46.6% | 36.6% | 6.6% | 56.6% | 43.3% |
| | አማካይ | 18.8% | 51.4% | 25.5% | 4.4% | 69.9% | 29.9% |

ሰንጠረዥ8፣9 እንደተገለጸው ጥያቄ3፣የሚያመለክተው አጭር ልቦለድ ማንበብ የንባብ ክሂልን ከማዳበር አንጻር ያለውን ሚና የሚያንጸባርቁበት ነው። በዚህም መሰረት በቁጥጥር

ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ምላሽ፣በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ ብለው የመለሱ ተማሪዎች ብዛት በመቶኛ 93.3% ሲሆኑ፣አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም ብለው የመለሱ ተማሪዎች ባዛት ደግሞ 6.6% ናቸው፡፡ ከዚህ በተቀራረበ ሁኔታ የቁጥጥር ቡድኑ በድህረ-ልምምድ ሂደት ለጥያቄ3፣በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ ብለው የመለሱ ተማሪዎች ብዛት 80% (ፐርሰንት) ሲሆኑ፣አልሰማማም እና ጭራሽ አልስማማም በማለት መልስ የሰጡ ተማሪዎች ብዛት ደግሞ 20% (ፐርሰንት) ናቸው፡፡ ከዚህ መግለጫ መረዳት የሚቻለው አባዛኛዎቹ ተጠኝዎች አጭር ልቦለድ ማንበብ የንባብ ክሂልን ማዳበር እንደሚያስችል ግንዛቤው አላቸው ማለት ይቻላል፡፡

በሰንጠረዥ8፣ እንደተጠቀመው ጥያቄ8፣ ማለትም አጭር ልቦለድ የቋንቋ መማር ሂደትን ሳቢና ማራኪ ያደርገዋል ለሚለው የተሰጡ ምላሾችን ስንቃኝ በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ላይ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ ብለው የመለሱ ተማሪዎች በፐርሰንት 80% ሲሆኑ፣አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም በማለት የመለሱ ተማሪዎች ብዛት ደግሞ 20% (ፐርሰንት) ያህሉ ናቸው፡፡ ይህ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ምላሽና ከሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ምላሽ ጋር ተመሳሳይነት ይታይበታል፡፡ በመሆኑም ተጠኝዎች፣ አጭር ልቦለድ የቋንቋ መማር ሂደትን ሳቢና ማራኪ ያደርገዋል በሚለውን ጽንሰ ሃሳብ ላይ ግንዛቤ እንደነበራቸው ውጤቱ ያመላክታል፡፡

በሰጠረዥ8፣እና9 እንደተጠቀመው ጥያቄ9፣ማለትም አጭር ልቦለድ ለቋንቋ መማር ሂደት እውነተኛ አውድን ይፈጥራል ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ጊዜ በጣም እስማማለሁ እና እስማማም ብለው መልስ የሰጡ ተማሪዎች 43.3% (ፐርሰንት) ሲሆኑ፣ አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም ብለው መልስ የሰጡ ተማሪዎች 56.6% (ፐርሰንት) ናቸው፡፡ በጥያቄ9፣ በቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምዱና በሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ጊዜ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የመለሱ ተማሪዎች 56.6% ሲሆኑ፣አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም በመለት የመለሱት 43.3% (ፐርሰንት) የሆኑት ናቸው፡፡

ከሰንጠረዣዊ መግለጫዎች መረዳት እንደሚቻለው አጭር ልቦለድ ለቋንቋ መማር ሂደት እውነተኛ አውድን ይፈጥራል የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ላይ ተጠኝ ተማሪዎች ግልጽ የሆነ እውቀት እንዳልነበራቸው የተገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡

የሰንጠረዥ10፣የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምልሽ
(ለዓይነታዊ ትንተና)

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | የተማሪዎች ምላሽ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በጣም እስማማለሁ ና እስማማለሁ | አልስማማም ና ጭራሽ አልስማማም |
| 3 | በቁጥር | 10 | 14 | 6 | — | 24 | 6 |
| | በፐርሰንት | 33.3% | 46.6% | 20% | — | 80% | 20% |
| 8 | በቁጥር | 6 | 19 | 4 | 1 | 25 | 5 |
| | በፐርሰንት | 20% | 63.3% | 13.3% | 3.3% | 83.3 | 16.6% |
| 9 | በቁጥር | 3 | 14 | 10 | 3 | 17 | 13 |
| | በፐርሰንት | 10% | 46.6% | 33.3% | 10% | 56.6% | 43.3% |
| | አማካይ | 21.1% | 52.1% | 22.2% | 4.4% | 73.3% | 26.6% |

የሰንጠረዥ11፣የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምልሽ
(ለዓይነታዊ ትንተና)

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | የተማሪዎች ምላሽ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በጣም እስማማለሁ ና እስማማለሁ | አልስማማም ና ጭራሽ አልስማማም |
| 3 | በቁጥር | 17 | 11 | 2 | — | 28 | 2 |
| | በፐርሰንት | 56.6% | 36.6% | 6.6% | — | 93.3% | 6.6% |
| 8 | በቁጥር | 15 | 11 | 1 | 3 | 26 | 4 |
| | በፐርሰንት | 50% | 36.6% | 3.3% | 10% | 86.6 | 13.3% |
| 9 | በቁጥር | 7 | 16 | 7 | — | 23 | 7 |
| | በፐርሰንት | 23.3% | 53.3% | 23.3% | — | 76.6% | 23.3% |
| | አማካይ | 43.3% | 42.1% | 11% | 3.3 % | 85.5% | 14.4% |

በሰንጠረዥ10፣ እንደተመለከተው ለጥያቄ3፣ በሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ምላሽ መሰረት በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የመለሱ ተማሪዎች ብዛት 80% ሲሆኑ፣ አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም በማለት የመለሱ 20% (ፐርሰንት) ናቸው፡፡

በሰንጠረዥ11፣እንደተመለከተው ለጥያቄ3፣ በሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ምላሽ መሰረት በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የመለሱ ተማሪዎች 80% (ፐርሰንት) ሲሆኑ፣ አልስማማም እና ጭራሽ አልማማም በማለት የመለሱ ደግሞ 20% (ፐርሰንቱ) ናቸው፡፡ በዚሁ ጥያቄ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ ብለዉ የመለሱ ተጠኝዎች ብዛት በፐርሰንት ሲሰላ 93.3% እንደሆነ ሰንጠረዡ ያሳያል፡፡ ይህም በሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ ጊዜ የተመዘገበው ውጤት በ13.3% (ፐርሰንት) ከሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ውጤት ብልጫ እንዳለው ያሳያል፡፡ ከዚህ በመንደርደር በሙከራ ቡድኑ የተካተቱ ተጠኝዎች በነበረው ቋንቋን በአጭር ልቦለድ የማስተማር ሂደት ድምጽ እያሰሙ እና ሳያሰሙ የማንበብ ተግባራትን መፈጸማቸው ስለንባብ ክሂል የነበራቸው ግንዛቤ እየሰፋ መሄዱን የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

በሰንጠረዥ10፣እና11፣ እንደተመለከተው የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ጥያቄ8፣ማለትም አጭር ልቦለድ የቋንቋ መማር ሂደትን ሳቢና ማራኪ ያደርገዋል፡፡ ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የመለሱ ተማሪዎችበፐርሰንት 73.3% ሲሆኑ፣ 26.6% የሚሆኑት ግን አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ በዚሁ በተራ ጥያቄ8፣ ሙከራ ቡድኑ በድህረ-ልምምድ ሂደት በጣም እማማለሁና እስማማለሁ በማለት 86.6% (ፐርሰንቱ) አዎንታዊ መልስ ሰጠዋል፡፡ 13.3% (ፐርሰንት) ሆኑት ደግሞ አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ በመሆኑም በሙከራ ቡድኑ በድህረ-ልምምድ ጊዜ የተመዘገበው ውጤት ከሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ውጤት ከሙከራ ቡድኑ ተጠኝዎች ውጤት 13.3% አሳይቱዋል፡፡

ይህን ውጤት መነሻ በማድረግ የሙከራ ቡድኑ ተጠኝዎች ቋንቋ በአጭር ልቦለድ አማካይነት መማራቸው፡፡ ከነበረው የክፍል ውስጥ ተግባራትና ከተማሪዎች ተሳትፎ በመነሳት በአጭር ለቦለድ ቋንቋን መማር ትምህረቱን ሳቢና ማራኪ እንደሚያደርገው ከሂደቱ ተገንዝበዋል ማለት ይቻላል፡፡

በሰንጠረዥ10 እና 11 እንደተመለከተው ለጥያቄ9፣ ማለትም አጭር ልቦለድ ለቋንቋ መማር ሂደት እውነተኛ አውድን ይፈጥራል፤ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ ሙከራ ቡድኑ በቅድመ-ልምምድ ጊዜ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት አዎንታዊ መልስ የሰጡ ተማሪዎች 56፤6% (ፐርሰንት) ሲሆኑ፣ አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም በማለት መልስ የሰጡት ደግሞ 43.3% ፐርሰንቱ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ ምላሽ ስናጤን፣ በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ በማለት የመለሱ ተማሪዎች ብዛት በፐርሰንት 76.6% ናቸው። ይህም ከሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ምላሽ በ20% (ፐርሰንት) ብልጫ እንዳለው ያመለክታል። ከዚህ በመነሳት አጭር ልቦለድ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ እውነተኛ አውድን ከመፍጠር አንጻር ያለውን ሚና ተማሪዎች አስቀድሞ ከነበራቸው እውቀት በልምምድ ሂደቱ መሻሻል እንዳሳዩ ያመለክታል። ማለትም የቋንቋ ትምህርት በአጭር ልቦለድ አማካይነት ሲሰጥ፣ የልቦለዱ መቼትና ገለጻ የገጸባህሪያቱ ንግግርና ትረካ ከእውናዊ ዓለም ጋር ተመሳስሎ እንዳለው በተግባር ማየታቸው በተጠቀሰው ጽንሰ ሃሳብ ላይ ሰፋ ያለ ግንዛቤ አስገኝቶላቸዋል ማለት ይቻላል።

ጠቅለል ብሎ ሲታይ በጥያቄ3፣ አጭር ልቦለድ የማንበብ ክሂልን ያዳብራል፤በጥያቄ8፣ አጭር ልቦለድ መማር ሂደትን ሳቢና ማራኪ ያደርገዋል፤ በጥያቄ9፣አጭር ልቦለድ ለቋንቋ መማር ሂደት እውነተኛ አውድን ይፈጥራል። የሚሉት ጽንሰ ሃሳቦች በተዛማጅነት ትንታኔ ተሰጥባቸዋል። ከዚህም ጽንሰ ሃሳቦች ተማሪዎች በልምምድሂደት የተሸለ ግንዛቤ እንንዳገኙ መረዳት ይቻላል።

በምድብ ሦስት ውስጥ የተዛመዱት የመጠይቁ ጥያቄዎች (አረፍተ ነገሮች)

ተራ ቁጥር 6. አጭር ልቦለድ ጥልቅ አስተሳሰብን ያጎለብታል።

ተራ ቁጥር 10. አጭር ልቦለድ ተማሪዎች የራሳቸውን አመለካከት እንዲገልጹ፣እንዲያንጸባርቁ ያስችላቸዋል።

ተራ ቁጥር 13. አጭር ልቦለድ ማንበብ የፈጠራ ችሎታን ያዳብራል።

ተራ ቁጥር 14. አጭር ልቦለድ ማንበብ የመገመትና የመተንበይ አቅምን ይጨምራል።

ተራ ቁጥር 18. አጭር ልቦለድ የማሰብና የመመራመር ተነሳሽነት እንዲጎለብት ያስችላል።

የሰንጠረዥ12፣የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ

(ለዓይነታዊ ትንተና)

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | የተማሪዎች ምላሽ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በጣም እስማማለሁ + እስማማለሁ | አልስማማም + ጭራሽ አልስማማም |
| 6 | በቁጥር | 9 | 16 | 5 | — | 25 | 5 |
| | በፐርሰንት | 30% | 53.3% | 16.6% | — | 83.3% | 16.6% |
| 10 | በቁጥር | 5 | 14 | 9 | 2 | 19 | 11 |
| | በፐርሰንት | 16.6% | 46.1% | 30% | 6.6% | 63.3% | 36.6% |
| 13 | በቁጥር | 2 | 8 | 16 | 4 | 10 | 20 |
| | በፐርሰንት | 6.6% | 26.6% | 53.3% | 13.3% | 33.3% | 66.6% |
| 14 | በቁጥር | 8 | 16 | 4 | 2 | 24 | 6 |
| | በፐርሰንት | 26.6% | 53.3% | 13.3% | 6.6% | 80% | 20% |
| 18 | በቁጥር | 5 | 20 | 5 | — | 25 | 5 |
| | በፐርሰንት | 16.6% | 66.6% | 16.6% | — | 83.3% | 16.6% |
| | አማካይ | 19.2% | 49.1% | 25.5% | 5.3% | 68.6% | 31.2% |

ሰንጠረዥ13፣የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ (ለዓይነታዊ ትንተና)

በሰንጠረዥ 12 እና 13 የተገጸውን ስንመለከት ጥያቄ 6፣አጭር ልቦለድ ጥልቅ አስተሳሰብን ያጎለብታል፣የሚለው ጥያቄ በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ምላሽ መስረት በጣም እስማማለሁና ዕስማማለሁ በማለት የመለሱ ተጠኝዎች 83.3%

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | የተማሪዎች ምላሽ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ | አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም |
| 6 | በቁጥር | 12 | 15 | 3 | — | 27 | 3 |
| | በፐርሰንት | 40% | 50% | 10% | — | 90% | 10% |
| 10 | በቁጥር | 2 | 15 | 9 | 4 | 17 | 13 |
| | በፐርሰንት | 6.6% | 50% | 30% | 13.3% | 56.6% | 43.3% |
| 13 | በቁጥር | 1 | 10 | 11 | 8 | 11 | 19 |
| | በፐርሰንት | 3.3% | 33.3% | 36.6% | 26.6% | 36.6% | 63.3% |
| 14 | በቁጥር | 1 | 20 | 6 | 3 | 21 | 9 |
| | በፐርሰንት | 3.3% | 66.6% | 20% | 10% | 70% | 30% |
| 18 | በቁጥር | 5 | 22 | 2 | 1 | 27 | 3 |
| | በፐርሰንት | 16.6% | 73.3% | 6.6% | 3.3% | 90% | 10% |
| | አማካይ | 13.5% | 54.6% | 20.8% | 7.71% | 68.6% | 31.3% |

(ፐርሰንት) ሲሆኑ አልስማማም እና ጭራሽ አልማማም የሚል መልስ የሰጡት ደግሞ 16.6% (ፐርንት) ናቸው። ጥያቄ6 ን በሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የተሰጠውን ምላሽ ስንመለከት፣ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት አዎንታዊ መልሽ የሰጡት 90% (ፐርሰነት) ሲሆኑ፣ አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም በማለት የመለሱ ተጠኝዎች ደግሞ 16.6% (ፐርሰንት) ናቸው።

ከዚህ መረጃ የምንረዳው አጭር ልቦለድ ማንበብ ለተማሪዎች ጥልቅ አስተሳሰብንና የመገንዘብ አቅምን እንደሚያጎለብትላቸው ነው፡፡ በዚህም ላይ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ግንዛቤው እንዳላቸው ያሳያል፡፡ ነገር ግን ጥቂት ተማሪዎች አጭር ልቦለድ ጥልቅ አስተሳሰብን እንደሚያዳብር በውል እንዳልተረዱ ያመላክታል፡፡

በሰንጠረዥ12 እና 13 እንደተገለጸው ጥያቄ10፣ አጭር ልቦለድ ማንበብ ተማሪዎች የራሳቸውን አመለካከት እንዲገልጹ እና እንዲያንጸባርቁ ያስችላቸዋል፤ለሚለው የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ምላሽ እንደሚያሳየው በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት አዎንታዊ ምላሽ የሰጡት በፐርሰንት 63.3% ሲሆኑ፣አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም በማለት አሉታዊ መልስ የሰጡት ደግሞ 36.6% ናቸው፡፤ለዚህ ጥያቄ ሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ምላሽ ደግሞ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት መልስ የሰጡ ተጠኝዎች በፐርሰንት 56.6% ሲሆኑ፣አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም በማለት አዎንታዊ መልስ የሰጡ ተጠኝዎች 43.3% ናቸው፡፡

ከሰፈረው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው አጭር ልቦለድ ተማሪዎች የራሳቸውን አመለካከት እንዲገልጹ፣እንዲያንጸባርቁ ያስችላቸዋል፣ የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ ከግማሽ የተወሰነ መጠን ብቻ የሚበልጡ ተጠኝ ተማሪዎች የተረዱት ይመስላሉ፡፡ ሆኖም ግን
መረጃው እንደሚያመለክተው ወደ ግማሽ የሚጠጉ ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ መልስ የሰጡ ናቸው፡፡ ይህም ማለት ጽንሰ ሃሳቡን በውል አለመረዳታቸውን ያሳያል፡፡ በሰንጠረዥ12 እና 13 እንደተገለጸው ጥያቄ13፣ አጭር ልቦለድ ማንበብ የፈጠራ ችሎታን ያዳብራል ለሚለው፣የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ምላሽ፣ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ ብለው የመለሱ ተጠኝዎች ብዛት 33.3% ሲሆኑ፣አሉታዊ መልስ የሰጡት ደግሞ 66.6% ናቸው፡፡ ለዚሁ ጥያቄ የሙከራ ቡድኑ በቅድመ-ልምምድ ጊዜ የሰጡት ምላሽ 36.6% (ፐርሰንት) ሲሆኑ፣ አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም በማለት የመለሱ ደግሞ 63.3% (ፐርሰንት) ናቸው፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው በቁጥጥሩም ሆነ በሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ወቅት ተጠኝዎች ልቦለድ ማንበብ የፈጠራ ችሎታን ያዳብራል፣ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ ዝቅተኛ ግንዛቤ እንደነበራቸው እንደሚያመላክት ነው፡፡
በሰንጠረዥ 12 እና 13 እንደሰፈረው ጥያቄ14፣አጭር ልቦለድ ማንበብ መገመትና የመተንበይ አቅምን ይጨምራል፣ለሚለው የቁጥጥር ቡድኑ፣በቅድመ-ልምምድ ጊዜ

በጣም እማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የመለሱ ተጠኝዎች 80% (ፐርሰንት)ሲሆኑ፣አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም በማለት አሉታዊ መልስ የሰጡ ደግሞ 20% (ፐርሰንት) ናቸው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው በሁለቱም ቡድኖች በቅድመ-ልምምድ ጊዜ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አጭር ልቦለድ ማንበብ የመገመትና የመተንበይ አቅምን እንደሚጨምር ያሳያል። ነገር ግን ውስን ተማሪዎች ጽንሰ ሃሳቡንና አተገባበሩን እንዳልተገነዘቡት መረጃው ያሳያል። እዚህ ላይ አጭር ልቦለድ ማንበብ የተማሪዎችን የመገመት፣የመተንበይ አቅምን ይጨምራል የሚለው ፅንሰ ሃሳብ አንብቦ በመረዳት ሂደት ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር (Top to bottom) የሚለውን አካሄድ ያገናዘበ ነው ማለት ይቻላል።

ከሰኝጠረዥ12 እና 13 መረዳት እንደሚቻለው ጥያቄ18፣ አጭር ልቦለድ የማሰብና የመመራመር ተነሳሽነት እንዲኀለብት ያስችላል፤ ለሚለው የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ-ልምምድ ጊዜ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የመለሱ ተጠኝዎች በፐርሰንት 83.3% ሲሆኑ፣አሉታዊ መልስ የሰጡት ደግሞ 16.6% (ፐርሰንት) ናቸው። እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ምላሽ፣በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት አዎንታዊ መልስ የሰጡ ተጠኝዎች 90% ናቸው። አሉታዊ መልስ የሰጡ ደግሞ 10% (ፐርሰንት) ናቸው። ከዚህ ማስተዋል የሚቻለው ተጠኝዎች በቅድመ-ልምምድ ጊዜ አጭር ልቦለድ የማሰብና የመመራመር ተነሳሽነት መኀልበት እንደሚችል የተሻለ ግንዛቤ እንደነበራቸው ነው።

ሰንጠረዥ 14 የቁጥጥር ቡድኑ ድህረልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምልሽ

(ለዓይነታዊ ትንተና)

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | የተማሪዎች ምላሽ | | | | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም | በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ | አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም |
| 6 | በቁጥር | 11 | 11 | 7 | 1 | 22 | 8 |
| | በፐርሰንት | 36.6% | 36.6% | 23.3% | 3.3% | 73.3% | 26.6% |
| 10 | በቁጥር | 2 | 16 | 12 | — | 18 | 12 |
| | በፐርሰንት | 6.6% | 53.3% | 40% | — | 60% | 40% |
| 13 | በቁጥር | 5 | 7 | 11 | 7 | 12 | 19 |
| | በፐርሰንት | 16.6% | 23.3% | 36.6% | 23.3% | 40% | 63.3% |
| 14 | በቁጥር | 3 | 19 | 6 | 2 | 22 | 8 |
| | በፐርሰንት | 10% | 63.3% | 20% | 6.6% | 73.3% | 26.6% |
| 18 | በቁጥር | 6 | 20 | 4 | — | 26 | 4 |
| | በፐርሰንት | 20% | 66.6% | 13.3% | — | 86.6% | 13.3% |
| | አማካይ | 17.9% | 48.6% | 26.6% | 6.6% | 66.6% | 33.9% |

ሰንጠረዥ15፣ የሙከራ ቡድኑ ድህረልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምልሽ
(ለዓይነታዊ ትንተና)

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | የተማሪዎች ምላሽ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ | አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም |
| 6 | በቁጥር | 8 | 21 | 1 | — | 29 | 1 |
| | በፐርሰንት | 26.6% | 70% | 3.3% | — | 96.6% | 3.3% |
| 10 | በቁጥር | 13 | 14 | 3 | — | 27 | 3 |
| | በፐርሰንት | 43.3% | 46.6% | 10% | — | 90% | 10% |
| 13 | በቁጥር | 5 | 12 | 10 | 3 | 17 | 13 |
| | በፐርሰንት | 16.6% | 40% | 33.3% | 10% | 56.6% | 43.3% |
| 14 | በቁጥር | 9 | 17 | 2 | 2 | 26 | 4 |
| | በፐርሰንት | 30% | 56.6% | 6.6% | 6.6% | 86.6% | 13.3% |
| 18 | በቁጥር | 12 | 16 | 2 | — | 28 | 2 |
| | በፐርሰንት | 40% | 53.3% | 6.6% | — | 93.3% | 6.6% |
| | አማካይ | 31.1% | 53.3% | 11.5% | 3.3% | 84.6% | 15. |

በሰንጠረዝ14 እና 15 የተገለጸውን መረጃ መሰርት በማድረግ በቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ ውጤትና በሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ ውጤት እንዲሁም በቅድመ-ልምምድ፣ጊዜ ከተሰጡ ምላሾች ጋር ለማነፃፀር ተሞክሩዋል፡፡

በዚህም መሰረት በጥያቄ6፣ የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የመለሱ ተጠኝዎች 96.6% ነው፡፡ ይህም ከቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ ምላሽ በ23.3 ፐርሰንት ልቆ ይታያል፡፡ በጥያቄ10፣ ላይ እንዲሁ የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የመለሱ ተጠኝዎች

ብዛት 90% (ፐርሰንት) ሲሆን ከቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ ምላሽ በ30% (ፐርሰንት) በልጦ ይታያል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በጥያቄ 13 የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ ምላሽ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የመለሱ ተጠኝዎች 56.6% ሲሆን፣ከቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ ውጤት በ16.6% (ፐርሰንት) በልጦ ታይቱዋል፡፡ እንዲሁም በጥያቄ 14 የሙከራ ቡድኑ በድህረ-ልምምድ፣በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት መልስ የሰጡ ተጠኝዎች ብዛት 86.6% ሲሆን ከቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ምላሽ በ13.3% ልቆ ተይቷል፡፡

በጥያቄ18፣ላይ የተመዘገበውን ውጤት ስንመለከትም የሙከራ ቡድኑ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የመለሱ ተጠኝዎች 93.3% (ፐርሰንቱ) ናቸው፡፡ ይህ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ ምላሽ በ6.7% (ፐርሰንት) ብልጫ አሳይቱዋል፡፡

እነዚህ በአንድ የተዛምዶ ክፍል ውስጥ የተቀመጡ ጥያቄዎች ማለትም ጥያቄ6፣አጭር ልቦለድ ጥልቅ አስተሳሰብን ከማጎልበት፣ጥያቄ10 አጭር ልቦለድ ተማሪዎች የራሳቸውን አመለካከት ከመግለጽና ማንጸባረቅ፣ ጥያቄ13 አጭር ልቦለድ የፈጠራ ችሎታን ከማዳበር፣ጥያቄ14 አጭር ልቦለድ መገመትና የመተንበይ አቅምን ከመጨመር፣ጥያቄ18 የማሰብና የመመርመር ተነሳሽነት እንዲጎለብት ከማስቻል አንጻር የተቃኙ ስለሆኑ ተቀራራቢ ጽንሰ ሃሳቦች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ከሰንጠረዦቹ መረዳት እንደሚቻለው በዚህ ክፍል ውስጥ በቀረቡት ጥያቄዎች የተሰጡ አዎንታዊ መላሾች በሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ ጊዜ ከቁጥጥር ቡድኑ ድህረ- ልምምድ ምላሽ ብልጫ ውጤት እንደተመዘገበ ያሳያል፡፡ ይህም ለውጥ ሊመጣ የቻለው በነበረው የመማር ማስተማር አደረጃጀት ተማሪዎች በቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች መሳተፋቸው፣ መልመጃዎችን ሲሰሩ በግልጽ የተቀመጡ ምላሾችንና ተመራምረው የሚያገኙዋቸው ነጥቦች መካተታቸው ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህም አእምሮአቸው በጥልቀት እንዲያስብና የበለጠ ተነሳሽነትን የሚያመጣ ሆኖ በመገኘቱ ልምምዱ ጉልህ ድርሻ እንደነበረው የሚያመላክት ነው ማለት ይቻላል፡፡

በምድብ አራት ውስጥ የተዛመዱት የመጠይቁ ጥያቄዎች (አረፍተ ነገሮች)

ተራ ቁጥር 7. አጭር ልቦለድ የቃላት ግባት መፍጠሪያ ምንጭ ነው፡፡

ተራ ቁጥር19 . አጭር ልቦለድ አንብቦ መረዳት ችሎታን ያዳብራል፡፡

ተራ ቁጥር 20. አጭር ልቦለድ ዘላቂ የአንባቢነት የሕይወት ልምድ እንዲኖረን ያስችላል፡፡

የሰንጠረዥ16፣ የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመል-ምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምልሽ
(ለዓይነታዊ ትንተና)

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | የተማሪዎች ምላሽ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ | አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም |
| 7 | በቁጥር | — | 16 | 10 | 4 | 16 | 14 |
| | በፐርሰንት | — | 53.3% | 33.3% | 13.3 % | 53.3% | 46.6% |
| 19 | በቁጥር | 13 | 16 | 1 | — | 29 | 1 |
| | በፐርሰንት | 43.3% | 53.3% | 3.3% | — | 96.6% | 3.3% |
| 20 | በቁጥር | 9 | 19 | 2 | — | 28 | 2 |
| | በፐርሰንት | 30% | 63.3% | 6.6% | — | 93.3% | 6.6% |
| | አማካይ | 24.7% | 56.6% | 14.4% | 4.4% | 81% | 8.8% |

የሰንጠረዥ17፣ የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምልሽ

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | የተማሪዎች ምላሽ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ | አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም |
| 7 | በቁጥር | 2 | 16 | 12 | — | 18 | 12 |
| | በፐርሰንት | 6.6% | 53.3% | 40% | — | 60% | 40% |
| 19 | በቁጥር | 11 | 19 | — | — | 30 | — |
| | በፐርሰንት | 36.6% | 63.3% | — | — | 100% | — |
| 20 | በቁጥር | 7 | 18 | 5 | — | 25 | 5 |
| | በፐርሰንት | 23.3% | 60% | 16.6% | — | 83.3% | 16.6% |
| | አማካይ | 22.1% | 58.8% | 18.1% | — | 81.1% | 18.8% |

በሰንጠረዥ16 እና 17 እንደተመለከተው ጥያቄ7፣ አጭር ልቦለድ የቃላት ግባት መፍጠሪያ ምንጭ ነው ለሚለው፣በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ፣ሂደት በጣም እስማማለሁ በማለት መልስ የሰጡ 53.3% ፐርሰንቱ ናቸው፡፡ ከዚህ ጥያቄ ላይ በጣም እስማማለሁ የሚል ምላሽ የሰጠ የለም፡፡ ነገር ግን አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም በማለት መልስ የሰጡ ተጠኝዎች 46.6% ፐርሰንት ናቸው፡፡ በዚሁ ጥያቄ ላይ በቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ መጠይቅ ምላሽ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ ብለው የመለሱ ተጠኝዎች ብዛት በፐርሰንቱ 56.6% ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አልስማማም እና ጭራሽአልስማማም በማለት መልስ የሰጡ 43.3% የሆኑት ናቸው፡፡

ከተጠኝዎቹ ምላሽ መረዳት የሚቻለው፣እስከ ግማሽ የሚደርሱ ተጠኝዎች አጭር ልቦለድ የቃላት ግባት መፍጠሪያ እንደሆነ ገንዛቤው አላቸው ማለት ይቻላል፡፡ በጥያቄ19፣ የተቀመጠው አሃዝ እንደሚያሳየው ወደ ግማሽ የሚጠጋ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች አጭር ልቦለድ የተለዩ ቃላት የሚታወቅበት ግባዓት መፍጠሪያ ስለመሆኑ የተገነዘቡት ነገር የለም ማለት ይቻላል፡፡ ወይም ደግሞ አጭር ልቦለድ የማንበብ ልምድ የሌላቸው ሊሆኑ ስለሚችሉ አችር ልቦለድ የቃላት ግባት በመፍጠር ረገድ ያለውን ሚና አልተገነዘቡም ማለት ይቻላል፡፡

ጥያቄ19፣ የሚያወሳው አጭር ልቦለድ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ያዳብራል የሚል ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ምላሽ መሰረት፣በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የመለሱ ተጠኝዎች ብዛት በፐርሰንት 96.6% ሲሆኑ፣አልስማማም በማለት የመለሱ ደግሞ 3.3% (ፐርሰንት) ናቸው፡፡ በዚሁ ጥያቄ የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ ምላሽ፣ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ ብለው የመለሱ ተጠኝዎች 90% ፐርሰንቱ ሲሆኑ፣ አልስማማም በማለት መልስ የሰጡ ተጠኝዎች ብዛት 10% ፐርሰንቱ ብቻ ናቸው፡፡ ከቀረበው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው፣አጭር ልቦድ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንደሚያዳብር አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ግንዛቤው እንዳላቸው ያመላክታል፡፡

ጥያቄ20ን ስንመለከት ደግሞ፣መሰረት ያደረገው አጭር ልቦለድ ማንበብ ወደ ዘላቂ አንባቢነት የሕይወት ልምድ ያሸጋግራል ወይም እንዲኖር ያስችላል፤የሚል ነው፡፡ በዚህም መሰረት በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ጊዜ ለዚሁ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ፣በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት መልስ የሰጡ ተጠኝዎች 93.3%

ፐርሰንቱ ናቸው። እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ ላይ የሰጠው ምላሽ አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም በማለት የመለሱት ደግሞ 16.6% የሆኑት ናቸው። የተጠቀሰው መረጃ እንደሚያመለክተው አብዛኛዎቹ ተመኝዎች አጭር ልቦለድ ማንበብ ዘላቂ የአንባቢነት ልምድ እንዲኖረን የሚያስችለን መሆኑን የተገነዘቡ ናቸው ማለት ይቻላል፡፤ ነገር ግን ጥቂት ተማሪዎች ጽንሰ ሃሳቡን በግልጽ የተረዱት አይመስልም። በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች አስቀድሞ አጭር ልቦለድ የማንበብ ልምድ የሌላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ከሆነ ደግሞ አጭር ልቦለድ የዘላቂ የሕይወት አንባቢነት ሊያመጣ ይችላል የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ በውል ላይረዱት ይችላሉ።

ሰንጠረዥ18፣ የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምልሽ
(ለዓይነታዊ ትንተና)

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | የተማሪዎች ምላሽ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ | አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም |
| 7 | በቁጥር | 3 | 14 | 10 | 3 | 17 | 13 |
| | በፐርሰንት | 10% | 46.6% | 33.3% | 10% | 56.6% | 43.3% |
| 19 | በቁጥር | 11 | 16 | 3 | — | 27 | 3 |
| | በፐርሰንት | 36.6% | 53፣3% | 10% | — | 90% | 10% |
| 20 | በቁጥር | 6 | 19 | 5 | — | 25 | 5 |
| | በፐርሰንት | 20% | 63.3% | 16.6% | — | 83.3% | 16.6% |
| | አማካይ | 22.2% | 54.4% | 19.9% | 3.3% | 76.6% | 23.3% |

የሰንጠረዥ19፣ የሙከራ ቡድኑ ድህረልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምልሽ (ለዓይነታዊ ትንተና)

| የጥያቄ ተራ ቁጥር | የተማሪዎች ምላሽ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ጭራሽ አልስማማም | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ | አልስማማም እና ጭራሽ አልስማማም |
| 7 | በቁጥር | 5 | 17 | 6 | 2 | 22 | 2 |
| | በፐርሰንት | 16.6% | 56.6% | 20% | 6.6% | 73.3% | 6.6% |
| 19 | በቁጥር | 19 | 10 | 1 | — | 29 | 1 |
| | በፐርሰንት | 63.3% | 33.3% | 3.3% | — | 96.6% | 3.3% |
| 20 | በቁጥር | 14 | 16 | — | — | 30 | — |
| | በፐርሰንት | 46.6% | 53.3% | — | — | 100% | — |
| | አማካይ | 42.1% | 47.7% | 7.7% | 2.2% | 89.9% | 3.3% |

በሰንጠረዥ18 እና 19 እንደተመለከተው በጥያቄ7፣አጭር ለቦለድ የቃላት ግባት መፍጠሪያ ምንጭ ነው፣ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ በሙከራ በድኑ ድህረ-ልምምድ ሂድት በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት መልስ የሰጡ ተጠኝዎች 73.3% ናቸው፡፡ ለዚሁ ጥያቄ በሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምድ፣በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት መልስ የሰጡ ተጠኝዎች 60% ፐርሰንት ናቸው፡፡ ከዚህ እንደሚስተዋለው የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ ምላሽ በ13.3% በልጦ ይታያል፡፡ ይህ የሙከራ ቡድኑ የድህረ-ልምምድ ውጤት በሰንጠረዥ19፣ ከተገለጸው የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ አዎንታዊ ምላሽ ድምር ከሆነው 53.3% ፐርሰንት በ20%፣እንዲሁም ከቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ አዎንታዊ ምላሽ ከሆነው 56.6% ፐርሰንት በ16.7% ልቆ ይታያል፡፡

ከዚህ በመነሳት የሙከራ ቡድኑ ተጠኝዎች በነበረው በአጭር ልቦለድ የመማር ልምምድ፣ከንባብ በፊትና ከንባብ በኋላ በተከታታይነት በተደራጁ መልመጃዎች አማካይነት የተለያዩ ተጋባራትን መስራታቸው፣ አጭር ለቦለዶች ከቃላት ግባት አንጻር ያላቸውን ሚና ተጠኝዎች ተረድተዋል ማለት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ከአጭር ልቦለድ

ምንባቦች ውስጥ የተመረጡ ቃላት በማውጣት አውዳዊ ፍቺ ተማሪዎች እንዲሰጡ በማድረግ መለማመዳቸው፣ አጫጭር ልቦለዶች ለቃላት ግባት መፍጠሪያነት ማገልገላቸውን በተግባር ማየታቸው አጫጭር ልቦለዶች የቃላት ግባት መፍጠሪያ ስለመሆናቸው ግንዛቢያቸውን አስፍቶላቸዋል ለማለት ይቻላል፡፡

በጥያቄ20፣የቀረበው ደግሞ፣አጭር ልቦለድ ማንበብ ዘላቂ የአንባቢነት የሕይወት ልምድ እንዲኖረን ያስችላል የሚል ጽንሰ-ሃሳብ የያዘ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ በሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ ጊዜ የተሰጠው ምላሽ ስንመለከት፣በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት መልስ የሰጡ ተጠኝዎች በፐርሰንት 100% ናቸው፡፡ የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ ምላሽ፣በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የመለሱ ደግሞ 83.3% ፐርሰንት ነበሩ፡፡ ስለዚህ የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ አዎንታዊ ድምር ምላሽ ከሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ አዎንታዊ ድምር ምላሽ በ16.7% (ፐርሰንት) በልጦ ታይቷል፡፡ የቁጥጥር ቡድኑ ተጠኝዎች በድህረ-ልምምድ ወቅት የሰጡት አዎንታዊ ምላሽም ድምር 83.3% ነው፡፡ በመሆኑም የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ አዎንታዊ ድምር ምላሽ ከቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ አዎንታዊ ድምር ምላሽ በተመሳሳይ ሁኔታ በ16.7% (ፐርሰንት) ልቆ ታይቱዋል፡፡

ከዚህ በመንድርድር ተጠኝ ተማሪዎች አጭር ልቦለድ ማንበብ ዘላቂ የሕይወት ልምድ አንባቢነትን ወይም የማንበብ ፍላጎትን እንደሚያመጣ አስቀድሞ በዙዎቹ ግንዛቤው የነበራቸው ቢሆንም፣በነበረው በአጭር ልቦለድ ቋንቋን የማስተማር ልምምድ ሂደት እውቀታቸው ሊጎለብት ይችላል፡፡ እንዲሁም በልምምድ ወቅት በአጭር ልቦለድ ምንባቦች ላይ ባደረጉት ምንባቦችን ደጋግሞ የማንበብና መልመጃዎችን መስራታቸው በነበራቸው እውቀት ላይ ተጽኖ ፈጥሩዋል ማለት ይቻላል፡፡

#### 4.1.2.2 ከጽሑፍ መጠይቅ በመጠናዊ መንገድ የተገኘ የጥናት ውጤት ትንተና

የጽሑፍ መጠይቁ ፓይለት ቴስት የተደረገበት ምላሽ ዝርዝር ውጤት በአባሪ ‹‹ሰ›› ይመልከቱ፡፡

ሰንጠረዥ 20 **የጽሑፍ መጠይቁ ፓይለት ቴስት የተደረገበት ምላሽ**

| ገላጭ እስታቲስቲክስ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተማሪ ዎች ብዛት | ዝቅተኛ ውጤት | ከፍተኛ ውጤት | አማካይ ዉጠየት | መደበኛ ልይይት |
| የሙከራ ቡድን | 10 | 43.00 | 62.00 | 54.4000 | 6.13188 |

ሰንጠረዠ 20 እንደሚያሳየው መጠይቁን የሞሉት በስብጥራዊና በእጣ ንሞና መሰረት በተጠኝነት ያልተካተቱ ነገር ግን በተመሳሳይ ደረጃ የሚገኙና አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች ናቸው፡፡ በዚህ መጠይቅ አንድ ተማሪ በሙሉ ጭራሽ አልስማማም የሚል ምላሽ ቢሰጥ የሚያገኘው ውጤት 20 ሲሆን፣ በጣም እስማማለሁ የሚል መልስ ቢሰጥ የሚያገኘው ውጤት 80 ነው፡፡ በዚህም የሚጠበቀው አማካይ ውጤት 20+80=100÷2=50 ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት ከሚጠበቀው በላየ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ሰንጠረዥ 21 **የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ**

| ገላጭ እስታቲስቲክስ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተማሪ ዎች ብዛት | ዝቅተኛ ውጤት | ከፍተኛ ዉጤት | አማካይ ዉጤት | መደበኛ ልይይት |
| የቁጥጥር ቡድን ቅድመልምም ድ | 30 | 42 | 64 | 55.43 | 5.894 |

ሰንጠረዥ 22 **የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ**

| ገላጭ እስታቲስቲክስ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተማሪ ዎች ብዛት | ዝቅተኛ ውጤት | ከፍተኛ ዉጤት | አማካይ ዉጤት | መደበኛ ልይይት |
| የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ | 30 | 46 | 64 | 55.03 | 4.552 |

የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ዝርዝር ውጤት በአባሪ ‹‹ሸ›› ይመልከቱ፡፡ የሙከራ ቡድኑ ቅድመልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ዝርዝር ውጤትና ድምር ደግሞ ባአባሪ ‹‹ቀ›› ይመልከቱ፡፡

በሰንጠረዥ 21 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመልምምድ የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ውጤት 55.43 ሲሆን፣ በሰንጠረዥ 22 የሙከራ ቡድኑ ቅድመልምምድ ምላሽ የተገኘው አማካይ ውጤት ደግሞ 55.03 ነው፡፡ ይህም የቁጥጥር ቡድኑም ሆነ የሙከራ ቡድኑ ከልምምድ በፊት ተመሳሳይ የአንብቦ መረደት ችሎታና ግንዛቤ እንደነበራቸውያሳያል፡፡

በሰኝጠረዥ21 እና በሰንጠረዥ22 የተመዘገቡት የመደበኛ ልይይት ውጤቶች ከአማካይ ወጤት ያላቸው ርቀት የተቀራረበ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህም ተጠኝ ተማሪዎች ያላቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተቀራራቢ እንደሆነ ያመላክታል፡፡

ሰንጠረዥ23 **የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ**

| **ገላጭ እስታቲስቲክስ** | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተማሪ ዎች ብዛት | ዝቅተኛ ውጤት | ከፍተኛ ዉጤት | አማካይ ዉጤት | መደበኛ ልይይት |
| የቁጥጥር ቡድኑ ድህረል-ምምድ | 30 | 40 | 64 | 54.73 | 5.644 |

ሰንጠረዥ 24 **የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ**

| **ገላጭ እስታቲስቲክስ** | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተማሪ ዎች ብዛት | ዝቅተኛ ውጤት | ከፍተኛ ዉጤት | አማካይ ዉጤት | መደበኛ ልይይት |
| የሙከራ ቡድኑ ድህረል-ምምድ | 30 | 44 | 75 | 58.70 | 5.541 |

የቁጥጥር ቡድኑ ድህረልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ዝርዝር ውጤትን በአባሪ ‹‹በ›› ይመልከቱ፡፡ የሙከራ ቡድኑ ድህረልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ዝርዝር ውጤት ደግሞ በአባሪ ‹‹ተ›› ይመልከቱ፡፡

በሰንጠረዥ 24 የሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ውጤት 58.70 ሲሆን፣በሰኝጠረዥ 23 የቁጥጥር ቡድኑ የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ውጤት ደግሞ 54.73 ነው፡፡ ይህም የሙከራ ቡድኑ ድህረልምምድ የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ውጤት፣ከቁጥጥር ቡድኑ የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ውጤት በ3.97 ብልጫ ያሳያል፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ ቅድመልምምድ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ውጤት 55.03 እንደሆነ ሰንጠረዥ 21 ያሳያል፡፡ ይህንን ውጤት የሙከራ ቡድኑ ድህረልምምድ የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ውጤት ጋር ሲነጻጸር የ3.67 ልዩነት ያሳያል፡፡ ከዚህም ሙከራ ቡድኑ ከድህረልምምዱ የተሻለ የአንብቦ መረዳት ችሎታና ግንዛቤ እንዳገኘ ማየት ይቻላል፡፡ በሰንጠረዥ 23 የሙከራ ቡድኑ የድህረልምምድ መደበኛ ልይይት 5.541 ነው፤ይህም

የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች የአንብቦ መረዳት ውጤት ከአማካይ ውጤቱ የተቀራረበ እንደሆነ ያሳያል፡፡

### 4.1.3 ከምልከታ የተገኘ የጥናት ውጤት ትንተና

ምልከታ1
ትምህርት-ቤት፡-ቀጠና2 መንደር2 ከ/ሁ/ደ/ት/ቤት
ቀን፡- 12/8/2008
ሰዓት፡-8፡30-10፡30
የትምህርት ርዕስ፡-ክንፋም ሕልሞች ክፍል አንድ
በዕለቱ የተገኙ ተማሪዎች ብዛት ወ 19 ሴ 11 ድ 30
ትምህርት አንድ
ክፍለ ጊዜ ፡-አንድ ተማሪዎች ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፤ለቃላት ፍች ይሰጣሉ፤የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፤ምንባቦን ያነባሉ፡፡

- ❖ መምህሩ ወደክፍል እንደገባ ሰላምታ ከሰጠ በኂላ ለአምስት ቡድኖች ለእያንዳንዳቸው የምንባቡን ሁለት ሁለት ቅጅ ከሰጠ በኂላ፣ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ጠየቀ፡፡

ለቅድመ-ንባባ ምላሽ የሰጡ

| ተ.ቁ | ተሳትፎ | ወ | ሴ | ድ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ለቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጅ ያወጡ | 9 | 7 | 16 |
| 2 | ለቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች በቂ ማብራሪያ የሰጡ | 2 | 2 | 4 |
| 3 | ለቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች ከፊል ማብራሪያ የሰጡ | 1 | 1 | 2 |

- ❖ ከዚህ በኂላ መምህሩ ተጨማሪ ማብራሪያ ሰጡ፡፡ በማስከተል ከምንባቡ የወጡ 5ቃላት ሰሌዳ ላይ ጽፈው ፍች እዲሰጡ ጠየቁ፤

1. ጨፌ፡-ልምለምሳር፣ሳር
2. ኾራፍ፡-ገመድ፣የእርሻ መሳሪያ
3. ብትህውና፡----------
4. ምዝግዝግ፡-ዱላ
5. አራት አይና፡-አራት ዓይን ያለው በማለት መልሰዋል፣

- ❖ መምህሩ ምንባቡን በድምጽ አልባ ንባብ አስነበቡ፣ ከማህል ላይ እንደደረሱ ለንባብ ጊዜ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ አደረገ፡፡

ጥያቄ1. መልስ፡-ደብዳቤ ጸሐፊው የሚኖርበት መንድር አልተመቸውም

ጥያቄ2. መልስ ፡-የሚሳካለት አይመስለኝም

መልስ፡-ይሳካለታል

ጥያቄ3. መልስ፡-የንዳድ በሽታ በመግባቱና ተማሪዎች መበታተናቸው

- ❖ መምህሩ ተማሪዎች ምንባቡን ካነባቡ በኃላ የቃላትን ፍች እንዲሰጡ አደረገ

1. ጨፌ፡-ልምለም የግጦሽ ሳር

2. ዥርፍ፦መግረፊያ፣በአገባቡ ረዥም ሳር
3. ብትህውና፦የስራ ስምሪት፣ድርሻ
4. ምዝግዝግ፦ቅዝምዝም
5. አራት አይና፦ብልህ የሚል መልስ ሰጠዋል፡፡ መምህሩ ተጨማሪ ማብራሪያ ሰጡ፦‹‹አዕምሮው ስሉ የሆነ›› የሚል ፍች ሰጡ፡፡

በምልከታ1፣ በትምህርት አንድ ስር ለማስተማሪያነት የቀረበው ምንባብ ‹‹ክንፋም ሕልሞች ክፍል አንድ›› የሚል የአጭር ልቦለድ ክፍል ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ክፍል በራሱ ሙሉ ታሪክ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ በዚህ መሰረት ተማሪዎች ለቀረቡላቸው ቅድመ-ንባብ ጥቄዎች እጅ በማውጣት ለመመለስ ፍቃደኛ የሆኑ ተማሪዎች 16 ናቸው፡፡ ይህም ከጠቅላላ ተማሪዎች በመቶኛ ሲሰላ 53.3% ያሳያል፡፡ እንዲሁም መልስ እንዲሰጡ መምህሩ የጠየቃቸው ተማሪዎች ቅድመ-ንባብ የትንበያ ጥያቄዎች አራቱም ከተሟላ ማብራሪያ ጋር መልስ ሲሰጡ፣ከከፊል ማብራሪያ ጋር መልስ የሰጡ ተማሪዎች ከተጠየቁት ውስጥ ሁለቱም ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር ተማሪዎች የትንበያ ሃሳብ ለመሰዘር ያላቸው ተሳታፊነት ከመካከለኛ በላይ እንደሆነ መረዳት ይችላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ለቃላት ፍች እንዲሰጡ ተጠይቀዋል፡፡ በአንብቦ መረዳት ሂደት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ማለትም ተማሪዎች ያላቸውን ቅድመ-እውቀት እንዲፈትሹ የሚያስችላቸው ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ለቀረቡ አምስት ቃላት ውስጥ ለሦስት ቃላት ትክክለኛ ፍቺ ሰጠዋል፡፡ ነገር ግን ለሁለት ቃላት ትክክለኛ ፍች መስጠት አልቻሉም፡፡ ይህም የሚሳየው ከተጠየቋቸው ቃላት ውስጥ 60% በመቶ መልሰዋል ማለት ይቻላል፡፡

በዚህ ምልከታ ሂደት ሌላው የተስተዋለው የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ሊለካ የሚያስችል ለንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ሃሳብ አደራጅቶ መልስ መስጠት መቻል ነው፡፡ በዚህም መሰረት መምህሩ ለእንዳንዱ የንባብ ጊዜ ጥያቄ ሁለት ሁለት ለመመለስ እጅ ያወጡ ተማሪዎች መልስ እዲሰጡ አድረገዋል፡፡ ለሦስቱም የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ሰጠዋል፡፡ ከዚህ በማያያዝ ተማሪዎች ንባባቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በመግቢያው ላይ ቀርበው ለነበሩ ቃላት ከምንባቡ አውድ አንጻር ፍች እንዲሰጡባቸው አድረጓል፡፡ በዚህም ሂደት ለአምስቱም ቃላት ትክክለኛ አውዳዊ ፍች መስጠት ችለዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ነገር፣ ለቃላት በቁማቸው ፍች ለመስጠጥ ከመሞከር ይልቅ በአውድ፣በምንባብ ውስጥ ሲመጡ በቀላሉ ለመረዳት እንደሚቻል ነው፡፡ በመሆኑም አጫጭር ልበቦለዶች በቋነቋ ትምህርት ውስጥ የቃላት ግባት መፍጠሪያ መሆናቸውን አመላካች ሊሆን ይችላል፡፡

ምልከታ2

ትምህርት-ቤት፦ቀጠና2 መንደር2 ከ/ሁ/ደ/ት/ቤት

ቀን፦ 19/8/2008

ሰዓት፦8:30-10:30

የትምህርት ርዕስ፦ክንፋም ሕልሞች ክፍል አንድ

በዕለቱ የተገኙ ተማሪዎች ብዛት ወ18 ሴ 11 ድ 29

ትምህርት አንድ

ክፍለ ጊዜ ፦ሁለት፣ተማሪዎች ምንባቡን ደግመው በጽሞና ንባብ ካነበቡ በኋላ ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት ምክንያት በመስጠት የብራራሉ፡፡ የምርጫ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡በዚህ ክፍል ስለምንባቡ መልዕክት ጥልቅ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያግዛችዋል፡፡

- መምህሩ ለ5 የ ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› ጥያቄዎች በ5 ቡድኖች ካሰሩ በኋላ መልሳቸውን ለክፍሉ እንዲያንጸባርቁ አደረጉ፡፡ በዚህ መሰረት ውጤቱ እንደሚከተለው ሰፍሩዋል፡፡

የቡድኖች የ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት››መልስ

| ቡድኖች | ስህተት መልስ | በምክንያት ያልተደገፈ ትክክለኛ መልስ | በምክንያት የተደገፈ ትክክለኛ መልስ |
|---|---|---|---|
| ቡድን 1 | 2 | 1 | 2 |
| ቡድን 2 | 1 | 1 | 3 |
| ቡድን 3 | — | 2 | 3 |
| ቡድን 4 | 2 | 2 | 1 |
| ቡድን 5 | 1 | 3 | 1 |
| ድምር | 6 =24% | 9=36% | 10=40% |

- በመቀጠል መምህሩ በምንባቡ መሰረት የሚሰሩ ስምንት የምርጫ ጥያቄዎች በቡድን እንዲሰሩ አደረገ፡፡ ከሰሩ በኋላ መልሳቸውን ተቀብሎ አረመ፣ በመጨረሻም ማብራሪያ ሰጠ፡፡ ተማሪም ማብራሪያ እንዲሰጥ ጠየቀ፡፡

የቡድኖች የምርጫ ጥያቄዎች ምላሽ

| ቡድኖች | የስህተት መልስ ብዛት | ትክክለኛ መልስ ብዛት |
|---|---|---|
| ቡድን 1 | 3 | 5 |
| ቡድን 2 | 2 | 6 |
| ቡድን 3 | 1 | 7 |
| ቡድን 4 | 2 | 6 |
| ብድን 5 | — | 8 |
| ድምር | 8=20% | 32=80% |

- የመምህሩ ማብራሪያ፦‹‹ወትሮም ቀን ሲያምጽ ተዕድሜ ቀድሞ ንሮ ያስረጃል›› ማለት የንሮ አለመመቸት፣ጉስቁልና ካለ ሰው ያለዕድሜው ያረጃል እንደማለት ነው፡፡
- የተማሪ ማብራሪያ፦ በምንባቡመስረት ‹‹አጋሰስነት›› ማለት በልቶ የማይጠግብ እንደማለት ነው፡፡

በምልከታ ሁለት ተማሪዎች ‹‹ክንፋም ሕልሞች ክፍል አንድ››የሚለውን ምንባብ ካነበቡ በኋላ ማገናዘብን የሚጠይቁ የ‹‹እውነት››ወይም‹‹ሐሰት›› በማለት የሚመለሱ ጥያቄዎችን በቡድን ሰርተዋል፡፡ በዚህም መስረት እያንዳንዱ ቡድን ምን ያህል ጥያቄዎችን በምክንያት አስደግፎ እንዳቀረበ፣ምን ያህሉን ደግሞ በምክንያት ሳያስደግፍ እንዳቀረበ፣ስንት ስህተት መልስ እንደተሰጠ ተመልክቷል፡፡ ለየቡድኖቹ የተሰጡት ጥያቄዎች እኩልና ተመሳሳይ ቢሆኑም የጥያቄዎችን ቁጥር ለቡድኑ ብዛት በማባዛትና 25 ጥያቄዎችን እድሰሩ በማሰብ በአጠቃላይ ተጠኚዎች ያገኙትን ውጤት በፐርሰንት ለማስላት ተሞክሩዋል፡፡ በዚህም መሰረት የቡድኖቹ በምክንያት የተረጋገጠ መልስ ድምር 10 በፐርሰንት 40%፣የቡድኖቹ በምክንያት ያልተደገፈ ትክክለኛ መልስ ድምር 9 በፐርሰንት 36% የቡድኖቹ ስህተት መልስ ድምር 6 በፐርሰንት 24% መሆኑ ያሳያል፡፡

ይህ አይነቱ አቀራረብ ተማሪዎች ነገሮችን በጥልቀት እዲገነዘቡ ሊረዳቸው ይችላል፡፡ ተማሪዎች መልሳቸውን በምክንያት ለማስደገፍ ምንባቡን ወደኋላ ተመልሰው እንዲመረምሩና ትኩረታቸውን ወደተፈለገው ነጥብ እንዲያነጣጥሩ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ትኩረትንንና ስሜትን ውጥሮ ለመያዝ ደግሞ የአጭር ልቦለድ ምንባቦች ተመራጭ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

በማስከተል ቡድኖቹ በቀረበው ምንባብ ስር የምርጫ ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት ሰርተዋል፡፡ መምህሩ የቡድኖችን ስራ ተመልክቶ ውጤት ከሰጠ በኋላ መልሳቸውን ለክፍሉ እንዲያንጸባርቁ እድርጓል፡፡ ውጤቱም በዚህም መሰረት ለየቡድኖቹ የቀረቡ የምረጫ ጥያቄዎች 8 ናቸው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎችን ለቡድኖቹ ቁጥር በማባዛትና 40 ጥያቄዎች እንደሰሩ በማሰብ ቡድኖቹ ያመጡትን ውጤት ለማስላት ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም ቡድኖቹ ትክክለኛ መልስ ድምር 32 በፐርሰንት 80% የቡድኖቹ ስህተት መልስ ድምር 8 በፐርሰንት 20% መሆኑን ተመልክቱዋል፡፡

በዚህ ስር የቀረቡት የምርጫ ጥያቄዎች የተማሪዎችን ጥልቅ አሰተውሎት የሚጠይቁ፣ጽንሰ ሀሳቦችን በማስተሳሰር ትርጓሜ ለመስጠት የሚያስችሉና ተማሪዎችን የሚያለማምዱ ናቸው፡፡ ከዚህ ላይ ተማሪዎች ያንጸበረቁትን ማብራሪያ ስንመለከት ‹‹ወትሮም ቀን ሲያምጽ

ተዕድሜ ቀድሞ ኑሮ ያስረጃል››የሚለውን ሲያብራሩ ሰው በኑሮ ካልተመቸው፣ እንግልት ከደረሰበት ጎስቋላ ይሆናል የሚል ፍችን ይሠጣል በማለት አብራርተዋል፡፡ በተጨማሪም‹‹አጋሰስነት›› የሚለው ቃል በአገባቡ ተመግቦ የማይጠግብ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ማጤን የሚቻለው ተማሪዎች ከገለጻው ተነስተው ተጨማሪ ትርጉምያስችላል፡፡

ምልከታ3
ትምህርት-ቤት፡-ቀጠና2 መንደር2 ከ/ሁ/ደ/ት/ቤት
ቀን፡- 20/8/2008

ሰዓት፡-8፡30-10፡30

የትምህርት ርዕስ፡-ክንፋም ሕልሞች ክፍል ሁለት

በዕለቱ የተገኙ ተማሪዎች ብዛት ወ 19 ሴ 11 ድ 30

ትምህርት ሁለት

ክፍለ ጊዜ ፡-ሁለት፣ተማሪዎች ተማሪዎች ምንባቡን በጽሞና ደግመው ካነበቡ በኋላ የምርጫ ጥያቄዎችን በቡድን ሰርተው ለመምህራቸው ያሳርማሉ፡፡ ለክፍት ጥያቄዎች መልስ ያንጸበርቃሉ፡፡

- በመቀጠል መምህሩ በምንባቡ መሰረት የሚሰሩ ስምንት የምርጫ ጥያቄዎች በቡድን እንዲሰሩ አደረገ፡፡ ከሰሩ በኋላ መልሳቸውን ተቀብሎ አረመ፣ በመጨረሻም ማብራሪያ ሰጠ፡፡ ተማሪም ማብራሪያ እንዲሰጥ ጠየቀ፡፡

የቡድኖች የምርጫ ጥያቄ መልስ

| ቡድኖች | የስህተት መልስ ብዛት | ትክክለኛ መልስ ብዛት |
|---|---|---|
| ቡድን 1 | 2 | 6 |
| ቡድን 2 | 1 | 7 |
| ቡድን 3 | 2 | 6 |
| ቡድን 4 | — | 8 |
| ብድን 5 | — | 8 |
| ድምር | 5=12.5% | 35=87.5% |

- የመምህሩ በመመሪያ ፫ ለቀረቡ ጥያቄዎች በመጀመሪያ በቡድን ከተወያዩ በኋላ በግል መልስ ሰጡ፡፡

  ጥያቄ1. መልስ 1፡-የጋዜጠኝነት ሙያ የግድ አዲስ አበባ መሄድ አያስፈልግም፣

  2፡-ባለታሪኩ ባለበት ከተማ ሆኖ ፍላጎቱን ማሟሟላት ይችላል፣

  ጥያቄ2. መልስ 1 ፡- ለመምህርነት ሙያ ዋጋ የሰጠ አይመስልም፣

  2፡-በያዘው ስራ ሲረካ አይታይም፣

ምልከታ3 መሰረት ያደረገው ‹‹ክንፋም ህልሞች ክፍል ሁለት››ምንባብ ላይ ነው። ምልከታው ያተኮረው ምርጫ ጥያቄዎች ላይ ነው። ተማሪዎች የምርጫ ጥያቄዎችን በቡድን እንዲሰሩ ከተደረጉ በኋላ የቡድኖቹ ውጤት በሰፍሯል። በሰኝጠረዡ በተገለጸው መሰርት የየቡድኖቹ ድምር ውጤት ባንድነት ሲጠቃለል፣የትክክለኛ መልስ ድምር 35 በፐርሰንት 87.5%ሲሆን፣የቡድኖቹ የስህተት መልስ ድምር 5 በፐርሰንት 12.5% ነው።

ከገለጻው መረዳት የሚቻለው ተማሪዎቹ የምርጫ ጥያቄዎችን የመስራት አቅማቸው በምልከታ2 በፐርሰንት 80% የነበረው በምልከታ3 በፐርሰንት 87.5 ደርሷል። ከዚህ አንጻር የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ መሻሻል አለ ማለት ይቻላል።

ቀጥሎ የታየው ነገር ተማሪዎች ለቀረበላቸው ክፍት ጥቄዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ተደርጓል።ይህን ሲያደርጉም የቀረበውን ምንባብ መልዕክት ጠቅለል አድርገው ከተረዱ በኋላ ስለሆነ የሚሰጡት አስተያየትም አንብቦ መረዳትን የሚያጠናክር ነው ማለት ይቻላል።

ምልከታ4

ትምህርት-ቤት፦ቀጠና2 መንደር2 ከ/ሁ/ደ/ት/ቤት

ቀን፦ 3/9/2008

ሰዓት፦8፡30-10፡30

የትምህርት ርዕስ፦ክንፋም ሕልሞች ክፍል ሦስት

በዕለቱ የተገኙ ተማሪዎች ብዛት ወ 19 ሴ 11 ድ 30

ትምህርት ሦስት

ክፍለ ጊዜ ፦ሁለት፣ተማሪዎች ተማሪዎች ምንባቡን በጽሞና ደግመው ካነበቡ በኋላ የምርጫ ጥያቄዎችን በቡድን ሰርተው ለመምህራቸው ያሳርማሉ። የማዛመድ ጥያቄ ይሰራሉ፤ለክፍት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ።

- በመቀጠል መምህሩ በምንባቡ መሰረት የሚሰሩ ስድስት የምርጫ ጥያቄዎች በቡድን እንዲሰሩ አደረገ። ከሰሩ በኋላ መልሳቸውን ተቀብሎ አረመ፣ በመጨረሻም ማብራሪያ ሰጠ። ተማሪም ማብራሪያ እንዲሰጥ ጠየቀ።

  የቡድኖች የምርጫ ጥያቄ መልስ

| ቡድኖች | የስህተት መልስ ብዛት | ትክክለኛ መልስ ብዛት |
|---|---|---|
| ቡድን 1 | 1 | 5 |
| ቡድን 2 | 2 | 4 |
| ቡድን 3 | 1 | 5 |
| ቡድን 4 | 1 | 5 |
| ብድን 5 | — | 6 |
| ድምር | 5=16.6% | 25=83.3% |

❖ መምህሩ ለእያንዳንዱ የማዛመድ ጥያቄ ተማሪዎችን በመጠየቅ ሁለት ሁለት መልስ ተቀበለ፣በሰሌዳ ላይ መልስ ጻፈ፡፡

1. አልጋ ባልጋ፦ መልስ1. የተደላደለ ኑሮ

 መልስ2. አሜሪካ መግባት

2. ጆሮየን አንቅቼ እጠብቃለሁ፦መልስ1. በጉጉት እጠብቃለሁ

 መልስ2. በሀሳብ መንጎድ

❖ መምህሩ ለክፍት ጥያቄዎች አስተያየት ተቀበሉ፤

ጥያቄ1.መልስ1. በሀገር ሰርቶ መለወጥ ይቻላል፤

 መልስ2. አሜሪካ ከሄዱ ሃብት ይገኛል፤

ጥያቄ2. መልስ1.የገንዘብ ችግር ብዙም የለባትም፤

 መልስ2. ንሮው አስቸግሯታል፤

ጥያቅ3. መልስ1. ስልምትሰራው ስራ አልተናገረችም፤

 መልስ2. በዚያው በጋዜጠኝነት ስራ ልሰማራ ትችላለች፤

❖ በመጨረሻ መምህሩ ማስተካከያ ሰጠ፡፡

በምልከታ 4 በመጀመሪያ ድረጃ የቀረበውን ምንባብ አገናዝበው የሚመልሱዋቸው የምርጫ ጥያቂዎች ናቸው፡፡ የምርጫ ጥያቄዎችን መጀመሪያ በቡድን እንዲሰሩ ከተደረገ በኂላ መልሳቸውን ለክፍል ተማሪዎ እንዲያንጸባርቁ ተደርጓል፡፡ ውጤታቸውም ተመዝግቧል፡፡ ይህም እያንዳንዱ ቡድን ተመሳሳይ የሆኑ ስድስት ስድስት ጥያቄዎች የሰሩ ቢሆንም የቡድኖችን ድምር ውጤት በፐርሰንት ለማስላት ጥረት ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ቡድኖቹ ያገኙት ትክክለኛ መልስ ድምር 25 ሲሆን በፐርሰንት 83.3% ነው፡፡ የቡድኖቹ ስህተት መልስ ድምር ደግሞ 5 በፐርሰንት 16.6% ሆኑዋል፡፡

የቡድኖቹ የምርጫ ጥያቄዎችን የመስራት ችሎታ ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የቀረቡት የምርጫ ጥያቄዎች ጥልቅ አስተሳሰብን ከማዳበር አንጻር፣ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡

ተማሪዎች በቀጣይነት የማዛመድ ጥያቄዎችን ሰርተዋል፡፡ የቀረቡት የማዛመድ ጥያቄዎች ተማሪዎች የተለያዩ አገላለጾችንና ጽንሰ ሃሳቦችን አንብበው መረዳታቸውን ማረጋገጥ የሚቻልበት ስልት ነው፡፡ ተማሪዎች ጽንሰሃሳቦችን በተመሳስሎአቸው ወይም በተዛምዶአቸው አማካይነት ዝምድና በመፍጠር የማደራጀት ተግባር የሚሰሩበት የልምምድ ክፍል ነው ማለት ይቻላል፡፡ መምህሩ ምሳሌ የሚሆኑ አገላለጾችን ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎቹ መልስ እንዲሰጡባቸው አድርጓል፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች ለክፍት ጥያቄዎች መልስ ሰጠዋል፡፡ በዚህ ተግባርም ተማሪዎቹ ውስጣዊ ስሜታቸውን በግለጽ ሰፋያሉ ገለጻዎችን እዲሰጡ ያስችላል፡፡ በዚህም የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት አቅም በዚያው ልክ እደሚጎለብት ያሳያል፡፡

ምልከታ5

ትምህርት-ቤት፦ቀጠና2 መንደር2 ከ/ሁ/ደ/ት/ቤት

ቀን፦ 10/9/2008

ሰዓት፦8፡30-10፡30

የትምህርት ርዕስ፦ክንፋም ሕልሞች ክፍል አራት

በዕለቱ የተገኙ ተማሪዎች ብዛት ወ 18 ሴ 11 ድ 29

ትምህርት ሦስት

ክፍለ ጊዜ ፦ሁለት፣ተማሪዎች ተማሪዎች ምንባቡን በጽሞና ደግመው ካነበቡ በኋላ የምርጫ ጥያቄዎችን በቡድን ሰርተው ለመምህራቸው ያሳርማሉ፡፡ የማዛመድ ጥያቄ ይሰራሉ፤ለክፍት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

❖ በመቀጠል መምህሩ በምንባቡ መሰረት የሚሰሩ ስድስት የምርጫ ጥያቄዎች በቡድን እንዲሰሩ አደረገ፡፡ ከሰሩ በኋላ መልሳቸውን ተቀብሎ አረመ፣ በመጨረሻም ማብራሪያ ሰጠ፡፡ ተማሪም ማብራሪያ እንዲሰጥ ጠየቀ፡፡

የቡድኖች የምርጫ መልስ

| ቡድኖች | የስህተት መልስ ብዛት | ትክክለኛ መልስ ብዛት |
|---|---|---|
| ቡድን 1 | 1 | 5 |
| ቡድን 2 | — | 6 |
| ቡድን 3 | 1 | 5 |
| ቡድን 4 | — | 6 |
| ብድን 5 | 1 | 5 |
| ድምር | 3=10% | 27=90% |

❖ መምህሩ ጥልቅ ግንዛቤ ለሚጠይቁ ጥያቄዎች ማብራሪያ እንዲሰጡ ጠየቀ፤

ጥያቄ1. ‹‹ከሆድ ወዲያ ማዶ ልብ እንዳለ አይዘንጋ››ሲል ምን ማለት ነው?

የተማሪ መልስ1፦በአካል ውስጥ ሆድ እቃና ለብ ትይይዩ ናቸው፤

የተማሪ መልስ2፦ሆድን በምግብ መሙላት ብቻውን የመንፈስ እርካታ አይሆንም

❖ መምህሩ ለእያንዳንዱ የማዛመድ ጥያቄ ተማሪዎችን በመጠየቅ መልስ ተቀበለ፣በሰሌዳ ላይ መልስ ጻፈ፡፡ ማብራሪያም እንዲሰጡበት አደረገ፤

ጥያቄ1. በባዕድ አደባባይ ላይ ፈሰስኩ፦መልስ1፣በውጭ ሀገር መንገዶች ተመላለስኩባቸው ማለት ነው፡፤

መልስ2. በባዕድ ሀገር በአደባባይ ላይ ወጥቼ ለጥቃት ተጋለጥሁ፤

❖ የማዛመድ ጥያቄዎች የቡድን መልስ መግለጫ በትዕዛዝ (፫)

| ቡድኖች | የስህተት መልስ ብዛት | ትክክለኛ መልስ ብዛት |
|---|---|---|
| ቡድን 1 | 1 | 5 |
| ቡድን 2 | — | 6 |

| | | |
|---|---|---|
| ቡድን 3 | — | 6 |
| ቡድን 4 | 1 | 5 |
| ብድን 5 | — | 6 |
| ድምር | 2=6.6% | 28=93.3% |

❖ መምህሩ በትዕዛዝ ፬ ለቀረቡ የጽንሰ ሃሳብ ጥያቄዎች በቡድን እንዲወያዩ ካደረገ በኋላ፣ማብራሪያ እንዲሰጡ አደረገ፤መምህሩ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ሁለት ሁለት ማብራሪያዎች በመቀበል ሰሌዳ ላይ ጻፈ፤

ጥያቄ1. መልስ1.የሚመለስ ይመስለኛል ምክንያቱም በባድ ሀገር መኖር ለመንፈስ ጭንቀት ዳርጎል፣

መልስ2. ላመለስ ይችላል እጮኛው ወደ አሜሪካ ለመሄድ ስለወሰነች፣

ጥያቄ2. መልስ1.በያዙት ነገር አለመርካት፣

መልስ2. ለውጥ አስፈላጊ መሆኑን፣

ጥያቄ3. መልስ1. ጠንክረው ከሰሩ በየትም ቦታ ቢሆን ጥሩ ንሮ መኖር ይቻላል፣

መልስ2. ሀገር ካላደገች ቢሰራም ለውጥ ላይመጣ ይችላል፤

ጥያቄ4. መልስ1. በእኛ አካባቢ ደቢ መሙላት አልተለመድም፤

መልስ2. ብዙ ሰው ውጭ ሀገር መሄድ ስለሚፈልግ፤

በምልከታ5 እንደተስተዋለው በዚህ የትምህርት ዕለት የቀረበው ምንባብ ‹‹ክንፋም ሕልሞች ክፍል አራት›› የሚል ነው፡፡ በዚህ የትምህርት ክፍል መምህሩ የምርጫ ጥያቄዎችን በቡድን እንዲሰሩ እድርጓል፡፡ በዚህም መሰረት የቡድኖች ትክክለኛ መልስ ድምር 27 በፐርሰንት 90% ሲሆን፣የቡድኖቹ ስህተት መልስ ድምር ደግሞ 3 በፐርሰንት 10% መሆኑን ተገልጿል፡፡ ተማሪዎች መልመጃዎችን በሚሰሩበት ጊዜ ምንባቡን በድጋሜ በማንበብና በመመርመር ጥልቅ አስታሰብን ያጎለብታሉ፡፡ በምርጫ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች በምንባቡ መነሻነት ጥልቅ እይታን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ የቀረበ ምሳሌን ስናይ‹‹ከሆድ ወዲያ ማዶ ልብ እንዳለ አይዘንጋ›› ለሚለው የተሰጠው ገለጻ፣ጥቂት ተማሪዎች ቀጥተኛ ፍቺ ሲሰጡ በአንጻሩ በጥልቅ የተረዱት ደግሞ‹‹በምግብ ሆድን ከመሙላት ባሻገር ዋጋ ያለው ወይም ለሰው ልጅ ሚያስፈልገው የመንፈስ ምግብ፣የሕሊና ነጻነት እንደሆነ በውል አብራርተዋል፡፡

ከዚህ በማስከተል ደግሞ ተማሪዎች ማዛመድ ጥያቄዎችን ሰርተዋል፡፡ በዚህ ተግባር ተማሪዎች ጽንሰሃሳቦችን በማቀናጀት፣በማደራጀት፣ የማዋገን፣ማዛመድ አቅማቸውን ያሳድግላቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ በምልከታ5 እንደተስተዋለው የተማሪዎቹ የአንብቦ መረዳት አቅም በነበረው የልምምድ ሂደት እየጎለበተ መምጣቱን ከተደረጉት ምልከታዎች ማጤን ይቻላል፡፡

ምልከታ6

ትምህርት-ቤት፦ቀጠና2 መንደር2 ከ/ሁ/ደ/ት/ቤት

ቀን፦ 11/9/2008

ሰዓት፦8፡30-10፡30

የትምህርት ርዕስ፦በወርቅ የተሞላ ገደል

በዕለቱ የተገኙ ተማሪዎች ብዛት ወ 19 ሴ 11 ድ 30

ትምህርት አምስት

ክፍለ ጊዜ ፦አንድ፣ተማሪዎች የቅድመ-ንባብ ጥያቄዎችን በቡድን በመወያየት መልሳቸውን ለክፍሉ ያንጸባርቃሉ ለቀረቡ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡

- መምህሩ ለቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች አወያይቶ መልስ ተቀበለ፤

    ጥያቄ1.መልስ1. የሌላን ንብረት መስረቅ

    መልስ2. አድልኦ መፈጸም፤

    ጥያቄ2.መልስ1. ታማኝ መሆን፣

    መልስ2. አለመዋሸት፣

    ጥያቄ3. መልስ1. ጠንክሮ በመስራት፣

    መልስ2. ድርጅት ምንድን ነው?

- መምህሩ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ፊቾ እንዲሰጡ፣ጠየቀ፡፡ የሚሰጡትን መልስ በሰሌዳላይ ጻፈ፡፡ ለአንድ ጥያቄ ለሁለት ተማሪዎች እንዲሞክሩ አደረገ፡፡

    ጥያቄ1. ወጠጤ፦ሙክት፣ፍየል

    ጥያቄ2. መናጥ፦መወዝወዝ፣መፍራት

    ጥያቄ3. ቀትረ ቀላል፦ክብደት የሌለው፣ያልተረጋጋ

    ጥያቄ4. ጓዳ፦ስውር ቦታ፣የዕቃ ቤት

    ጥያቄ5. ሞዠቀ፦ፈተገ፣አጠበ

- በማስከተል መምህሩ ምንባቡን ተማሪዎች እንዲያነቡ አደረገ፣ ንባባቸውን ገተው የንባብ-ጊዜ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ አደረገ፡፡

ጥያቄ1. መልስ1፦ባሻዘለቀ የተባለ ሰው ከመስሪያቤት ዕቃ ሰርቆ መያዙን፣

    መልስ2፦ሰውየው በመያዙ መናደዱን፣

ጥያቄ2. መልስ1፦እውነታውን የሚናገሩ ይመስለኛል፣

    መልስ2፦አውነቱን ሊደብቁ ይችላሉ፣እዋረዳለሁ ስለሚሉ፣

ምልከታ6 ላይ እንደተስተዋለው በምንባብነት የቀረበው ‹‹በወርቅ የተሞላ ገደል›› የሚል ነው፡፡ የአጭር ልቦለዱ ርዕስ በራሱ ተማሪዎችን ለንባብ የሚገፋፋና የሚያነሳሳ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ወርቅ አለ ነገር ግን በገደል ውስጥ ነው የሚል ስሜትን ሊፈጥር ይችላል፡፡ ተጠኝዎች ወደ ምንባቡ ከመግባታቸው በፊት የሰዎችን አካባቢያዊ እና ማህበራዊ እውቂያን ሊያስሱ የሚችሉ የቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች ማብራሪያ ሰጠዋል፡፡

በመቀጠልም ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ፍቺ ለመስጠት ቅድመ-እውቀታቸውን ፈትሸዋል፡፡ ይህም የንባብ ሂደትን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር (up to bottom) የሚለውን ስልት ለማዳበር ያስችላቸዋል ብሎ ማሰብ ይቻላል፡፡ በዚህ ሂደት ካለፉ በኋላ ምንባቡን በማንበብ መካከል ላይ እንደደረሱ ንባባቸውን ገታ አድርገው እስከደረሱበት ያለውን ጠቅለል ያለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለሚያስችሉ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጠዋል፡፡ በሂደቱ በተለያየ ፍቺ በያዙ ቃላት፣ለየት ያሉ አገላለጾች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ በማስቻል አንብቦ የመረዳት አቅማቸውን ሊያጎለብትላቸው ይችላል፡፡

### 4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

በጥናቱ ላይ በታየው የውጤት ትንተና መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ የተፈተሸው የቁጥጥር ቡድንና የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ንጽጽር ነው፡፡ በቅድመ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና  በተገኘው ውጤት ሁለቱ ቡድኖች ከልምምድ በፊት የጎላ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት እንደሌላቸው የስታቲስክስ ስሌት አረጋግጧል፡፡

ሁለቱም ቡድኖች ያላቸውን ተመሳሳይ የሆነ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መነሻ በማድረግ፣የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው መንገድ እንዲማር ተደርጓል፡፡ የሙከራ ቡድኑ ደግሞ በአጥኚው አማካይነት በተዘጋጀ፣ አጭር ልቦለድን ለቋንቋ ማስተማሪያነት በመጠቀም ቋንቋን እንዲማር ተደርጓል፡፡ ሁለቱም ቡድኖች በዚህ ሁኔታ ሲማሩ ከቆዩ በኋላ ለሁለቱም ቡድኖች ድህረ-ልምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ተሰጦዋቸዋል፡፡ በዚህም የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የላቀ ውጤት እዳስመዘገበ የእስታቲስቲክስ መረጃው ያሳያል፡፡ ልዩነቱም ጉልህ እንደሆነ /$p<0.05$/ የእስታቲስቲክስ ስሌት አሳይቱዋል፡፡ ይህ ልዩነት የተፈጠረው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎችን ለንባብ በሚያነሳሱ አጫጭር ልቦለዶች የአንብቦ መረዳት ችሎታን ሊያጎለብቱ በሚችሉ የተለያዩ የመልመጃ አቀራረቦች መማራቸው ሊሆን ይችላል፡፡ የሙከራ ቡድኑ በአጭር ልቦለድ ምንባቦች አማካይነት በቅድመ-ንባብ፣በንባብ ጊዜና በድህረ-ንባብ ተቀናጅተው በቀረቡ ጥያቄዎች እና መልመጃዎች አማካኝነት ተማሪዎች በቀጥታ ከምንባቦች ተገንዝበው በሚሰሩዋቸው እና በቀጥታ ያልተገለጹትንም በአመስጥሮ

በመመርመር መልስ የመፈለግ ተግባር መስራታቸውና መለማመዳቸው አንብቦ መረዳት ችሎታቸውን አዳብሮላቸው ሊሆን ይችላል፡፡

እያንዳንዱ ቡድን በተናጠል የድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ውጤት፣ከቅድመ-ልምምድ ውጤት ሲነፃፀር ልዩነት አሳይቶ እንደሆነና እንዳልሆነ በትንታኔው ተፈትሿል፡፡ በመሆኑም የሙከራ ቡድኑ በድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ፈተናው ከቅድመ-ልምምዱ የበለጠና የጎላ /p<0.05/ ውጤት አሳይቱዋል፡፡ በአንጻሩ ግን የቁጥጥር ቡድኑ ውጤት ጉልህ ልዩነት /p>0.05/ አለማሳየታቸውን ትንተናው አመላክቷል፡፡ ስለዚህም ከልምምድ በኋላ በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራ ቡድኑ መካከል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት አይታይም የሚለው የጥናቱ አልቦ መላምት /Ho/ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በምትኩ ከልምምዱ በኋላ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የጎላ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት አለ፡፡ የሚለው ተለዋዋጭ መላምቱ /Hi/ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ይህም አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ማስተማሪያነት መማራቸው፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው እና ስለ አንብቦ መረዳት ያላቸው ግንዛቤ ሊጎለብት ይችላል ወደሚለው ማጠቃለያ ሊያደርስ ይችላል፡፡

የሙከራ ቡድኑ ተጠኝዎች በተደረገው ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው እና ስለ አንብቦ መረዳት ያላቸው ግንዛቤ መሻሻል እንደታየባቸው በተሰጡት ፈተናዎች ለማረጋገጥ ተችሉዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተጠኝ ተማሪዎች ከልምምድ በኋላ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው መሻሻሉን ከጽሑፍ መጠይቆች የተገኘው ውጤት ያመላክታል፡፡ ተጠኝ ተማሪዎች ከልምምዱ በፊት የነበራቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅ ያለ እንደነበር መረጃዎች አሳይተዋል፡፡ ነገር ግን የሙከራ ቡድኖች በአጭር ልቦለድ ምንባቦች አማካኝነት፣ በቅድመ-ንባብ፣በንባብ ጊዜ፣ በድህረ -ንባብ ጊዜ በሚሰሩ የተለያዩ ተግባራት ባላቸው መልመጃዎች መሳተፋቸውና መለማመዳቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ለመሻሻሉ ምክንያት ሆኑዋል ማለት ይቻላል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳቦች

አስቀድሞ በተደራጁት ምዕራፎች የጥናቱ ዳራ፣ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ንድፈ-ሃሳባዊ ቅኝቶችና ተዛማጅ ጥናቶች፣ የአጠናን ዘዴው፣ የጥናት ውጤት ትንተናና ማብራሪያ በዝርዝር በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የጥናቱ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳቦች በጥናቱ ውጤት ላይ የተመሰረቱ አስተያየቶች በቅደም ተከተል ለማቅረብ ተሞክሩዋል፡፡

### 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር፣ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና መፈተሽ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ጥናቱ፣ በጉዳዩ ላይ በጥናቱ ዓላማ ተመርኩዞ ንድፈ-ሃሳቦች ላይ ፍተሻ በማድረግ ምላሽ ለመስጠት ትኩረት ያደረገባቸው ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

- በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር፣ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣ አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ሚና ምን ያህል ነው?
- ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ማስተማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ፍላጎት ላይ ያለው ተጽዕኖ ምንድን ነው?
- አማርኛ ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ማስተማር ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ሂደት፣ጥልቅ አስተሳሰብን፣ ማመዛዘንንና የነገሮችን ምክንያታዊ ትስስር መረዳትን እንዲያዳብሩ ያለው ሚና ምን ያህል ነው?
- በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር፣በአንብቦ መረዳት ሂደት፣የተማሪዎችን ተራክቦና ክንዋኔ ለማበረታታት ያለው ሚና ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎችን የያዙ ናቸው፡፡

በጥናቱ ለተነሱ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ለመስጠት፣ አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተመርጠው ተተግብረዋል፡፡ የመረጃ መተንተኛ መንገዶች ተለይተው የተሰበሰቡ መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡

በዚህም መሰርት የዚህ ጥናት ተጠኝዎች በፓዊ ወረዳ በቀጠና ሁለት መንድር ሁለት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት-ቤት አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ በ2008ዓ.ም 9ኛ ክፍል በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ናቸው፡፡ የክፍሉ አመራረጥ ዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ሀገር አቀፍ ፈተና ተፈታኝ ስለሆኑ ከዝግጅትና ጊዜ መጣበብ አንጻር ሁኔታዎች የተመቻቹ ስላልነበሩ በጥናቱ አልተካተቱም፡፡ በትምህርት-ቤቱ አራት የ9ኛ ክፍሎች ወይም ሴክሽኖች

አሉ፡፡ ከትምህርት ቤቱ በተገኘ ሰነድና አጥኝው ከተማሪዎች ጋር በአካል በመገናኘት በተደጋጋሚ ባደረገው ማጣራት መሰረት በየክፍሉ ያሉ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች ተለይተው ሊታወቁ ችለዋል፡፡ በዚህም መሰረት 9ኛ‹‹A››35፣ 9ኛ‹‹B››36፣ 9ኛ‹‹C››40፣ 9ኛ‹‹D››30 በድምሩ 141 ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከየክፍሎቹ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ከሆኑ ተማሪዎች ተመጣጣኝ ቁጥር ለማካተት ሲባል ስብጥራዊና ተራ የዕጣ ንሞና አመራረጥ ተግባራዊ በማድረግ 60 ተጠኝዎች በጥናቱ ተካተዋል፡፡

ጥናቱ መጠናዊ የጥናት ስልትን የተከተለ እንደመሆኑ 60ዎቹን ተጠኝዎች የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድን ተብለው በሁለት ተከፍለዋል፡፡ ተጠኝዎችን የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድን ብሎ ለመክፈል ጥቅም ላይ የዋለው ቅድመ-ልምምድ ፈተና ነው፡፡ ቅድመ-ልምምድ ፈተናው በአጥኝው ከተዘጋጀ በኋላ በሁለት አማርኛን በኮሌጅ ደረጃ በሚያስተምሩ መምህራን ተገምግሞ በአማካሪው አስተያየት ተሰጦበት ማስተካከያዎች ተደርጎበታል፡፡

ቅድመ-ልምምድ ፈተናው ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ቅደመ-ልምምድ ፈተና 25 ጥያቄዎቸን የያዘ ሲሆን፣በውስጡ ሁለት ምንባቦችን አጣምሮ የያዘ ነው፡፡ አንደኛው ‹‹ትንሽ ቢገርማችሁ›› የሚል ካጭር ትረካ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ‹‹ደብዳቤው›› የሚል አጭር ልቦለድ ነው፡፡ ምንባቦቹ ለደረጃው በሚመጥንና ለፈተና በሚያመች መልኩ መጠነኛ ማስተካከያዎች ተደርጎባቸዋል፡፡ የመጀመሪያው ቅድመ-ልምምድ ፈተና ተጠኝ ሆነው ባልተካተቱ፣ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በሆኑ 10 ተማሪዎች የሙከራ ጥናት ተደርጎበት፣አስተማማኝነቱም በክሮባኽ አልፋ ቀመር መሰረት ሲለካ /0.580/ ሆኑዋል፡፡

ሁለተኛው የቅድመ-ልምምድ ፈተና ‹‹የልደት በዓል ጥሪ›› በሚል አጭር ልቦለድ ምንባብ መሰረት የቀረበ ሲሆን፣ 20 ጥቄዎችን የያዘ ነው፡፡ የሁለተኛው የቅድመ-ልምምድ ፈተና፣የሙከራ ፍተሽ ተደርጎበት፣በክሮንባኽ አልፋ መለኪያ መሰርት አስተማማኝነቱ /0.631/ ሆኑዋል፡፡

ቅድመ-ልምምድ ፈተናው ክፍል አንድና ሁለት በቅደም ተከተል በአራት ቀን ልዩነት ተጠኝ ተማሪዎች እንዲፈተኑት ተደርጓል፡፡ ቅድመ-ልምምድ ፈተናው ክፍል አንድ 25 ክፍል ሁለት 20 በድምር ከ45 የተያዘ ሲሆን፣ውጤቱም ለእያንዳንዱ ተጠኝ ተመዝግቧል፡፡
አስቀድሞ እንደተገለጸው የቅድመ-ልምምድ ፈተናው ውጤት፣ ተጠኝ ተማሪዎችን በተመጣጣኝ የአንብቦ መረደት ችሎታ፣የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን ብሎ ለመክፈል አገልግሉዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ተጠኝዎች በቅድመ-ልምምድ ፈተናው ባመጡት ውጤት መሰረት ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ እንዲደረደሩ ተደርጓል፡፡ በማስከተል አንድ ተማሪ ከከፍተኛ

ውጤት ሌላ ተማሪ ደግሞ የመጨረሻ ዝቅተኛ ውጤት ካለው ጋር በማጣመድ ጥንዶች እንዲመሰረቱ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ከከፍተኛው ውጤት ወደታች ከመጨረሻ ዝቅተኛ ውጤት ወደላይ በመውጣት ሁሉም ተጠኝዎች በውጤታቸው መሰረት እንዲጣመዱ ተደርጓል፡፡ በዚህም ሂደት 30 ጥንዶች ተመስርተዋል፡፡ እንደገና የጥንዶችን አቀማመጥ ቅደም ተከተል ሳይለቅ በድጋሚ አንድ ጥንድ በመጀመሪያው አረድፍ ቀጣዩ ጥንድ በቀጣዩ አረድፍ እንዲደረደሩ በማድረግ በመጀመሪያው ረድፍ 15ጥንዶች፣በሁለተኛው ረድፍ 15ጥንዶች እንዲቀመጡ ከተደረገ በኋላ ተራየዕጣ ንሞና በመጠቀም የመጀመሪያው ቡድን‹‹ሀ›› የቁጥጥር ቡድን፤ሁለተኛው ቡድን‹‹ለ›› የሙከራ ቡድን ሆኖ ተሰይሟል፡፡

የቅድመ-ልምምድ ፈተናው ውጤት የሁለቱን ቡድኖች ቅድመ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ በአቻ ደረጃ ላይ እንደነበሩ አሳይቱዋል፡፡ ይኸውም የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት 21.23 ሲሆን፣የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት 21.28 መሆኑን መረዳት ተችሉዋል፡፡ ስለሆነም የቅድመ-ልምምድ አንብቦ መረዳት ፈተናው አማካይ ውጤት እንደሚያመላክተው በሁለቱም ቡድኖች መካከል ተመጣጣኝ የሆነ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አለ ማለት ይቻላል፡፡ ከቅድመ-ልምምድ ፈተናው ውጤት አንጻር የቡድኖቹ ጉልህነት ደረጃ ($p>0.05$) እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህም በቡድኖች መካካል፣ በቡድን ደረጃ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የጎል ልዩነት የለም ማለት ይቻላል፡፡

ቡድኖቹ በቡደን ደረጃ አቻ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንዳላቸው በቅድመ-ልምምድ ፈተናው ከተረጋገጠ በኋላ፣ የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው መንገድ፣ የሙከራ ቡድኑ ደግሞ በአጥኝው ተዘጋጅቶ፣በሁለት አማርኛ ቋንቋን በኮሌጅ ደረጃ በሚያስተምሩ መምህራን ተገምግሞ፣ በአጥኝው አማካሪ አስተያየት ተሰጥቶበት በተደራጀው ቴክስት መሰረት የአንብቦ መረዳት ትምህርት በሳምንት ሁለት ቀን ረቡዕ እና ሐሙስ ከ8፡30 እስከ 9፡30 ለስድስት ሳምንት ተምረዋል፡፡

ከልምምድ በኋላ ሁለቱም ቡድኖች ድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መመዘኛ ፈተና ተፈትነዋል፡፡ ድህረ-ልምምድ ፈተናው በአጥኝው የተዘጋጀ ሲሆን፣ በአጥኝው አማካሪ እና አማርኛን በኮሌጅ ደረጃ በሚያስተምሩ መምህራን ተገምግሞ በሰጡዋቸው አስተያየቶች መሰረት ማስተካከያዎች ተደርጎበታል፡፡

ድህረ-ልምምድ ፈተናው የተዘጋጀው በሁለት የተለዩ ክፍሎች ነው፡፡ ክፍል አንድ ‹‹ክፍተት›› በሚል ርዕስ የተጻፈ አጭር ልቦለድ ምንባብ መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን፣20 ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ ድህረ-ልምምድ ፈተና ክፍል አንድ፣አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ በተጠኝነት ላልተካተቱ 10 ተማሪዎች በፓይለት ፈተና ተፈትሾ፣ በክሮንባኽ አልፋ መለኪያ መሰርት የአስተማማኝነቱ ደረጃ /0.726/ ሆኑዋል፡፡

ክፍል ሁለት የድህረ-ልምምድ ፈተና የተዘጋጀው ‹‹ጆርዳን›› በሚል ርዕስ ከተጻፈ አጭር ልቦለድ ምንባብ ነው፡፡ ምንባቡ ለደረጃው በሚመጥንና ለፈተና በሚያመች መልኩ መጠነኛ ማስተካከያዎች ተደርጎበታል፡፡ ፈተናው 25ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን፣በፓይለት ፈተና ተፈትሾ፣በክሮንባኽ አልፋ መለኪያ መሰርት የአስተማማኝነቱ ደረጃ /0.609/ ሆኑዋል፡፡

ድህረ-ልምምድ ፈተናው ክፍል አንድና ሁለት በቅደም ተከተል በአራት ቀን ልዩነት ተጠኝ ተማሪዎች እንዲፈተኑት ተደርጓል፡፡ ድህረ-ልምምድ ፈተና ክፍል አንድ 20 ክፍል ሁለት 25 በድምር ከ45 የተያዘ ሲሆን፣ውጤቱም ለእያንዳንዱ ተጠኝ ተመዝግቧል፡፡ የድህረ-ልምምዱ ድምር የፈተና ውጤት ከቅድመ-ልምምድ ፈተና ውጤት ጋር በማነጻጸር በስታቲስቲካዊ ስልቶች ተተንትኑዋል፡፡

በዚህም መሰርት የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት 21.60 ሲሆን፣ የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት ደግሞ 26.68 ሁኑዋል፡፡ ይህም የሙከራ ቡድኑ፣ከቁጥጥር ቡድኑ በ5.05 አማካይ ውጤት ብልጫ አሳይቱዋል፡፡ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው የአንብቦ መረዳት ችሎታ የልዩነት የጉልህነት ደረጃ $p<0.05$ ሆኑዋል፡፡ ይህም ልዩነት ሊመጣ የቻለው የሙከራ ቡድኑ ተጠኝዎች በአጭር ልቦለድ አማካይንት አማርኛ ቋንቋ መማራቸው እና የአንብቦ መረዳት ችሎታን ሊያጎለብቱ በሚያስችሉ መልመጃዎች መለማመዳቸው እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ በመነሳት፣ በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር፣አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ሚና ምን ያህል ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ አስገኝቱዋል መለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የሙከራ ቡድኑ ተጠኝዎች አጭር ልቦለድ ምንባቦችን መሰረት አድርገው በተዘጋጁ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ለስድስት ሳምንት ያህል በሳምንት ሁለት ቀን መለማመዳቸው የውጤት ልዩነት አምጥቱዋል ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የሙከራ ቡድኑ የድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ፈተናውን ከቁጥጥር ቡድኑ በተሻለ ሁኔታ እንደሰራ የስታቴስቲክስ መረጃው አመላክተዋል፡፡ ከዚህም፣ከአጭር ልቦልድ የተደራጁ ምንባቦች ጽንሰ-ሃሳቦችን በተለያየ አገላለጽ የሚያቀርቡ፣ሃሳብን አምቀው የሚይዙ እና የልምምዱ መልመጃዎች አደረጃጀት ተጠኝዎች

ጥያቄዎችን በምክንያት እንዲያብራሩ፣ጽንሰ-ሃሳቦችን በማመዛዘን እንዲመርጡና እንዲያቀናጁ፣ በግልጽ ያልተቀመጠን መልዕክት በመገመት እዲያገኙ የሚያበረታቱ መሆኑ፣አማርኛ ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ማስተማር፣ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ሂደት፣ጥልቅ አስተሳሰብን፣ማመዛዘንንና የነገሮችን ምክንያታዊ ትስስር መረዳትን፣ እንዲያዳብሩ ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት በውጭ ሀገር ከተጠና ከ (Yeasmin,N. ; Kalam Azad,Md.A. and Ferdoush,J. 2011) የጥናት ውጤት ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው መገንዘብ ይቻላል፡፡ የ(Yeasmin,N. ; Kalam Azad,Md.A. and Ferdoush,J. 2011) የጥናት ዓላማ ስነ-ጽሁፍ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ያለውን ውጤታማነት ማሳየት ነው፡፡ ጥናቱ፣በስነ-ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ አጫጭር ልቦለዶች ተማሪዎች የተለያዩ ውይይቶች፣ክርክሮች፣ ገለጻዎች እንዲያደርጉ የሚያነሳሱ መሆናቸውን አሳይቱዋል፡፡

ከፈተና ሌላ ይህ ጥናት የጽሑፍ መጠይቅን በመረጃ መሰበሰቢያነት ተጠቅሙዋል፡፡ አጥኝው፣ Dr. Nimer A, Abu Zahara, Dr. Mohammd A, Farrah (2016)፣ ‹‹አጭር ልቦለድን በውጭ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ መጠቀም›› በሚል ርዕስ የተጠቀሙበትን 18 ጥያቄዎችን የያዘ የጽሁፍ መጠይቅ‹፣ ዋቢ በማድረግ፣ በመተርጎምና ከነዚህ ጽንሰሀሳቦች ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው 2 ጥያቄዎች በመጨመር የጽሑፍ መጠይቁ ተዘጋጅቱዋል፡፡ በማስከተልም በሁለት አማርኛ ቋንቋን በኮሌጅ ደረጃ በሚያስተምሩ መምህራን ተገምግሞ ማስተካከያዎች ተደርገውበታል፡፡ በዚህ ሁኔታ የተዘጋጀው መጠይቅ፣ሙከራ ጥናት ተደርጎበታል፡፡ ይህም ሙከራ ቡድኑን አጭር ልቦለድን ማንበብና በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መጠቀም አንብቦ መረዳትን ለማሻሻል ያለውን ሚና በተመለከተ ያላቸውን ግንዛቤ ለመመዘን አስችሏል፡፡ በማስከተልም በሙከራ ጥናቱ ውጤት መሰረት አስተማማኝነቱ በክሮንባኽ አልፋ ተሰልቶ 0.748 ሆኑዋል፡፡

የጽሑፍ መጠይቁ በፐርሰንት ተደግፎ በቋንቋ ገለጻ የተተነተነበት ውጤት እንደሚከተለው ተጠቃሏል፡፡ በጽሑፍ መጠይቁ የተካተቱ የተለያዩ ጽንሰ-ሃሳቦችን የያዙ አረፍተ ነገሮች የተተነተኑት እንደ ተዛምዶአቸው ተቀናጅተው ነው፡፡ በዚህም መሰረት ተራ ቁጥር 1፣12 እና 15 በአንድ ላይ ተዛምደው የቀረቡ ናቸው፡፡ የተካተቱት ጽንሰ-ሃሳቦችም አጭር ልቦለድ ማህበራዊ ተግባቦትን፣የሌሎችን ስሜት መረዳትን ያጎለብታል የሚሉ ናቸው፡፡ ተጠኝዎቹ ለነዚህ ጽንሰ-ሃሳቦች የሰጡት አማካይ አዎንታዊ ምላሽ የቅድመ-ልምምድ የቁጥጥር ቡድኑ 69.9% (ፐርሰንት)፣ የሙከራ ቡድኑ 71% (ፐርሰንት) ነው፡፡ ከዚህ ውጤት እንደመንረዳው

ቡድኖቹ በቅድመ-ልምምድ ጊዜ አጭር ልቦለድ ለማህበራዊ ተግባቦት ያለው ሚና ከፍ ያለ እንደሆነ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ግንዛቤው አላቸው፡፡ በድህረ-ልምምድ ጊዜ የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ አዎንታዊ ምላሽ 72.2% ፣ የሙከራ ቡድኑ ደግሞ 76.6% (ፐርሰንት) እንድሆነ በትንታኔው ተመልክቱዋል፡፡ ስለሆነም አጭር ልቦለድ የሰዎችን ስሜት ለመረዳትና ማህበራዊ ተግባቦትን ለማዳበር እንደሚያስችል መገንዘብ ተችሏል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በተመሳስሎአቸው የተጣምሩ ተራቁጥር 3፣8 እና 9 ናቸው፡፡ እነዚህም አጭር ልቦለድ የንባብ ክሂልን ያዳብራል፣የቋንቋ መማር ሒደትን ሳቢና ማራኪ ያደርጋል፤እንዲሁም እውነተኛ አውድን ይፈጥራል የሚሉ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት በቅድመ-ልምምድ ሂደት ቁጥጥር ቡድኑ አማካይ አዎንታዊ ምላሽ 72.1% (ፐርሰንት) ሲሆን፣የሙከራ ቡድኑ ደግሞ 69.9%(ፐርሰንት) ነው፡፡ ስለሆነም ተጠኝዎች አጭር ልቦለድ ለቋንቋ ትምህርቱ እውነተኛ አውድን በመፍጠር፣ሳቢና ማራኪ ማድረግ እንደሚያስችል ግንዛቤው በመካካለኛ ደረጃም ቢሆን አላቸው ማለት ይቻላል፡፡ ከነዚህ ጽንሰ-ሃሳቦች አንጻር በድህረ-ልምምድ ጊዜ የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ አዎንታዊ ምላሽ 73.3%(ፐርሰንት) ሲሆን፣ የሙከራ ቡድኑ ደግሞ 85.5%(ፐርሰንት) መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ላይ እንደሚስተዋለው ተማሪዎች በአጭር ልቦለድ አማካይነት ቋንቋን መማራቸው አጭር ልቦለድ እውነተኛ አውድን መፍጠር የሚያስችል፤ትምህርቱንም ሳቢና ማራኪ የሚያደርግ እንደሆነ አሳውቋቸዋል፡፡ ይህም በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ላይጉልህ ድርሻ እንዳለው ያስገነዝባል፡፡

በተራ ቁጥር6፣10፣13፣14 እና 18 ቀረቡት ጽንሰ ሃሳቦች አጭር ልቦለድ ጥልቅ አስተሳሰብን፣ ያጎለብታል፤ ተማሪዎች አመለካከታቸውን እንዲያንጸባርቁ ያስችላቸዋል፤የፈጠራ ችሎታን ያዳብራል፤ የመተንበይ፣ የማሰብና መመራመር ተነሳሽነትን የሚሉ ናቸው፡፡ በጥቅሉ እነዚህ ጽንሰ-ሃሳቦች ከጥልቅ አስተሳሰብ ጋር የተያዙ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በቅድመ -ልምምድ ሂደት የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ አዎንታዊ ምላሽ 68.6% (ፐርሰንት) ሲሆን፣የሙከራ ቡድኑም በተመሳሳይ 68.6% ነው፡፡ ከዚህም ከልምምድ በፊት ተማሪዎች በቀረቡት ጽንሰ-ሃሳቦች ያላቸው ግንዛቤ ከመካከለኛ በመጠኑ ከፍያለ እንደሆነ መረዳትይቻላል፡፡ ነገር ግን ከልምምድ በኋላ የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ አዎንታዊ ምላሽ 66.6%(ፐርሰንት) ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ደግሞ 84.6% (ፐርሰንት) እንደሆነ የትንተናው ውጤት አመላክቷል፡፡ ስለሆነም በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ማስተማር ተማሪዎች ጥልቅ አስተሳሰብን እንዲያዳብሩ፣ የመመራመር አቅማቸው እንዲጎለብት አድርጓል፡፡

በአራተኛ ደረጃ ተዛምደው የቀረቡት የመጠይቁ ተራ ቁጥር 7፣19 እና 20 ናቸው፡፡ እነዚም በቅደም ተከተል አጭር ልቦለድ የቃላት ግባት መፍጠሪያ ነው፤አንብቦ መረዳት ችሎታን ያዳብራል፤ዘላቂ የአንባቢነት የሕወት ልምድን ያስገኛል የሚሉ ጽንሰ ሃሳቦችን የያዘ ነው፡፡ ስለሆነም ከነዚህ ጽንሰ ሃሳቦች አንጻር በቅድመ-ልምምድ ሂደት የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ አዎንታዊ ምላሽ 81% (ፐርሰንት) ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ደግሞ 81.1%(ፐርሰንት) ነው፡፡ ከዚህም ተማሪዎች በተጠቀሱት ጽንሰ-ሃሳቦች ዙሪያ ግንዛቤው እንደነበራቸው የትንታኔው ውጤት ያሳያል፡፡ ከልምምድ በኂላ የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ አማካይ አውንታዊ ምላሽ 76.6%(ፐርሰንት) ሲሆን የሙከራ ቡድኑ አዎንታዊ ምላሽ ደግሞ 89.9% (ፐርሰንት) ነው፡፡ ከዚህም የምንረዳው በተሰጠው ትምህርት፣ ተጠኝዎች በአጭር ልቦለድ ቋንቋን መማር ስላለው ጠቀሜታ ግንዛቢያቸው መጨመሩን ነው፡፡

በማስከተል ደግሞ የጽሑፍ መጠይቁ በጣም እስማማለሁ(4)፣እስማማለሁ(3)፣ አልስማማም(2)፣ ጭራሽ አልስማማም(1) በማለት ተጠኝዎች መልስ የሰጡበት በገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት መሰረት አማካይ ነጥብ፤መደበኛ ልይይት ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሰረት የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ልምምድ አማካይ ውጤት ምላሽ በቅደም ተከተል 55.43 እና 55.03 ነው፡፡ ይህም ቡድኖቹ በቅድመ-ልምምድ ጊዜ ተመጣጣኝ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንደነበራቸው ያሳያል፡፡ መደበኛ ልይይታቸውም በቅደም ተከተል 5.894 እና 4.53 ነው፡፡ ይህም የተጠኝዎች የአንብቦ መረዳት ግንዛቤ ከአማካይ ነጥቡ ያለውን የዝቅታና ከፍታ ርቀት ያሳያል፡፡ በማስከተል የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኑ የድህረ-ልምምድ ምላሽ አማካይ ነጥብ በቅደም ተከተል 54.73 እና 58.70 መሆኑ በትንታኔው ተገልጿል፡፡ በመሆኑም የሙከራ ቡድኑ ተጠኝዎች በአጭር ልቦለድ አማካይነት ቋንቋን መማር አጭር ልቦለድ፤ በአንብቦ መረዳት ላይ የሚያሳድረውን አዎንታዊ ተጽዕኖ የበለጠ መገንዘባቸውን ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ቋንቋን በአጭር ልቦለድ መማራቸው ጥልቅ አሳቢና ተመራማሪ የመሆን ችሎታን እንዳስገኘላቸው ተገንዝበዋል ማለት ይቻላል፡፡ የቡድኖቹ መደበኛ ልይይት ስንመለከት፣ የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ልምምድ መደበኛ ልይይት 5.644 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ልምምድ መደበኛ ልይይት 5.54 ነው፡፡ ይህም ቡድኖቹ አጭር ልቦለድ አንብቦ መረዳትን ከማሻሻል አንጻር ያላቸው የግንዛቤ ውጤት ካማካዩ ያለውን ዝቅታና ከፍታ አመልክቱዋል፡፡ በመሆኑም መደበኛ ልይይቱን መሰረት አድርገን የተጠኝዎቹ በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ስለመማር ያላቸው ግንዛቤ በመካከለኛ ደረጃ ተቀራራቢ እንደሆነ ያሳያል፡፡

አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች በአጭር ልቦለድ መሳሪያነት ማስተማር ተማሪዎች ትምህርቱን በተነሳሽነት እንዲማሩ ያደርጋል፡፡ የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታን ያሳድጋል፡፡

በምልከታ ወቅት ትኩረት የተደረገባቸው ነጥቦች፣ የሙከራ ቡድኑ በጭር ልቦለድ ቋንቋ በሚማርበት ወቅት ተማሪዎች ያላቸው ተነሳሽነትና ተሳትፎ፣ የተለያዩ መልምጃዎችን የመስራት አቅማቸው፣ ባመስጥሮ የቀረቡ ሃሳቦችን የመረዳትና ስሜትን የመግለጽ ችሎታ መሻሻሉን አላክቷል፡፡ በዚህም መሰረት ከተደረገው ገለጻ መረዳት እንደተቻለው ተማሪዎቹ በተደረገው ልምምድ ከመነሻው ጀምሮ በአንብቦ መረዳት ተግባራት ላይ ግንዛቢያቸው እምርታ አሳይቷል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

በየደረጃው የቀረቡትን የጥናቱ ውጤት ትንተና እና ማጠቃለያና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ተከታዮች መደምደሚያዎች ላይ ተደርሱዋል፡፡

- በአጭር ልቦለድ አማካይነት ቋንቋን መማርና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል አዎንተዊ ግንኙነት እንዳለ መረዳት ተችሉዋል፡፡ ስለሆነም ቋንቋን በተለመደው መንገድ ከተማሩት ይልቅ ቋንቋን በአጭር ልቦለድ አማካይነት የተማሩት የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ተሻሽሎ ታይቱዋል፡፡
- በአጭር ልቦልድ አማካይነት ቋንቋን ማስተማርና የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ተግባራትን መተግበር ስለ አንብቦ መረዳት የተሻለ ፍላጎትና ግንዛቤን ያስገኛል፡፡
- በአጭር ልቦልድ አማካይነት ቋንቋን ማስተማርና ተማሪዎችን በተደራጁ የተለያዩ ተጋባራትን ማለማመድና ማስተግበር፣ ተማሪዎች ጥልቅ የሆነ የማገናዘብ ችሎታ እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡
- ተማሪዎች በአጭር ልቦለድ መማራቸው በአንብቦ መረዳት ሂደት፣ እርስ በእርስ ያላቸው ተራክቦና ክንዋኔ እንዲጎለብት ያደርጋል፡፡

### 5.3 የመፍትሄ ሃሳቦች

ከጥናቱ ውጤትና መደምደሚያ በመነሳት አጥኚው የሚከተሉተን መፍትሄዎችንና አስተያየቶችን ሰጥቱዋል፡፡

- አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው እንዲሻሻልና እንዲጎለብት ቋንቋን በአጭር ልቦለድ አማካይነት እንዲማሩ ቢደረግ ያለው አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው፡፡
- አጭር ልቦለድ ምንባቦች ለደረጃው በሚመጥን መልኩ ተመርጠው ቢካተቱ፣እንዲሁም የሚካተቱት ምንባቦች ቀጥታ ስነ-ጽሑፍን ለማስተማር ከማገልገላቸው ባሻገር አንብቦ መረዳትን ለማስተማር(ለማጎልበት)በሚያስችሉበት ሁኔታ ቢካተቱ ይመረጣል፡፡
- የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር፣ ለማስተማሪያነት የሚመረጡ ምንባቦች ሳቢነት ያላቸውና ተነሳሽነትን የሚፈጥሩ፣ የተማሪዎችን የመተንበይ፣ምክንያት የመስጠት፣ከላአላይ ፍች በመነሳት የተመሠጠሩ ጥልቅ ሃሳቦችን የመረደት፣ትርጓሜ የመስጠትና የራሳቸውን ሃሳብ እንዲያንጸባርቁ የሚያስችሉ መሆናቸው ተኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡
- የስርዓተ-ትምህርት አዘጋጆች በደረጃው በሚዘጋጁ አማርኛ መጽሐፍት ውስጥ አጭር ልቦለድ ምንባቦች ከሌሎች ምንባቦች አንጻር ተመጣጥነውና አሁን ካሉበት በቁጥር ተሻሽለው ቢቀርበ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት አቅም ከማሳደጉም ባሻገር የንባብ ፍላጎት ሊያማነሳሳ ይችላል፡፡
- ለስርዓተ-ትምህርት ባለሙያዎች፣ለመምህራን እና በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ምርምር ለሚያካሂዱ ባለሙያዎች እንደመነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች


መሰረት ሀሰን ፡፡(2007)፡፡ በአንከሻ ወረዳ በሚገኙ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ተምህርት-ቤቶች የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ትምህርት አቀራረብ ቅኝት፡፡ባህርዳር ዩኒቨርስቲ፡፡ (የማስተርስ የመመረቂያ ጽሑፍ) ያልታተመ፡፡

በሪሃና አብዱራሃማን፡፡(2007)፡፡የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ሲያስተምሩ የሚጠቀሙባቸዉ አህዶች መምረጫ መስፈርት ፍተሸ፡፡በህርዳር ዩኒቨርስቲ፡፡ (የማስተርስ የመመረቂያ ጽሑፍ) ያልታተመ፡፡

በዕዉቀቱ ስዩም ፡፡(2004)፡፡ ክንፋም ሕልሞች፡፡ ክንፋም ሕልሞችና ሌሎች አጫጭር ልቦለድ ታሪኮች በአንጋፋና ወጣት ደራሲያን፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፡፡

በድሉ ዋቅጅራ ፡፡(1996)፡፡ **በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር**፡፡ አዲስ አበባ፣ንግማተሚያ ድርጅረት፡፡

ተስፋዬ ገብረአብ ፡፡(1991)፡፡ በወርቅ የተሞላ ገደል፡፡ እፍታ 63 ተረካዎች፣ቅጽ ሁለት፣(ገጽ29-37)፣አዲስ አበባ፣ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣

አለም እሸቱ፡፡ (1992)፡፡ **መሰረታዊ የምርምር ዘገባ አጻጻፍ፡፡** አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

አማረ አበባው፡፡(2001)፡፡ ተራክቧዊ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለዉ ተፅእኖ-ፍትነታዊ ጥናት፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ፡፡(የማስተርስ የመመረቂያ ጽሑፍ) ያልታተመ፡፡

እንዳለ ጌታከበደ ፡፡(2007)፡፡ ከጥቁር ሰማይ ስር፡፡አዲስ አበባ፣ክፍተት፣ኤች.አይ.ቪ ኢንተርናሽናል ማተሚያ ድርጅት፡፡

እንድሪስ አባይ።(2000)። የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን መማር ከአንብቦመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ዝምድና።ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ። (የማስተርስ የመመረቂያ ጽሑፍ) ያልታተመ።

ካሕሳይ ገ/እግዚአብሐር።(1995)። ህብረ-ብዕር።አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ድርጅት፣

ወርቁ ዓለሙ።(2000)። የሥነ-ጽሁፍ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት አተገባበር በሁለ ተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች።ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ።(የማስተርስ የመመረቂያ ጽሑፍ) ያልታተመ።

ወይንሸት ግርማ ።(2007)። ማህበረስሜታዊ ብልሃት የአማርኛን ቋንቋን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ላይ የአንብቦ መረዳት ችሎታን እና የንባብ ፍላጎትን በማጎልበት ረገድ ያለዉ ሚና (በጫንጮ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት-ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት)። ባህርዳር ዩኒርሲቲ።(የማስተርስ የመመረቂያ ጽሑፍ) ያልታተመ።

ዘሪሁን አስፋው ።(2007)። **የስነጽሑፍ መሰረታዊያን**። ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣አዲስ አበባ።

የሽጥላ ኮከብ ።(1991)። የልደት በዓል ጥሪ። እፍታ 63 ትረካዎች፣ቅጽ ሁለት፣ (ገጽ309-318)

ያለዉ እንዳወቀ ።(2004)።**የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር**።ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ጻርሶሞትባይኖር ክሩቤል ።(1992)። አስኮጌታሁንና ሌሎች ታሪኮች። ጆርዳን፣አዲስ አበባ።

Ahmed sallal, I.(2014). The effect of using story on Reading Comprehension and Motivation for English Departement Students. Diyla university / Iraq.

Bachman,J. “etal”.(1999). Fiction; An introduction to short stories. NTCI

Contemperery published group; Chicago.

Brumfit, C.J.(1986). Literature and Language Teaching. Oxford Univerisity Press;Oxford New York.

Collie and Slater.(1987). Literature in the language classroom.A resource book Of ideas and activities; Cambridge University press, New York.

Dornyei,Z .(2007).Research methods in applied Lingustics. Oxford University Press; Oxford New York.

Feeman, D .(2000). Techniques and principiles in language Teaching. Oxford; Oxford university press. Indian Edition.

Ghasemi,p.Rasool,H.(2011).Teaching L2 Reading comprehension through Short story.IACSTE press Singapore;IPEDR.vol.26.

Ghasemi,P.(2011). Teaching the short story to improve L2 Reading and Writing skills internatinal jornal of Arts and science;CRROM.ISSN. 1944-6934; 4(18) (265-273).shipaz university,Iran.

Gray, D.(2004). Doing Research in the Real world.SAGE publications Lon don.

Hall, G.(2005).Literature in Language Education. Palgrave macmilan; contemporary published group; Chicago

Hernandez,J.Riwes.(2010).The Role of Literature and culture in English Language Teaching.htt;//relinguistica.azc.no.007/artog.htm.

Hill, J.(1986).Reading Literature in the Language classromm. Macmilan Publishers.

Khatib,M. “etal”.(2012).Literature and Language Teaching.Journal of Acadamic and Applied Studies. vol.2(6) June 2012,pp.32-38;

Tabataba 'I university,Tehran,Iran.

Khatib,M and Nasrollahi,A. (2o12).enhancing reading comprehension Through shortstories in Iranian EFL learners. Vol.2,pp.240- 246; Acadamic publisher in Finland.

Lazar, G. (1993).Literature and Language Teaching.United kingdom;Combr Idge university press.

Nimer and Mohammed .(2016). Using short stories in the EFL classroom. JUG Journal of Humanities Research Peer-reviewed Journal of Isl Amic university Guza vo124, No1, 2016,ppp11-24.

Nuttall, C. (1982) . Teaching Reading skills in a Foreign language.Pract Ical Language; Heinemann Educational Books Ltd22 Bedford squre. London WC1B 3 HH.

Pettit and Cockriel. (1974). A factor study of literal reading Comprehension Test and the inferential Reading comprehension Test. Journal of read Ing Behavior (1974) VI, 1;ijl sesepub.com by on guest on August 28; 2016.

Pourbulhor, O. and Kohan, N. (2013). Teaching Reading Comprehenson thr Ough Short stories in advanced classes.ISSN; 2186-8492,ISSN;Vol.2 No.2 May 2013; Islamic Azad University,Tonekabon Branch,IRAN.

Souhila, R.(2013/2014). The use of Reading stratagies in improving Reading comprehension.University Kasdi; merbahouargla.

Texas Education Agency .(2002). Comprehension instruction.revised Editoin, Texas 78701-1494.

Yeasmin, N.”etal.“ (2011).Teaching Language through Literature;Desig Appro Priate classroom Activities.ASA Universtiy Revew,vol.5 No.2,July-December

## የአባሪ ማውጫ

### አባሪ ‹‹ሀ›› የቁጥጥር ቡድን ‹‹ሀ›› ቅድመ ልምምድ የፈተና ውጤት

| ተ.ቁ | ፆታ | ሴክሽን | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | 25% | 20% | 45% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ | C | ሽናሻ | 24 | 14 | 38 | |
| 2 | ሴ | D | አገው | 4.5 | 3 | 7.5 | |
| 3 | ወ | B | አገው | 21.5 | 15.5 | 37 | |
| 4 | ወ | B | ጉሙዝ | 8 | 1 | 9 | |
| 5 | ሴ | D | ሽናሻ | 21.5 | 13 | 34.5 | |
| 6 | ሴ | B | አገው | 5 | 5 | 10 | |
| 7 | ወ | A | አገው | 21 | 12.5 | 33.5 | |
| 8 | ሴ | B | አገው | 7 | 3 | 10 | |
| 9 | ሴ | B | አገው | 21.5 | 12 | 33.5 | |
| 10 | ወ | D | አገው | 8.5 | 4 | 12.5 | |
| 11 | ወ | B | ሽናሻ | 20.5 | 12.5 | 33 | |
| 12 | ሴ | A | አገው | 6.5 | 6 | 12.5 | |
| 13 | ሴ | C | ጉሙዝ | 15 | 11.5 | 26.5 | |
| 14 | ወ | B | ጉሙዝ | 8 | 5 | 13 | |
| 15 | ወ | C | ጉሙዝ | 20 | 9 | 29 | |
| 16 | ወ | A | አገው | 9 | 5 | 14 | |
| 17 | ሴ | D | አሮሞ | 17.5 | 11 | 28.5 | |
| 18 | ወ | A | ጉሙዝ | 8.5 | 6 | 14.5 | |
| 19 | ወ | A | ጉምዝ | 13.5 | 14 | 27.5 | |
| 20 | ሴ | B | አገው | 9 | 6 | 15 | |
| 21 | ሴ | B | አገው | 14.5 | 12 | 26.5 | |
| 22 | ሴ | D | ኦሮሞ | 9.5 | 6 | 15.5 | |
| 23 | ወ | C | አገው | 18 | 6.5 | 24.5 | |
| 24 | ሴ | D | አገው | 13 | 3 | 16 | |
| 25 | ሴ | D | ኦሮሞ | 16 | 7 | 23 | |
| 26 | ወ | B | ጉሙዝ | 9.5 | 7.5 | 17 | |
| 27 | ሴ | C | ሽናሻ | 13 | 9 | 22 | |
| 28 | ወ | D | ጉሙዝ | 10 | 7 | 17 | |
| 29 | ወ | D | ጉሙዝ | 10.5 | 10 | 20.5 | |
| 30 | ወ | A | ሽናሻ | 12.5 | 5 | 17.5 | |

አባሪ ‹‹ሎ›› የሙከራ ቡድን ‹‹ ለ ›› የቅድመ ልምምድ የፈተና ውጤት

| ተ.ቁ | ፆታ | ሴክሽን | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | 25% | 20% | 45% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሴ | B | ኦሮሞ | 19.5 | 18.5 | 38 | |
| 2 | ሴ | D | ጉሙዝ | 3 | 5 | 8 | |
| 3 | ወ | B | አገው | 20.5 | 15 | 35.5 | |
| 4 | ሴ | A | አገው | 4.5 | 4 | 8.5 | |
| 5 | ወ | A | ሽናሻ | 20.5 | 13 | 33.5 | |
| 6 | ወ | C | ጉሙዝ | 5 | 5 | 10 | |
| 7 | ወ | A | አገው | 24 | 9.5 | 33.5 | |
| 8 | ሴ | C | ሽናሻ | 6 | 5 | 11 | |
| 9 | ወ | D | ሽናሻ | 20 | 13 | 33 | |
| 10 | ሴ | C | አገው | 6.5 | 5 | 11.5 | |
| 11 | ወ | C | ሽናሻ | 19.5 | 11 | 30.5 | |
| 12 | ሴ | D | አገው | 9 | 4 | 13 | |
| 13 | ወ | C | ጉሙዝ | 20.5 | 10 | 30.5 | |
| 14 | ወ | D | አገው | 8.5 | 5 | 13.5 | |
| 15 | ሴ | A | ሽናሻ | 17 | 12 | 29 | |
| 16 | ሴ | B | አገው | 10 | 4 | 14 | |
| 17 | ወ | A | ሽናሻ | 16.5 | 12 | 28.5 | |
| 18 | ሴ | B | አገው | 12 | 3 | 15 | |
| 19 | ሴ | A | ሽናሻ | 13.5 | 14 | 27.5 | |
| 20 | ወ | A | ጉሙዝ | 5 | 10 | 15 | |
| 21 | ወ | C | አገው | 18.5 | 8 | 26.5 | |
| 22 | ወ | C | ጉሙዝ | 11.5 | 4 | 15 | |
| 23 | ወ | A | ሽናሻ | 16 | 8 | 24 | |
| 24 | ወ | B | ጉሙዝ | 7 | 9 | 16 | |
| 25 | ወ | D | ሽናሻ | 15 | 8 | 23 | |
| 26 | ወ | B | ጉሙዝ | 11 | 6 | 17 | |
| 27 | ሴ | D | አገው | 10 | 11 | 21 | |
| 28 | ወ | C | ኦሮሞ | 11 | 6 | 17 | |
| 29 | ወ | A | አገው | 13 | 8 | 21 | |
| 30 | ወ | A | ጉሙዝ | 7.5 | 10 | 17.5 | |

አባሪ ‹‹ሐ›› የቁጥጥር ቡድን ‹‹ሀ›› የድህረ ልምምድ የፈተና ውጤት

| ተ.ቁ | ፆታ | ሴክሽን | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | 20% | 25% | 45% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ | C | ሽናሻ | 16 | 20 | 36 | |
| 2 | ሴ | D | አገው | 7 | 9 | 16 | |
| 3 | ወ | B | አገው | 15 | 19 | 34 | |
| 4 | ወ | B | ጉሙዝ | 4 | 10 | 14 | |
| 5 | ሴ | D | ሽናሻ | 12 | 18 | 30 | |
| 6 | ሴ | B | አገው | 5 | 6 | 11 | |
| 7 | ወ | A | አገው | 14 | 20.5 | 34.5 | |
| 8 | ሴ | B | አገው | 5 | 10 | 15 | |
| 9 | ሴ | B | አገው | 10 | 18.5 | 28.5 | |
| 10 | ወ | D | አገው | 5 | 9 | 14 | |
| 11 | ወ | B | ሽናሻ | 13 | 18.5 | 31.5 | |
| 12 | ሴ | A | አገው | 8 | 8 | 16 | |
| 13 | ሴ | C | ጉሙዝ | 14 | 10.5 | 24.5 | |
| 14 | ወ | B | ጉሙዝ | 5 | 7 | 12 | |
| 15 | ወ | C | ጉሙዝ | 8 | 14 | 22 | |
| 16 | ወ | A | አገው | 8 | 8 | 16 | |
| 17 | ሴ | D | አሮሞ | 15 | 18 | 33 | |
| 18 | ወ | A | ጉሙዝ | 7 | 9 | 16 | |
| 19 | ወ | A | ጉምዝ | 13 | 13.5 | 26.5 | |
| 20 | ሴ | B | አገው | 7 | 10 | 17 | |
| 21 | ሴ | B | አገው | 12 | 15 | 27 | |
| 22 | ሴ | D | ኦሮሞ | 7 | 10 | 17 | |
| 23 | ወ | C | አገው | 7 | 17.5 | 24.5 | |
| 24 | ሴ | D | አገው | 5 | 12 | 17 | |
| 25 | ሴ | D | ኦሮሞ | 8 | 14 | 22 | |
| 26 | ወ | B | ጉሙዝ | 7 | 9 | 16 | |
| 27 | ሴ | C | ሽናሻ | 8 | 15 | 23 | |
| 28 | ወ | D | ጉሙዝ | 9 | 10 | 19 | |
| 29 | ወ | D | ጉሙዝ | 9 | 9.5 | 18.5 | |
| 30 | ወ | A | ሽናሻ | 6 | 10.5 | 16.5 | |

አባሪ ‹‹መ›› የሙከራ ቡድን ‹‹ ለ ›› የድህረ ልምምድ የፈተና ውጤት

| ተ.ቁ | ፆታ | ሴክሽን | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | 20% | 25% | 45% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሴ | B | ኦሮሞ | 19.5 | 21 | 40.5 | |
| 2 | ሴ | D | ጉሙዝ | 10 | 9 | 19 | |
| 3 | ወ | B | አገው | 18 | 23 | 41 | |
| 4 | ሴ | A | አገው | 5 | 8 | 13 | |
| 5 | ወ | A | ሽናሻ | 14 | 21.5 | 35.5 | |
| 6 | ወ | C | ጉሙዝ | 8 | 7 | 15 | |
| 7 | ወ | A | አገው | 14 | 19 | 33 | |
| 8 | ሴ | C | ሽናሻ | 12 | 9 | 21 | |
| 9 | ወ | D | ሽናሻ | 20 | 16 | 36 | |
| 10 | ሴ | C | አገው | 8 | 8.5 | 16.5 | |
| 11 | ወ | C | ሽናሻ | 10 | 18 | 28 | |
| 12 | ሴ | D | አገው | 11 | 11 | 22 | |
| 13 | ወ | C | ጉሙዝ | 14 | 18 | 32 | |
| 14 | ወ | D | አገው | 10 | 14 | 24 | |
| 15 | ሴ | A | ሽናሻ | 15 | 16 | 31 | |
| 16 | ሴ | B | አገው | 11 | 13 | 24 | |
| 17 | ወ | A | ሽናሻ | 17 | 14.5 | 31.5 | |
| 18 | ሴ | B | አገው | 9 | 14.5 | 23.5 | |
| 19 | ሴ | A | ሽናሻ | 16 | 12.5 | 28.5 | |
| 20 | ወ | A | ጉሙዝ | 6 | 11.5 | 17.5 | |
    ሀ. የእትዬ ሻሾ ወሬ መሰረተ ቢስ መሆኑ፣ ለ. ከሠራተኛዋ ጋር በሚስጢር ያደረጉት ነገር በአባወራው ፊት መቅረቡ፣ ሐ. የሠራተኝዋ እምነተ ቢስ መሆን፣ መ. መልስ አልተሰጠም፣
11. ዘርፌና ባለቤቷ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቁበት ሁኔታ ምን ነበር?
    ሀ. የዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያሉ፣ ለ. አንድ መስሪያ ቤት ሲሰሩ፣ ሐ. እሷ ማትሪክን ባላለፈችበት ሰዓት ጎረቤት ተከራይቶ ሲኖር፣ መ. የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያሉ፣
12. እንደ ዘርፌ አገላለጽ፣‹‹ባለቤቴ ሞቅ ብሎት ሲመጣ የምናምንቴዎችን ያህል እንኳ ክብር አይሰጠኝም›› ስትል ምንን ይገልጻል?
    ሀ. የሴተኛ አዳሪዎችን ያህል፣ ለ. የሰፈር ቡና አጣጮችን ያህል፣ ሐ. የሰፈር ወሬ አቀባችን ያህል፣ መ. የአውነተኛ ፍቅረኛሞችን ያህል፣

**፫. ምንባቡን መሰርት በማድረግ በ‹‹ሀ›› ስር ለተዘረዘሩት ጽንሰ ሀሳቦች በ‹‹ለ››ክፍል ከቀረቡት ማብራሪዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡**

‹‹ሀ›› ‹‹ለ››

13. ቁመው ቀሩሳ፣ ሀ. ትዳር ሳይመሰርቱ እድሜዎ ገፋ፣
14. ጎረቤት የሚፈተፍተው ነገር፣ ለ. የተዋለላትን ውለታ አለማስታውስ፣
15. የበላሸበትን ወጭት ሰባሪ፣ ሐ. የታቀደው ጉዳይ ቀርቶ ያልተገመተዉ መድረስ
16. በእርግቢቱ የተመሰለችው፣ መ. ዘርፌ
17. ፀጉሬን እሰራለሁ ብላ ሄዳ ተላጭታ መጣች፣ ሠ. እትዬ ሻሾ፣
ረ. አልተቀመጡም፣
ሸ. ሠፈርተኛው የሚያወረው ጉዳይ፣

**፬. ለሚከተሉት ጥያቂዎች ከምንባቡ የተረዳችሁትን መሰረት በማድረግ አጭር ማብራሪያ ስጡ፣**

18. አባወራው ባሉባልታ ተመርቶ ሰራተኛይትን መደባደቡ እና ያደረገው ዛቻ ተገቢነው ወይስ አይደለም? ምክንያት በመስጠት በጽሁፍ አብራሩ፣

---

19. በትዳር ውስጥ የልጆች መወለድ የተጋቢዎችን ፍቅርና መተሳሰብ ይቀንሰዋል ወይስ አይቀንሰውም?

---

20. የልቦለዱ ጭብጥ ምንድን ነው? በጽሁፍ አብራሩ-------------------------------------

አባሪ ‹‹ዐ›› **ድህረልምምድ ፈተና፦ክፍል ሁለት**

ክፍል ሁለት፣ ‹‹ **ጆርዳን**›› በሚል የምንባብ ርዕስ የቀረበ ሲሆን፣በእዚህ ሥር ከ1 እስከ 25 ያሉ ጥያቄዎች እንደ ትዕዛዛቸው በዚህ ምንባብ መሰረት ይሰራሉ፡፡ የዚህ ምዘና ክፍል ዋና ዓላማ ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ልምምድ ሂደት ያዳበሩትን ልምድ ለመለካት የተዘጋጀ ነው፡፡ የተፈቀደ ጊዜ 55፣ደቂቃ፣
የተማሪ ስም------------------------------ ክፍል -----ምድብ ------ጾታ ----

**ጆርዳን**

እንዴት እንደተዋወቅን አስታውሳለሁ፡፡ እሁድ ቀን ስለነበረ አባዬም፣አያቴም ቤት ውስጥ ቡና ይጠጣሉ፡፡ እንቅርታሟ የአያቴ ወዳጅ እመት አባይነሽም የውጭውን ቆርቆሮ በር ገርበብ አድርገው ወደ ውስጥ እንደገቡ፣ ስለወገባቸው፣ ስለቁርጥማቱ፣ እንደሁልግዜው እያማረሩ ሲያወሩ፣ ከቶም ማይለወጠው‹‹ዘሐር ይመስገን››የሚል የአያቴ መልስ ከቤት ውስጥ ተሰማ፡፡ አባዬ ሳይተርፈው ያበደረውን አስራሁለት ብር ከቦኖ ውሃ አስቀጅው አባባ ሳጅን ዘንድ እንዳመጣ ደጋግሞ በሞቅታ የነገረኝን ረስቶት ይሆን? ወይስ ብቅ ብሎ ‹አንተ ልግመኛ አልላክም ማለትህ ነው?› ይለኛል እያልሁኝ በአንድ በኩል የመንገዱ ርቀት ጣዕር ሲታሰበኝ፣ለይምሰል ደብተር ገልጨ ብሳናው ዛፍ ስር አድፍጫለሁ፡፡

የምንኖርበት ግቢ ጐኑ የሚገኘው እንጨት መሰንጠቂያ ባለንብረት ሊያስፋፉት አስበው አጥረው የተውት ቅጥር ነው፡፡ ፊት ለፊቱ በወፍራም የጣሊያን ቆርቆሮ የተገጠመ ሲሆን፣አንዱን ጐኑን የእንጨት መሰንጠቂያው ረጅም ግንብ፣ሌላኛውን አዲስ የተሰራው የአበባው ገነት ትልቅ ቤት ያዋስኑታል፡፡ የኮኩ፣የጥዱ፣የባህር ዛፍና ትልቁ ብሳና ዛፍ ጥግ

ጥጉን ደግሞ የሰንሰልና የሳማ ቁጥቋጦ ወርሶታል፡፡ አስቀድሞ ለዕቃ ማከማቻነት የተሰራችው ቤታችንም ጢስ ጢሶባት መኖር ከጀመረች ጊዜው ረጅም ነው፡፡
ታዲያ ያንን እሑድ ልውጣ ልቅር? እያልኩኝ ሳመነታ፣ ከመጣበት ያልታወቀ ትልቅ ቆዳ ኳስ ደብተሬ ላይ ነጥሮ አንዱን ገጽ ገነጠለና ወደሰንሰሉ ተንከባለለ፡፡ የመጣበትን አቅጣጫ ስፈልግ፣መቼም ከዓይኔ የማይጠፋው ራስ በሁለት የኰክ ዛፎች መሀከል አዲሱ የግንብ ጫፍ ላይ ብቅ አለ፡፡ ቁልቁል ይመለከተኛል፤ቁመቱ እኔን ነው የሚያክለው፡፡ የፈረስ ጋማ የመሰለ ቡና ዓይነት ፀጉር ከፊት ቅንድቡ ላይ ደርሷል፡፡ በጣም የነኩኝ ድመት መሰል ዓይኖቹ ናቸው፡፡ ሽቅብ እየተመለከትኩት ብትንታኟን ደብተሬን በማሳየት‹‹ይሄ ምንድን ነው? ፈረንጅ ዩ ኖ ሄድ?›› አልኩት፤ ዓይኖቹን ላዬ ላይ ተክሎ ፣በተቀላጠፈ አማርኛ‹‹ነጥሮ ነው የመጣብኝ ልክፈል?››አለ፡፡ ከኋላ ኪሱ ምናምን ለማውጣት እየሞከረ፤ሽቦ የተወጠረበትን እንጨት ሲለቅ እግሩ ሚለጨና በደረቱ ሽቦው እሾህ ላይ አረፈ፡፡ እግሮቹም ሽቅብ ስለተነሱ የሰውነቱ ሙሉ ክብደት እሾሁ ላይ ስላረፈ በጣም አሰቃየው፡፡ የኰኩን ዛፍ እንዴት እንደወጣሁ እኔእንጃ ግንቡ ጫፍ ደርሼ አንገቱን ቀና እሰታደርገዉ ድረስ ከደረቱ የገባው ሽቦና ለመላቀቅ የታገለበት እጁ ተሰንጥሩዋል፡፡ ቅልስልስ በማለት ወርዶ አሸዋው ንጣፍ ላይ አረፈና ሸሚዙን በጥንቃቄ ያወልቅ ጀመር፡፡ አለማልቀሱ እጅግ አስገረመኝ፡፡ አሁን እኔ ነኝ ቁልቁል እምመለከተው፡፡

ከወገቡ በላይ ተራቁቶ የተላላጠ ሰውነቱን ሲመለከት በጣም አሳዘነኝ፡፡ የኔ ጥፋትም መሰለኝ ባልጮህበት ይሻል ነበር ይሆን? አንዲት ባለሽርጥ ሴት ከቤት ብቅ ብለው‹‹አንተ እነማዳም ጥለዉህ ካቴድራል መሄዳቸው ነው፣አትመጣም?››ቢሉት በአበቦቹ ሰውነቱን እየከለለ‹‹መጣሁ፤ፀሐይ እሞቃለሁ›› አላቸው፡፡ መቁሰሉን የደበቀበት ምክንያት ምን ይሆን? ብቻ አሁን መታከም አለበት፡፡ ‹‹የእኔ አያት ቁስል ማከም ያውቃሉ፣እኔ ቤት ና›› አልኩት፣ሽቅብ ተመለከተኝ፡፡ የጣቶችን ደም እየመጠጠ፣ ብጠብቅ አይተፋም፣ይውጠዋል፡፡ የጥርጣሬ አስተያይቱ እንዳበቃ ወደቤቱ ተገላመጠና ሸሚዙን ብድግ አድርጎ ያንኑ ግንብ መውጣት ጀመረ፡፡ ፊት ፊት ቀድሜ ወደ ቤት መራሁት፡፡

ውስጥ ብንገባ ማንም ሰው የለም፡፡ ረከቦቱና ፍንጃሎቹ ግን አልተነሱም፡፡ ወደ ውጭ ብቅ እንዳልን አያቴ ጭራሮ ለቃቅመው ሲመለሱ ተገጣጠምን፡፡ እኔን ትተው ደረቱን ገልጦ የቆመውን ፈረንጅ በመገረም እየተመለከቱ ቆዩና ምንድን ነው ጉዱ? ኧረ ምንድን ነው?›› አሉ፡፡ በጥድፊያ ማስረዳት ጀመርኩኝ ‹‹ጓደኛዬ ነው፤ ከግንቡ አናት ያለው ሽቦ ቀደደው፡፡ እኔን እንዳከሙኝ በጨርቅ እንዲያክሙት ነው፡፡›› አልኳቸው፡፡ ጭራሮአቸውን መሬት ላይ ዘረገፉና ተከታትለን ገባን፡፡

ፈረንጁ ቤታችንን እንደብረቅ ነገር ይመለከታል፤ወደ ማድ ቤት እንደገቡ አልጋው ላይ የነበረውን ዳዊት ከነማህደሩ ብድግ አደረገ፡፡ በድንገት ሳስጥለው በድንጋጤ አፈጠጠብኝ፡፡ ጥቅርሻውን፣የሸረሪት ድሩን፣የጠፍር አልጋውን፣ስሌትንና‹‹ጽድቅና ኩነኔ››የሚለውን ጥቅስ ሁሉ በአንክሮ ተመልክቷል፡፡ ‹‹ብቅበል እስቲ ሳሚቲ››ሲሉ ተጣሩ አያቴ፣ሊተኩሱበት ያቀጣጠሉትን አሮጌ ጨርቅ እንዳንጠለጠሉ‹‹ ይኸን ይዘህብኝ መጣህ?ቆይ አባትህ ይምጣ፣አሁን የሰው ፈረንጅ እጀላይ አንድ ነገር ቢሆንስ?...እግዜር ይቅር ይበልህ ጦሰኛ ሆነሃል ሳሙኤል››በጣም ተጨንቀዋል፣ግን ማከሙን ፈልገዋል፡፡ ነገሩን ለማቃለል ‹‹ምን ይሆናል?›› እኔን ያኔ እንኳን እንደተኮሱኝ ይተኩሱት በቃ›› አልኳቸው፡፡

ፈረንጁጋ ስመለስ የመቁጠሪያቸውን ዶቃዎች ሲቆጥር ደረስኩበትና መንጭቁ አልጋው ላይ ስወረውር ፣አሮጊቷ ጨርቁን እያጨሱ ብቅ አሉ፡፡ አያቴ እጅ ላይ የሚጨሰው ቡቱቶ ከመደሐኒት ጋር ምን እነደሚያገናኘው ሊገባው ስላልቻለ፣ አፍጥጦ ጨርቁን ሲያስተዉል አያቴ በንዴት እየሳቁ‹‹በጀርባው አስተኛው፡፡ ምን አባህ ያፈዘሃል?›› ሸሚዙን ተቀብየ ሳስተኛው ሳቁ መጣ፡፡ አሮጊቷ አማርኛ አያውቅም ብለዉ መሸሽጋቸው ነው፡፡ እንደሚባበል ሕጻን ‹‹አይዞህ ልጄ አይዞህ ምንም አይደል ቀላል ነው››አሉት፡፡ ፈረንጁም ተደናግጦ እምር

ለማለት እየከጀለው በግድ የጎድን ተጋደመ፡፡ አሮጊቷ በከፍተኛ ጥንቃቄ እጃቸው የቆሰለውን በሙሉ ተኩሰው ሲያበቁ አምላክን አመስግነው በረጅሙ ተነፈሱና ‹‹ሳሙኤል ጉድ አድርገኸኝ ነበር፡፡ አባትህይምጣ ግድ የለም፡፡››ወደ እሱ ደግሞ ዘወር ብለው‹‹ተነስ ልጄ በቃ ተነስ›› አሉት፡፡ ብድግ ብሎ ከእጃቸው ጨርቁን ተቀበለና በደንብ አገላብጦ አየው፤አሸተተው፡፡

አሮጊቷ ወጣ ብለው ቅጠል በመዳፋቸው እያሻሹ አመጡና የተኮሱትን ቦታ ሁሉ ጠራርገውት ሲያበቁ፣በፍርሃት ሽሚዙን አጠለቀ፡፡ ‹‹ለመሆኑ ከየት አባህ ነው ጎትተህ ያመጣኸው?››አሉኝ፡፡ በመሐል አቋርጦ‹‹አይ! አልጎተተኝም እራሴነው የመጣሁት፡፡ አሁን ሰሞን እዚህ ቤት ገብተናል እያለ ወደ ትልቁ ቤት በጣቱ ጠቆማቸው፡፡ ወደ ፍንጃሎቹ እየጠቆመ ‹‹ቡና እወዳለሁ አጠጡኝ››ሲል እጅግ ሳቁና፣ቡናውን ቀዱና እንካ ብቻ ሶስተኛ ነው›› አሉት፡፡ አልገባውም፣ጭንቅላቱን በመነቅነቅ ‹‹አይ አንድ ብቻ ነው የምፈልገዉ›› አላቸው፡፡ ቡናውን በስሜት እየሳበ ‹‹የኔ ስሜ ጆርዳን ነው፡፡ ያንተ ማንነው?አለኝ፡፡ ‹‹ሳሙኤል››አለኩት፡፡ በግራእጁ እየጠቆመ ‹‹የእሷስ?›› ቢል አሮጊቷ በሚያስገርም ሁኔታ እያዩት በአድናቆት አጨበጨቡና ‹‹ግሩም፣ ግሩም፣ እኔን አፈር ይብላኝ››አሉ፡፡ አንቺ ማለቱን እንደንቀት አልወሰዱትም፡፡ እሳቸውም ስም አላቸው ግን አያቴ ነው የምላቸው፡፡ ከአፌ ነጥቆ‹‹አያቴ ቡናው ስኳር የለውም ስጭኝ›› አለ፡፡ ‹‹ትልቅ ሰው ናቸው አንቱ ማለት አለበህ፡፡ ዝምብለህ አያቴ ማለት የለበህም›› አልኩት፡፡ ግን አሮጊቷን ‹‹አያቴ››እያለ ሲጠራቸው ኖረ፡፡ ከጆርዳን ጋር የተዋወቅነው በዚህ አይነት ሁኔታ ነበር፡፡

ያን ጠዋት አሮጊቷን አመስግኖ እንደወጣን ጠጠር እያነሳሳ ከዛፍ ላይ ወፎችን ሲያባርር፣ከጅማ በቅርቡ እንደመጡና እሱም የተወለደው እዚህ ሀገር እንደሆነ፣አባቱ ግሪክ ነጋዴ እንደሆኑ ሲነገረኝ፣የወፎች ስም በማላውቀው ቋንቋ እየጠራ ‹‹ይች ብርድ አትወድም፣ይች ጥሩ ትዘፍናለች… ››እያለ ሲያወራ አንድም ነገር አልገባኝም፡፡ ኳሷን ከጥሻው ውስጥ አውጥተን ጥዊት ከለጋናት በኋላ መለስብሎ ወደ ወፎች ያተኩራል፡፡

ከወደ መሰንጠቂያው የወደቀ ጣውላ ላይ አረፍ ብለን ይህንንም ያንንም ስንጠያየቅ ድንገት አንድ ድምጽ ከወደቤታቸው ሲጣራ ሰምቶ ፊቱን አዞረና፣‹‹ወይኔ፣ ተመለሱ ከካቴድራል!››አለ፡፡ ‹‹ምንድን ካቴድራል?››፣‹‹ፀሎት የሚደረግበት ቦታ ነው፡፡››፣‹‹የእኔ እናት ስላሴ ነው ሚሄዱት፣ ወይም ባታ፡፡›› ፣ ‹‹ትሂድ እኔ ምን ቸገረኝ አለና ወደሚጣራው ድምጽ አኳያ አንገቱን አስግጎ ‹‹አንጀሊክ›› መጣሁ ሲል ጮኸ፡፡ አማርኛ በደንብ ይናገራል፡፡ እኔ ለምጠይቀው የሚሰጠኝ መልስ ግን ይገርመኛል፡፡ ከተርኪ ደሮዎችና በረንዳ አበቦች ጋር ሲታገሉ የሚኖሩት እናቱ፣ከአበሻና የውጭ ሰው ጋር እንዲገጥም አይፈልጉም፡፡ አባቱም በስራቸው ተጠምደው አያዩትም እንጅ ቢያውቁ እንደሚገርፉት አይጠረጠርም፡፡

እኔና እሱ ግን ጓደኝነታችንን ወደነው እንጫወታለን፡፡ ጆርዳን ጋር እያደር ተቀራረብን፡፡ ከቤትም ምግብ ሲጠፋ፣አያቴ ወዳጅ ያሉዋቸው ዘንድ ‹‹ምናምን›› ፍለጋ ሲወጡ፣ባዶቤት ተዘግቼ እውላለሁ፡፡ ድንገት ከተፍ የሚለው ጆርዳን ፊቱን እየደባበሰ ወጥሮ ይጠይቀኛል፡፡ እንዴት ብዬ ልንገረው? ‹‹ደሃ ነን የሚበላ ስለጠፋ እርቦኝ ነው›› ማለት ያስፈራኛል፡፡ ጓደኛዬ ግን ለማወቅ ጊዜ አይፈጅበትም፡፡ ድንገት ይሰወርና እያለከለከ ተመልሶ ሰሊጥ የፈነጠቀበት ዳቦና ቋሊማ ከሹራቡ ስር አውጥቶ ‹‹አብረን እንድንበላ ነው ያመጣሁት›› ብሎ አልጋው ላይ ሲዘረግፈው፣ መጀመሪያ ለመንካትም ያስፈራኛል፡፡ በተለይ አያቴ ‹‹የሰው እጅ ከማየት አድነኝ›› የሚሉትን ሳስብ የባሰ እሸማቀቃለሁ፡፡ ግን እያመነታሁ ያኮረፍኩበትን ሌላ ምክንያት ዋሽቸው ቶሎ ቶሎ እበላለሁ፤ እንበላለን፡፡ አንድ ቀን አያቴ የከንፈሬን ወዝ አይተው እንደልሞት እንደልሽር አረገው በሳማ የገረፉኝን አይቶ ‹‹ምን ሆንክ?›› አለ፡፡ አፌ ላይ የመጣልኝን ‹‹ቆርቆሮ ቧጠጠኝ››አልኩት፡፡ ከልቡ እየሳቀ ‹‹ቆርቆሮ አያሳብጥም ይቧጭራል›› አለ፡፡ ስላወቀብኝ በጣም በሽቁ እንድንጫወትበት ያመጣውን ዶሚኖ የተባለ ነገር አፍንጫው ላይ ወርውሬለት ሄድኩኝ፡፡ ለሶስት ቀን ተኮራርፈናል ብየ ሳስብ ድንገት መጣና ‹‹ሰበታ ሄጀ ነው የጠፋሁት 'ኮ›› አለ፡፡ አንደንዴ ጥያቄው ያናድዳል፡፡ ለምን? መልስ

የለውማ፡፡ ‹‹አባትህ ለምን ብዙ ምግብ ገዝቶ አያመጣም?›› ይላል፡፡ ‹‹ደሞዙ ትንሽ ነው፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ ጠጅ ይጠጣል›› ብለው የት ይገበዋል፡፡ ለተርኪዎቹ ደሮዋች ቤት ማደሻ ካስመጡት የሸንበቆ ክምር ጥቂት መዞ አመጣና እኛ ግቢ ውስጥ አጥሩ ጥግ ባለጠለል የመሰለች ጎጆ ሰራንና ጓደንነታችንን አደራን፡፡

‹‹ለምን እንዲህ ትወደኛለህ?››አልኩት አንድ ቀን፡፡ በአይኖቹ ጭምር እየሳቀ ‹‹ጓደኛየ ነሃ›› አለኝ፡፡ አያቴ ‹‹ከሰላቶ ጋር ገጥመህ ማበድህ ነው፡፡ እግዚአብሄር ማብረጃውን ይስጥህ›› ቢሉኝም ጆርዳንን ይወዱታል፡፡ ምጣድ ላይ እንዳሉ ማድቤት ገብቶ በጭሱ እያለቀሰ፣‹‹ቆሎ ቁሉልኝ›› ብሎ በግድ እጎን ያስጥዳቸዋል፡፡ ቆልተዉ ሲጨርሱ ትኩሱን ሽንብራ በኪሱ እየሞሉለት ‹‹ዮርዳኖስ ስራየን ልስራበት እባክህ፣ ለራሴ ምጣድ አልሰማ ብላኝ ተቸግሪያለሁ›› ብለው ያባርሩታል፡፡
እጅግ የሚያስደስቱን የዝናብ ቀናት ነበሩ፡፡ የሸንበቆ ጎጇችን ውስጥ ገብተን ሻይ እናፈላለን፡፡ እህቱን አንጀሊክን በልዩ ዓይን መመልከት የጀመርኩት እዚሁ እሸንበቆ ጎጆ አጥር ውስጥ ነው፡፡ ብይ የመሰሉ ዓይኖቿን ብስማቸው ተመኘሁ፡፡ ስትስቅ ጥርሶቿን በጣቴ እነካለሁ፡፡እረጅም ጥቁር ከሰል ቅንድቦቿ እያስገረሙኝ በእጀ ስሄድባቸው በመገረም ዝም ትለኛለች፡፡ ‹‹ስታድጊ ምንድን ነው የምትሆኝው?›› አልኳት፡፡ ያላንዳች ማመንታት ‹‹ዶክተር ነዋ›› አለች፡፡ ‹‹ስታድጉ አንቺም ጆርዳንም እንደሌሎች ትላልቅ ፈረንጆች ትኮራላችሁ ›› አልኳት፡፡ ‹‹የጆርዳንን እንጃ እኔ ግን እንደዚሁ ነኝ የምሆነው››አለችና መሀከል መዳፌ ላይ መስቀል ሰርታ ግራ ጉልበቷን አጣፋችው፡፡ የበለጠ ለማረጋገጥ ፈለኩና ‹‹አንች እራስሽ እናቴ ከሀበሻ ጋር አትሂጅ ትለኛለች አላልሽም?›› እንደማፈር ብላ ‹‹ታዲያ እሷናታ የተናገረችው አለች፡፡ ግን ከልቤ አመንኳት፡፡ ጆርዳን የተሰረቀውን ስኳር ይዞ ከተፍ እንዳለ በቋንቋቸው አንድ ነገር ነገረችው፡፡ እሱም የሶስታችንን መዳፎች ደራርቦ ጸሎት መሳይ ነገር አነበነበ፡፡ መሃላ መሆኑ ነው፡፡

ጎጇችን በጢስ እንደታበቀች ደስ ብሎኝ ሳለሁ፣ አያቴ ጭንቅላታቸውን ብቅ አድርገው በአሮጌ ዣንጥላ ጫፍ እየወጋጉኝ ‹‹ና ውጣ አንተ ከንቱ፣አንተ አጥፊ›› እያሉ ፈልፍለው አወጡኝ፡፡ እነ ጆርዳንን ለዘብ ባለ ድምጽ፣ እዚህ ሽንበቆ ውስጥ እሳት ማንደድ አደጋ እንደሚያመጣ ነግረዋቸው ለያዩን፡፡ ማታ ተገረፍኩኝ፡፡  ምንም አላጠፋሁኝ ከነጆርዳን ጋር ስናድግ እንዳንከዳዳ ብቻ ነው የተማማልነው፡፡ የሆነው ሆኖ ተገረፍኩ፡፡ አያቴ በየጊዜው ቢደበድቡኝም ብቻችንን ሰንሆን ማባበላቸው አይቀርም፡፡ ‹‹ለአንተው ብየ ነው ዱርዬ ሆነህ ብትቀር የሚያስተውስህ አታገኝም፡፡ ከዚህ ልጅ ጋር ያለህን ጓደኝነት በልክ አድርገው›› ይሉኛል፡፡ ግን ጆርዳንን ይወዱታል፡፡

የጋለ የድንጋይ ጉልቻ ፈንድቶ ፍንጣሪው እግራቸውን የመታቸው ዕለት እንኳን ጆርዳን እየሮጠ ሂዶ ከቤቱ የእሳት ቁስል ይዞ ሲመጣ መንገድ ላይ ከነቢልቃጡ ወድቆ እጁን ቢቆርጠዉ ሲያባብሉት በመገረም አይቻለሁ፡፡ በአሮጌ ሻሽ ጠምጥመውለት ስንወጣ ፈትቶ ጣለዉ፡፡ ‹‹ምነው?›› ብለው፤ ‹‹ከአበሻ ምንም እንዳናመጣ ይቆጡናል፤ታውቃለህ አይደለም›› አለኝ፡፡ እኔ የአፌን ወዝ አስሬ እንደምጠርግ እሱም አንዲት የቆሎ ጥሬ እንኳን በኪሱ እንዳትገኝ ኪሱን ገልብጦ አራግፎ ነው የሚገባው፡፡

መቼም የማልረሳው አሮጊቷ የሰጡትን ጥኩስ እንጎቻ እየገመጠ ሲጫወት፣ድንገት የመኪና ድምጽ ቢሰማ ወደ ግቢው ሮጦ ቢገባ ከእናቱ ጋር ተገናኘ፡፡ ማዳም እንደብራቅ ጮኸው ተእጁ ነጥቀው ለውሻው ሲወረውሩ፣ጆርዳን በእልህ እንጎቻውን ለማስጣል ከውሻው ጋር ሲተናነቅ ዘበኛውና ማዳም ተጋግዘው አላቀቁት፡፡ የአያቴን እንጎቻ ዓይኔ እያየ ውሻ በላው፡፡ መካከላችን የተሰመረው የቤተሰቦቹ አባሻ ጠልነት፣ደሃ ተጠያፊነት ባይኖር ኖሮ እንዴት የበለጠ ልንደሰት እንደምንችል አለውቅም፡፡ ከሰፈራችን ልጆች ጋርም በዚሁ ‹‹የሰላቶ አሽከር›› በሚል ስድባቸው የተነሳ አብሬ መዋል አልቻልኩም፡፡ እሱ ግን አይገባውም ነበር፡፡

ድንገት እቤታችን ውስጥ አንድ ነገር ሆነ፤ይኸውም የአባቴ ሚስት ማግባት ነው። አያቴ ደረታቸው ላይ አስደግፈው ፀጉሬን እየዳበሱ ‹‹ወደ ቢሾፍቱ እናትህ ዘንድ መሄድ አለብህ ከዚህ የአኗኗራችን መልክ መቀየሩ ነው›› አሉኝ። ከእርሳቸውና ከጆርዳን እንዴት እንደምለይ እንኳን ከግምት ማስገባት አቃተኝ። ሁለት ሶስት ጊዜ ሸንኮራ አገዳ ሰጥታኝ ስትሄድ ያለቀሰቸው ሴትዮ እናትህ ናት መባሌን ሰምቻለሁ ከዚህ በተረፈ አላውቃትም። አያቴ በእየጊዜው እየመጡ እንደሚጠይቁኝ አባብለው ቃል ገቡልኝ። ‹‹ሚሲት ተብዮዋም ዘላቂ አትመስለኝም እስከዚያው እንደምንም እናትህ ዘንድ ቆይ። ምንም ቢሆን የወላድ አንጀት ነው ያላት። አሉኝና አዲስ አበባን በለቅሶ ተለየኒት።

አስኮ ጌታሁንና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች ‹‹ጆርዳን››መጠነኛ ማስተካከያ ተደርጎበት የተወሰደ (1992፣61-81)

፩. ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት››በማለት መልሱ ለመልሳችሁም ምክንያት ስጡ።

1. የሳሙኤል አባት ሞልቶ የተረፈው ቱጃር ነው።
   ---------------------------------------------------------------------------------------------
2. ሳሙኤል ከብሳናው ስር ተቀምጦ በተመስጦ እያጠና ነበር።
   ---------------------------------------------------------------------------------------------
3. እነ ሳሙኤል የሚኖሩበት ቤት ከመጀመሪያው ለመኖሪያ ተብላ የተሰረች ናት።
   ---------------------------------------------------------------------------------------------፣
4. አሮጊቷ ለጆርዳን ያደረጉት ህክምና፣ ባህላዊ ነው።
   -------------------------------------------------------------------------------------------፣
5. ሳሙኤል ከአያቱ ዘንድ ወደ እናቱ ዘንድ ቢሾፍቱ የተጓዘዉ በደስታ ነው።
   ---------------------------------------------------------------------------------------------
6. አሮጊቷ እነጆርዳንን ካሽንበቆዉ ጎጆው እንዲወጡ ያደረጉት የእሳት ቃጠሎ እንዳይነሳ በመስጋት ነው እንጂ ለእነጆርዳን ባላቸው ጥላቻ አይደለም።
   ---------------------------------------------------------------------------------------------

**፪. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቂዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

7. የሳሙኤልና የጆርዳን የመጀመሪያ የመታወቅ ክስተት ምን ነበር?
   ሀ. የጆርዳን ኳስ ነጥሮ ግንቡን አልፎ በመምጣት የሳሙኤልን ደብተር መገንጠሉ፣
   ለ. ጆርዳንና እና ሳሙኤል ግቢያቸው ውስጥ የአዋፍ ዝርያዎች በሚመለከቱበት ወቅት፣
   ሐ. ጆርዳንና እና ሳሙኤል ከወንዝ የተገናኙበት አጋጣሚ፣
   መ. በገበያ ቦታ ተገናኝተው፣
8. ከሚከተሉት ውስጥ ጆርዳንን የማይመለከተው ምንድን ነው?
   ሀ. የድመት መሳይ አይኖች፤ ሐ. ሞላላ ቅል የመሰለ የፊት ገጽታ፤
   ለ. ፀጉሩ ከፊት ቅንድቡ ላይ የደረሰ፤ መ. የፈረስ ጭራ የመሰለ ቡናማ ፀጎር፣
9. ጆርዳን የጨበጠውን፣ ሽቦ የተወጠረበትን እንጨት የለቀቀው ለምንድን ነው?
   ሀ. ለእህቱ ሰላምታ ለመስጠት ሲል፣ ሐ. የተወረወረለትን ኳስ ለመቀበል ሲል፣
   ለ. ወፎችን ለመያዝ ሲል፣ መ. ከኪሱ ገንዘብ ለማምጣት ሲል፣
10. ጆርዳን በደረቱ ሽቦው ላይ ባረፈ ጊዜ አቃንቶ ያስለቀቀው ማን ነው?
    ሀ. ሳሙኤል ለ. የሳሙኤል አባት ሐ. የሳሙኤል አያት መ. እህቱ አንጀሊክ
11. ጆርዳን፣‹‹ቡናው ሦስተኛ ነው›› ሲባል፣አንድ ብቻ ነው የምፈልገው ማለቱ ምንን ያመለክታል?
    ሀ. ቡናው መቀጠኑን ስለገመተ፣ ሐ. ጆርዳን የሀገራችንን የቡና ሥርዓት አለማወቁን፣
    ለ. ጆርደን ያለስኳር ቡና አለመጠጣቱን፣ መ. ጆርዳን የቀዘቀዘ ቡና አለመውደዱን፣

12. የጆርዳን የትውልድ ቦታ የት ነው?
   ሀ. ኢትዮጵያ ለ. ግሪክ ሐ. ጣሊያን መ. ጀርመን
13. አሮጊቷ፣ የሳሙኤልን የከንፈር ወዝ አይተው ለምን ደበደቡት?
   ሀ. ሲጋራ አጭሷል ብለው ስለገመቱ፣
   ለ. ከነጆርዳን ቤት ምግብ ተመግቧል ብለው ስለጠረጠሩ፣
   ሐ. ከራሱ ቤት ምግብ ሰርቆ በልቱዋል ብለው ስለገመቱ፣
   መ. መልስ የለም
14. አሮጊቷ፣ ሳሙኤል ከጆርዳን ጋር ያለው ግንኙነት ምን እንዲሆን ይፈልጋሉ?
   ሀ. እንዲቋረጥ ለ. እንዲጠናከር ሐ. በልክ እንዲሆን መ. እንዲሻሻል
15. ጆርዳን፣ ሳሙኤል ለሚያነሳለት አንዳንድ ጥያቄዎች ግራየሚያጋባ መልስ የሚሰጠው ለምንድን ነው?
   ሀ. በሁለቱ መካከል የበህል ልዩነት ስላለ፤ ሐ. ጆርዳን የመስማት ችግር ስላለበት፣
   ለ. ጆርዳን አማርኛ መናገር ስለማይችል፣ መ. ሁሉም መልስ ናቸው።
16. የአንጀሊክ የወደፊት ምኞት ምን መሆን ነው?
   ሀ. ፓይለት ለ. ኢንጅነር ሐ. መሐንዲስ መ. ዶክተር
17. የሳሙኤልና የነጆርዳን ጓደኝነት ተጠናክሮ እንዳይቀጥል ምን ችግሮች ነበሩ?
   ሀ. የጆርዳን ወላጆች አበሻ ጠልነት፣
   ለ. አሮጊቷ ሳሙኤልን ከሰላቶ ጋር ገጥመህ ባለጌ ሆንህ ትቀራለህ ማለታቸው፣
   ሐ. ሌሎች የሳሙኤል ጓደኞች የሰላቶ አሽከር እያሉ መሳለቃቸው፣
   መ. ሁሉም መልስ ናቸው።
18. በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ጓደኝነት ለመመሥረት ወሳኙ አካባቢ ነው፤
   ለ. ጓደኝነት ለመመሥረት በባህል መመሣሠል የግድ ይላል፤
   ሐ. የወላጆች ተጽንኦ የልጆችን ጓደኝነት ሙሉ ለሙሉ ይገድባል፤
   መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

**ፎ. ምንባቡን መሰርት በማድረግ በ‹‹ሀ›› ስር ለተዘረዘሩት ጽንሰ ሀሳቦች በ‹‹ለ››ክፍል ከቀረቡት ማብራሪዎቻቸው ጋር አዛምዱ፣**

| **‹‹ሀ››** | **‹‹ለ››** |
|---|---|
| 19. ቅንድቦቿን በእጀ ስሄድባቸው፣ | ሀ. ለመኖሪያነት መገልገል መቻል፣ |
| 20. እጀ ላይ ቢጠናወተውስ፣ | ለ. ተመጽዋች አታድርገኝ፣ |
| 21. በአይኖቹ ጭምር እየሳቀ፣ | ሐ. ስዳብሳቸው፣ |
| 22. ጢስ ጢሶባት መኖር ከጀመረች፣ | መ. ድንገት ቢታመም፣ |
| 23. የሰው እጅ ከማየት አድነኝ፣ | ሠ. እጅግ መደሰት፣ |
| | ረ. እረፍት ማጣት፣ |

**ፎ. ለሚከተሉት ጥያቂዎች ከምንባቡ የተረዳችሁትን መሰረት በማድረግ አጭር ማብራሪያ ስጡ፣**

24. ጆርዳን የአሮጊቷን የመተኮሻ ጨርቅ አፍጥጦ የተመለከተበት ምክንያት ምንድን ነው?
   ------------------------------------------------------------------------------------------------

25.ሳሙኤል ወደ አያቱ ቤት ተመልሶ የሚመጣ ይመስልሃል? ለምን?

------------------------------------------------------------------------------------------------፣

## አባሪ ‹‹ዘ›› **የማስተማሪያ ጽሑፎች (ቴክስት)**

*አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን በአጭር ልቦለድ ቋንቋን ለማስተማር ታስቦ የተዘጋጀ ጽሑፍ(ቴክስት)፡፡ ይህ ቴክስት አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች ውስጥ የሙከራ ቡድኑን በአጭር ልቦለድ በማስተማር በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና ለመመርመር የተዘጋጁ የማስተማሪያ ጽሑፎች የያዘ (ቴክስት) ነው፡፡*

*የትምህርት ክፍለ ጊዚያት ከሚያዚያ*10/8/2008 *እስከ ግንቦት* 30/9/2008 *ለስድስት ሳምንት ከሰዓት በኂላ ፈረቃ ዘወትር ረቡዕና ሐሙስ ከ*8፡30*እስከ*10፡30 *ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ በቀን ለሁለት ሰዓት፤ተሰጥቱዋል፡፡*
*የመማሪያ ቦታ በትምህርት ቤቱ ባለው የመማሪያ ክፍል፤ትምህርቱ የሚሰጠው በአጥኚው፤*

***ትምህርት አንድ፦*** *የትምህርት ርዕስ ‹‹ ክንፋም ሕልሞች፣ክፍል አንድ››በሚለው የአጭር ልቦለድ ክፍል የአንብቦ መረዳት ተግባራትን ማስተማር ወይም ተማሪዎች እንዲሰሩ ማድረግ ፤*

***የትምህርቱ ዓላማ፦*** *ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች በምንባቡ መሰረት ለአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፤የቅድመንባብ፣የንባብጊዜና የድህረ-ንባብ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡*

**የተመደበ ክፍለ ጊዜ፦ ሦስት ክፍለ ጊዜ ለ6ሰዓት**
**ክፍለ ጊዜ አንድ፦**ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች ይሰራሉ፣ለቃላት ፍች ይሰጣሉ፡፡ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ተማሪዎች ምንባቡን መጀመሪያ ድምጽ በማሰማት ያነባሉ፤በማስከተልም በጽሞናንባብ ያነባሉ፡፡

***i. የቅድመ-ንባብ ጥያቄዎችን በቡድን በመወያየት መልሱ፣መልሳችሁን ለክፍሉ ተማሪዎች አንጸባርቁ፡፡***

1. ‹‹ክንፋም ሕልሞች›› የሚለው ርዕስ ስለምን የሚያብራራ ይመስለሃል/ሻል?
2. ምኞትና ሕልም ምን ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል?
3. ለወዳጅ ዘመድ የሚጻፍ ደብዳቤ ምን ምን ይዘቶች ሊኖሩት ይችላል?

***ii. ለሚከተሉት ቃላት ፍቻቸውን ለመስጠት ሞክሩ፤***

1. ጨፌ
2. ዥራፍ
3. ብትህውና
4. ምዝግዝግ
5. አራት ዓይና

**ክንፋም ሕልሞች**
**ክፍል አንድ**

ይድረስ ለወንድሜ ለአንዱአምላክ ዘነበ፡፡ እንዴት አለህ? አክስቴስ ደህና ናት ወይ? ያች ታምረኛ አገር ማርቆስስ እንዴት ናት? አዲሳባ ያለችዉ እህትህ ሰናይትስ እንዴት ናት? እጮኛዋ ተክለሚካኤልስ እንደምን ነዉ? አብዬን ጨምሮ እዚህ ያሉት የቅርብ ሰዎቻችን ደህና ናቸዉ፡፡

ባለፈዉ የሐምሌ አቦ ዝክረ ማርቆስ አክስቴ ዘንድ ደርሽ ተተመለስኩ ወዲህ የድሮው አይደለሁም፡፡ አገሬ ማንኩሳም የጥንቲቱ አልመስለኝ ብላለች፡፡ ጥንት እንደሐር ይለሰልሰኝ የነበረ ኑሮ፣አሁን እንደ አባጨጓሬ ይኮሰኩሰኝ ጀምሩዋል፡፡ ገላ እንዲህ ወረተኛ መሆኑን መች አውቄ? ‹አሁን ሁለት ሰንበትም ጥንት ሆነች?› ብለህ እንዳትለኝ ወድጀ አይደለም፡፡ ተማርቆስ የተመለሰው ገላዬ ነው፡፡ ልቤስ እንደጋኒን ዕጢ እዚያው ማርቆስ ዱብ ብሎ ቀርቱዋል፡፡

በዚህ ሰሞን…የቅኔ ትምህርቴን ሳልፈጥም የኔታ መርሓ ዕድቅን ንዳድ ጣላቸው፡፡ እኩሌታው ተማሪ እየተንጠባጠበ ተከተላቸው፡፡ ሞት ትንኝ እጋለበ ገብቶ ቤቱን ኦና አደረገው፡፡ ቀለሙ ተደፍቶ፣ ብራናው ሻግቶ፣ አጓዛው ተዘንግቶ ቀረ…ይሄን ሲያይ አብዬ ወስዶ ጥጃ ጠባቂነት መደበኝ…ይኸውልህ ንዳድ ታራቆተው ትምህርት ወጥቼ ውሎዬ ተጥጃ ጋር ሆነ፡፡ ለነገሩ ዘንደሮ በምዝግዝግ የሳተኝ ሞት ከርሞ በጨበጣ አይለቀኝም፡፡ ‹ማርቆስን የሚያህል የመድህን ከተማ እያለ ማን በስጋት ይኖራል?› እያልሁ እራሴን እጠይቅ ዠምሪያለሁ፡፡

የቅኔ ትምህርቴን አለመፈጸሜ ልቡናዬን አጉል አደረገው፡፡ ብፈጥምስ ኑሮ መሸጋገሪያ የሚሆን ምክንያት አገኝ ነበር፡፡ ነፍሳቸውን ይማርናና የኔታ ‹‹ይኸ ልዥ በዚህ አያያዙ አራት ዓይና መባሉ የተፈጸመ ትንቢት ነው!›› ማለታቸው እንዲያው በድፍኑ ሳይሆን የልቦናየን ብሩህነት መዝነው ነበር፡፡ ‹‹ያን የመሰለ የተባ ማሰላሰያ ይዘህ ጥጃ ጥጃ ስትሸት ተምትኖር ምንው ወደ ማርቆስ ወጥተህ የረባ ነገር ብትማር›› እያሉ ባለፉ ባገደሙ ቁጥር የሚነካኩኝ ባልጀሮቼ በርክተዋል፡፡

**የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. እስከ አሁን ያነበባችሁትን ጽሁፍ መልዕክት ምንድን ነው? ቡድን በመመስረት ተነጋገሩ ከዚያም ለክፍል ተማሪዎች አንጸባርቁ፡፡
2. ሀብታሙ መሄድ ወደፈለገበት ቦታ ‹‹ማርቆስ›› ለመሄድ ይሳካለት ይመስለሃል/ሻል? ምክንያታችሁን ተናገሩ፣
3. ለቅኔ ትምህርቱ መበተን ምክንያቱ ምንደን ነው?

ተማርቆስ ተመጣሁ ወዲህ የጥጆቸ ጠባይ ሳይቀር ተለውጦ ጠበቀኝ፡፡ በደህነኛ ጨፌ ላይ ተተሰማሩ ዕኩለቀን ግጠው እንቧይ ይመስሉ ነበር፡፡ በዚህ ሰሞን ግን እምብርታቸውን ምን እንደወሰደባቸው እንጃ አሲዳም ሆነውብኛል፡፡ ካፊያ አይፈሩ ሐሩር እንዲያው ሙሉ ቀን ይሄን ዥራፍ የሚመስል ሰርዶ ይመነጥሩና በሰርዶው ላይ ጨፌውን በጨፌው ላይ ቃርሚያውን ይዘግኑና ሲመሽ ወደ ጋጣቸው ለመመለስ ያቅማማሉ፡፡ እንዲያውም አበዛው አትበለኝ እንጅ ሲግጡ እንጅ ሲያመነዥኩ ታየኋቸው ቆየሁ፡፡ ‹ነገሩ እንዴት ነው? በምትሃት አጋሰስነት ተደገመባቸውን?› ማለት ዠምሪ ነበር፡፡

አሁን አብዬ ንዳዱ አልፎለታል፡፡ ታልጋው ሲነሳ ግን ሌላ ሰው ሆኖ ነበር፡፡ ወባይቱ ገላው ሲሰለቻት ለእርጅና አስረክባው ሄደች፡፡ ጠቁሮ ተኝቶ፣ ገርጥቶ ተነሳ፡፡ ወትሮም ቀን ሲያምጽ ተዕድሜ ቀድሞ ኑሮ ያስረጃል፡፡ ማታ ማታ ተመስክ መልስ እራታችንን ባንድ በልትን

ወደየብትሁናችን እንበታተናለን፣ የምንጋራው ወግ ብዙም የለንም፡፡ እሱ ባለጸለት እኔ በባለትካዜ ሆንንና ተለያየን፡፡ ያንተን የአክስቴንና የሰናይትንም ስም እያነሳ ያሳስባል፣ይለማመናል፡፡ ተሱ ያለት ያመለጠው ስም ለኔ ምኞት ማሳሰቢያ ይሆናል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በህልሜ እንደ አቡነ ዘራአብሩክ ክንፍ ሳበቅል አያለሁ፡፡ ብንን ብየ ጎኔን ስዳብስ ግን በጄ የምነካው ያሞጠሞጠ ጎድን እንጅ ልስልስ ላባ አይደለም፡፡

ተትናንት ወዲያ ታብዬ ጋር አብረን እራት እየበላን ሳለ የአሳቤን ጫፍ ጫፍ እንኳ ልንገረው ብዬ ከንፈሬን ስወጥር ሳረግብ ነበር፡፡ እንደ ልማዱ ማዕዱ ላይ አጎንብሶ ድንቹን ሲልጥ ምን ብዬ እንደምዠምር ተራሴ ጋር እሟገት ዠመር፡፡ እሱም ቀና ብሎ አትበላም ወይ ቢለኝ ‹‹ተማርቆስ ተመጣሁ ወዲህ ሆድ ቀንሻለሁ››አልሁት፣አልሳቀልኝም፡፡ ወትሮም እንዲህ ነው፡፡ንዴት እንጅ ሧልት አያስቀውም፡፡ በጀመርኩት ወሬ ይቀጥልልኛል፤ ብዬ ነበር፣ ጭጭ አለ፡፡ አንድ ሁለቴ ከጎረስን በኋላ ‹‹በለንዠሮችህ ደህና ናቸው?›› አለኝ ‹ተማርቆስ ተመጣሁ ወዲህ አንድ ሁለቴ አግኝቻቸዋለሁ፡፡ ደህና ናቸው› አልሁት፡፡ በኔ ቤት ‹እስቲ ስለማርቆስ አውጋኝ ብሎ የሚቀጥል መስሎኝ ነው፡፡ እሱ ግን ዋናው ደህና መሆናቸው ነው ብሎ ወደ ድንቹ አጎነበሰ፡፡

አኩርፌ ተማዱ ተነሳሁ፣ ደፍሬ ሳልጠይቀዉ ቀረሁ፡፡ ግን ብጠይቀዉ ምን ይላል? አርፈህ ባገርህ ተቀመጥ ይለኝ ይሆናል፡፡ ግን ሀገሬ ማንኩሳ ብቻ ናትን? ግድየለም ይዘገዷል እንጅ አብዬን ማሳመን አያቅተኝም፡፡ እሱ ብዙም አያሳስብም፡፡ ብመጣ ተሸሽዬ አሻሽለዋለሁ፡፡ ብማር ተጉንዳን እተጋለሁ፡፡ ባክህ እንደምንም ብለህ ገላግለኝ አንተዘንድ ሆኘ ልማር፡፡ ደፍተሬን እስክርብቶዬን ብለህ ነው፡፡ እሱንም እየተማርሁ የምሰራ ከሆነ አግዘሃለሁ፡፡ እምቢ የምትለኝ ከሆነ ምንይደረጋል እኔ ደግሞ አይኔን ጨፍኘ እሞክራለሁ፡፡

ወንድምህ ሀብታሙ፣

ክንፋም ሕልሞች ከበዕውቀቱ ሥዩም ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ (2004፣69-76)

**ክፍለ ጊዜ ሁለት፦** ምንባቡን ደግመው በጽሞና ንባብ ካነበቡ በኋላ ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት ምክንያት በመስጠት ያብራራሉ፡፡ የምርጫ ጥያቄዎችን፣ይሰራሉ፡፡ በዚህ ክፍል ስልምንባቡ መልዕክት ጥልቅ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያግዛቸዋል፡፡

## ፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት መልሱ፡፡ ለመልሳችሁም ምክንያት ስጡ፡፡

1. ሐብታሙ የቅኔ ትምህርት በመማር ላይ ነው፡፡
2. ሐብታሙ የማንኩሳ ኑሮ ይኮሰኩሰው የጀመረው የሐምሌ አቦ ዝክረ ማርቆስ አክስቱ ዘንድ ደርሶ ከተመለሰ በኋላ ነው፡፡
3. ደብዳቤ ጻሐፊው አንዱአምላክን በደብዳቤው የሚጎተጉተው ለንግድ መነሻ የሚሆን ወረት እንዲሰጠው ነው፡፡
4. ሐብታሙ ጥጃ ጠባቂነት የተመደበው ዘመናዊ ትምህርት አልገባው ስላለ ነው፡፡
5. ሐብታሙ የሰላ አዕመሮ እንዳለው የቅኔ መምህሩም ሆነ ባልዠሮቹ ገልጸውለታል፡፡

## ፪. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ሐብታሙ ደብዳቤ የጻፈው ለማን?
   ሀ. ለአንዱዓምላክ ዘነበ ሐ. ለተክለ ሚካኤል
   ለ. ለሰናይት መ. ለአክስቱ
2. ሐብታሙ የቅኔ ትምህርቱን ያላጠናቀቀው ለምንድን ነው?

ሀ. ንዳድ ባስከተለው ሞትና ሕመም የቅኔ ትምህርት ቤቱ በመዘጋቱ፣

ለ. ዘመናዊ ትምህርት ለመማር በራሱ ፍቃድ የቅኔ ትምህርቱን ስላቋረጠ፣

ሐ. የቅኔ ትምህርቱ ስላልገባው በራሱ ፍቃድ የቅኔ ትምህርቱን ስላቋረጠ፣

መ. አባቱ ጥጃ ጠባቂነት ስለመደቡት፣

3. ‹‹ዘንድሮ በምዝግዝግ የሳተኝ ሞት ከርሞ በጨበጣ አይለቀኝም›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. ለሞት የሚያደርስ ህመም ታሞ መዳኑን ይገልጻል፣

ለ. የንዳድ ወይም የወባ ህመም እሱን እንደማያጠቃው ይገልጻል፣

ሐ. አሁን ከደረሰበት ችግር የከፋ፣ሌል ችግር እንደመማይደርስበት ይገልጻል፣

መ. በአካባቢው ያሉ ብዙሰዎች በንዳድ ስለሞቱ፣ከፍተኛ ስጋት ስለፈጠረበት፣

4. በምንባቡ መሰረት ‹‹...እኩለ ቀን ግጠው እንቧይ ይመስሉ ነበር፡፡›› ሲል ምን መልዕክት ያዘለ ነው?

ሀ. መጥገብን ለ. መራብን ሐ. መወፈርን መ. መክሳትን

5. በምንባቡ መሰረት ‹‹አጋሰስነት››ምን ማለት ነው?

ሀ. የሰው ሐብት የሚፈልግ፣ ሐ. ስግብግብ ነጋዴ፣

ለ. በልቶ የማይጠግብ፣ መ. ብዙ ክብደት የሚሸከም፣

6. የሐብታሙ አባት በጸለት የሚያስቡትና የሚያሳስቡለት ማንን ነው?

ሀ. አንዱዓምላክን ለ. ሰናይትን ሐ. ተክለሚካኤልን መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው፡፡

7. ሀብታሙ፣አንዱዓምላክ ዘንድ ማርቆስ ሄዶ ለመማር ያለውን ፍላጎት ለአባቱ ለማውጋት የፈለገበት ሁኔታ ምን ነበር?

ሀ. ከአባቱ ጋር አራት እየበሉ እያለ፣ ሐ. ከአባቱ ጋር ጥጆች እያገዱ ሳለ፣

ለ. ከአባቱ ጋር ማርቆስ ሄደው ሳለ፣ መ. ሐብታሙ አክስቱ ዘንድ ደርሶ ሳይመለስ፣

8. ‹‹ወትሮም ቀን ሲያምጽ ተዕድሜ ቀድሞ ኑሮ ያስረጃል›› ይህ አባባል ምን ሃሳብ ይዙዋል?

ሀ. የኑሮ ጉስቁልና ያለእድሜ ያስረጃል፡፡ ሐ. ያረጁ ሰዎችን በሽታ ያጠቃቸዋል፡፡

ለ. የተደላደለ ኑሮ ያለው ፈጽሞ አያረጅም፡፡ መ. ቀን ሲጠም ለስደት ይዳርጋል፡፡

**ክፍለ ጊዜ ሦስት፦** የማዛመድ ጥያቄዎችንና ክፍት ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡ በዚህ ክፍል ያሉ ተግባራት ስልምንባቡ መልዕክት ጥልቅ ግንዛቤ እንዲያገኙ፣እንዲወያዩ፣የተለያዩ ጽንሰ ሃሳቦችን ፣አገላለጾችን እንዲረዱ ያግዛቸዋል፡፡ ገጸባህሪያትን እንዲረዱና የራሳቸውን አመለካከት እንዲያንጸባርቁ ያስችላል፡፡

**አዛምዱ፡፡ ፫. በምንባቡ መሠረት ለሚከተሉት በ‹‹ሀ›› ክፍል ለቀረቡ ሐረጎች ወይም ጽንሰ ሀሳቦች በ‹‹ለ›› ክፍል ከቀረቡት መገለጫዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡**

| **‹ሀ›** | **‹ለ›** |
|---|---|
| 1. ‹ሁለት ሰንበትም ጥንት ሆነች› | ሀ. የሁለት ቀን ቆይታ ሩቅ ግዜ ሊባል ነው? |

2. ንዳድ የፈታው ትምህርት፣
3. አራት ዓይና፣
4. እምቧይ መምሰል፣
5. ከንፈርን መወጠርና ማርገብ፣
6. ጉንዳን፣
7. እምብርት አለመኖር፣

ለ. ብሩህ ልቦና ያለው፣
ሐ. የትጋት ተምሳሌት፣
መ. በልቶ አለመጥገብ፣
ሠ. የፀሐይ ሐሩር የፈታው ትምህርት፣
ረ. የጥጋብ ተምሳሌት፣
ሰ. በሽታ ያራቆተው ትምህርት፣
ሸ. የሁለት ሳምንት ቆይታ የሩቅ ጊዜ ሊባል ነው?
ቀ. ለመናገር ዝግጁ መሆን፣

**፫. በሚከተሉት ከምንንባቡ ለወጡ አባባሎች ወይም ሀሳቦች ላይ በቡድን በመወያየት የሚያስተላልፉትን መልዕክት ለሌሎች አስረዱ።**

1. ሃብታሙ ወንድሙን ‹‹እምቢ የምትለኝ ከሆነ ምን ይደረጋል እኔ ደግሞ አይኔን ጨፍኜ እሞክረዋለሁ›› ሲል ምን ለማድረግ አስቦነው?
2. ሐብታሙ፣ ‹‹አብዬ ከአልጋው ሲነሳ ሌላ ሰው ሆኖ ነበር።››ሲል በአገባቡ ምን መልዕክት ያስተላልፋል? በጽሑፍ አብራሩ።

**ትምህርት ሁለት፦** የትምህርት ርዕስ ‹‹ **ክንፋም ሕልሞች፣ክፍል ሁለት**››በሚለው የአጭር ልቦለድ ክፍል የአንብቦ መረዳት ተግባራትን ማስተማር ወይም ተማሪዎች እንዲሰሩ ማድረግ ፤

**የትምህርቱ ዓላማ፦** ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች በምንባቡ መሰረት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ይሠራሉ፤የቅድመንባብ፣የንባብ ጊዜና ድህረንባብ ጥያቄዎችን ይሰራሉ።

**የተመደበ ክፍለ ጊዜ፦ ሁለት ክፍለ ጊዜ ለ4ሰዓት**

**ክፍለ ጊዜ አንድ፦** ቅድመንባብ ጥያቄዎች ይሰራሉ፣ለቃላት ፍች ይሰጣሉ። የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ይሰራሉ። በዚህን ጊዜ ተማሪዎች ምንባቡን መጀመሪያ ድምጽ በማሰማት ያነባሉ፤በማስከተልም በጽሞና ያነባሉ።

***መመሪያ አንድ፦*** የቅድመ-ንባብ ጥያቄዎችን በቡድን በመወያየት መልሱ፣መልሳችሁን ለክፍሉ ተማሪዎች አንጸባርቁ። የግንዛቤ ጥያቄዎችን ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት ምክንያት በመስጠት አብራሩ።

**¡. ቅድመ-ንባብ ጥያቂዎች**

1. ‹‹ክንፋም ህልሞች›› ክፍል ሁለት ስለምን የሚያወሳ ይመስለሃል/?
2. በትምህርት ቤታችሁ የሚኒሚዲያ ክበብ አለ? ምን ምን ተግባራትን ያከናውናል?
3. አንድ ሰው ያለፍላጎቱ በአንድ ሙያ ላይ ቢሰማራ ምን ችግር ሊገጥመው ይችላል?

**¡¡. ለሚከተሉት ቃላት ፍቻቸውን ለመስጠት ሞክሩ፤ምንባቡን ካነበባችሁ በኃላ ደግሞ የሰጣችሁትን ፍች ከአውዳዊ ፍቻቸው ጋር አገናዝቡ፤**

1. ሽፈተ
2. መነረት
3. ስኬት
4. ተሰጥኦ
5. መዲና

## ክንፋም ሕልሞች
## ክፍል ሁለት

አንዱዓምላክ ለሰናይት፡-

ውድ እህቴ እንደምን አለሽ፣ኑሮ ከተባለ ይኸው እየኖርሁ ነው፡፡ ደህና ነኝ፡፡ እነማየም በጎ ናቸው፡፡ ማንኩሳ ያሉት ዘመዶቻችን ጭምር፡፡ ሐብታሙ በቅርቡ ደብዳቤ ጽፎልኝ ነበር፡፡ ደብረማርቆስ መጥቶ መኖር ይፈልጋል፡፡ የራሴ ዓላማ ስላለኝ ፊት አልሰጠሁትም፡፡ ስራዬ ብዙ አልመጠነኝም፡፡ መቼም አዲስ አበባ ካልመጣሁ ሰው እንደማልሆን የታወቀ ነው፡፡ ማስተማር ጀምሬ እንደነበር ሳትሰሚ የቀረሽ አይመስለኝም፡፡ ከደብረማርቆስ ፈንጠር ብላ በምትገኝ ገጠር ቀመስ መንደር ውስጥ ያንደኛ ክፍል ተማሪዎችን አማርኛ አስተምር ነበር፡፡ አስተማሪነት የቀጠሩኝ ትምህርት ቤቱ ተሰርቶ ሳይጠናቀቅ ነው፡፡ እኔ ፊደል እያስቆጠርኩ ተማሪዎች ጣራውን በመደሻ የሚነርተውን አናጢ ሽቅብ ይመለከታሉ፡፡ አናጺውም ከጉዳይ ሳይፅፈኝ የተኮለኮሉትን ሕጻናት ቁልቁል እየተመለከተ... ‹‹እስቲ ተናንተ ውስጥ ማን ጎበዝ ነው ሚስማር የሚያቀብለኝ?›› ሲል ይጮሃል፡፡ አያድርስ ነው እንጅ አንድቀን መጋዝ ከእጁ ቢያፈተልክ፣ወይ እራሱ ሰውየው ቁልቁል ቢመጣ ምን ይውጠኛል? ብዬ መስጋት ጀመርኩ፡፡

ማስተማር ስጀምር ትልቁ ችግሪ የምግብ ነበር፡፡ በእግር በፈረስ አፈላልጌ አንድ ምግብ ቤት አገኘሁ፡፡ ገብቼ ምን ምን አላችሁ? ብላቸው ‹ሽሮና የቅቤ ሽሮ› አሉኝ፡፡ ሁለተኛውን አዘዝሁ፡፡ በማግስቱ ጠዋት ቁርስ ፈልጌ ብመለስ አስተናጋጇ ደጁን ትጠርጋለች፡፡ አለፊያት ልገባ ስል ምንሆነህ ነው? አለችኝ፡፡ ቁርስ የለምንዴ? ብላት፣ ነነዊ መግባቱዋን ረሳሃው መሰል አለችና ጀርበዋን ሰጠችኝ፡፡ ከዚያ በኂላ ነው እንግዲህ ሁሉንም ጣጥየው ወደ ማርቆስ የተመለስኩ፡፡ ከመምጣቴ እመዬ የፀጉር ማስተካከያ ከፈተችልኝ፡፡ በቴሌቪዥን ስለአዲስ አበባ የማየው ነገር ልቤን እያሸፈተው ነው፡፡

#### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስከ አሁን ያነበባችሁትን መልዕክት ተናገሩ፣
2. አንዱዓምላክ መምህርነት ሙያን ትቶ በፀጉር አስተካካይነት እየሰራ ቢሆንም በስራው ደስተኛ አይመስልም፡፡ ለምን? እሱ የሚፈልገው ሙያ ምን ይመስለሃል/ሻል

አዲስ አበባ የስኬት አገር ናት፡፡ የዕድል መ፣ንደር ናት፡፡ እኔ ደግሞ ከልጅንት ጀምሮ የጋዜጠኝነት ተሰጥኦ አለኝ፡፡ ትዝ ይልሽ እንደሆነ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እዳለሁ ሚኒሚዲያውን የምቆጣጠረው እኔ ነበርኩ፡፡ ያኔ እንደነጎድጓድ በሚያስገመግመው ድምጼ ‹ተማሪዎች ማትሪክን ድባቅ ለመምታት ቃል ገቡ› ብየ ስናገር አማርኛ መምህራችን ጋሽ ጣሰው ‹ ይኸ ልጅ አለምነህ ዋሴን ያልተካ እንደሁ ታዘቡኝ› እያለ ይተነብይ ነበር፡፡ የታሪክ መምህራችንም ምሰጣዬን ባስተዋለ ቁጥር ‹‹ እንደምንም ብለህ አዲስ አበባ ግባ ያንተ ቦታ ይህ አይደለም›› ይሉኝ ነበር፡፡ አሁን

አሁን ሳስበው በሚናገሩት ውስጥ እውነት ውስጥ እውነት ማግኘቴ አልቀረም፡፡ አንች ጋዜጠኛ ስለሆንሽ ከትላልቅ ሰዎች ጋር ልታስተዋውቂኝ ትችያለሽ፡፡ አንድጊዜ መንገዱ ከተከፈተልኝ ከልካይ የለኝም፡፡ አዲስ አበባ የትጋት አገር መሆኑዋን ስለማውቅ ጠንክሬ

ሌትና ቀን እደክማለሁ። ክሌጆች ውስጥ ብታስገቢኝ ባጭር ጊዜ ውስጥ የማይታመን ውጤት አስመዘግባለሁ። በትርፍ ጊዚዬ ተቀጥሬ እሰራለሁ።

ሠንዬ... አዲስ አበባ ሰው የምታደርገኝ የእጣ ፈንታዬ መዲና ናት። እዚህ ሆኘ ከዘመኑ ቴክኖሎጅ ጋር መፎካከር አልችልም። ተረስቼ መቅረቴ ነው። የት ይደርሳል የተባለው ተረት ሊተረትብኝ ነው። በነገራችን ላይ ሰሞኑን ከዚህ ጋር የተያያዘ ሕልም አይቼ ነበር።

እልም ባለ ምድረበዳ ውስጥ የምራመድ ይመስለኛል፤የውሃና የዕፅዋት ዘር አይታይም። በእግሬ እየተጓዝሁ ነው። ላብ ከገላዬ ላይ ይዘንባል። ጉልበቴ ይደክማል። ወዲያው ግን ከፊት ለፊቴ ትልቅ የግንብ አጥር ይታየኛል። ወደ ግንቡ ተጠግቸ በሩን አንኳኳለሁ። አንድ አንችን የምትመስል ሴት ትከፍትልኛለች፤ለዕልት ነች። ‹‹ልዕልት ሆይ ይኸ ግንብ ምን ይባላል?›› ብዬ እጠይቃታለሁ። ‹‹የአበባ ግንብ ይባላል›› ብላ ስትለኝ ብንን አልሁ። አይገርምም? እንግዲህ ወደዝህ የአበባ ግንብ የምትጠሪኝ አንቺ ነሽ። ምልስሽን በፍጥነት ላኪልኝ።

አክባሪ ወንወድምሽ
አንዱዓምላክ ዘነበ

ክንፋም ሕልሞች ከበዕውቀቱ ሥዩም ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ (2004፣69-79)

**፩. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቂዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ። ለመልሳችሁ ምክንያት ስጡ።**

1. አንዱዓምላክ፣ሐብታሙ ላቀረበለት ማርቆስ መጥቶ የመማር ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ ሰጦታል።
2. አንዱዓምላክ በመምህርነት ሙያ የተቀጠረው፣ትምህርት ቤቱ ተሰርቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ነው።
3. የአማርኛ መምህሩ ብቻ ነበር፣ ለአንዱዓምላክ የጋዜጠንነት ተሰጥኦ እንዳለው የመሰከረለት።
4. ስለአዲስ አበባ በቴሌቪዥን የሚሰማው ነገር፣አንዱዓምላክን ልቡ ወደ አዲስ አበባ እንዲሸፍት አድርጎታል።
5. ሠናይት ወደ አዲስ አበባ ባትወስደውም፣ አንዱዓምላክ በራሱ ጊዜ ለመሄድ ወስኑአል።

**ክፍለ ጊዜ ሁለት፡** ምንባቡን ደግመው በጽሞና ንባብ ካነበቡ በኋላ የምርጫ ጥያቄዎችን፣ይሰራሉ። በዚህ ክፍል ስልምንባቡ መልዕክት ጥልቅ ግንዛቤ እንዲያ
ገኙ
ያግዛቸዋል። ክፍት ጥያቄዎችን ይሰራሉ። እንዲወያዩ፣እንዲከራከሩ፣ ያግዛቸዋል። ገጸባህሪያትን እንዲረዱና የራሳቸውን አመለካከት እንዲያንጸባርቁ ያስችላል።

**፪. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ለጥያቂዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

1. ‹‹ለራሴ ዓላማ ስላለኝ ለሐብታሙ ፊት አልሰጠሁትም...›› ሲል አንዱዓምላክ ዓላማው ምንድን ነው?
   ሀ. አሜሪካ ሄዶ መማር፣ ሐ. ፀጉር ቤት ከፍቶ የመስራት፣

ለ. አዲስ አበባ ሄዶ የጋዜጠኝነት ሙያ መማር። መ. አዲስ አበባ ሄዶ ምህንድስና መማር

2. በጸሀፊው አመለካከት አዲስ አበባ ምን ዓይነት ከተማ ናት?

ሀ. ከዘመኑ ቴክኖለጅ ጋር የምታስተዋውቅ፣

ለ. የትምህርት ዕድል በስፋት የሚገኝባት፡

ሐ. የትጋትና የስኬት ሀገር ናት፣

መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

3. የጋዜጠኝነት ተሰጦኦ እንዳለው፣አንዱዓምላክን ከመነሻው የተነበየለት ማን ነው?

ሀ. የአማርኛ መምህሩ ሐ. የሒሳብ መምህሩ

ለ. የታሪክ መምህሩ መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው።

4. ማስተማር እንደጀመረ፣አንዱዓምላክን የገጠሙት ችግሮች ውስጥ የሚካተተው የትኛው ነው?

ሀ. ትምህርት ቤቱ ለማስተማር ስጋት መሆኑ፣

ለ. በገጠር ቀመስ ቀበሌው ውስጥ አማራጭ ምግብ ቤቶች አለመኖራቸው።

ሐ. በአካባቢው ለመምህራን የሚሆን መጠለያ አለመኖሩ።

መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው።

5. እንደጸሀፊው እምነት ተሰጥውን ለመጠቀም የሚያስችለው ቦታ የቱ ነው?

ሀ. መርቆስ ለ. ከማርቆስ አካባቢ ያለው የገጠር ቀበሌ ሐ. አዲስ አበባ መ. አሜሪካ

6. አዲስ አበባ ያለቸው ሰናይት የተሰማራችበት ሙያ ምንድን ነው?

ሀ. መምህርነት ለ. መሀንዲስነት ሐ. ፀጉር አስተካካይነት መ. ጋዜጠኝነት

7. አንዱዓምላክ ‹‹ ይሄ ለጅ አለምነህ ዋሴን ይተካል ›› የተባለበት መሰረት ምንድን ነው?

ሀ. በተክለ ቁመናው፣ ሐ. በተመራማሪነቱ

ለ. በፀሐፊነቱ፣ መ. ሲያነብ እንደነጎድጓድ በሚስገመገመው ድምጹ፣

8. ሐብታሙ በራሱ አረዳድ በሕልሙ ያየው የአበባ ግንብ በምን ይመሰላል?

ሀ. በአዲስ አበባ ሐ. በአሜሪካ

ለ. በማርቆስ መ. በማንኩሳ

**፫. በሚከተሉት ጽንሰ ሃሳቦች ዙሪያ በቡድን ተከራከሩ፣**

1. የጋዜጠኝነት ሙያ ተሰጦን ለመጠቀምና ለማዳበር አዲስ አበባ መሄድ ብቸኛ አማራጭ ነው ወይስ አደለም።
2. አንዱአምላክ የመምህርነት ሙያን በጣም ይወዳል ወይስ አይወድም።

**ትምህርት ሦስት፦** የትምህርት ርዕስ ‹‹**ክንፋም ሕልሞች፣ክፍል ሦስት**››በሚለው የአጭር ልቦለድ ክፍል የአንብቦ መረዳት ተግባራትን ማስተማር ወይም ተማሪዎች እንዲሰሩ ማድረግ ፤

**የትምህርቱ ዓላማ፦** ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች በምንባቡ መሰረት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን የመልሳሉ፤የቅድመንባብ፣የንባብ ጊዜና ድህረንባብ ጥያቄዎችን ይሰራሉ።

**የተመደበ ክፍለ ጊዜ፦ ሁለት ክፍለ ጊዜ ለ4ሰዓት**

**ክፍለ ጊዜ አንድ፦**ቅድመንባብ ጥያቄዎች ይሰራሉ፣ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ይሰራሉ። በዚህን ጊዜ ተማሪዎች ምንባቡን መጀመሪያ ድምጽ በማሰማት ያነባሉ፤በማስከተልም በጽሞና ያነባሉ።

*መመሪያ አንድ፦* የቅድመ-ንባብ ጥያቄዎችን በቡድን በመወያየት መልሱ፣መልሳችሁን ለክፍሉ ተማሪዎች አንጸባርቁ። የግንዛቤ ጥያቄዎችን ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት ምክንያት በመስጠት አብራሩ።

### ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች

1. ለመለወጥም ሆነ ሃብት ለማፍራት በሀገር ውስጥ ከመኖርና በውጭ ሀገር ከመኖር የቱ ይመረጣል?
2. ዲቪ መሙላት ማለት ምን ማለት ነው?

### ክንፋም ሕልሞች
### ክፍል ሦስት

ሠናይት ለተክለሚካኤል

ከዚች ሀገር ልትመነጭቀኝ ደፋ ቀና እያልህ እንደሆነ ሳስብ ልቤ በደስታ ይሞላል። ከአዲስ አበባ ለመውጣት ስጥር ብዙ ዕድሚየን ገፍቻለሁ። እንደጥረቴ ቢሆን ኑሮ ቢያንስ ከአምስት አመት በፊት ወጥቼ የሚሲፒፒን ውሃ መጠጣት ነበረብኝ።

አዲስ አበባ የመጨራሻዋ ምስኪን አገር ሆናለሃለች። ኑዋሪዎቿ፣ አዲስ አበባ ውስጥ ሰው ከመሆን ዋሽንግተን ውስጥ ጥንቸል ሆኖ መፈጠር ይሻላል ማለት ጀምረዋል። ለምን መሰለህ? የመቶ ሃያ ዜና ጥንቸሎች በብዙሺህ ዶላር ሲሰረግላቸው ያሳያል። የኛ ሰዎች ግን በሳንቲም እጥረት ትዳራቸው ይፈርሳል።

የአዲስ አበቤ ግብ መሄድ ብቻ ሆኗል። የአዲስ አበባ ሰው እንደያቆብ ድንጋይ ተንተርሶ እያደረ ከቦሌ እስከ ዋሽንግተን የተዘረጋ መሰላል በህልሙ ያያል። ዲቪ አለመሙላት እንደነውር እየተቆጠረ ነው። አዲስ አበባ የወላድ መካን ሆናለች። ልጆቿ ክንፍ አብቅለው ይወለዳሉ። ኑሯቸው ማኮብኮብና መብረር ሆኑዋል። ምን መአድረግ ይቻላል? እኔ እራሴ ክንፍ እያቆጠቆጥኩ ነው። የዚህ ትውልድ አባል መሆኔን አትዘንጋ። ከገርጂ ፒያሳ ከፒያሳ ቦሌ ሰፈር ስቀያይር ኑሪያለሁ፤በስራዬ አልረካም። በኑሮየ አልደሰትም። መሻሻል እፈልጋለሁ።ሰው መሆን እፈልጋለሁ። ሰው የምታደርገኝ አገር ደግሞ አሜሪካ ናት።

#### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ሠናይት ሕልሟ ዕውን የሚሆን ይመስልሃል?/ይመስልሻል?
2. እስከ አሁን ካነበባችሁት ስለባለታሪኳ ምን ተረዳችሁ?

በዚህ አመት እነደምንም ብለህ ብትጨርስልኝ በሙሉ ልብህ እንደምትወደኝ አረጋግጣለሁ። ጆሮዬን አቅንቼ የምጠባበቀው የአንተን ጥሪ ነው። አሁን እዚህ አዲሳ አበባ ውስጥ በአካል እንጅ በመንፈስ የለሁም። ፊልሞችን የምመለከተው እንደድሮው አይደለም። ሁኔታቸውን እየሸመደድኩ ነው። ሳቅህብኝ እንዴ?

አገር ቤት ያሉት ደህና ናቸው። አንደንዶቹ እዚህ አዲስ አበባ ለመምጣት ይጓጓሉ። ሁሉ ነገር አልጋ ባልጋ ይመስላቸዋል። እኔ እንደሁ እንኳን ሌላ ሰው ልጨምር እራሴንም አውሎ ማሳደር እያቃተኝ ነው። አሁን ብረሪ ብረሪ እያለኝ ነው። በርሬ የት አርፋለሁ? አንተ ታውቃለህ። ጓደኛህን ታመነን ሰላም በልልኝ።

(ለማስተማር በሚያመች መልኩ መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎበት የተወሰደ፣ክንፋም ሕልሞች 69-84)

**፩. ምንባቡን መሰረት በማደረግ ሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ።**

1. በአሁኑ ዘመን ዲቪ አለመሙላት እንደነውር እየተቆጠረ ነው።
2. በሀገራችን በገንዘብ እጥረት ትዳር ሊፈርስ ይችላል።
3. ሰናይት በሀገሯ ሰርታ ትልቅ ደረጃ እንደምትደርስ ጽኑ እምነት አላት።
4. ሰናይት ከሀገር ለመውጣት ከዚህ በፊት ብዙ ጥረት አላደረገችም ።

**ክፍለ ጊዜ ሁለት፦** ምንባቡን ደግመው በጽሞና ንባብ ካነበቡ በኋላ የምርጫ፣የማዛመድ ጥያቄዎችን፣ይሰራሉ። ስልምንባቡ መልዕክት ጥልቅ ግንዛቤ እንዲያገኙ፣ ክፍት ጥያቄዎችን ይሰራሉ። እንዲወያዩ፣እንዲከራከሩ፣ ያግዛቸዋል። ገጸባህሪያትን እንዲረዱና የራሳቸውን አመለካከት እንዲያንጸባርቁ ያስችላል።

**፪. በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቂዎች ትክክለኛ መልስ ምረጡ።**

1. ሠናይት ወደ አሜሪካ ለመሄድ የፈለገችው ለምንድን ነው?
   ሀ. ሥራ አጥ ስለሆነች፣ ሐ. በሥራዋና በኑሮዋ ስለማትረካ፣
   ለ. ከሥራ ስለተቀነሰች፣ መ. እጮኛዋ አሜሪካ እንድትመጣ ስለሚጎተጉታት፣
2. ደብዳቤ ጸሐፊዋ ‹‹የዚህ ትውልድ አባል መሆኔን አትዘንጋ ›› ስትል ምን ማለቱዋ ነው?
   ሀ. ትውለዱ፣በሀገር ውስጥ ሰርቶ መለወጥን የሚያምን መሆኑን፣
   ለ. ትውልዱ፣ሀገሩን ለማልማት ቁርጠኛ መሆኑን፣
   ሐ. ትውልዱ፣ የውጭ ሀገር ኑሮ ናፋቂ መሆኑን፣
   መ. ትውለዱ፣ በመጠጥ እና በጫት ሱስ የተጠመደ መሆኑን፣
3. ምንባቡን አስመልክቶ ትክክል የሆነዉ የቱ ነው?
   ሀ. ሠናይት ከሷዘንድ ሊመጣ ያሰበውን አንዱዓምላክን ለመቀበል እየተዘጋጀች ነው።
   ለ. ተክለሚካኤል ወደ ሀገሩ እንዲገባ ሰናይት ዕለት በዕለት እየጎተጎተችው ነው።
   ሐ. ሠናይት ባለችበት ስራዋን ተረጋግታ እየሰራች ትገኛለች።
   መ. ሠናይት አዲስ አበባ እየኖረች ቢሆንም ልቦነዋ ግን አሜሪካ ነው።
4. ‹‹አዲስ አበባ የወላድ መካን ሆናለች››የሚለው ምንን ይገልጻል?
   ሀ. ሕዝቦቹዋ በንሮ ውድነት መጎሳቆላቸውን፣
   ለ. ሕዝቦቹዋ በበሽታ መሞታቸውን፣
   ሐ. ሕዝቦቹዋ ወደ ወጭ ሀገር እየጎረፉ መሆናቸውን፣
   መ. ሕዝቦቹዋ አለመማራቸውን፣
5. የአንዱዓምላክ አዲስ አበባ የመምጣት ሕልም በሰናይት በኩል ተቀባይነት ያላገኘበት ምክንያት ምንድን ነው?
   ሀ. ሰናይት አሜሪካ የመሄድ ዓላማ ሰላላት፣
   ለ. ሰናይት በኑሮዋ ራሷን ማሳደር ያቃታት መሆኑ፣
   ሐ ሰናይት አንዱዓምላክን ከልብ ስለማትወደው፣
   መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው።
6. ሠናይት በአዲስ አበባ ውስጥ ከኖረችባቸው ሰፈሮች ውስጥ የሚካተተው የቱ ነው?
   ሀ. ፒያሳ ለ. ገርጅ ሐ. ቦሌ መ. ሁሉም

፫. በምንባቡ *መሠረት* ለሚከተሉት በ‹‹ሀ›› ክፍል ለቀረቡ ሐረጎች ወይም ጽንሰ ሀሳቦች በ‹‹ለ›› ክፍል ከቀረቡት *መገለጫዎቻቸው* ጋር አዛምዱ፡፡

| ‹ሀ› | ‹ለ› |
|---|---|
| 1. አልጋ ባልጋ | ሀ. አሜሪካ መግባት |
| 2. ጆሮየን አንቅቼ እጠብቃለሁ | ለ. ጥሜን አረካለሁ |
| 3. የሚሲሲፒን ውሃ መጠጣት | ሐ. በሀሳብ መንጎድ |
| 4. በሙሉ ልብ መውደድ | መ. የአሜሪካ የመውጣት ሂደትን ማስጨረስ |
| 5. በአካል እንጅ በመንፈስ አለመኖር | ሠ. በጉጉት እጠብቃለሁ |
| 6. ሰው የምታደርገኝ አገር አሜሪካ ናት | ረ. የተደላደለ ኑሮ |
| | ሰ. የተደላደለ ኑሮና የብልጽግና ሕይወት የሚኖርባት ሀገር |
| | ሸ. የማያውቁት አገር አይናፍቅም |

**፬. ለሚከተሉት ጽንሰሃሳቦች ማብራሪያ ስጡ፡፡**

1. አሜሪካ በሜሄድ ብቻ የሰዎች ችግር ተነቅሎ የሚወድቅ ይመስልሃል/ሻል? ለምን? ተወያዩበት፣
2. ሠናይት በአዲስ አበባ ኑሮዋ የገንዘብ ችግር ወይም እጥረት ያለባት ይመስልሃል/ሻል? ምክንያት በመስጠት አብራሩ፣
3. ሠናይት አሜሪካ ስትሄድ ምን እንደምትሰራና በምን ሙያ እንደምትሰማራ አስቀድማ ወስናለች ወይስ አልወሰነችም አብራሩ፣

**ትምህርት አራት፦** የትምህርት ርዕስ ‹‹**ክንፋም ሕልሞች፣ክፍል አራት**››በሚለው የአጭር ልቦለድ ክፍል የአንብቦ መረዳት ተግባራትን ማስተማር ወይም ተማሪዎች እንዲሰሩ ማድረግ ፤

**የትምህርቱ ዓላማ፦** ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች በምንባቡ መሰረት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን የሠራሉ፤የቅድመንባብ፣የንባብ ጊዜና ድህረንባብ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡

**የተመደበ ክፍለ ጊዜ፦ ሁለት ክፍለ ጊዜ ለ4ሰዓት**

**ክፍለ ጊዜ አንድ፦**ቅድመንባብ ጥያቄዎች ይሰራሉ፣ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ተማሪዎች ምንባቡን መጀመሪያ ድምጽ በማሰማት ያነባሉ፤በማስከተልም በጽሞና ያነባሉ፡፡

***መመሪያ አንድ፦*** የቅድመ-ንባብ ጥያቄዎችን በቡድን በመወያየት መልሱ፣መልሳችሁን ለክፍሉ ተማሪዎች አንጸባርቁ፡፡ የግንዛቤ ጥያቄዎችን ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት ምክንያት በመስጠት አብራሩ፡፡

**ቅድመ-ንባብ ጥያቂዎች**

1. በባእድ ሐገር የሚኖር ሰው ምንምን ችግሮች ሊገጥሙት ይችላሉ?
2. ከሐገራችን ወደ ውጭ ሐገር የመሄድ ፍላጎት እንዳለ ሁሉ ወደ ሀገር ውስጥ የመመለስ ፍላጎትም ይኖራልን? ማብራሪያ ስጡበት፡፡
3. የመንፈስ ነጻነት ሲባል ምን ማለት ነው?

**፤፤ ለሚከተሉት ቃላት ፍቻቸውን ለመስጠት ሞክሩ፤ምንባቡን ካነበባችሁ በኃላ ደግሞ የሰጣችሁትን ፍች ከአውዳዊ ፍቻቸው ጋር አገናዝቡ፤**

1. ምጻተኛ
"  2. መስረግ
3. ቀኖና
4. ሩጫ
5. የተኮረከመ

## ክንፋም ሕልሞች
## ክፍል አራት

ተክለሚካኤል ለታመነ ማትያስ፣ ካሊፎርንያ
ውድ ታሚ እንደምን አለህ። እኔ እንደምንም እንደምንም አለሁ። ጊዜየን ቅርጥፍ አድርጌ እየበላሁ! መንፈሴ እንደደጋን ተወጥሯል፤ሁሉነገር ብዥ ብሎብኛል። እቀናብሃለሁ። ባለማማረርህ ይሁን ምሬትህን ባለመግለጥህ ከእኔ ትለያለህ። እነሱ እንኳን ሰው ቆቅ ያለምዳሉ። አሁን እዚህ በመንፈስ እየተረገጥሁ ዶላር እለቅማለሁ። ከዚያስ ትርፉ ምንድን ነው? የመንፈስ ህመም በስንት ብር ይፈወሳል? እኔኮ አበሻ ነኝ። ማንም እንደምጻተኛ እንዲቆጥረኝ አልፈልግም። ሰው በፈረንጅ በርገር ብቻ አይኖርም በኢትዮጵዊ ኩራትም ጭምር ነውእንጂ። ከሆድ ወዲያ ማዶ ልብ እንዳለ አይዘንጋ፣ የልብ መጽናኛው ምንድን ነው? ክብረን መጠበቅ ነው ወዳጄ፣ስለዚህ ራሴን እወደዋለሁ። ጠይም ወንዝ ነህ እለዋለሁ ወይም ጠይም ወንዝ ነኝ።
ሽለቆውን አየሁት፣ በረሃውን መረመርኩት፣ ወደ ከተሞች ተንዥቀዥኩ፣ በባእድ አደባባይ ላይ ፈሰስኩ። ከዚያስ! በድአሎት አሸዋ ውስጥ ሳልሰርግ መንቃት ፈለኩ። ‹‹የኒልዮሽ ወደ ምንጩ የሚፈስ ጅረት ነኝ የሚለውን አነበብኩ። ቁዘማዬ በረታ፣በተደጋጋሚ የከፍተኛ ቁዘማ ሰለባ ነበርኩ። ፈውሱን ስጠይቃቸው ቀላል ቁዘማ ነው እያሉ የህመሜን ስም ይነግሩኛል። ወትሮም እነሱን ማመን ጭጋግ መዝገን ነው። እየተፈራረቁ ሊመክሩኝ ሊመረምሩኝ (counsel) ሊያደርጉኝ ሞከሩ። እኔ ችግሬን ስነግራቸው እነሱ ዕድሜ ልካቸውን ያጠኑትን ቀኖና ያሰላስላሉ። ወይኔ አገሬ እንዲህ ሕልም ትሆኝብኝ?..ያች የጊዮን አገር፣ ያልተበረዘች ያልተከለሰች፤ በቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሄር መንፈስ በውሃዎች ላይ ሰፎ ነበር ይላል። በየትኛው ውሃ? በሚሲሲፒ እንዳይመስልህ። ያኔ ሚሲሲፒ የት አለና? ቢኖርም ባዶሽለቆ እንጅ ውሃ አልነበረውም። የእኛ ግዮን ግን ገነትን ያጠጣ ነበር። የፈርኦን ፒራሚዶች ጡብ የተቦካው፣ የኪሊዮፓትራ ገላ የታጠበው በየትኛው ውሃ ይመስለሃል? ናይል ነው ወዳጄ ናይል።

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስከ አሁን ካነበባችሁት ስለባለታሪኩ ምን ተረዳችሁ?
2. ባለታሪኩ ወደፊት ምን ውሳኔ ላይ ሊደርስ ይችላል?

እኔ ግን ከእትብቴ ጋር ወኒየም አብሮ ተቀብሮአል መሰለኝ እልፈሰፈሳለሁ። ያባቴ ያባትህ ምልክት ቆራጥነትን፣ፅናትናን ቀጥብሎ መቆምን የሚያሳይ ነበር። ወደ አክሱም ተመልከት የአባቶችህ የአባቶቸ ጽናት፣ የአእምሮ ጥልቀትና የተመራማሪነት ተምሳሌት ነው። አየህ እንዴት እንደተቀዳደምን? የትነናንቶቹ ሩጫቸውን ጨርሰው እንኳ አልደረስንባቸውም። በሕልሞቼ ወደ ራሳችን ጥንት ወደማውቃት አፈር ወደምትመስለው ማንኩሳ እመለሳለሁ። በአፈሩዋ ውስጥ ፈውሴን አገኛለሁ። ከሞራል ስብራቴና ከአካል ዝለቴ መፈወሻ የሚሆነኝን የአባቶቼን አጥንት ድንግል መሬት ውስጥ አገኛለሁ። ይህን ስልህ ትፎክራለህ እንጅ አትታገልም እያልህ እንደምትሳለቅብኝ አውቃለሁ። ከዚህ በኋላ የምፎክርበት አቅም እንደማይኖረኝ ይሰማኛል። በምበላው፣በምሰራው፣በማየው ጭምር ደስተኛ አደለሁም። ይህ ሳያንስ አዲስ አበባ ያለችው እጮኛዬ ልታጽናናኝ ሲገባት ካልጎተተችኝ እያለች ታጣድፈኛለች። እኔ ግን መመለስ አለብኝ። እናቶቸ ቅጠል በልተው ቅጠል ለብሰው እየኖሩ

ደስተኛና ጥበበኛ ነበሩ፡፡ አያቴ ስትጸልይ ምን ትል ነበር መሰለህ? ‹‹አቤቱ የተኮረኮመ ልብ ስጠኝ፡፡ ለመኖር አንድ ዛፍ ይበቃኛል፡፡ ከፍሬው እራቴንና መድሃኒቴን እሰራለሁ ከቅጠሉ ቀሚሴን እሰፋለሁ ሽመላዎች ንቦችና ሽኮኮዎች ባልጀሮች ይሆኑኛል፡፡ የተመረጠውን ማህሌት ያሰሙኛል፡፡ የተመረጠውን ወለላ ያጠጡኛል፡፡››
አሁን እግሬ አሜሪካ ውስጥ ስላለ ወገኖቼ የአሜሪካ ሰው ብለው ይጠሩኛል፡፡ አዎ በመንፈስ በናት ምድሬ እቅፍ ውስጥ ነኝ፡፡ ለማንኛውም ሰሞኑን፣ኢ-ሜል አደርግለሃለሁ፡፡ የልጅነት የስደት የእብደትም ጓደኛህ ተክለሚካኤል፡፡

(ለማስተማር በሚያመች መልኩ መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎበት የተወሰደ፣ክንፋም ሕልሞች 69-84)

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡ ለመልሳችሁም ምክንያት ስጡ፡፡**

1. ለተክለሚካኤል የመንፈስ ውጥረት መንስኤው የገንዘብ እጥረት ነው፡፡
2. የሰው ልጅ ሆዱን ሞልቶ ካደረ ለኑሮው በቂ ነው፡፡
3. የፈርኦን ፒራሚዶች ጡብ የተቦካው፣ የኢሊዮፓትራ ገላ የታጠበው በሚሲሲፒ ወንዝ ነው፡፡
4. ተክለሚካኤል በውጭ ሀገር በመኖሩ ደስተኛ ነው፡፡
5. ታመነና ተክለሚካኤል በውጭ ሀገር ኑሮ ላይ ተመሳሳይ አቋምና አመለካከት አላቸው፡፡
6. ተክለሚካኤል የእጮኛውን ጥያቄ በቅርቡ እንደሚያሳካ ወስኑዋል፡

**ክፍለ ጊዜ ሁለት፦** ምንባቡን ደግመው በጽሞና ንባብ ካነበቡ በኋላ የምርጫ፣የማዛመድ ጥያቄዎችን፣ይሰራሉ፡፡ ስልምንባቡ መልዕክት ጥልቅ ግንዛቤ እንዲያገኙ፣ ክፍት ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡ እንዲወያዩ፣እንዲከራከሩ፣ ያግዛቸዋል፡፡ ገጸባህሪያትን እንዲረዱና የራሳቸውን አመለካከት እንዲያንጸባርቁ ያስችላል፡፡

**፪. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. ‹‹ከሆድ ወዲያ ማዶ ልብ እንዳለ አይዘንጋ››ሲል ምን ማለት ነው?
   ሀ. በሰውነታችን ውስጥ ልብ ከሆድ በላይ እንዳለ ይገልጻል፡፡
   ለ. ጠግቦ ማደር ሰውነትን ያለመልማል፡፡
   ሐ. መታሰብ ያለበት ጠግቦ ስለማደር ብቻ ነው፡፡
   መ. ጠግቦ ማደር ብቻ ሳይሆን የመንፈስ፣የህሊና ደህንነትም ሊታሰብበት ይገባል፡፡
2. ‹‹…በድሎት አሸዋ ውስጥ ሳልሰጥም ለመንቃት ፈለኩ›› ሲል ምንን ይገልጻል?
   ሀ. ጸሐፊው በተንሳቆለ አካባቢ እየኖረ መሆኑን፣
   ለ. ጸሐፊው በአሸዋማ በረሃ እየተጓዘ መሆኑን፣
   ሐ. ጸሐፊው ምቾት በሞላበት ኑሮ ውስጥ ተስቦ እሱነቱን አለመርሳቱን፣
   መ. ጸሐፊው ምቾት ከተሞላበት የኑሮ አካባቢ መውጣት እንደማይፈልግ ያሳያል፣
3. ‹‹…የጥንቶቹ እሩጫቸውን ጨርሰው እንኳ አልደረስንባቸውም››ሲል ምን ማለቱ ነው?
   ሀ. የጥንቶቹ ዛሬም እየሮጡ እንደሆነ ይገልጻል፣
   ለ. የዘመኑ ስልጣኔ  የጥንቶቹን በልጦና መጥቆ እንደሄደ ያሳያል፣
   ሐ. የጥንቶቹ የጥበብ ግስጋሴ ዛሬም አልተገታም፣
   መ. የዘመኑ ስልጣኔአችን፣ጥበባችን፣የጥንቶቹ በደረሱበት መድረስ አልቻለም፣
4. ‹‹እልፈሰፈሳለሁ›› ሲል ምን ማለት ነው?

ሀ. ቀጥ ብሎ መቆም የተሳነው መሆኑን፣
ለ. ባሰበው ጉዳይ ላይ መወሰን አለመቻሉን፣
ሐ. እጮኛውን አሜሪካ ማምጣት አለመቻሉን፣
መ. የፈረንጅ በርገር ያልተስማማው መሆኑን፣

5. ‹‹አያቱ ስትጸልይ ‹አቤቱ የተኮረኮመ ልብ ስጠኝ› ትል ነበር፡፡››የሚለው ሃሳብ የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድን ነው?
ሀ. ምኞት ልንተገብረው በምንችለው ጉዳይ ላይ መወሰን እንዳለበት ይገልጻል፣
ለ. ፍላጎትና እድገት ድንበር ሊኖረው ይገባል የሚል ሃሳብ ይዙአል፣
ሐ. የሌሎችን በደልና ጫና የሚሸከም ትእግስት ይስጠኝ ማለት ነው፤
መ. የተጎዱትንና የተጎሳቆሉትን የመርዳት አስተሳሰብ ይዳብር እንደማለት ነው፡፡

6. ‹‹ ከአሁን በኋላ የምፎክርበት አቅም የለኝም ››ሲል ምንን ያመለክታል?
ሀ. ወኔው መዳከሙንና ተስፋ መቁረጡን፣
ለ. አደርጋለሁ ከሚል  አጉል ተስፋ ተላቆ ወደ ቁርጥ ውሳኔ መግባቱን ያሳያል፣
ሐ. ወደ ሀገሩ የመመለስ ተስፋ ተሟጦ ማለቁን፣
መ. ሀ እና ሐ  መልስ ናቸው፡፡

**፫. በምንባቡ መሠረት  ለሚከተሉት በ‹‹ሀ›› ክፍል ለቀረቡ ሐረጎች ወይም ጽንሰ ሀሳቦች በ‹‹ለ›› ክፍል ከቀረቡት መገለጫዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡**

| ‹ሀ› | ‹ለ› |
|---|---|
| 1. በባዕድ አደባባይ ላይ ፈሰስኩ፣ | ሀ. በውጭ ሀገር መንደዶች በደስታ ተመላለስኩባቸው፣ |
| 2. ተደጋጋሚ ቁዘማ፣ | ለ. በባድ አደባባይ ላይ ወጥቼ ለጥቃት ተጋለጠሁ፣ |
| 3. ቀኖና፣ | ሐ. የመንፈስ ጭንቀት፣ |
| 4. ጭጋግ መዝገን፣ | መ. መንፈሳዊ መዝሙር፣ |
| 5. አፈር ወደምትመስለው ማንኩሳ፣ | ሠ. የማይጨበጥ ተስፋ፣ |
| 6. ምጻተኛ፣ | ረ. ተጨባጭና ተገቢ የሆነ፣ |
| | ሰ. ገና ያልሰለጠነ አካባቢ፣ |
| | ሸ. ለሀገሩ ባይተዋር የሆነ ስደተኛ፣ |
| | ቀ. የሕይወት ቀመር፣ |

**፬. ለሚከተሉት ጽንሰሃሳቦች ማብራሪያ ስጡ፡፡**

1. ተክለሚካኤል ቆርጦ ወደ ሀገሩ የሚመለስ ይመስላችኋል፣ማስረጃ እያጣቀሳችሁ ተወያዩ፣የውይይታችሁን ፍሬ ነገር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንጸባርቁ፡፡
2. ክንፋም ሕልሞች በሚል ረዕስ በተከታታይ በአራት ክፍሎች ከቀረቡት የደብዳቤ ጽሁፎች የተረዳችሁት አጠቃላይ መልዕክት ምንድን ነው? በጋራ የተወያያችሁበትን ሀሳብ እያንዳንዳችሁ በአጭሩ በጽሁፍ ግለጹ፣
3. የተደላደለ ኑሮ መኖር የሚቻለዉ በሐገራችን ኢትዮጵያ ነው ወይስ በውጭ ሀገር? ቡድን መስርታችሁ ተከራከሩ፡፡

4. ክንፋም ሕልሞች ክፍል ሶስት ላይ እንደቀረበው፣በዚህ ዘመን ዲቪ አለመሙላት እንደነውር የሚቆጠረው ለምንድን ነው? በዚህ ላይ ያለህ/ሽ የግል አስተያየት ምንድን ነው? አስተያየታችሁን በጽሁፍ አስፍሩ፡፡

***ትምህርት አምስት፦*** *የትምህርት ርዕስ ‹‹**በወርቅ የተሞላ ገደል**›› በሚለው የአጭር ልቦለድ ክፍል የአንብቦ መረዳት ተግባራትን ማስተማር ወይም ተማሪዎች እንዲሰሩ ማድረግ ፤*
***የትምህርቱ ዓላማ፦*** *ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች በምንባቡ መሰረት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ይሠራሉ፤የቅድመንባብ፣የንባብ ጊዜና ድህረንባብ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡*
**የተመደበ ክፍለ ጊዜ፦ ሦስት ክፍለ ጊዜ ለ6ሰዓት**
**ክፍለ ጊዜ አንድ፦***ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች ይሰራሉ፣ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ተማሪዎች ምንባቡን መጀመሪያ ድምጽ በማሰማት ያነባሉ፤በማስከተልም በጽሞና ያነባሉ፡፡*
***መመሪያ አንድ፦*** *የቅድመ-ንባብ ጥያቄዎችን በቡድን በመወያየት መልሱ፣መልሳችሁን ለክፍሉ ተማሪዎች አንጸባርቁ፡፡*

**ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች**

1. *ሙስና ማለት ምን ማለት ነው?*
2. *ሀቀኝነት፣ታማኝነትና በአቋም መጽናት ማለት ምን ማለት ነው?*
3. *አንድ ሰው በተሰማራበት ሙያ ለሚሰራበት ድርጅት ያለው ተቆርቋሪነት እንዴት ይገለጻል?*

**¡¡ ለሚከተሉት ቃላት ፍቻቸውን ለመስጠት ሞክሩ፤ምንባቡን ካነበባችሁ በኃላ ደግሞ የሰጣችሁትን ፍች ከአውዳዊ ፍቻቸው ጋር አገናዝቡ፤**

1. ወጠጤ
2. መናጥ
3. ቀትረ ቀላል
4. ጓዳ
5. ሞዠቀ

**በወርቅ የተሞላ ገደል**

*የአራተኛ ፖሊስ ጣቢያ የምሽቱ ተረኛ መኰንን በቢሮው ወንበር ላይ እያለ፣ እንቅልፍ ሸለብ ሊያደርገው ሲሞክር ከደጅ ጫጫታ ሰማ፡፡ ግልፅ ነው፡፡ ሌባ ተይዞ ሊሆን ይችላል፡፡ አለያ ጥጋበኛ ጎረምሶች በቢራ ጠርሙስ ተፈናክተዋል፡፡ ከዚያ አያልፍም፡፡ ግን እንደምገምተው ሳይሆን ቀረ፡፡ አንድ ግርማ ሞገስ ያላቸው ሽማግሌ በሁለት የፖሊስ ወታደሮች ግራና ቀኝ እንደተያዙ፣ እየተራገሙና እየተሳደቡ ዘለቁ፡፡*

*‹‹ምንድን ነው ጉዳዩ!?›› ተረኛ መኰንኑ እንቅልፍ በተጫነው ድምፅ ጠየቀ፡፡ ከፖሊስ ወታደሮች አንዱ ፈጥኖ ምላሽ ሰጠ፡፡ ‹‹ከጭማድ እቃ ከሰረቁት መካከል አንዱ ናቸው፡፡ ምላሳቸው አይቻልም፡፡ ያላወረዱብን የስድብና የእርግማን መአት የለም፡፡ አፋቸው ውስጥ ጩቤ ነው ያለው፡፡››*

*‹‹ልብ አድርጉልኝ!›› ሲሉ በቁጣ ጮሁ ሽማግሌው ‹‹...ክብሬ ተነክቱዋል፣ሌባ ተብየ ተሰድቢያለሁ፡፡ እኔ ሌባ አይደለሁም በአደባባይ ሌባ መባሌ ግን ይመዝገብልኝ፡፡ የተከበርኩ መንግስት ሰራተኛ ሆኜ ሳለሁ፤ሀምሳ አራት አመት በክብርና በመልካም ስም*

በኖርኩበት፤አገር፣ከተማ፣ወረዳ፣ቀበሌ፣መንደር፣ሕዝብ ፊት ሌባ ተብያለሁ፡፡ የአራት ትላልቅ እድሮች ሙሉ አባል የሆንኩ ሰው ነኝ፡፡ በአካባቢየ የታፈርኩና የተፈራሁ ሽማግሌ ነኝ፡፡ ለጡረታ ስምንት ወራት ከአንድ ሳምንት ብቻ የቀረኝ ሰው ሆኜ ሳለሁ

እኔን ለማዋረድ ሴራ እየተጠነሰሰ ነው፤እነኝህ ጢም እንኳ ገና ያላበቀሉ ወጠጢዎች ‹‹ሌባ!›› እያሉ እኔን ማዋረዳቸው ይያዝልኝ፡፡ የፖሊስ አዛዡ አዳምጦ ሲያበቃ በእርጋታ አናገራቸው፡፡ ‹‹አረፍ ይበሉ አባቴ በቅድሚያ አረፍ ይበሉ›› ሽማግሌው ቁና ቁና እየተነፈሱ አጠገባቸው ከነበረው ያረጀ አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀመጡ፡፡ ተቀምጠው ሲያበቁም እራሳቸውን በሁለት እጃቸው መካከል ቀብረው፣ በሽበት የተወረረ እራሳቸውን በቁጭት ገራ ቀኝ እየናጡ ይንገበገቡ ጀመር፡፡ ‹‹ይሰሙኛል አባቴ!›› ሲል ቀጠለ ተረኛ መኰንኑ ‹‹…ያለ ሃጢያትዎ የሚወነጅልዎ ማንም የለም፡፡ ቃልዎን ከሰጡ በኋላ አጠራጣሪ ነገር ከሌለብዎ ወደ መኖሪያ ቤትዎ ይመለሳሉ፡፡ ይሰሙኛል?›› ፣ ‹‹ሰምቻለሁ የእኔ ልጅ›› አሉ በደከመ ድምፅ፡፡ ‹‹…ስላከበርሽኝ ቀጨኔ መድኃኒያለም ያክብርህ በልጆችህ ተከፈል፡፡ ተርኛ መኰንኑ ከሁለት የፖሊስ ወታደሮች ጋር ወደ ቀጣዩ ክፍል አመራ ከግማሽ ሰዓት በሁዋላ ብቻውን ተመልሶ ሲመጣ፤ሽማግሌው ተረጋግተው ነበር፡፡ እንዲያውም ከጠቀመጡበት ወንበር ተነስተው ኖር አሉት፡፡ ‹‹በእግዜር ብሎ እንዲቀመጡ አደረገ፡፡›› ተረኛ መኰንኑ ወንበር ላይ ጠቀምጦ፤ ብእርና ወረቀቱን ካዘጋጀ በሁዋላ የተለመደውን የፖሊስ ስራ ጀመረ፡፡

‹‹ስም ማን ልበል አባት?››
‹‹ባሻ ዘለቀ ሞላ››
‹‹እድሜ?››
‹‹አምሳ አራት››
‹‹የቤተሰብ ሁኔታ?››
‹‹እንዴት?››
‹‹አግብተዋል…አላገቡም?...››
‹‹አምስት ልጆች አሉኝ፡፡ ክብሩ ይስፋ ለፈጣሪ፡፡››
‹‹ስራ?››
‹‹ጥበቃ››
‹‹የሚሰሩበት መስሪያቤት?››
‹‹ጭማድ››

ተረኛ መኰንኑ ጻፅፎ ከጨረሰ በሁዋላ ቀና አለ፡፡ ‹‹እሽ እንግዲህ ባሻ ዘለቀ፤ ከስራ ኃላፊነትዎ ጋር በተየያዘ ክስ ሊመሰረትብዎ ስለሆነ የኔ የሚሉትን ቃል በትክክል ይስጡኝ፡፡›› ‹‹ደግ›› ከሶስት ወራት በፊት ርስዎ የጥበቃ ስራ ከሚሰሩበት መስሪያቤት መጋዘን ግምቱ ከመቶ ሺህ ብር በላይ የሆነ ቁሳቁስ ተሰርቋዋል፡፡ ባለፉት ሁለት ወራት ከጉዳዩ ጋር የተነካካና በወቅቱ በጥበቃ ስራ የነበሩ ዘበኞችና የአስተዳደር ኃላፊዎች በሙሉ ታስረዋል፡፡ ይህን እርስዎም የሚያውቁት ይመስለኛል፡፡ ከምርመራ መዝገቡ አሁን እንደተረዳሁት ደግሞ እርስዎም በስርቆቱ እጅዎን ማስገባትዎ ተጠቁሙዋል፡፡ ስለጉዳዩ የሚያውቁትን ቢገልፁልኝ፡፡
ባሻ ዘለቀ በጎልማሳ ሰው ኃይል ከተቀመጡበት ተስፈንጥረው ተነሱ፡፡ ጠይም ገጽታቸው ባንድ አፍታ የተቃጠለ ላስቲክ ሲመስል ተረኛ መኰንኑ አስተውሎ ተሸማቀቀ፡፡ ንፅህነታቸው ከቅንነታቸው ጋር ገፅታቸው ላይ በግልፅ ይነበባል፡፡ በእርጅና የደከሙ ዓይኖቻቸውን ፖሊሱ ላይ እንደተከሉ ቃል እንኳ መተንፈስ ተስኖአቸው ይንቀጠቀጡ ጀመር፡፡‹‹ባሻ ረጋ ይበሉ!›› ፖሊሱ ሊያበርዳቸው ይጥር ጀመር ‹‹እንዲህ የሚያናድድ ነገርየለውም፡፡ንጹህእስከሆኑ ድረስ፤ያለስምዎ ስም፤ያለወንጀልዎ ወንጀል የሚለጥፍብዎ ከቶ ማንም የለም፡፡ ይመኑኝ!›› ሆኖም ሽማግሌው በቀላሉ አልረገቡም፡፡ የሚንቀጠቀጠውን እጃቸውን እርስ በእርስ እያፋተጉ፣‹‹ሌባ አልከኝ እኮ!›› ሲሉ በቆሰለ ድምጽ ተነፈሱ ‹‹…ሌባ አልከኝ! እኔ ሌባ አይደለሁም፡፡ የተዋረድኩ ሰው አይደለሁም፡፡ ቀትረ ቀላል አይደለሁም፡፡ በሞት አፋፍ ላይ የምንዘላዘል የተናቀ ሽማግሌ አይደለሁም…›› ተረኛ መኰንኑ በቁጣ አቋረጣቸው፤ ‹‹ይህን

ሁሉ ማን አለ? እኔ ወጣኝ? ሌባ-ወራዳ ፣ቀትረ-ቀላል፣ዘልዛላ አልኩዎ? አልወጣኝም፡፡ በርስዎ ላይ ጥቆማ ደርሶናል፡፡ በጥቆማው መሰረት የግድ ቃልዎን መቀበል አለብን፡፡ ጉዳዩ ተጣርቶ ደሞ ነፃ ከሆኑ፣ወይም የደረሰን ጥቆማ መሰረተቢስ ከሆነ ወደቤተዎ በክብር ይሸኛሉ፡፡ እኛ እርስዎን እዚህ አስረን የማዋረድ ፍላጎት የለንም፡፡ ተረድተውኛል?››
ረጅም አየር አውጥተው በእሽታ ራሳቸውን ላይ ታች ወዝውዘው ወደ መቀመጫቸው ተመለሱ፡፡

‹‹እንቀጥል ባሻ?››
‹‹ደግ››
‹‹በሉ ስለጉዳዩ የሚያውቁትን ይግለጹልኝ?››
‹‹ምኑን ልግለጽልህ ልጄ?››
‹‹የሚያውቁትን ያህል አውነቱን ይንገሩኝ?››

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስከ አሁን ያነበባችሁትን መልዕክት አጠቃላችሁ ተናገሩ፡፡
2. ባለታሪኩ ወደፊት የሚያውቁትን ነገር ሳይደብቁ ለመርማሪ ፖሊሱ የሚናገሩ ይመስልሃል?/ሻል?

‹‹እውነቱንማ ነው የምናገር፣አሉ በኩራት፡፡ ‹‹…በአምሳ አራት አመቴ እንዴት እዋሻለሁ? በቀጨኔው መድሃኒያልም እያመንሁ እንዴት አሰት ከአንደበቴ ይወጣል?›› ፣ ‹‹ይዋሻሉ ማለቴ አይደለም፡፡ እንዲሁ ለአባባል ያሃል ያልሁት ነው…›› ዝምታ ሆነ፡፡ ‹‹በሉ ይቀጥሉ… ባሻ››፣ ‹‹እሺ ልጄ›› ካሉ በሁዋላ ‹‹…እንግዲህ ስለጉዳዩ በቅድሚያ የነገረኝ ታምሩ ነው…›› ብለው ተንደረደሩ፡፡ ፖሊሱ አቋረጣቸው፡፡ ‹‹ማነው ታምሩ?›› ፣ ‹‹የዘቦች የሽፍት አለቃ ነዋ፡፡ አሁን እናንተ ዘንድ እስር ላይ ነው፡፡››፣ ‹‹መልካም፣ምን ብሎ ነገረዎት?››

‹‹ጭማድ ስለከሰረ ሊዘጋ ነው፡፡ ባለስልጣኖችም በየፊናቸው ጉዋዳቸውን እየሞሉ ነው፡፡ ‹የአባትህ ንዋይ ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ› ነው ከነተረቱ፣ሙልጫችንን ሳንቀር እኛም ለአንድ ቡሀቃ የምትሆነንንኳ እንያዝ አሉኝ፡፡ እኔ ታዲያ መልሴ ምን ሆነ? ‹ውሻን ጭራውን ቢቆርጡት ያው ውሻ ነው› እንዲሉ ሌቦች ሌባ ናቸውና በሌብነት መንገድ ይሄዳሉ፤ የተከበሩት ደግሞ ክቡራን ናቸውና በብርሃናዊው ጎዳና እንደ ሱራፌል በልበ ሙሉነት ይራመዳሉ› አልሁና ሸኘሁት፡፡ የቀጨኔው መድሃኒያለም ምስክሬነው ይህን ተባብለናል፡፡ ‹‹ ይቀጥሉ ባሻ…››

‹‹ደሞ በሳልስቱ ተመልሶ መጣ፡፡ ‹ሳይደግስ አይጣላም እንዲሉ ሁሉም መልኩን መያዝ ጀምሮዋል፡፡› አለኝ፡፡ አያያዘናም ‹ከደላሎችም ከገዥዎችም ጋር ተገናኝተን ተነጋገርን ሁሉም ስምም ሆኑዋል፡፡ ምን ይመስለዎታል?› አለኝ፡፡ ይህን እንዳለኝ ታዲያ እኔ ምን ሆንኩ? የተቆጣ ነብር፤ ምላሼ ምን ነበር? ‹ሰይጣን ሆይ! ሰይጣን ሆይ- ሞኙ ሰይጣን ሆይ! ወርቁን አየህና እሳቱን ሳታይ! እልም ካለው ሲኦል ወድቀህ ቀረህ ወይ!› ነዋ! እንደ ሽማግሌነቴም መከርኩት፡፡ ‹አታነካካኝ እናንተም አርፋችሁ ተቀመጡ አልኩት፡፡ የዘብ አለቃ ሆነህ ሳለ እንዲህ ማድረግ ነውረኝነት ነው› አልኩት፡፡ እንዲህ ብየ መለስኩለት…››፣ ‹‹በጄ!››

‹‹…ደሞ ቆየ ቆየና መጣ፡፡ በለሰለሰ አንደበት ወግ ጀመረኝ፡፡ ‹ከቅዱስ መፅሐፍ› ሲል ጀመረ ‹እግዚያብሐየር አምላክ በቅዱስ መጽሐፍ ሲነግረን - እእዋፍን አትመለከቱምን? ምን እንበላለን፣ምን እንመገባለን ብለው አይጨነቁም፡፡ እኔ አምላካቸው አለሁላቸው - ከእናንተ ከተገፋችሁትም ጎን ሁሌ አለሁ - ይላል ፈጣሪ፡፡ ይኸዉ በዘብ ላይ ላለነው ለአምስታችን 35 ሺህ ብር ተመድቡዋል፡፡ ሀሉም ተፈ ፅሙዋል፡፡ የቀረው እቃውን መጫንና ገንዘቡን መቀበል ብቻ ነው፡፡ እርስዎም ያለምንም ጣጣ እንደ ጲላጦስ ከደሙ ንጹህ ነኝ ብለው እጅዎን ታጥበው ክምር ብርዎን ይረከባሉ› አለኝ፡፡ የኔ ምላሽ ታዲያ ምን ሆነ? በአጭሩ መለስኩታ፤

‹ዲያቢሎስ ንፁሀነን ሊያስት ሲሻ፣ ቅዱስ መፅሐፍን ይጠቅሳል› አልኩት - በፈገግታ። ይህን ስለው ስቆ -ስቆ ሲያበቃ ‹ሊቀ - ሊቃውንት ኖት። ከርስዎ አንጎል ጋር ማን ይስተካከላል› ብሎ እብስ አለ። እኔም የእለቱ እለት ወደ ኃላፊው ቢሮ ሄጀ አመለከትኩ።››፣ ምን ብለው አመለከቱ?››

‹‹ዘቦች እቃ ተመጋዘን ሰርቅ ሊሸጡ እየተሰናዱ ነው። ስማቸውም እገሌ…እገሌ…እገሌ ይባላል ብዬ ለአቶ ቢታው ለራሱ ነገርኩት። ይህን ጊዜ ቢታው ምናለኝ? በግራ እጁ ጠጉሩን እያሻሸ፣ ‹ግድየለም ጥበቃውን እናጠናክራለን› አለኝ። እኔ ታዲያ በልቤ ምን አልኩ? ‹ኢትዮጵያ አባቱ ሞኝ ነህ ተላላ፤ የሀቅ ሰው ቀርቶ የአሰት ሰው በላ› አልኩዋ፤ ካስተዳደር በላይ አላውቅ ምላሴን ሰብስቤ ተመለስኩ። ‹‹ከዚያስ?››

‹‹ከዚያማ የዘብ አለቃው ተመልሶ መጣ›› አሉ በደከመ ድምፅ ‹‹…ተመልሶ መጣና ‹የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል፤እንዲሉ እርስዎ የሰው አይፈልጉምና አባክዎ አንድ እቃ እርስዎ ዘንድ ቢያኖርልኝ አለኝ። የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ፤እንዲሉ ቃሌ ቃል መሆኑን አትጠርጥር። የሆነውስ ሆነና ዕቃው ምንድን ነው?› ስል ጠየቅኩት። ምላሽም ሳይሰጠኝ ከቀኝ ኪሱ ያደፈች ከረጢት ውልቅ አድርጎ ሲያበቃ እጀ ላይ ቁጭ አደረጋት። ‹ምንደነው?› አልኩት ‹ገንዘብ ነው። ሰባት ሽህ ብር ነው። የሰው ነውና
ይያዙልኝ አደራ› ሲል ተማጠነኝ። እሺ ካሬ ወጥቶአልና ከረጢቱን ይዤ ሄድኩ።›› ፣ ‹‹ከዚያስ?››

‹‹ማታ ቤቴ መጣ›› አሉ በትካዜ።

‹‹በጄ››

‹‹የባጥ የቆጡን አውርቶ ሲያበቃ ነገረኝ።››

‹‹ምን ብሎ?››

‹‹ከረጢቱ ውስጥ ያለው በሙሉ ያንተነው አለኝ።››

‹‹እርሰዎ ታዲያ ምን አሉት?››

ሽማግሌው ግን ለዚህ ጥያቄ መልስ መስጠት ሳይቻላቸው ቀረ። በተጨማደደ እጃቸው ፊታቸውን ሞዠቁት። ያሳለፉት ረዥም ዘመን እንደ መብረቅ ብልጭ ብሎ ድርግም ሲል ታያቸው። ወጣትነታቸው፤በወጣትነት በፍቅር ያበዱበት ዘመን፤ በውትድርናው ዘመን የፈጸሙት ተጋድሎ፤ የጀግንነት ጊዚያት፤ የሞትና የሕይወት ትንቅንቆች፤ በልጅ ፍቅር አቅላቸውን ያጡባቸው፤በክብርና በታማኝነት የኖሩባቸው እነዚያ ዘመናት። የሽማግሌነት ጊዚያት፤የእድር ገንዘብ ያዥ ሆነው በታማኝነት ማገልገላቸው፤የአካባቢው ክብር አንቱታ፤የባለቤታቸው እረፍት የብቸኝነት ዘመናት፤ የልጅ ልጆች ብቸኝነታቸውን ለመግፈፍ ወደ ኦና ቤታቸው ያመጡት የልጅልጅ። የልጅልጃቸው መቅበጥ ወደ ውጭ ሀገር እሄዳለሁ እያለ ፋታ ማሳጣቱ፤እያደር መጠጥ ለምዶ ውደ ዱርየነት ማምራቱ፤ከሰይጣን የተላከው የዘብ አለቃ ፈተና ያቺ የመጨረሻዋ ደቂቃ …ሽማግሌው እንባቸውን መገደብ ሳይችሉ ቀሩ። በተጨራመተ ገጽታቸው ላይ የእልህ የእንባ እንክብሎች ሲወርዱ ታዩ…

ወንጀለኛ መሆናቸው ታወሳቸው።ስለህግ ትርጓሚዎች ለአፍታአሰቡ። የህግ ትርጓሚዎች ብዙውን ጊዜ ስለ ቅንነት ደንታ የላቸውም። ‹ነፃ እወጣ ይሆን?› ሲሉ እራሳቸውን ጠየቁ። ግን ከእንግዲህ ምን እረብ አለው? ስማቸው እንደሁ ቆሽሾአል። ከነገ ማለዳ ጀምሮ በአራቱም የዕድሮቻቸው አባላት በጎረቤቶቻቸው፣በድፍን መንደሪቷ፣የሚከብሩዋቸው ወዳጆቻቸው፣ሌላው ቀርቶ ገና ጢም ያላበቀሉ ሕጻናት አፍ ስማቸው እንደ ሽንኮራ አገዳ ይታኘካል፤ይመጠጣል፤ይተፋል። መቃብራቸው ላይ ‹ሌበው ባሻ ዘለቀ እዚህ አርፈዋል።› ተብሎ ባይጻፍም እንደ ተጻፈ ይቅጠራል። ልጆቻቸው ባባታቸው ያፍሩ ይሆናል። ወሬ እንደሁ አርባ አራት ክንፎች አሉት። ይበራል። ዕተወለዱበት መንደር ድረስ። ሰይጣን ከቶ ምን ስራ አለውና?

‹‹አባት?››

የተረኛ መኰንኑ ጥሪ ከጠዋጡበት አሳብ መለሳቸው።

‹‹የኔ ልጅ››

‹‹እንግዲህ ማረፊያ ቤት ይቆያሉ፡፡››

እፍታ 63 ትረካዎች ‹‹በወርቅ የተሞላ ገደል›› ለማስተማሪያነት በሚያመች ሁኔታ የተወሰደ(          )

**ክፍለ ጊዜ ሁለት፦** ምንባቡን ደግመው በጽሞና ንባብ ካነበቡ በኋላ ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት ምክንያት በመስጠት ያብራራሉ፡፡ የምርጫ ጥያቄዎችን፣ይሰራሉ፡፡ በዚህ ክፍል ስልምንባቡ መልዕክት ጥልቅ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያግዛቸዋል፡፡

፩. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1. የፖሊስ ወታደሮች ግርማ ሞገስ ያላቸውን ሽማግሌ ይዘው ሲገቡ፣ ተረኛ መኰንኑ ሶፋ ላይ ቁጭ ብሎ ነበር፡፡
2. በጥርጣሬ በፖሊሶች የተያዙት ሽማግሌ ንዴት ያንገበገባቸው ጥፋታቸውን ለመደበቅ ነበር፡፡
3. ባሻ ዘለቀ ከሚሰሩበት መስሪያ ቤት ውስጥ፣ በስርቆት በተያያዘ ምክንያት የታሰሩት ያስተዳደር ሰራተኞች ብቻ ናቸው፡፡
4. ባሻ ዘለቀ አስር ልጆች አሉዋቸው፡፡
5. የዘቦች አለቃ ታምሩ፣ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ባሻ ዘለቀ የተመለሰው ከሳምንት በኋላ ነበር፡፡
6. ታምሩ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ባሻ ዘለቀ በመጣ ጊዜ ሁሉነገር ስምም መሆኑን ሲነግራቸው ውሳኒያቸውን ሽረው ገንዘብ ለመውሰድ ተስማምተዋል፡፡
7. ባሻ ዘለቀ፣ ታምሩ ለመጨረሻ ጊዜ መጦ በገንዘብ ክፍፍሉ እንዲያምኑ ሲነግራቸው፣ለአስተዳደር ሰራተኛው አመልክተዋል፡፡
8. የዘቦች አለቃ ታምሩ፣ የገንዘብ ከረጢቱን ለባሻ ሲሰጣቸው ወዲያው የራሳቸው ድርሻ እንደሆነ ነግሩዋቸው ነው፡፡
9. ባሻ ዘለቀ የሆነውን ሁሉ በእውነት ስለተናገሩ መርማሪ መኮንኑ ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ አድርገኋል፡፡

፪. በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ‹‹አፋቸው ውስጥ ጩቤ ነው ያለው›› ሲል ምን ምን ማለት ነው?
   ሀ. የንግግር ጥበብ መቻልን፣ ሐ. ብዙ ቋንቋ ተናጋሪ መሆንን፣
   ለ. ተሳዳቢ መሆንን፣ መ. ንግግራቸው መልዕክት አዘል ነው፣
2. ባሻ ዘለቀ የተያዙት በምን ተጠርጥረው ነው?
   ሀ. በዕቃ ስርቆት ሐ. በነፍስ ግድያ
   ለ. በእንስሳት ስርቆት መ. አደገኛ እፅ በማዘዋወር
3. ተረኛ መኰንኑ ከሁለቱ የፖሊስ ወታደሮች ጋር ወደ ሌላ ክፍል ሄደው የቆዩት ለምን ይመስለሃል/ሻል?
   ሀ. ተጠርጣሪው የሚገረፍበትን ሁኔታ ለመመካከር፤
   ለ. ከተጠርጣሪው በሙስና ገንዘብ ለመቀበል፤
   ሐ. የተጠርጣሪው ቤት የሚፈተሽበትን ሁኔታ ለመመካከር፤
   መ. ተጠርጣሪው ቃል የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመመካከር፤
4. በምንባቡ መሰረት ከመካዝን የተዘረፈው ንብረት ግምቱ ምን ያሃል ይሆናል?
   ሀ. መቶ ሽህ ብር፣ ሐ. አንድ ሚሊየን ብር፤

ለ. ሁለት መቶ ሽህ ብር፤ መ. ሦሥት ሚሊዮን ብር

5. ተጠርጣሪው እጃቸውን በስርቆቱ እንዳስገቡ ተገልጾላቸው የሚያውቁትን እንዲገልጹ ሲጠየቁ ስሜተቸው ምን ነበር?

 ሀ. ባንዴ ገጽታቸው ተለዋውጦ ፊታቸው የተቃጠለ ላስቲክ መሰለ፤

 ለ. ዘናና ፈገግ ብለው አዳመጡ፤

 ሐ. ነገሩን ለማጥፋፋት ምንም ነገር እንዳልተፈጠረ ዘና ብለው ተቀመጡ፤

 መ. ምንም ዓይነት የመደንገጥ ስሜት አልተሰማቸውም፤

6. ባሻ ዘለቀ ቃላቸውን ሲሰጡ ለአለመዋሸት የወሰኑበት ምክንያት ምንድን ነው?

 ሀ. በእድሜ መብሰላቸውና በእምነታቸው የጸኑ መሆናቸው፤

 ለ. ተጨባጭ መረጃ ስለተገኘ እውነቱ መውጣቱ አይቀርም ብለው ስላሰቡ፤

 ሐ. የሚደርስባቸውን ድብደባ ስለፈሩ፤

 መ. የአስተዳዳሪዎች ደባ ማጋለጥ ስለፈለጉ፤

7. ለባሻ ዘለቀ ሽለጉዳዩ የነገራቸው ማን ነው?

 ሀ. የዘቦች አለቃ ለ. የአስተዳደር ሰራተኛው ሐ.ከመስሪያቤት ውጭ ያለሰው መ.ሁሉም

8. የዘቦች አለቃ ታምሩ እንደገለጸው ከጭማድ የድርሻቸውን ለመውሰድና ሙስና ውስጥ ለመግባት ምክንያት የሆነው ጉዳይ ምንድን ነው?

 ሀ. የጭማድ ድርጅት መክሰር፤ ለ. ጭማድ ድርጅት ለግለሰብ ሊሸጥ መሆኑ፤

 ሐ. ጭማድ ድርጅት ከፍተኛ ትርፍ ማስገኘቱ፤ መ. መልስ አልተሰጠም፤

9. ‹‹ሙልጫችንን ሳንቀር›› ሲል ምን ማለት ነው?

 ሀ. ሀብት ንብረት አለማፍራትን፣ ለ. ባዶ እጅ መቅረትን፣

 ሐ. ብዙ ሀብት ማፍራትን፣ መ. በሌሎች መሰረቅን፣

10. ባሻ ዘለቀ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ታምሩ ለአቀረበላቸው የድርሻችንን እንያዝ ለሚለው ጥያቄ መልሳቸው ምን ነበር?

 ሀ. በንጽህናቸው ጸንተው አሰናብተውታል፤ ለ. ስለሚያገኙት ድርሻ ጓጉተዋል፤

 ሐ. ስለሚያገኙት ድርሻ ያነሰ በመሆኑ ተቃውመዋል፤ መ. ለመወሰን ተቸግረዋል፤

11. ባሻ ዘለቀ፣ በመጨረሻ ወንጀለኛ መሆናቸው ሲታሰባቸው፣ ያስጨነቃቸው ጉዳይ ምንድን ነው?

 ሀ. በህግ የሚጠየቁ መሆናቸው ስላሳሰባቸው፣ ሐ. የወሰዱትን ገንዘብ ስለሚመልሱ፣

 ለ. የነበረ ክብራቸውና ስማቸው ስለሚጎድፍ፣ መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው፣

12. የዘብ አለቃው ታምሩ ለባሻ የድርሻቸውን ገንዘብ ለመስጠት ተደጋጋሚ ሙከራ ያደረገው ለምንድን ነው?

 ሀ. ለባሻ ባለው ተቆርቋሪነት፣ ለ. የአስተዳዳሪዎች ግፊት ስላለ፣

 ሐ. ሁሉንም በማነካካት ሚስጢር እንዲጠበቅ ለማድረግ፣ መ. መልስ አልተሰጠም፣

**ክፍለ ጊዜ ሦስት፦** ለጥያቄዎች የተብራራ መልስ በጽሑፍ ይሰጣሉ። ክፍት ጥያቄዎችን ይሰራሉ። በዚህ ክፍል ያሉ ተግባራት ስልምንባቡ መልዕክት ጥልቅ ግንዛቤ እንዲያገኙ፣እንዲወያዩ፣የተለያዩ ጽንሰ ሃሳቦችን ፣አገላለጾችን እንዲረዱ ያግዛቸዋል። ገጸባህሪያትን እንዲረዱና የራሳቸውን አመለካከት እንዲያንጸባርቁ ያስችላል።

**፫. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች የተብራራ መልስ በጽሁፍ ስጡ።**

1. የአስተዳደር ኃላፊው ቢታው፣ እቃ ከመካዘን ወጥቶ ሊሸጥ እንደሆነ፣ ከባሻ ዘለቀ ጥቆማ ሲደርሳቸው የወሰዱት እርምጃና አቋማቸው ምን ይመስል ነበር፡፡
2. የዘቦች አለቃ ለመጨረሻ ጊዜ ማታ ተመልሶ በመምጣት፣ ከረጢቱ ውስጥ ያለው ገንዘብ የአንተ ነው ሲላቸው ምን ምላሽ የሰጡ ይመስለሃል?
3. ባንተ አመለካከት ባሻ ዘለቀ ሀቀኛ ሰው ናቸው ወይስ አይደሉም፣መልሳቸሁን በምክንያት አስረዱ፡፡

**፬. በሚከተሉት ጥያቄዎች በሚገባ ተወያዩ፣ተከራከሩ፡፡**

1. የፀና እምነት፣ሀቀኝነትና የእውነትን መንደድ የመከተል አቋም ካለ በሌሎች ሰዎች ተጽእኖ ሊዘባ ይችላል ወይስ አይችልም በሚለው በቡድን ተከራከሩ፡፡
2. ባሻ ዘለቀ በእስር መቀጣታቸው ተገቢነው ወይስ አይደለም፣ ቡድን መስርታችሁ ተወያዩ፡፡